# አውራምባ ታይምስ

ልዩ ዕትም

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

3ኛ ዓመት ቁጥር 131 ነሐሴ 29 ቀን 2002 ዋጋ 5.00 ብር




# ፳፻፪ እና ጉልህ ክስተቶቹ




PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

አውራምባ ታይምስ
ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

የካቲት 2000 ዓ.ም ተመሠረተ

አውራምባ ታይምስ፡- በብሉ አርዝ ጀነራል ቢዝነስ ኃላ/የተ/የግል/ማህበር ስር የሚታተም፤በፖለቲካዊ ና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በቁጥር 020/2/6572/2001 የተመዘገበ ሳምንታዊ ጋዜጣ ነው፡፡

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ዳዊት ከበደ

**ዋና አዘጋጅ**
ፍፁም ማሞ
(አድራሻ የካ ክ/ከ
ቀበሌ 03/04 የቤ.ቁ 1540)

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ግዛው ለገሰ
ውብሸት ታዬ

**አዘጋጅ**
አቤል ዓለማየሁ

**ከፍተኛ ሪፖርተሮች**

ሰናይት ግርማ
ኤልያስ ገብሩ
ሱራፍኤል ግርማ

**ዓምደኞች**
አበበ ቶላ
ትዕግስት ወንድሙ

**ሽያጭና ማስታወቂያ**
ሲሳይ ጌትነት
ተሻለ ወዳጅ

**ኮምፒውተር ፅሁፍ**
መቅደስ ፍስሐ

**ግራፊክስ ኤዲተር**
ነብዩ መስፍን
(0911 18 09 33)
E-Mail:nebiyou1st@yahoo.com

**የዝግጅት ክፍሉ ስልክ**
ስልክ፡- 0911 62 92 78
0911 62 92 82
0911 11 03 90
ፖ.ሣ.ቁ 19325
awrambatimes@gmail.com
http://www.awramba.com

**የአሳታሚው አድራሻ**
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02
የቤት ቁጥር 181
ዋናው ፖስታ ቤት ጀርባ
ከአምሳደር ወደ ንግድ ማተሚያ ቤት በሚወስደው መንገድ ላይ ከተስፋ ድርጅት ፊት ለፊት

ብሉ ኤርዝ ጀነራል ቢዝነስኃላ/የተ/የግል/ማ
Blue Earth General Business PLC

አታሚ፡-
ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ፡-አራዳ
ቀበሌ፡-17
የቤት፡-ቁ.984

## ርዕሰ አንቀፅ

# የተረከብነው ብዙ የምናስተላልፈው ግን ጥቂት እየሆነ ነው

መረጃ የለውጥ አይነተኛ ኃይል በሆነበት የዘመን ምዕራፍ ላይ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም፡፡ የሕዝብ አይንና ጆሮ ናቸው፡፡ በዜጎች መካከል የሚደረጉ የተለያዩ አመለካከቶችን በመድረክነት በማንሸራሸርና አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን የነጠሩ ኃሳቦች ለተደራሹ በማቅረብ ተቋማዊ ተልዕኳቸውን ይወጣሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉበትና በጥብቅ የሚከተሉት ሙያዊ ስነ ምግባርም አላቸው፡፡ አውራምባ ታይምስ ጋዜጣም የመጀመርያ ዕትሟን ለንባብ ካበቃችበት የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ይህንን ተቋማዊ ተልዕኮ ለማሳካት የድርጅቱ ባልደረቦች አቅማችን የቻለውን ያህል ጥረት ስናደርግ ቆይተናል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ እጅግ ፈታኝ ጉዞዎችን አልፈናል፤በዚያው ልክ የእናንተ ውድ አንባብያን አጋርነትና ማበረታቻዎች በአቋማችን ጸንተን እንድንገሰግስ አድርገውናል፡፡

ምንም እንኳ ማሕበረሰባዊ ሁነቶች የሚገዙበት የራሳቸው ሕግና ስርዓት መኖሩን ብናውቅም ሲያጋጥሙን የቆዩት ፈታኝ ነገሮችም ሆኑ ገንቢ ምቹ ተሞክሮዎች የተለያዩ አመለካከት መንሸራሸር ውጤቶች ናቸው ብለን እንረዳቸዋለን፡፡ በዚህ የዓመቱን አበይት ክስተቶች መለስ ብለን በዳሰስንበት ልዩ ዕትማችን አንባብያንን ግንዛቤ ያስጨብጣሉ፣ በተሳሳተ አካሄድ ላይ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ያነሳሳሉ እንዲሁም መፍትሄውን ያመላክታሉ በምንላቸውና መበረታታት አለባቸው በምንላቸው ጅምሮች ላይ አጋርነታችንን ስናሳይ ቆይተናል፡፡

በዚህ ፅኑ ዕምነት ስናስተላልፋቸው ከቆዩት አንኳር ነጥቦች የተወሰኑት ቀጥሎ ያሉት ሲሆኑ መለስ ብለን በመመርመር ተፈጻሚ አድርገናቸዋል ወይ ብለን ልንጠይቅ ይገባናል እንላለን፡፡ ከኢኮኖሚያዊ ጉዳዮቻችን አንዱ አገራችን ከሌሎች አገራት ጋር የምታደርጋቸው የንግድ ግንኙነቶች ሚዛናዊነትና የውስጥ ግብይቶች ምን በመሰለ ስርዓት መከናወን እንዳለባቸው የሚጠቁመው ይገኝበታል፡፡ *«ከአገራት ጋር የሚደረጉ የንግድ ግንኙነት ውሳኔዎቻችን ነገ የማንጸጸትባቸው ሊሆኑ ይገባል»* በሚል ርዕስ አንገብጋቢ ያልናቸውን ነጥቦችን አንስተን እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይህ ጉዳይ በጣም አሳሳቢና ጊዜ ሊሰጣቸው የማይገቡ ችግሮች የሚስተዋሉበት ሲሆን ሕብረተሰቡ በሕጋዊነት ሽፋን ለሚፈጸሙ ምዝበራዎች የተጋለጠበት መሆኑን አሳስበናል፡፡

ከችግሮቹ የተወሰኑት ተገቢው ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደአገር ውስጥ በመግባት ገበያው ላይ በገፍ የተረጩት ሸቀጦች የሕጋዊ ነጋዴዎችን አከርካሪ በመስበር ከግብይት ስርአቱ እያስወጧቸው የሚገኙ መሆኑና አገሪቷንም ማግኘት የነበረባትን መጠኑ የማይታወቅ ከፍተኛ ገቢ እያሳጧት መሆኑ፣ ተመሳስለው የተሰሩ ሸቀጦች በገፍ ከሚቸበቸብባቸው አገራት አንዷ ኢትዮጵያችን በመሆኗ እና እነዚህ አስተኔ ሸቀጦች ከትክክለኛው ምርት ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ ስለሚቀርቡ የሸማቹን ትኩረት ቢስቡም ቶሎ ቶሎ በመበላሸት ለተደጋጋሚ ወጪ መዳረጋቸው፣ ከፍተኛ ወጪ ለወጣባቸው ንብረቶች መበላሸት መንስኤ በመሆንና (የዋስትና ሽፋንም የላቸውም) ሕጋዊ ነጋዴዎችን በማክሰም የሕግን ልዕልና እንደሚያንኳስሱ፣ የተበላሹ /ጊዜያቸው ያለፈ/ ሸቀጦች በየአደባባዩ እንደሚሸጡ በመግለጽ የሚመለከታቸው ወገኖች አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡-እነዚህ ችግሮች አሁንም አሉ፤ይስተካከሉ እንላለን፡፡

አገርን በጋራ ስለመገንባትም የሌሎች አገራትን ገንቢ ተሞክሮ በማንሳት *«ምራሉ የተገነባ ማህበረሰብ ታሪክ መስራት የሚችል ትውልድ የሚፈጠረው ፖለቲካው ሲስተካከል ብቻ ነው»* በሚል ርዕስ በምርጫ ገዢ ፓርቲ ከመሆን ቀጥሎ ስለሚከተሉ ኃላፊነቶች ጠ/ሚ/ሩ ተቃዋሚዎችን በአገራዊ ጉዳዮች ማሳተፍን አስመልክቶ ያቀረቡት ጥሪ የነበረውን ክፍተት ለማመላከት ሞክረናል፡፡

በምዕራቡ ዓለም አንድ ፓርቲ አብላጫ ድምጽ አግኝቻለሁና ሁሉንም ለራሴ ልጠቅልል አይልም፡፡ በምርጫ ክርክር ወቅት በተቀናቃኝ ፓርቲዎች መካከል የፈለገውን ያህል እሰጣ ገባ እና መወነጃጀል ቢኖር የኋላ ኋላ የመንግስትን ስልጣን የሚጨብጠው ፓርቲ ስልጣኑን ከያዘ በኋላ ለዚህ ኃላፊነት ማን ይመጥናል? የሚል መመዘኛ መሰረት አድርገው ከራሳቸውም ሆነ ከተቀናቃኝ ፓርቲ ብቁ የሚሏቸውን ሰዎች ያሰባስባሉ እንጂ «አሸንፌአለሁና የግድ አምስት አመት መታገስ ይኖርባችኋል» አይሉም በማለት ለአገር ለወገን የሚጠቅም ርዕይ እንዲሁም ብቃት ያለው ተቃዋሚ ካለ አመለካከቱን እንደያዘ ቢሾም? ካቢኒ ውስጥ ቢገባስ? የሚል አገርን በጋራ የመገንባትን አስፈላጊነት ጠቁመናል፡፡ ዛሬም ጊዜው አልመሸም፤ ይታሰብበት ለማለት እንወዳለን፡፡

ከዚህ አገርን በጋራ የመገንባት ተግባር ጋር የራሳቸውን አስተዋፅኦ ከሚያበረክቱ ወገኖች መካከል አንዱ በውጭ የሚገኙ ኢትጵየውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው *«ዳያስፖራው፣የፖለቲካ አመለካከቱን እንደያዘ አገሩን እንዲያሳድግ ልባዊ ጥሪ ይቅረብለት»* የሚል መልዕክት ማስተላለፋችን ይታወሳል፡፡ እንዲያውም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን የሚመለከት ዳይሮክቶሬት ቢቋቋምም፤የመስሪያ ቤቱ የትኩረት አቅጣጫ የኢህአዴግን ፖሊሲ በሚደግፉት ላይ ብቻ በማነጣጠሩ በውጭ የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ ለአገራቸውና ለወገናቸው ቤዛ ሊሆኑ አልቻሉም ስንል አስጠንቅቀናል፡፡

በየአመቱ ሚሊዮኖች የሚራቡባትና በአስከፊ ድህነት ውስጥ ያለችው አገራችን እንድትበለፅግና አንገታችንን የሚያስደፋን ሁኔታ እንዲለወጥ ሲባል በመቻቻልና በሆደ ሰፊነት በየሰው አገር የሚገኘው የተማረ ኃይል አገሩን እንዲጠቅም ልባዊ ጥሪ የማይደረግለት ለምንድነው? ይህንን የማመቻቸቱ ኃላፊነትስ ከሚመለከታቸው አገር ወዳድ ወገኖችም ሆነ ከመንግስት ቢቀርብ ምን ክፋት አለው? ስንል ጠይቀናል፡፡-አሁንም እየጠየቅን ነው፡፡

በመርሕ ደረጃ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ማሕበረሰባዊ ለውጥና ዕድገት እንዳይኖር፣ አገር እንዳትበለጽግ ወይም መሰል እመርታዎች እውን እንዳይሆኑ ይፈልጋል ብለን አናምንም፡፡ ታዲያ ችግሩ ምንድነው? ስንል ሁኔታዎችን አጥብቦ የመመልከት መሆኑን *«በድርጅታዊ ታማኝነት ብቻ ከሚደግፉ በአገራዊ ተቆርቋሪነት የሚሞግቱ ይሰሙ»* በሚለው ርዕስ አንቀጻችን ያካተትነው አንዱ ነጥብ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

«ይደረስባቸዋል የተባሉ ግቦችን አስመልክቶ አዎንታዊ ሆኖ መነሳት ተገቢ ቢሆንም ይህ አቋም የመነጨው ከስሜት ሳይሆን ከሳይንሳዊ እውቀት መሆን አለበት እንላለን፡፡ ይህ እውቀት ተግባራዊ ሊሆኑ ከሚችሉ ዓለም አቀፍ የስኬት ተሞክሮዎች፣ ግባቸውን ያልመቱ ዕቅዶችን ጉድለት በመፈተሽና በማረም በዋንኛነትም የተገኘውን እውቀት ከሕዝቡ ውስጣዊ መስተጋብር ጋር በማዛመድ ሲተገበር ነው፡፡ እቅዶቹ ሊተገበሩ በሚችሉ ስትራቴጂዎችና በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ይሁኑ፡፡ ለዚህም «አዎ» እና «እሺ» ብቻ ከሚሉ የድርጅት ታማኞች ይልቅ እንዴት እና ለምን? ብለው በስነ አመክንዮ የሚሞግቱ የአገር ተቆርቋሪዎች እንደሚሻሉ አምኖ መቀበል ያስፈልጋል ፤ከብዙ ውድቀትም ያድናል፡፡» የሚለው መልዕክት የምንጊዜም መልዕከታችን ነው፡፡

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አስመልክቶም ዜጎችን በማደራጀት ወደ ውጤታማነት ከመገስገስ ይልቅ ምዕራባውያንን የስልጣን አቆናጣጭ አድርጎ የማየቱ አስተሳሰብ እንዲታረም *«**በምዕራባዊያን ላይ መንጠላጠል የዜጎችን ሁለንተናዊ ጥቅም አያስጠብቅም!**»* በሚል ርዕስ ዋንኛው ትምክህት መጣል ያለበት በኢትዮጵያውያን ላይ ብቻ ነው ብለናል፡፡ በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን ኢትዮጵያውያን በመሰል ጉዳዮች ላይ ያላቸው አቋም አንድና አንድ ብቻ በመሆኑ አሁንም ችግሩን ወደ ሕዝቡ፣መፍትሄውን ወደ ምዕራባውያን አንውሰደው እንላለን፡፡

"አገር በአንድ ቀን አትገነባም" የሚል አባባል አለ፡፡ ትልቅ አባባል ነው፡፡ ምንም እንኳ አስከፊ ድሕነትና አጃቢዎቹ ውበቷን ቢጋረዱትም በኩራት የምንናገርላት ኢትዮጵያችን የማንነቷን መሰረት ለመጣል ዘመናትን አልፋለች፡፡ በየዘመናቱም የማንነታችንን አሻራ ጠብቀው ለትውልድ የሚያሸጋግሩ ተምሳሌታዊ ግለሰቦች ነበሩን፡፡ *«ጠንካራ ተቋማትና ተምሳሌታዊ ግለሰቦች ያስፈልጉናል»* በሚል ርዕስ የዳሰስናቸው ሃሳቦች መነሻም ይኸው ነው፡፡


በአንድ ማሕበረሰብ፣ ቡድን ወይም ግለሰብ ላይ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲፈፀም «አይሆንም!» በሚሉ የሚሞግቱ ተምሳሌት መሆን የሚችሉ ዜጎችስ አፍርተናል? የአንቱታን ካባ ደርበው የታዋቂነት ማማ ላይ የሰፈሩት «አንጋፋ» ሰዎቻችን የበደልና እንግልት ዜና መዋዕል ምንዱባን በሚነበብባት አገራችን ሰማይ ስር ከመሞካሸትና የግል ካዝናቸውን ከመሙላት አልፈው ያላቸውን ተቀባይነት በመጠቀም ለምን ለወገኖቻቸው መድህን አይቆሙም? ለምን አጥፊውን ገስፀው፣ ተበዳዩን አስክሰው የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ካስማችንን አያጠብቁም? ለምን ታሪካዊ እዳቸውን አይከፍሉም? ስንል ጠይቀናል፡፡ ዛሬም አበክረን እንጠይቃለን፡፡

ከውድ አንባቢዎቻችን ጋር በመሆን እነዚህንና ሌሎችንም ኃሳቦች በጋራ አንስተን ተወያይተናል፣ተመካክረናል፣ይሻላል የምንለውን ለማመላከት ሞክረናል፡፡ በመግቢያችን ላይ እንደጠቀስነው መረጃ የለውጥ አይነተኛ ኃይል በሆነበት የዘመን ምዕራፍ ላይ የሚጠበቅብንን ሙያዊ ኃላፊነት የመወጣት ጥረታችንን አጠንክረን እንገፋበታለን፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ካለፈው የተረከብነው ትውልድ የተረከብናቸው ሁለንተናዊ እሴቶች መኖራቸውን እናምናለን፡፡ እንደ ትውልድ የተረከብነው ብዙ የምናስተላልፈው ግን ጥቂት እየሆነ መሄዱ ግን ድርብ ኃላፊነቶችን መሸከማችንን እንድናስተውል ሊያደርገን ይገባል፡፡


ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## VERBATIM

# ማን ምን አለ ?????








«በ97ቱ ምርጫ በተወሰኑ ምርጫ አስፈፃሚዎች በተወሰነ ሁኔታም ቢሆን ፍትሃዊ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ የተወሰነ ፈሪሃ እግዚአብሔር ወይም ፈሪሃ ፈረንጅ ነበረው፡፡ አሁን የተካሄደው ምርጫ ቅርጫም አልመስል አለኝ፡፡ . . . ስትንተናም አስቸጋሪ ብኛል፡፡»

**ዶ/ር መረራ ጉዲና**
**የመድረክ ምክትል ሊ/መንበር**
***(ከሐምሌ 3/2002 አውራምባ ታይምስ እትም)***
*«የፖለቲካ ምህዳሩ ፍትሃዊ ባልሆነበት ሁኔታ በምርጫ ተወዳድሮ ማሸነፍ ይቻላል?» በሚል ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፡፡*



«ይህ ውይይት በራሱ ኤሌክትሪክ አያመነጭም፤ ኤሌክትሪክ የሚያመነጨው ፊንጫአና ግልገል ጊቤ ነው»

**አቶ መለስ ዜናዊ**
**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር**
***(ከጥቅምት 10/2002 አውራምባ ታይምስ እትም)***
*/ፓርላማው የ2002 የስራ ዘመኑን በጀመረበት ዕለት በፕሬዝዳንቱ ንግግር ውስጥ የመብራት ችግር መካተት እንደነበረበት ተቃዋሚዎች ያቀረቡትን የማሻሻያ ሞሽን አስመልክቶ ከተናገሩት የተወሰደ፡፡/*



«... ምስጢሩ፣ በመጀ[illegible] ቤት እያሉ መጠነኛ የሆነ ይቅርታ እንዲጠይቁ ያቀረብንላቸውን ነጥብ እምቢ አሉ፡፡ ... በኋላም የፍ/ቤቱ ጉዳይ እየፈጠነ ሄደ፡፡ ጥፋተኛ ናቸው፡፡ ሲባልና ጠንከር ያለ ነገር ሲመጣባቸው እሺ አሉን፡፡ ምናልባት ለኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ስላልተናገርን ከሆነ «ያልተነገረ ምስጢር አለ» የምንባለው ይህ ግልጽ ሲሆን ይገባል፡፡»

**ፓስተር ዳንኤል ገብረሥላሴ**
**የቅንጅት አመራሮችን ካሸማገሉ የአገር ሽማግሌ አንዱ**
*በ1997 ዓ.ም የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ በተፈጠረ አለመግባባት መንግስትንና በወቅቱ እሥር ቤት የነበሩ ሰዎችን በመሸምገል ሂደት ይፋ ያልሆነ ያሉትን ምስጢር አስመልክቶ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከሰጡት አስተያየት የተወሰደ፡፡*



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# እግዚአብሔርን የምንጠይቀው እርቅን ሳይሆን ምሕረትን ነው

## ■ሳም ባልዋለችበት ኩበት ለቀማ

በአለፈው ሳምንት አበበ በለው፣ ታማኝ፣ አብርሃ እና ጃዋር ስለብሔራዊ እርቅ ያደረጉትን ውይይት አስመልክቶ አውራምባ ታይምስ ያቀረበውን ሐተታ አነበብሁና በጣም ሐዘንና ትካዜ ገባኝ፤ አራቱም ሰዎች ስደተኞች ናቸው፤ እንደሚመስለኝ ከነቤተሰባቸው እዚያው ከባሕር ማዶ ናቸው፤ በአገር ውስጥ የምንኖረው የፍርሃት ቆፈን ይዞን ይሆን ወይም ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል ብለን ችላ ብለነው ነው? ወይስ ከጉዳይ የቆጠረን የለም! ጉዳዩ ከእያንዳንዳችን ሕይወትና ዕድሜ፣ ምኞትና ጥቅም በጣም የላቀ ነው፤ የዚህ አገር መሠረታዊው ችግር መነጋገር አለመቻል እንደሆነ ሁላችንም የገባን አይመስለኝም፤ ገዢዎችና ተገዢዎች፣ የሥልጣን ተቀናቃኞች አይነጋገሩም፤ ሁሉም ለየብቻው በየፊናው ይናገራል፤ የግንበ ሰናኦር ቁጣ!

ለማናቸውም ዋናው መነሻ ቁምነገር ጃዋር የተናገረው ነው፤--

*አንድ መንግሥት ለመደራደር ሁለት ነገር ያስፈልጉታል፤ አንደኛው እንዲደራደር (የሚያስገድደው?) ወይም ካልተደራደረ የሚያጣው ነገር ሲኖር ነው የሚደራደረው፤ አሁን ባለው ሁኔታ በውትድርናም ሆነ በሌላ ነገር የሚፈታተነው ኃይል እስከሌለ ድረስ የሚፈራው አለ ወይም የሚያጣው ነገር አለ ብዬ አላምንም፤ ይሄ ምክንያት አይሆንም:: ሁለተኛው ደግሞ ከድርድር የሚያገኘው ነገር ካለ ነው፤ በመደራደር ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመመስረት አገኛለሁ ብሎ የአቶ መለስ ዜናዊ መንግስት የሚያስብ አይመስለኝም::*

ጃዋር የጣለው መሠረት የውሃ ልክ ያንሰዋል እንጂ በጣም ጥሩ ነው፤ አንደኛ ከመነሻው አልተነሳም፤ ለድርድር ምክንያት የሚሆነው ምንድን ነው? በአንድ አገር ውስጥ የጎደለ ወይም የተበላሸ ሁኔታ ተፈጥሮ ሕዝብ የተከፋ እንደሆነ ነው፤ እንዲያውም ሕዝብ መከፋቱ ብቻ በቂ አይደለም፤ የመከፋቱ ዓይነትና ልክ፣ ምን እንዳስከፋውና ማን እንዳስከፋው በገሀድና በይፋ ሲታወቅ ነው፤ ይህ የሚሆነው የበደለና የተበደለ በአደባባይ ጉዳያቸውን ገልጠው ለመነጋገር ሲችሉ ነው፤ በደሉ ከመከፋት አልፎ ጉዳት ወደማድረስ ሲሸጋገርና እየተባባሰ ሲሄድ ጉዳዩ ወይም ችግሩ ከበደለና ከተበደለ አልፎ ወደታዛቢዎች እይታ ውስጥ ይገባል፤ የበደለና የተበደለ በአደባባይ ሲጋለጡ ለታዛቢዎች፣ ለመንፈሳዊ አባቶችና ለሰላም ሰዎች ጫና የሚፈጥሩበትን መንገድ ይከፍትላቸዋል፤ የመደራደርም ሀሳብ ሊመጣ ይችላል::

በዚህ ጊዜ የመደራደር አስፈላጊነት በተበደለውና በታዛቢዎች በኩል ግልጽ ሆኖ ይታይ ይሆናል፤ የበደለው ወገን ግን የመደራደር አስፈላጊነት ላይታየው ይችላል፤ እዚህ ላይ የጃዋር መጀመሪያው ቁም-ነገር ይመጣል፤ **እንዲደራደር የሚያስገድደው ወይም ካልተደራደረ የሚያጣው ነገር እንዲኖር ያስፈልጋል፤** አንድ መንግሥት ታዛቢዎችና ሽማግሌዎች ለራሱ ይበጃል ብለው ሲያቀርቡለት ካልተቀበለ ሰዎቹ እንደገለባ እንደቀለሉ ይሰማቸዋል፤ እነሱም በበኩላቸው ለመንግሥት የዚያኑ ዓይነት የንቀት ስሜት ያድርባቸዋል፤ ሆኖም ይህ ሁሉ ለዚያ መንግሥት አይሰማውም ወይም ግድ የለውም ይሆናል፤ ስለዚህም እርቅንና ድርድርን አሻፈረኝ የሚል ለጊዜው ባይሰማውም፣ አስገዳጅነቱ ባይሰማውም ሁልጊዜም የማያጣው ነገር አለ፤ ክብሩ ዘቅ ይላል፤ ስለዚህ ማስገደድ ሲባል በጉልበት ወይም በትጥቅ ብቻ አይደለም፤ የውስጥም የውጭም የፖለቲካ ኃይል አለ፤ የገንዘብ ኃይልም አለ፤ ክብርም ድጋፍም አለ፤ ይህንን ሁሉ የናቀ ወደሚናቅበት ደረጃ ይወርዳል፤ ለምሳሌ በኢትዮ-ኤርትራ ጉዳይ እንወያይ አያለ የሚጨቀጭቀው በጦርነት የያዘውንና ፍርድ ቤት ለኤርትራ የሰጠውን መሬት የያዘው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ነው፤ ከድርድር በፊት የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይፈጸም ብሎ የማይነቃነቅ አቀዋም የያዘው ደግሞ የኤርትራው ፕሬዚደንት ነው፤ የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር ለድርድር የሚገፋው ባለመደራደር የሚያጣው ነገር ኖሮ ሳይሆን በመደራደር የሚያጣው በመኖሩ ነው፤ የኤርትራው ፕሬዚደንት በበኩሉ በመደራደር የሚያገኘውም አለ፣ የሚያጣውም አለ፤ ባለመደራደር ደግሞ የሚያጣው አለ፣ የሚያገኘውም አለ፤ ከሚያጣውና ከሚያገኘው የትኛው ይበልጥበታል? ጠቅላይ ሚኒስትሩና ፕሬዚደንቱ የሚያገኙ-ትና የሚያጡ-ት የሚሰላው ለየአገራቸውና ለየሕዝባቸው ሳይሆን ለየራሳቸው ለግላቸውም ነው፤ ይህ ነገሩን የበለጠ ውስብስብ ያደርገዋል፤ ከአንድ ሰው ወደብዙ፣ ከመዋቲ ወደሕያው፣ ከውሱን ወዳልተወሰነ እየተለወጠ የተደራዳሪዎቹን መሠረታዊ ባሕርይ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤


ጃዋር ያቀረበው ሁለተኛው ቁም-ነገር **ከመደራደር የሚገኝ ጥቅም እንዲኖር ያስፈልጋል፤** የሚል ነው፤ አሁንም ጃዋር የጥቅሙ ባለቤት አንድና የታወቀ አድርጎ አይቶታል::

እስቲ አስታውሱ፣ ደርግም አገር ውስጥ ያሉትን እንደራደር ብሎ አያውቅም፤ ወያኔ/ኢሕአዴግም ለአገር ውስጥ ተቀናቃኞች ፋይዳ አልሰጠም፤ ይህ የሚሆነው ማን በሚያጣውና ማን በሚያገኘው ስሌት ነው? የሚታጣውስ የሚገኘውስ ጥቅም ምንድን ነው?

እርቅን የሚሻ ማን ነው? ወደእርቅ ፈላጊው ከመሄዳችን በፊት በምን ምክንያት እርቅ አስፈላጊ ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ስንሞክር፣ እርቅ አስፈላጊ የሚሆነው አንድ መሠረታዊ ነገር ሲጎድል ነው፤ ይህ መሠረታዊ ነገር መጉደሉን የተገነዘበ ሰው በውስጡ የአካባቢው ጎዶሎነት ይሰማዋል፤ አየሩን የመረዘው የሐዘንና የስጋት አባራ ያፍነዋል፤ የማኅበረሰቡ ችግር ነፍሱን ጠልቆ ይሰማዋል፤ ሙሉው ሲጎድል፣ ደስታው ሲደበዝዝ፣ ጥላቻ ሲጠበድል፣ የላዩም የታቹም በፍርሃት ተቀስፎ በቀል ሲያውጠነጥን፣ ማስፈራራት የአስተዳደር ዘዴ ሲሆን፣ የሚሰማው የማኅበረሰብ አካል የሆነና ለማኅበረሰቡ ጤንነት ኃላፊነት የሚሰማው ሰው ከሆነ ውጤት ያለው እርቅ ተፈላጊም ስኬታማም ይሆናል::

እነኃይሉ ሻውል የሚለው የክስ ፋይል እንዴት እንደተዘጋ ብናውቅም አሁንም «*ሕገ ወጥ ተግባራቸው ለፍርድ ቤት በቀረበ ስፍር ቁጥር የሌለው ማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን በመጨረሻም እነሱው ራሳቸው ባቀረቡት የምሀረት ጥያቄ ውንጀላቸውን አምነው ተቀብለዋል (አዲስ ራዕይ ሐምሌ-ነሐሴ 2002 ዓ.ም ቁጥር 3 ገ. 23)::*» በዚህ ውሸት ማን ምን አገኘ? ማን ምን አጣ?

ከግል ትምክህትና ትዕቢት ስንወጣና በአንድ ሰው ዕድሜ ክልል ውስጥ ማሰብን ስንተው የአገርና የወገን ጉዳይ በልባችንና በአእምሮአችን ሰፊና ጠንካራ ቦታ ሲኖረው፣ የምናገኘውንና የምናጣውን የምናይበት ዓይኖች፣ የምንለካበትም የኅሊና ሚዛን ይለወጣል፤ ለዚያ አልበቃንም፤ የሚገኘውንና የሚታጣውን የምናውቀው እግዚአብሔርን፣ ሕግን፣ ሕዝብንና አገርን ስናውቅና ፍርዳቸውን መገመት ስንችል ነው፤ ማስረጃውን ቀደም ሲል ከአዲስ ራዕይ (አዲስም አይደለ፤ ራዕይም አይደለ፤) ጠቅሻለሁ፤ ግን ተስፋ አንቁረጥ፣ ለአዲሱ ዓመት አዲስ እንድናስብ እግዚአብሔር ይርዳን::



በመስፍን ወልደ ማርያም (ፕሮፌሰር)

# የጊዮርጊሱ ግርግር

# መልካም አዲስ ዓመት



ግርማ ሳካ (ከቺካጎ)

muziky 68@yahoo.com

አዲስ አበባ ጊዮርጊስ አካባቢ ነው:: ሰዎች ባንድ ቦታ ተከማችተዋል:: ግርግር ነገር ይታያል:: በመንገድ የሚያልፉ አንድ አባት በመኪና ውስጥ አብረዋቸው ያሉትን «ምንድን ነው የተፈጠረው?» ይሉና ይጠይቃሉ:: ሹፌራቸው መኪናውን ቀስ አድርጎ እንዲያቆም ያዛሉ:: ከሹፌሩ ሌላ አብሯቸው መኪናው ውስጥ የሚገኝ አንድ ወጣት ከመኪናው ወርዶ፣ ነገሩ ምን አንደሆነ አጣርቶ እንዲመጣ ይላካል:: ወጣቱ፣ ብዙ ሰዎች ወደ ተሰበሰቡበት ፈጥኖ ያመራል:: እየሆነ የነበረውን ተመልክቶም ይመለሳል::

አንዲት ድሃ ነፍሰ ጡር ኢትዮጵያዊት ውሃ ፈሷት፣ ምጧ በድንገት መጥቶ ትሰቃይ ነበር:: ይሄዱበት የነበረውን መኪና አስቁመው፣ የተፈጠረውን ነገር ለማወቅ ወጣቱን የላኩት አባት ደግሞ፣ የልእልት ሳራ ግዛው ባለቤት፣ የአጼ ኃይለሥላሴ ልጅ፣ ተወዳጁ ልዑል መኮንን ነበሩ::

ልዑሉ የተፈጠረውን ጠንቅቀው ከተረዱ በኋላ መንገዳቸውን ወደ ቤተ መንግስት አልቀጠሉም:: ከኋላቸው አጅቦ በሚከተለው ሌላ መኪና፣ በአስቸኳይ ኢትዮጵያዊቷ ተጭና ወደ ሆስፒታል እንድትሄድ ያዛሉ:: እርሳቸውም በመኪናቸው ይችን መንገድ ላይ የወደቀች ሴት ተከትለው ሆስፒታል ድረስ ይጓዛሉ::

ይህ ሲሆን ገና አልተወለድኩም:: ስለ ልዑል መኮንን ብዙም አላውቅም:: ነገር ግን ድሃ የሚወዱ፣ በሕዝብ በጣም ተወዳጅ እንደነበሩ ብዙ ጊዜ ሰምቼያለሁ:: የዚችን፣ የነፍሰ ጡሯን ሴት ታሪክ ግን በቅርቡ ነበር የሰማሁት:: ልቤ በጣም ተነካ:: ከአንድ መሪ ማየት የምፈልገውን ከልዑል መኮንን አየሁ::

ልዑል መኮንን የጊዮርጊሱን ግርግር ባዩ ጊዜ «እኔ የምኖረው አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ነው፤ ከኔ ጋር የሚገናኝ ነገር የለም:: ጊዜዬን በዚች ድሃ ሴት ዙሪያ ከማጠፋ በቶሎ ወደ ቢትወደድ እንትና፤ ራስ እገሌ... ጋር መሄዱ ይሻለኛል» ብለው መንገዳቸውን መቀጠል ይችሉ ነበር:: ነገር ግን መሪ ማለት፣ የሚመራውን ሕዝብ ችግር የሚያይ፣ የሚያውቅ፣ መፍትሔም የሚፈልግ መሆኑን የተረዱ ሰው ነበሩ::

ልዑል መኮንን በሴቲቱ ላይ የደረሰውን ችግር በተረዱ ጊዜ ታክሲ እንዲወስዳት ሳንቲም መወርወር ይችሉ ነበር:: ነገር ግን መሪ ማለት ለሚመራው ሕዝብ የሚያስብ፣ የሚመራው ሕዝብን ችግር የራሱ ችግር አድርጎ የሚቆጥር እንደሆነ አውቀው ነበር:: በመሆኑም የዚችን ሴት ችግር የራሳቸው ችግር አድርገው ወሰዱት:: መኳንንት በሚሳፈሩበት መኪና፣ ይህች ምስኪን ድሀ ሴት እስከነ ደሟ እንድትቀመጥ አስደረጉ:: የራሳቸውን ሚስት፣ እህቶች፣ የቅርብ ዘመድ እንደሚንከባከቡት ለዚች ድሀ ሴትም እንክብካቤ አደረጉላት:: በሰላም ሆስፒታል አደረሷት:: ሴቲቱም በሰላም ተገላገለች::

ከ19 ዓመታት በፊት ነበር:: አስመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበርኩኝ ጊዜ መድሃኔ አለም የሚባል የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አምላክን ላመስግን እሄዳለሁ:: አንድ አባት በዚህ ተቀምጠዋል:: እዘያው አስመራ በለመድኩት የተንተባተበ ትግሪኛ ከርሳቸው ጋር ጨዋታ ጀመርኩ:: በአስመራ ከተማ ስለሚፈነዳውና ሻእቢያ ከሩቅ ስለሚተኩሰው ሚሳዬል (ያኔ ግራፒ ነበር የምንለው) አነሳን:: ትዝ ይለኛል፣ በሚፈነዳው ሚሳዬል ምክንያት ከቴራ ቦሎና አይሮፕላን ማረፊያው አካባቢ (ደቡብ አስመራ) ሕዝቡ ቀዬውን እየለቀቀ ወደ መሃልና ሰሜን አስመራ ይፈልስ ነበር:: «እንደው እግዚአብሔር ሰላምን ያምጣልን፣ መፍትሔው እርሱ ብቻ ነው» አልኳቸው እኝህን አባት:: እርሳቸውም «ልክ ነህ፣ ሰላም ነው መፍትሔው:: ከጅምሩ ቀውሱና ጦርነቱ በሰላም በንግግር ቢፈታ ኖሮ ብዙ ሺህ ወጣት ባልሞተ ነበር::» ሲሉ ስለ አንድ ሰው አጫወቱኝ፤ ጄኔራል አማን አንዶም!

በአብዮቱ ወቅት ነው:: ጀግናውና ዝነኛው የጦር መኮንን ጄኔራል አማን አንዶም የደርግ ሊቀመንበር ሆነው ተሾመዋል:: በኤርትራ ሻእቢያና ጀበሃ እየበረቱ የመጡበት ጊዜ ነበር:: በተለይም በኤርትራ የነበረውን ፌዴሬሽን በአጼ ኃይለሥላሴ ከፈረሰ ጀምሮ፣ የመገንጠል ጥያቄ ስር እየሰደደ የመጣበት ወቅት ነበር::

ጄኔራል አማን አንዶም ነፍጥ አንስተው የሸፈቱትን አነጋግረው እያሳመኑ በኤርትራ የተፈጠረውን ቀውስ በንግግር ለመፍታት ትልቅ ጥረት ጀምረው ነበር:: ኤርትራ የኢትዮጵያ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ አካል እንደሆነች፤ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ የጀመረው ከትግራይና ከኤርትራ እንደሆነ፤ በሰንአፈ ኤርትራ እንደተወለዱት የአክሱሙ ንጉስ ኢዛና ብዙ ታላላቅ የኢትዮጵያ ነገስታት ከኤርትራ ጋር ትስስር እንዳላቸው፤ ለኢትዮጵያ አንድነት ከጣሊያኖችና ከግብጾች ጋር በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን (ኤርትራውያንንም ጨምሮ) ደማቸው በኤርትራ ምድር እንደፈሰሰ፤ ከኤርትራ ውጭ በመቶ ሺዎች የኤርትራ ተወላጆች ኢትዮጵያ ውስጥ፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ከተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል የመጡ በኤርትራ ውስጥ እንደሚኖሩ፤ ሕዝቡ እንደተደባለቀና እንደተዛመደ እያስረዱ ሻእቢያና ጀብሃ የመገንጠል ጥያቄያቸውን ትተው ወደ ሰላም እንዲመጡ እያሳመኑ ነበር::

አዲስ አበባ የተቀመጡት፣ አርቆ ማስተዋል የተሳናቸው፣ በግርግር ሥልጣን የጨበጡትና ትንሽ እውቀት ይዘው የሚንጠራሩ መቶ አለቆች፣ የሰላሙን ጥረት ቀጬት:: የትላንቱ ጀግንነት ተረስቶ፣ የትላንቱ ጥሩ ሥራ አመድ ለብሶ፣ በትግሪኛ ሕዝቡን ማናገራቸው እንደ ሐጢያትና ወንጀል ተቆጥሮ ጄኔራል አማን አንዶም «የወንበዴ ረዳት» ተደርገው ተወሰዱ:: አዲስ አበባ አይሮፕላን ማረፊያ በሚገኘው ቤታቸው በግፍና በጭካኔ ተገደሉ::

በኢትዮጵያ ታሪክ ነበሩ ከሚባሉ ታላቅ የጦር መሪ አንዱ ጄኔራል አማን አንዶም ነበሩ:: ጦር መርቶ፣ በጦርነት ድል ማድረግ የለመዱና የሚችሉ የወታደራዊ አመራር ብቃት የተላበሱ ነበሩ:: ነገር ግን፣ በተለይም የራስን ወገን በጠመንጃና በመድፍ ከማስፈራራት እንዲሁም በጉልበትና በጡንቻ ሕዝብን ከማስገበር ይልቅ፣ ትሁት ሆኖ በንግግርና በማሳመን የሚገኝ ውጤት ዘለቄታ ያለው መሆኑን የተረዱ ሰው ነበሩ:: «ጠመንጃ ያነሳውን ብትገድለው ነገ ልጁ ደግሞ ይነሳብሃል:: ጠመንጃ ያነሳውን ግን አሳምነህ ወዳጅ ብታደርገው ነገ ልጁ፣ የልጅ ልጁ ወዳጆችህ ይሆናሉ» በሚል እምነት ነበር ያኔ በሰላሙ ሀሳብ የተንቀሳቀሱት::

የልዑል መኮንን እና የጄኔራል አማን አንዶምን ምሳሌ ያለ ምክንያት አላመጣሁም:: አገራችን ኢትዮጵያ ለዓመታት ያጣችውና የጎደላት ነገር ቢኖር እንደዚህ ዓይነት መሪዎችን ነው::

በአሁኑ ጊዜ የትኛው የአገራችን መሪ ይሆን ለተጠቃው፣ ለተጎዳው፣ በግፍ

*ወደ ገፅ 23 ዞሯል*



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# የሶስት ትውልድ እንባ
## /ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ/

በግዛው ለገሠ



«እንነጋገር የቡርትዬን ነገር»፣ «መሰናበቻ መሰናበቻ አንድ የቀረችን ብርቱካን ብቻ»፣ እንዲሁም መሰል ዝማሬዎች የተደመጡት ህዳር 13 ቀን 2002 በተደረገው የኢትዮጵያ ታላቁ ሩጫ ላይ ከተሳተፉ ዜጎች አንደበት ነበር::

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በቅድመ ሁኔታ የተሰጠ ይቅረታዋ ተነስቶ ለዳግም እስር ከተዳረገች አንድ ዓመት ከስምንት ወር አልፏታል:: አሁንም እንደታሰረች ናት:: ታዲያ በዚህ ባገባደድነው ዓመት እርሷን በተመለከተ ምን ተከስቷል? አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት... ብለን እናያቸዋለን:: ሆኖም የብርቱካንን ዳግም መታሰር ከዚህ ኢህአዴግ «በኩምታ ካሸነፈበት» ምርጫ 2002 ጋር እጅጉን አያይዘውት የነበሩ፣ ወይም «ብርቱካን የኢህአዴግ የምርጫ ስጋት ነበረች» የሚሉ ወገኖች ምርጫው እንዲህ አልፎ እንኳን እስካሁን በእስር መቆየቷ በራሱ «የዓመቱ ጉልህ ክስተት» እንደሆነ ይናገራሉ:: ኢህአዴግ ወይም መንግስት ግን አቋሙን አልቀየረም:: የወ/ት ብርቱካን ጉዳይ የምርጫ (የፖለቲካ) ሳይሆን «የሕግ ጉዳይ ነው» እንደለ አለ:: ለማንኛውም እንቀጥል ...

### ለጠ/ሚኒስትሩ የተላከ ደብዳቤ

እለተ ዓርብ ነው፤ የወ/ት ብርቱካን ወላጅ እናት፣ ወ/ሮ አልማዝ ገብረእግዚአብሔር አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የመጡት፤ ታህሳስ 16 ቀን 2002 ዓ.ም:: እንደሚታወቀው ማተሚያ ቤት የሚገባበት ቀን ስለሆነ የመጡበት ቢሮ በዚህ ቀን ውጥረት ይበዛዋል:: በወቅቱ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ የነበረው ውብሸት ታዬ ከበር ተቀብሎ አስተናገዳቸው:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ አንድ ቅጠል ወረቀት አቀብለውት ተሰነባበቱ:: ዋና አዘጋጁም ወረቀቷን ይዞ ወደ ኤዲቶሪያ መሰብሰቢያ ክፍል ሲዘልቅ ሌሎቹም የጋዜጣው አዘጋጆች ተከተሉት:: እናም ክብ አሰርቶ፣ ቃላት ማስወጫ ትንፋሽ እያጠረው፣ እየተናነቀው ወረቀቷ ላይ የሰፈረውን ፅሁፍ አነበበላቸው:: ይህ ፅሁፍ ከወ/ሮ አልማዝ ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተላከ ደብዳቤ ነበር፤ የ«ልጄን ፍቱልኝ» መልዕክት ያዘለ ደብዳቤ::

በርግጥም ደብዳቤው ልብ የሚነካ ነበር:: ወ/ሮ አልማዝ ዕድሜያቸው 70 እንደሆነና በተለያየ ሕመም መድከማቸውን በደብዳቤው ይገልፃሉ:: «በደካማ ጉልበቴ የአምስት ዓመትዋን የልጅ ልጄን ሃሌንም በቅጡ መያዝ አቅቶኛል:: ከዚህ ሁሉ ስቃይ፣ የልጄና የልጅ ልጄን ስቃይ ከማየት የልጄ እስር በእኔ ሞት መለወጥ ቢችል ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር::» ይላሉ:: ሕፃን ሃሌም «በየቀኑ ቡርቴ መቼ ትመጣለች? ለልደቴ አትገኝም ወይ? መቼ አብረን እንጫወታለን? መቼ ከእርስዋ ጋር እተኛለሁ? መቼ? መቼ? እያለች» እንደምታስጨንቃቸው ይገልፃሉ::

በማግስቱ፣ ጋዜጣው በወጣበት ዕለት ለአስተያየት ከሚደውሉ ሰዎች መካከል አረጋዊያን ቁጥራቸው በርካታ ነበር:: ሁሉም ምኞቱን፣ ሀዘኑን፣ ቁጭቱን ይገልፃል:: አንድ በእድሜ ገፋ ያሉ ሴት «አልቅሼ አልቅሼ ነው የምደውለው፤... እንደው ደብዳቤው ደርሷቸው ይሆን?... እንደው ይፈቷት ይሆን?...» በማለት ስሜታቸውን እንደገለፁለት አንዱ የጋዜጣው አዘጋጅ ያስታውሳል::

የወ/ሮ አልማዝ ደብዳቤ (እስካሁን) ግቡን «አይምታ» እንጂ ብዙዎችን ያስደመመ ነበር:: «እኔ አልተማርኩም:: የታሰረችበትን ጉዳይ በቅጡ ባልረዳም መጀመሪያ በታሰረች ጊዜ ይቅርታ መጠየቋን ነግራኛለች... እኔ ዝርዝር ሁኔታውን ባልረዳም ብርቱካን መቼም ቢሆን መንግስትንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅዋን አትክድም» እያለ ይቀጥላል:: በመጨረሻም፣ «... እንደ ወላጅ አባትነትዎ በሰብዓዊ ርህራሄ ልጄን እንዲፈቱልኝ እግርዎ ስር ወድቄ እለምንዎታለሁ::» በማለት ይደመድማል::

እንዲህ ዓይነት እና መሰል አያሌ ደብዳቤዎች ጠ/ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ሊደርሱ ይችላሉ:: በቅርቡም ጠ/ሚኒስትሩ ይህንን ሁላ፣ እያንዳንዱን እያገላበጡ ማንበብ ሌላውን ሥራ የሚያስቀር መሆኑን መግለፃቸው ይታወሳል:: ያም ሆነ ይህ፣ ወ/ሮ አልማዝ ልጃቸውን ብርቱካን ሚደቅሳን ይፈቱላቸው ዘንድ ለአቶ መለስ ደብዳቤ ያስገቡት በዚህ ባገባደድነው ዓመት ነበር::

### «ያለ አግባብ የታሰረች»

ጥር 7 ቀን 2002 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (የተ.መ.ድ) የሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት አንድ ሪፖርት አውጥቶ ነበር:: የምክር ቤቱ ሪፖርት በስሩ የሚንቀሳቀሰው አግባብ የለሽ እስረን የሚመለከተው ግብረ-ኃይል ያጠናቀረውን ውሳኔና አስተያየት መሠረት ያደረገ ነው:: ግብረ-ኃይሉ በ29 ሀገራት ላይ ያደረገው የአግባብ የለሽ እስሮች ምርመራ አስተያየቶች ይፋ በተደረገበት በዚህ የምክር ቤቱ ሪፖርት ላይ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አለአግባብ በእስር ላይ ከሚገኙ ግለሰቦች አንዷ መሆኗ ሰፍሯል::

የሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤቱ አግባብ የለሽ እስርን በሚመለከተው ግብረ-ኃይል አማካኝነት የወ/ት ብርቱካንን ጉዳይ መመልከት የጀመረው በጥር ወር 2001፣ ማለት ይቅርታው ተነስቶ የእድሜ ልክ እስራቱ ከፀናባት ከወር በኋላ ነበር:: የይቅርታውን ጉዳይ፣ ተገልሎ መታሰርን፣ ጉብኚ መከልከልንና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ነበር ሲያጣራ የቆየው:: ከኢትዮጵያ መንግስት ጋርም በመገናኘት ጉዳዮን መርምሯል::

በግንቦት ወር 2001 በወጣ የምክር ቤቱ ሪፖርትም የኢትዮጵያ መንግስትን ምላሾች ማየት ይቻላል:: ለወ/ት ብርቱካን ከሌሎች እስረኞች የተለየ አያያዝ እንዳልተደረገ፣ በቤተሰብ የመጐብኘት መብቷ እንዳልተገደበ፣ በጠበቃዋ እንደምትጐበኝ፣ ... ያስረዳው የኢትዮጵያ መንግስት የይቅርታውም መነሳት ለደጋፊዎቿ ባደረገችው ንግግር ይቅርታ አለመጠየቋን መናገሯን ያስታውሳል:: አስከትሎም፣ «የመጀመሪያውን እና ሁለተኛውን የይቅርታ ቅድመ ሁኔታዎች በተቃረነ መልኩ ተንቀሳቅሳለች፤ ይኸውም ለተፈፀሙት ድርጊቶች በግል እና በጋራ ኃላፊነቱን መቀበል እና ወደፊትም እንዲህ ካለ ተግባራት መቆጠብ::» በማለት ይቀጥላል::

አንድን ግለሰብ «አለአግባብ የታሰረ» ለማለት ግብረ-ኃይሉ የተቀመጡለት ሶስት መመዘኛ ዎች አሉ፤ ይሁንና ግን የግለሰቡ ጉዳይ በአንዱ ብቻ እንኳን ቢወድቅ አለአግባብ ለመታሰሩ በቂ ነው:: በሌላ በኩል የወ/ት ብርቱካን ጉዳይ ግን በሶስቱም መመዘኛዎች ስር መውደቁን የምክር ቤቱ ሪፖርት ያስረዳል:: መመዘኛዎቹ ምን ምን ናቸው? በምርመራው የተገኙ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ አንደኛ - ነፃነትን ለመንፈግ የሚያስችል ምንም ሕጋዊ መሠረት በግልፅ ለመጥቀስ የማይቻል ሲሆን፤ ሁለተኛ - ነፃነት ክልከላው የመነጨው በሁል-አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጾች የተቀመጡ መብቶች ወይም ነፃነቶች፣ ወይም በሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን የሰፈሩ መብቶች ወይም ነፃነቶች በመተግበራቸው ከሆነ፤ ሶስተኛ-ክፍትሃዊ የፍርድ ሂደት ጋር የሚያያዙ በዓለም አቀፍ ሰነዶች የተካተቱ መስፈርቶች በሙሉ ወይም በከፊል አለመከበራቸው ለነፃነት ክልከላው አስተዋጽኦ ሲኖራቸው ነው::

እናም ምክር ቤቱ ጥር 7 ቀን 2002 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በግብረ-ኃይሉ 2ኛ እና 3ኛ መመዘኛዎች፣ እንዲሁም ይቅረታው ከተነሳበት ቀን ጀምሮ በ1ኛ መመዘኛው መሠረት በኢትዮጵያ መንግስት አለአግባብ መታሰራቸው ተገልጽዋል:: ይህ ምክር ቤት ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስር ያለ ተቋም በመሆኑ ብርቱካንን ለማስፈታት ለሚደረጉ ዓለማቀፋዊ ጫናዎች አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ታምኖ ነበር::

> «ወይዘሮ ብርቱካን ከእናትዋና ከልጅው ጋር ሁሉም እያለቀሱ ሲለያዩ እንባቸው መሬቱን አያደርቅም? ልጅ ለእናትዋ ሕመምዋን በመናገርዋ ብቻ የብርቱካን እናት፣ ብርቱካንና ልጅዋ ሶስት ትውልድ ሲያለቅስ እግዚአብሔር አያይም? ዓለም አይታዘብም?

### የሶስት ትውልድ እንባ

ስለብርቱካን የጤና ሁኔታ ወላጅ እናትዋ በታህሳስ 2002 ዓ.ም የተናገሩት ነበር፤ ለጠ/ሚኒስትር መለስ በፃፉት ደብዳቤ፤ «በአሁኑ ጊዜ ጤናዋ ታውኮ ሰውነቷ ተጐሳቁሎ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ላይ ስትገኝ ትሞትብኛለች እያልኩ ነጋ ጠባ በጭንቀት ላይ እገኛ ለሁ» በማለት:: ታዲያ በመጋቢት ወር ብርቱካንን ጠይቀው ሲመለሱ የጤናዋ ሁኔታ መባሱንና መታመሟን ለፓርቲዋ ያሳውቃሉ:: ፓርቲዋም «የሕሊና እስረኛዋ ብርቱካን ሚደቅሳ በህይወት የመኖር መብት ይከበር» በሚል መግለጫ አወጣ፤ ብርቱካን በገለልተኛ የሕክምና ቡድን እንድትመረመርም ጠየቀ::

በዚህ ጊዜ ነበር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ለኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ የፃፉትን ግልፅ ደብዳቤ በአወራምባ ታይምስ ጋዜጣ ያነበብነው፤ መጋቢት 18 ቀን 2002 ዓ.ም:: ፕሮፌሰሩ የአክብሮት ሰላምታቸውን ካቀረቡ በኋላ፣ «ይህንን ደብዳቤ የምፅፍልዎ ተራራ ላይ ወጥቼ እሪ! ኡ! ኡ! የሕግ ያለህ! እያልሁ እንድጮህ የሚገፋፋ ስሜት ሰንጐ ስለያዘኝና እግዚአብሔርና ህሊናዬ ስላስገደዱኝ ነው እንጂ ላስቸግርዎ ብዬ አይደለም» ይላሉ:: ይቀጥላሉ::

«ወይዘሮ ብርቱካን ከእናትዋና ከልጅው ጋር ሁሉም እያለቀሱ ሲለያዩ እንባቸው መሬቱን አያደርቅም? ልጅ ለእናትዋ ሕመምዋን በመናገርዋ ብቻ የብርቱካን እናት፣ ብርቱካንና ልጅዋ ሶስት ትውልድ ሲያለቅስ እግዚአብሔር አያይም? ዓለም አይታዘብም? ይህንን ሁነት በሰብዓዊነት ሚዛን፣ በመንፈሳዊና በጨዋነት ሚዛን፣ በሕጋዊነት ሚዛን፣ በታሪክ ሚዛን ሲመለከቱት የሶስት ትውልድ ለቅሶና ሐዘን የት ይደርሳል? የት ያደርሳል?» እያሉ ይጠይቃሉ:: በመጨረሻም ለፕሬዝዳንት ግርማ የፃፉትን ደብዳቤ «ትሑት ታዛዥዎ» በማለት ከመደምደማቸው በፊት፣ «ለወይዘሮ ብርቱካን የሕክምና መንገድ እንዲከፍቱ በኢትዮጵያ አምላክ እማፀንዎታለሁ» ብለዋል::

በወቅቱ ጠ/ሚኒስትር መለስ ለውጭ ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ላይ ስለብርቱካን የጤና ሁኔታ ተጠይቀው፣ «የጤንነት ሁኔታዋ የተሟላ ነው፤ በርግጥ ባገኘሁት መረጃ መሠረት ክብደቷ ጨምሯል፤ ያ ደግሞ ተገቢ የሰውነት እንቅስቃሴ ባለማድረግ የተፈጠረ ነው» ብለው ነበር::

ሂውማን ራይትስ ዎች እና የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርቶች ግን የብርቱካን የጤና ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ነው የሚል መግለጫ ይፋ ማድረጋቸው ይታወሳል:: እነዚህ ሪፖርቶች ይፋ በተደረጉ ማግስትም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አንድ ፕሮግራም ቀርቦ ነበር፤ በማረሚያ ቤት የእስረኞች አያያዝን በተመለከተ::

በፕሮግራሙ የፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ ዳይሬክተር የሆኑትና ቅንጅቶች ከእስር ሲፈቱ ከሽማግሌዎቹ አንዱ የነበሩት ፓስተር ዳንኤል ገብረሥላሴ ብርቱካንን ጨምሮ ጥቂት ሴት እስረኞችን ሲጐበኙ ይታያል:: «የፖስተር ዳንኤል ጭብጥ የሳተ ምስክርነት» በሚል ርዕስ ሚያዝያ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ ፅሁፉን ያሰፈረው የጋዜጣው ማኔጂንግ ኤዲተር ዳዊት ከበደ «በእኔ እምነት በብርቱካን ዙሪያ ያሉ አወዛጋቢ ነገሮችን ለማጥራት መፍትሔው ምስሉን በቴሌቪዥን ማቅረብ ሳይሆን እንደማንኛውም እስረኛ ማንም ወዳጅ ዘመድ ገብቶ እንዲጠይቃት መፍቀድ ነው» ብሎ ነበር::

### አንድ ብርቱካን ለሁለት!

ነገሩ ሌሎች አስተዳደራዊ ሁኔታዎች ይደመሩበት እንጂ አንድነት ፓርቲ መድረክን የመቀላቀሉና አቶ ስየ እና ዶ/ር ነጋሶ የፓርቲው አባል ሆነው የኃላፊነት ቦታ መያዛቸው የጉዳዩን ጥንስስ እንዳፈላው ይነገራል:: «መርህ ይከበር» የሚሉት መርህ ጥሳችኋል ተብለው ከፓርቲው እንደተወገዱ ተነገራቸው::

ያባረረው አካል የፓርቲውን ሕጋዊ ሠርተፍኬት ይዟል፤ የተባረረው ደግሞ ፕ/ር መስፍንን ይዟል:: ከውጭ ሆኖ የሚመለከተው ደግሞ «ተዉ፤ ይኼ ለኢህአዴግ የሚጠቅም ይሆናል» ይላል፤ «ካልደፈረሰ አይጠራም» ሲል የነበረም አልጠፋ:: የፓርቲው የውስጥ ግጭት በሚፋፋምበትን ቦታ እያነፈነፈ ደረሶ «ይኸው ተጋደሉላችሁ» በሚል ዓይነት ሁኔታውን ለሕዝብ ይፋ ማድረጉን የተያያዘው ኢቴቪ ምስጋና እና ውግዘትን በተመሳሳይ ማግኘቱ ያስገረመው አይመስልም ነበር::

የሁለቱ ወገኖች እሰጣ-ገባና ውዝግብ ምርጫው ቀናት እስኪቀሩት ድረስ የዘለቀ ሆነ:: «መርህ ይከበር» የሚለው ቡድን አባላት መስፈርቱን እንዳሟሉ ገልፀው የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባኤ ጠሩ:: ጉባኤውም ሚያዚያ 10 ቀን 2002 ዓ.ም በኮከበ ፅባፅ ት/ቤት ተካሄደ:: መካሄድ ብቻ አይደለም አዲስ የአመራር አባላትን በቀድሞዋቹ የመተካት ውሳኔ አስተላለፈ:: በአዲሱ አመራር ፕ/ር መስፍን ም/ሊቀመንበር ተብለው ተሾሙ፤ ያው የሊቀመንበርነት ቦታው የወ/ት ብርቱካን:: ይኼኔ ነው ሚያዚያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም የወጣው *ሪፖርተር* ጋዜጣ (ረቡዕ ዕትም) አስገራሚ ርዕስ ያስነበበን - «አንድ ብርቱካን ለሁለት»::

ይህ ጉባኤ ሌላም ተያያዥ ውሳኔ አስተላልፎ ነበር፤ «አሁን በአመራር ስም የተቀመጡ ግለሰቦች የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት በኦዲት አስመርምረው ለተመረጠው አዲስ አመራር እንዲያስርክቡ» የሚል:: ይሁንና ግን ውሳኔውን ተከትሎ ማያዚያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም ንብረትና ሰነዳ ሰነድ ለመረከብ አንድነት ቢሮ የተገኘው አዲሱ አመራር ወይም የመርህ ይከበር አባላት አይሆኑ ግጥመት ገጠማቸው:: ለወትሮ እንዲህ ባለ የፓርቲው የውስጥ ሽኩካ «ድራሹም አይገኝ» እየተባለ ሲታማ የነበረው ፖሊስ ፕሮፌሰር መስፍንን ጨምሮ 11 አባላቱን በቁጥጥር ስር አዋላቸው::

በወቅቱ አውራምባ ታይምስ ቃለ-ምልልስ ያደረገላቸው የአንድነት ፓርቲ ም/ሊቀመንበር ኢንጅነር ግዛቸው፣ ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት እቤታቸው ድረስ ሄደው ፕ/ር መስፍንን በጉዳዩ ላይ እንዳነጋገሯቸው ይገልፃሉ:: እሳቸውን ጨምሮ የሥራ አስፈፃሚው በሙሉ ለመልቀቅ ዝግጁ መሆኑንና ጉዳዩን ተወያይተው መፍታት እንዳለባቸው ለፕ/ር መስፍን መንገራቸውን ያስታወሱት ኢንጅነሩ፣ «ይህን ስለው እሱ ግን ይኼማ የ«ጋንግስተር» ሥራ ነው፤ እንዴት ሊሆን ይችላል ብሎ አፌዘብኝ» ማለታቸው ይታወሳል:: ፕሮፌሰሩ ደግሞ በኩላቸው በዋስ ከተለቀቁ በኋላ «እነ ግዛቸው ዳያስፖራ ጋ ሄደው እኛን በወያኔነት ይከሳሉ፤ እዚህ ደግሞ መንግስት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዳይካሄድ አደናቃፊ ሆነዋል በሚል ይከሰናል» በማለት ለአውራምባ ታይምስ ገልፀው ነበር::

ሆነም ቀረ ጉዳዩ ከዚህ በኋላ እየረገበ ይምጣ እንጂ በዚህ ባገባደድነው ዓመት «አንድ ብርቱካን ለሁለት» መባሉ አይዘነጋም::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# በፖለቲካ አቋማቸው ትኩረት የሳቡት ፖለቲከኛ- አቶ ያሬድ ጥበቡ

በግዛው ለገሠ

አዲስ አበባ ነው የተወለዱት፤ ለዚያውም ፒያሳ ደጃች ውቤ:: ወደ አሲምባ በማቅናት በኢ.ህአፓ የትጥቅ ትግል የተሳተፉት አቶ ያሬድ ጥበቡ ከአቶ ታምራት ላይኔ፣ አቶ አዲሱ ለገሠ እና ከአቶ በረከት ስምዖን ጋር በመሆን ኢ.ህዴንን መስርተዋል:: «አዲሱን ከዚርና፣ እኔን ከፊንፊኔ፣ በረከትን ከጎንደር ያገናኘን የኢ.ህአፓ ፖለቲካ ቢሆንም ያዳበርነው ፍቅር ግን ያን የዘለለ ይመስለኛል» በማለት አቶ ያሬድ ስለ ቀድሞ ጓደቻቸው ያጫወቱን ሚያዚያ 2 ቀን 2002 ዓ.ም ከአውራምባ ታይምስ ጋር በነበራቸው ቆይታ ነበር::

በኢ.ህዴን ድርጅት ውስጥ በተፈጠረ ልዩነት በ1970ዎቹ መጨረሻ ለስደት የተዳረጉት አቶ ያሬድ፣ በ1997 ምርጫ በቀስተ ደመና ፓርቲ በኩል የቅንጅት አባልና የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ አሰባሳቢ ነበሩ:: ከምርጫው ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የቀድሞው ቅንጅት በደሴና ሌሎች ከተሞች ባዘጋጃቸው ህዝባዊ ስብሰባዎች ተሳታፊ ነበሩ::

በምርጫው ማግስት ሰኔ 01/1997 ዓ.ም በተቃዋሚ ደጋፊዎችና በጸጥታ አስከባሪዎች መካከል በተፈጠረው ግጭት ከ40 በላይ ዜጎች ህይወታቸውን ሲያጡ አቶ ያሬድ በሰላ ብዕራቸው «አልቅሼ ዝም ከምል» በሚል ርዕስ የቀድሞ ጓደቻቸው አቶ አዲሱና አቶ በረከትን የሚተች መጣጥፍ በ«ሀዳር» ጋዜጣ ተስተናገደ:: በጥቅምት ወር 1997 የቅንጅት አመራሮች፣ጋዜጠኞችና የስቪክ ማህበራት መሪዎች ሲታሰሩ አቶ ያሬድም በሌሉበት ህገመንግስቱን በሀይል በመናድ ወንጀል አብረው ተከሰሱ:: ከዚህ በኋላ ነበር አቶ ያሬድ በሰላማዊ ትግል የትም እንደማይደረስ በተለያየ አጋጣሚ ቁጣቸውን መግለጽ የጀመሩት በ1998 ዓ.ም ሰኔ ወር በውጭ የሚገኙ የተቃዋሚ ኀይሎች (አርበኞች ግንባር፣ ኦነግ፣ ኦብነግ፣ቅንጅት እና ሌሎች) ተቀናጅተው ትብብር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ (Alliance for Freedom and Democracy) የተሰኘ ግንባር ሲመሰርቱ አቶ ያሬድ (ጌታቸው ጀቤሳ በተሰኘው የብዕር ስማቸው) «በሽብሸባ እንቀበላቸዋለን» የሚል ርዕስ ያለው መጣጥፍ በማዘጋጀት ለተለያዩ ድረገጾችና ሬዲዮኖች ላኩ በግንባሩ ውጤታማነትም እንደሚተማመኑ በመጣጥፋቸው ገለጹ::

አቶ ያሬድ ጥበቡ በዚህ ባገባደድነው ዓመት ለአውራምባ ታይምስ በሰጡት ቃለ-ምልልስ የብዙዎችን ትኩረት የሳበ አቋም አንፀባርቀዋል:: በርግጥም እንዲህ የጥላቻ ፖለቲካ በተንሰራፋበት አገር እንዲህ ያለውን አመለካከት የሚጠብቀው ላይኖር ይችላል:: አቶ ያሬድ ግን «ሁሌም ጓደኝነት ፖለቲካን ይዘላል ብዬ አስባለሁ» ባይ ናቸው:: አንድ ገጠመኛቸውን አጫወቱን:-

*የቅንጅት መሪዎች እስር ላይ እያሉ አንድ ምሽት ብርሃነ መዋ ቤት ተሰባስበን ነበር:: ስብሰባው አልቋጭ ብሎ ሲራዘም «በሉ እኔ ዳዊት ዮሐንስ ጋር ሲልቨር ስፕሪንግ ላንጋኖ ምግብ ቤት ቀጠሮ ስላለኝ መሄዴ ነው» ስል አንዳርጋቸው [አሁን የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ዋና ፀሐፊ ናቸው] ቱግ አለ:: «ከነብስ ገዳዮች ጋር የሚያገናኝህ ምክንያት ምንድነው? ... ወዘተ» ብሎ ብዙ ለመናገር ሞከረ:: «የኛ ጓደኝነት ፖለቲካን ይዘላል፤ ሄጄ ጭራዬን አልቆላም፤ ተቃውሞዬን አሰማዋለሁ፤ ቅሬታዬን እገልፅለታለሁ፤ እንከራከራለን፤ ደግሞም በመሃል እንደንሳለን፤ በሰው ልጅ የመቀየር ኃይል ላይ ተስፋ አልቆርጥም» የሚል ዲስኩር ሰጥቼው ወደ ቀጠሮዬ አቀናሁ::*

የአቶ ያሬድን ቃለ-ምልልስ አውራምባ ታይምስ ላይም ሆነ በድረ-ገፆች አማካኝነት ያነበቡ በውጭም፣ በአገር ውስጥም የሚገኙ አያሌ ኢትዮጵያዊያን የተለያየ አስተያየት ሰንዝረዋል:: የሰውዬውን ጤንነት መጠራጠራቸውን የሚገልጹ ደዋዮችም ነበሩ:: ይህንን አስመልክተው ወደ ዘጠኝ የሚጠጉ መጣጥፎች ለአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ተልከው ነበር:: «ሕዝብ የመሆን ጣጣ» በሚል ርዕስ ከኢንግላንድ፣ ሊድስ ተልኮ በጋዜጣው ሚያዚያ 23 ቀን 2002 ዓ.ም የተስተናገደው የአቶ ህሩይ አማኑኤል ፅሁፍ ቃለ-ምልልሱን መሰረት ካደረጉ መጣጥፎች አንዱ ነው:: ፀሐፊው ይህንን ፅሁፍ ያዘጋጁት ቃለ-ምልልሱን በማንበባቸው እንደሆነ ይገልፃሉ:: «አቶ ያሬድ እንደነ አቶ አዲሱ እና በረከት ስምዖን ላሉት የትግል ጓደኞቻቸው ያላቸው የወዳጅነት ስሜት ከሰብዓዊነት አኳያ የሚከበርም የሚበረታታም ነው» የሚለው የአቶ ህሩይ ፅሁፍ፣ «የፖለቲካው ጣጣ አንዳንዱን የድሃ እምባና ደም አፍሳሽ ባያደርገው ኖሮ በርግጥም ማህበራዊ ህይወትን የሚያጠቁር ጥቀርሻ መሆን አይገባውም» በማለት የአቶ ያሬድን አቋም በአንድ ወገን ይደግፋል::

ይሁንና ግን ፅሁፉ በዚህ አያበቃም:: «በአንፃሩ እስከ ዛሬ አስቤ የማላውቀው የፖለቲካ ባላንጦች የወዳጅነት መስመሩ እስከምን ነው የሚለው ጥያቄ መልሶ መላልሶ ወደ አዕምሮዬ መጥቷል» የሚሉት ፀሐፊው፣ «እነ አቶ ያሬድና ሌሎቹም የ60ዎቹ ፖለቲከኞች ዘላቂ ጥቅም እንጂ ዘላቂ ጠላት የለም ዓይነት ፍልስፍና ያላቸው ይሆን?» በማለት ይጠይቃሉ:: «እነርሱ ከፖለቲካው ግመትና ፍንዳታ በኋላ በየሬስቶራንቱም ተገናኝተው ገብስ ገብሱንም ይሁን ሌላውን ይጨዋወታሉ:: አንዳንዶቹ ግን ቢያንስ ቢያንስ ከመሬታቸው ወይም ከሥራቸው ተፈናቅለው የዕለት ጉርስም ይርባቸዋል» ካሉ በኋላ «ሕዝብ የመሆን ጣጣ» ማለት ይህ እንደሆነ ይገልፃሉ::



አቶ ያሬድ ይህ እና መሰል ትችት ሊገጥማቸው እንደሚችል አስቀድመው ተናግረዋል:: «ይህን ሁሉ ስናዘዝ፣ በተለይ በበረከት ጥላቻ ያበዱና በአድራጎቱም ሆነ አልፎ አልፎ በተናገራቸው ነገሮች የሚጠሉት የአገሬ ሰዎች እጅግ ብዙ መሆናቸውን እያወቅሁ ነው:: ነገ ተፋሰሱ ወደኔ እንደሚመጣም አውቃለሁ፣ ሆኖም ለፍቅር የሚከፈል መስዋዕትነት አድርጌ ለመቀበል ፍቃደኛ ነኝ:: ሁሌም ጓደኝነት ፖለቲካን ይዘላል ብዬ አስባለሁ» ብለው ነበር::

በተለይ ከወዲያ ፅንፍ የሚገኘው የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባል የአቶ ያሬድ ነገር ሊያስደነግጠው ይችላል:: በአሁኑ ሰዓት የየትኛውም ፓርቲ አባል አለመሆናቸውን ይናገራሉ:: «ከጥቂት የኦሮሞ ወጣቶች ጋር በመሆን "የጥናት ክበብ" አቋቁመን፣ ዲሲ በሚገኘው የኦሮሞ ኮሙኒቲ ማዕከል ቅዳሜ ቅዳሜ እየተሰባሰብን «ለምንድን ነው ሕዝባችን ከአገዛዝ ራሱን ማላቀቅ ያልቻለው?» በሚለው ጥያቄ ዙሪያ እንላቀሳለን እንቆዝማለን:: ተስፋቸውን ያጭሩብኛል:: ልምዴን አካፍላቸዋለሁ» በማለት አቶ ያሬድ አሁን የሚገኙበትን ሁኔታ ይገልፃሉ::

አቶ ያሬድ ጥበቡ ከ97 ምርጫ በኋላ በተከሰተው ቀውስ ምክንያት በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል መዝገብ ውስጥ ከተካተቱ ተከሳሾች ውስጥ ነበሩ:: ሆኖም የእሳቸውና ጥቂት ተከሳሾች ጉዳይ «እጃቸው በተያዘ ጊዜ ክሳቸው ይንቀሳቀስ» የሚል ውሳኔ ተሰጥቶበታል:: በዚህ ምክንያትም የተቀሩት የቅንጅት አባላት ከእስር የተፈቱበት ይቅርታ «ተጠቃሚ» አይደሉም፤ በተያዙ ጊዜ ለፍርድ ይቀርባሉ:: «ወደ አገሬ መመለስ እንኳን አልችልም፤ በህይወቴ ከደረሰብኝ ጉዳት ሁሉ አጥንቴ ውስጥ ገብቶ ያላመጠኝ እምዬን ቆሜ መቅበር አለመቻሌ ነበር» በማለት እናታቸውን ባለመቅበራቸው ይቆጫሉ:: «... ቆሜ ልቀብራት እንደማልችል ስረዳ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: የበረሃ እንግልቴን እንኳ ቆጥረው "ገብተህ ስትወጣ አላየንም፤ ለሦስት ቀን ብቻ ፈቅደንልሃል" ሊሉኝ በተገባ:: በእነርሱ ቦታ ብሆን አደርገዋለሁ ብዬ አስባለሁ::» ነበር ያሉት አቶ ያሬድ::


ሆነም ቀረ ይህ የአቶ ያሬድ ከጥላቻ፣ ከቂም፣ ከበቀል እና ከእልህ የፀዳ የፖለቲካ አቋም ብዙዎችን ያስደመመ፣ ብዙዎችን ያስገረመ ነበር:: ፖለቲካ በሰፈር ልጅነትና በወለድ አግድ ሳይሆን በዕምነትና ራዕይ መካሄድ አለበት የሚል አመለካከት ያላቸው አቶ ያሬድ አሁን በሥልጣን የሚገኙ የኢ.ህአዴግ አመራሮች ጓደኝነታቸው እንደሚናፍቃቸው ሲናገሩ በግልፅ ነው:: «ስለጥንት የትግል ጓደኞቼ "ሳቃቸው ይናፍቀኛል" ስል፣ እንደዘመኑ ሰው ወለድ አግድ የሚያዝ ልቦና ኖሮኝ አይደለም:: ሥራም ለማመልከት ፈልጌም አይደለም:: ምንስ ሥራ ይመጥነኛል? የመለስ ወንበር እንደሆነ ሁለት ቦታ አይከፈል?» ይላሉ:: አቶ ያሬድ ጥበቡ ያንፀባረቁት አመለካከት ብዙዎችን ለረዥምም ጊዜ ያነጋገረ ከመሆኑ ባሻገር በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ያልተለመደ አቋም ሆኖ ተገኝቷል:: በዚህ ባገባደድነው ዓመት እጅግ ትኩረት የሳበ የፖለቱካ አቋም ነበር ስትልም አውራምባ ታይምስ መርጣዋለች::

ማስታወቂያ

ጥምረት አግሮ ኢንዱስትሪ አ. ማ

Timret Agro Industry S.Co.

እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ



በአጭር ጊዜ ወደ ስራ የገባ አ.ማ
አክሲዮን ማህበሩ የካፒታል
አቅሙን ለማጠናከር የአክሲዮን
ሽያጩን ቀጥሏል::

አክሲዮኑን አሁኑኑ በመግዛት
ቀድመው የትርፍ ተካፋይ ይሁኑ

በሸኖ በቅርብ ጊዜ ሊተከል
በዝግጅት ላይ ያለ የወተት
ማቀነባበሪያ ፋብሪካ

ሰንዳፋ አካባቢ የተጀመረው
የወተት ማምረት ሥራ

የቦርድ አባላት
1. ዶ/ር ታፈሰ መስፍን
2. አቶ ዳመኑ በቀለ
3. አቶ ዱባለ አድማሱ
4. ወ/ሮ አሚናት ኑር መሀመድ
5. አቶ ገበየሁ በቀለ
6. አቶ ሀብታሙ ገቢሳ
7. አቶ መንገሻ ደ/ክርስቶስ ናቸው::





ሰንዳፋ አካባቢ የተጀመረው የወተት ማምረት ሥራ







የዶሮ እርባታ | የንብ እርባታ | የእርሻ ሥራ

አድራሻ:- ቦሌ መድሀኒያለም ፊት ለፊት ሸገር ሐውስ ቢሮ ቁጥር 203 ስልክ 011850 09 43/0911 122704



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ሀ ዩ ሰ ት ም

# አወዛጋቢው የአቡነ ጳውሎስ «የምስክርነት ሐውልት»

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በየዓመቱ የሚከበር በዓል ነው - የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዓለ ሢመት:: «አቡነ ጳውሎስ ለሢመተ ፕትርክና በተመረጡበት ቀን የሚከበረው ይህ በዓል፣ ለቤተክርስቲያኗ የነፃነት በዓል ነው» ያሉት የአውራምባ ታይምስ የሐምሌ 10/ 2002 ዓ.ም እትም ተጋባዥ ጸሐፊ የነበሩት ባሮክ ዘሳልሳይ ሺ.ህ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን «ከኮፕት ቤተክርስቲያን ሞግዚትነት ተላቃ ከራስዋ አበው፣ መነኮሳት እና ሊቃውንት በተመረጡ አባቶች ለመመራት የበቃችበት» መሆኑ ለምን በዓለ ሢመቱ እንደነፃነት በዓል እንደሚታይ አመክንዮአቸውን አቅርበው ነበር:: እናም፣ ይህ በቤተክርስቲያኗ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የዚህኛው ዓመት በዓለ ሢመት - የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ 18ኛ ዓመት በዓለ ሢመት - የተከበረው በሐምሌ 4/2002 ዓ.ም ላይ ነበር:: እንዲሁም፣ በዓለ ሢመቱ ከተከበረበት ቀን ጋር እንዲገጥም የታቀደለት እና «ከ300 ሺ.ህ ብር በላይ የፈጀው» የአቡነ ጳውሎስ «የምስክርነት ሐውልት»ም በይፋ የተመረቀው በተመሳሳይ ቀን ነበር::

ከሐውልቱ መገንባት ጋር በተያያዘ፣ ሐውልቱን የማቆም እቅድ ይፋ ከተደረገበትና በምረቃ ሥነ-ሥርዓት እስከተቋጨበት ጊዜ ድረስ በርካታ ውዝግቦች ተደምጠዋል:: አብዛኞቹ እጅግ ጽንፈኝነት የታየባቸው አመለካከቶች ነበሩ:: ከጽንፍነት በላይም አልፈው የሄዱ ነበሩ ብንል አጋነናችሁት እንደማንባል እርግጠኞች ነን:: የሐውልቱ መቆም ካለው ሃይማኖታዊ አንደምታ ባሻገር፣ የሚያስገርሙ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ «ትንታኔዎች» ከሐውልቱ ግንባታና ምርቃት ጋር በተያያዘ ተሰንዝረዋል:: ሆኖም፣ የሐውልቱ መቆም ሃይማኖታዊ አግባብነት አለው ወይስ የለውም በሚለው ላይ የተሰጡት ነጥቦች እጅግ ትኩረት የሚስቡ ሆነው አግኝተናቸዋል::

## «አቡነ ጳውሎስ የምስክርነት ሐውልት ይገባቸዋል!»

**«ሐውልት ማቆም በቤተክርስቲያኗ ሕግ፣ ቀኖና ሥርዓት የተደገፈና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፣ መሰረትም አለው»**

የሐውልቱን መቆም የደገፉ ወገኖችን የመወከልና የመደገፍ አቋም የተንጸባረቀበትና የመንበረ ፓትሪያርክ የጠቅላላ ቤተክህነት ሕጋዊ ወኪል በሆኑት ሊቀካህናት ጌታቸው ዶኒ የተፃፈ ጽሑፍ በአውራምባ ታይምስ የሐምሌ 10/ 2002 ቁጥር 124 እትም ላይ ተስተናግዶ ነበር - *«ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የምስክርነት ሐውልት ይገባቸዋል»* በሚል ርዕስ:: የአቡነ ጳውሎስ ሐውልት መተከል ከቤተክርስቲያኗ ሥርዓትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንፃር አግባብነት እንዳለው በፅሁፋቸው የተከራከሩት ሊቀካህናት ጌታቸው፣ አምስት አይነት ሐውልቶች እንዳሉ ያስረዳሉ - የሙታን፣ የአምልኮ ጣዖት፣ የሥልጣኔ፣ የመታሰቢያና የምስክርነት ሐውልቶች:: የምስክርነት ሐውልት «የሃይማኖት አባቶች የክርስቶስ እንደራሴዎች ገና በሕይወት እያሉ ለምስክርነት እንዲያቆሙት የታዘዘ የፈጣሪ መመሪያ ነው» ለሚለው መከራከሪያ የተወሰኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን ሰጥተዋል፤

፩

### ያዕቆብ በሕይወት ሳለ የራሱን ሐውልት አቁሟል

እግዚብሔር «ለእስራኤል ሁሉ አባት ያዕቆብ በሕልም ተገልጦለት ከነገረውና ከባረከው በኋላ ስሙን ቀየረለት:: «እስራኤል» ብሎ ጠራው:: «ያዕቆብም ሕልሙን ባየበት ስፍራ ተንተርሶ የነበረውን ደንጊያ መሰረት በማድረግ የምስክርነት ሐውልት አቆመ (ዘፍ 28፣18፤ 31፣45-54)::

፪

### አቤሴሎም ለራሱ ሐውልት አቁሟል

የንጉስ ዳዊት ልጅ አቤሴሎም በሕይወት ሳለ በስሙና በራሱ ቅርፅ ሐውልት አቁሟል:: ለማቆሙም ምክንያቱ ልጅ አልነበረውምና ነው:: «ለዚህም ምስክርነት ይሆንው ዘንድ በእስራኤል ዋና ከተማ አደባባይ ላይ ሐውልቱን ዘቆመ (2 ሳሙ 18:18)::

፫

### ኢያሱ 12ቱ የእሰራኤል መሪዎች በሕይወት ሳሉ ሐውልት አቁሞላቸዋል

ከሙሴ በኋላ የእስራአልን ሕዝብ ለመራው ኢያሱ፣ እግዚአብሔር «ጠላቶቹን መትቶለት የዮርዳኖስ ባሕርን እንደመሬት እየረገጡ እንዲሻገሩ በማድረጉ፣ የፈጣሪን እርዳታ ለምስክርነት እንዲሆን የ12ቱን የእስራኤል መሪዎች ሐውልት በዮርዳኖስ ባሕር ዳርቻ በስማቸውና በቅርፃቸው አቁሞላቸዋል::» (ኢያሱ 4፤ 1-9)

፬

### የኢያሱ የምስክርነት ሐውልት

እያሱ «አገልግሎቱን፣ የሕጉንና የአስተዳዳር ሥርዓቱን ለሕዝቡ ሲሰጥና ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን ሲያደርግ፣ በሕይወት ሳሉ በራሱ ስምና መስል ሐውልት አሰርቶ በእግዚአብሔር ቤት ደጅ አቁሟል»:: ከሰራው ሐውልት ፊት ቆሞም፣ «እነሆ ይህ ሐውልት እግዚአብሔር የተናገረንን ሁሉ ሰምቷል:: በእኛም ይመሰክርብናል:: እናንተም በአምላካችሁ ዘንድ እውነተኞች ሆናችሁ ባትገኙ ምስክር ይሆንባችኋል» ብሏቸው ነበር:: እናም የራሱን ሐውልት - የመስክርነት ሐውልት - «ምስክር አድርጓል»::



፭

### ታሪካዊ የድጋፍ መከራከሪያ

ግብጽ፣ ሕንድ፣ አርመንና ሶሪያ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጋር ሕብረት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት እንደሆኑ የሚያወሱት ሊቀካህናት ጌታቸው ዶኒ፣ አብያተ ክርስያናቱ «የሃይማኖት መሪያቸውን መልክ በሰውነታቸው በመነቀስ፣ በመቀለምና በመወቀር፣ ብሎም ገና በሕይወት እያሉ ሐውልታቸውን በማቆም በታሪክ ቀዳሚዎች» መሆናቸውን ያስረግጣሉ:: በአጠቃላይይ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ «ሐገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ የሥራ ግንኙነት በጥልቀት በማብራራትና በማስረዳት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት ፕሬዝዳንት የዓለም ሃይማኖቶች በሰላምም የክብር ፕሬዝዳንት፣ ለቅድስት ቤተክርስቲያን የወንጌል አገልግሎት የተጉ በመሆናቸው» ሐውልቱ «ይገባቸዋል» ይላሉ ደጋፊዎቻቸው::

፮

### ተዓምራዊ ክስተትና ምሪት

በሐምሌ 4/2002 በቦሌ መድኃኔዓለም ካቴድራል ደጀ ሰላም ለቆመው የምስክርነት ሐውልት ስማቸው በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የቃሊቲ ሰፈረ ገነት ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያም እና ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ አባላትና ምዕመናን ናቸው:: ለአቡነ ጳውሎስ የምስክርነት ኃውልት እንዲያቆሙ ያነሳሳቸው ልዩ ተዓምራዊ ክስተት እና ምሪት» መሆኑ የተፃፈ ነው:- «የቃሊቲ ደብረ ቁስቋም ማርያም ታቦተ ሕግ ለጥምቀት በዓል እንደወጣች ወደ መንበረ ክብሯ ሳትመለስ ለዓመታት ደጅ ነበረች:: ብዙ አባቶች፣ ካህናትና ጳጳሳት ይህችን ታቦተ ሕግ ወደቀደመ የክብር መንበሯ ለመመለስ ያደረጉት ተደጋጋሚ ጥረት አልተሳካላቸውም:: በዚህ ምክንያት ቅዱስ ፓትሪያርኩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በሄዱበት ዕለት ግን የእመቤታችን የድንግል ማርያም ታቦት ገና ቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ በእጃቸው ሲዳስሷት ተነስታ ወደ መንበረ ክብሯ ተመለሰች»::

## «አቡነ ጳውሎስ የምስክርነት ሐውልት አይገባቸውም!»

**«ሐውልት ማቆም በቤተክርስቲያኗ ሕግ፣ ቀኖና ሥርዓት ያልተደገፈና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ነው፤ መሰረትም የለውም»**

«ሐውልት ማቆም በቤተክርስቲያኗ ሕግ፣ ቀኖና ሥርዓት የተወገዘና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፣ መሰረትም የለውም» የሚለው አቋም በሌላኛው ጽንፍ ባሉ ወገኖች የተያዘ ነበር:: «ሐውልት መትከል ሥርዓተ አበውና ሕገ-ሃይማኖት» አለመሆኑን፣ ሐምሌ 10/2002፣ ቁ. 124 የአውራምባ ታይምስ ዕትም ላይ ባሮክ ዘሳልሳያ ሺ.ህ የተባሉ ተጋባዥ ጸሐፊ ምልከታቻቸንና ምክንያቶቻቸውን ገልጸው ነበር::

፩

**የሐውልት «ትርጉም»**

የሐውልትን ምንነትና አጀማመር በተመለከተ በመስከረም 1987 ዓ.ም *«ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም»* የሚል ርዕስ ያለውን መጽሐፍ በማስረጃነት የጠቀሱት ባሮክ ዘሳልሳይ፣ «ሐውልት አንድ ወጥ የሆነ ክብነት ወይም ማዕዘንነት ያለው፣ ከድንጊያ ተጠርቦ፣ ከኖራና አሸዋ፣ ከሲምንቶና ከተፈጨ ድንጊያ ተሰርቶ ለመታሰቢያ የሚተከል፣ እንደ አምድ (እንደ ምሶሶ) የሚቆም መዘክር ነው:: ... የሚያመለክተውም በአንድ ዘመን በአንድ ቦታ ላይ የተፈፀመን ድርጊት ነው:: ... በቀድሞ ጊዜ ሐውልት የሚቆመው በጦር ሜዳ ወድቀው ለሚቀሩ ጀግኖች፣ በስደትና በሽሽት ግዜ በጉዞ ላይ በሚደርስ ድንገተኛ ሞት፣ ከቤተሰብ ተለይተው በመንገድ ዳር ለሚቀበሩ ወገኖች መታሰቢያ» እንደነበር መጽሐፉ ጽፏል ብለው የተሰጠውን ትርጓሜ እና ጠቀሜታ አስረድተዋል:: «ሐውልት የመቆሙም ጥቅም 'ይህ መቃብር የእገሌ ወይም የእገሊት መቃብር ነው ተብሎ ለመታወቂያና ለመታሰቢያ ነው እንጂ መንግስት ሰማያት የሚያወርስ፣ ሰማያዊ ጥቅምን የሚያስገኝ አይደለም'::» በማለት ትርጓሜውን ጠቅለል አድርገው ደምድመዋል::

«ለሙታን ሐውልት ማቆም በያዕቆብ ወልድ ይስሐቅ ዘመን የተጀመረ ልማድ» እንደሆነና መጽሐፍ ቅዱስም፣ «ያዕቆብ በራሔል መቃብር ላይ ሐውልትን አቆመ፤ እስከዛሬም የራሔል ሐውልት ተብሎ ተሰየመ» (ዘፍ 35፣20) ብሎ መፃፉን ጠቅሰዋል - ባሮክ::

፪

### ገድለ ቅዱሳን

«ከገድለ ቅዱሳን እንደምንረዳው፣ እንኳን በሕይወት ያለ ይቅርና ሃይማኖታቸውን ጠብቀው፣ ሥነ-ምግባራቸውን አሳምረው በሞተ-ዕረፍት የተለዩንን ደጋግ አባቶችና እናቶች በመካነ መቃብራቸው ተዓምራት እየተደረገ እንኳን ምልክት (ትክል ድንጋይ) ይቆማል እንጂ ሐውልት አይሰራም»:: «አንድ ወጥ የሆነ የቆመ ደንጊያ (ተክል) ምልክት እንጂ ዛሬ በዘመናችን፣ የአቡነ ጳውሎስን የ«ምስክርነት ሐውልት ጨምሮ፣ በተለያየ ቅርፅና መልክ እንደሚሰራው ያለ ጥርብ ደንጊያና የእምነበረድ፣ የአሸዋና የሲሚንቶ፣ የኖራና የጠጠር ክምር» እንዳይደልና «ያዕቆብ ለራሔል የመታሰቢያ ሐውልት ያቆመበት ምክንያት ወደሀገሯ ሳትገባ በድንገት በመንገድ ዳር አርፋ ከወገኖቿ ጋራ ለመቀበር ዕድል ሳታገኝ በመቅረቷ ለመታሰቢያ ነው»::

፫

### የባዛንታይን ወሳኔ

«በባዛንታይን በ787 ዓ.ም በተወሰነው ውሳኔ መሰረት ቤተክርስቲያን የቅብ ወይም የጭረት ሥዕልን እንጂ ቅርፅን ወይም ሐውልትን አትጠቀምም:: . . . በቤተክርስቲያን ትምህርት፣ ታሪክ እና ትውፊት ሐውልት ሳይሆን ሥዕል የተፈቀደ፣ የተለመደ እና ሥርዓታዊ ነው» ይላሉ - ባሮክ ዘሳልሳይ ሺ.ህ::

፬

### «የተቀረፀ ሐውልት ምድቡ ከአምልኮ ባዕድ ነው»

እግዘብሔር አምላክ ለሙሴ ከሰጣቸው አስርቱ ትዕዛዛት አንዱ «በላይ በሰማይ፣ በታች በምድርም ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረፀውን ምስል ለአንተ አታድርግ»የሚለው እንደሚጠቀስ እና «የተቀረፀ ሐውልት ቁጥሩ ከአምልኮ ባዕድ» በመሆኑ «ቤተክርስቲያን አትቀበለውም»::

፭

### የታሪክ መዛግብት

ቀደምት የቤተክርስቲያን አበውና የታሪክ ጸሐፊዎች በቤተክርስቲያን ሥዕል እንጂ አውልትን አልፈቀዱም፣ አላስተማሩምም:: በባዛንታይን መንግስት የቅዱሳት ስዕላትን በተመለከተ «ታላቁ ሊቅ ዮሐንስ ዘደማስቆ፣ ስዕል በቤተክርስቲያን ሁለት አይነት ጥቅም አለው:: አንደኛው በዋሻ እንደነበሩት ክርስቲያኖች ተዓምራት ነክ የቅዱሳት መጽሐፍትን ታሪክ ማንበብ ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ለማስረዳት ነው:: ሁለተኛው ሃይማኖቱን ሳይፈራ ሳያፍር መስክሮ በሰማዕትነት የሞተ ወይም ስለዓለም እና ስለራሱ በመጸለይ መላ ሕይወቱን ከፍትወት፣ ከእኩያት፣ ከአጋንንት፣ ጋር በመጋደል ያሳለፈውን ሰማዕት ወይም ጻድቅ በስዕል ለመዘከር፣ በስዕሉም አማካይነት እያንዳንዱ ምዕመን ለስዕሉ ባለቤት ክብርና ለመግለጥ ነው» በማለት ጽፏል፣ ስለሐውልት ግን አልጠቀሰም::

፮

**የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት ትውፊት**

ሁለተኛው የኒቂያ ጉባዔ ውሰኔን (787 ዓ.ም) የጠቀሱት ባሮክ፣ «የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት ሥዕል ሲሉ ሶስት ማዕዘናዊ የሆነውን ሐውልትን በመተው ወካይ ትርጉማዊ እውነታን የሚያሰፍረውን ሥዕል» እንደሚጠቀሙ ያስረዳሉ:: እናም «በምስራቅያውያን ትውፊት ስዕል ሊታይ ወይም ሊዳሰስ የሚችል ቅርጥ የሌለው ሁለት ማዕዘናዊ የሆነ በቀለም የሚሰራ ነው»::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ

## ዘመኑ የብልፅግና የሰላም የእድገት እንዲሆን እንመኛለን

## ሕብር ስኳር አክሲዮን ማህበር
## Hiber Sugar Share Company

### የጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ በሚሊኒየም አዳራሽ!

**በሕብር ስኳር አክሲዮን ማህበር አክሲዮን ለገዛችሁ በሙሉ**

**ማህበሩ መደበኛና ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ነሀሴ 30/2002 ስለሚካሄድ በስብሰባው ላይ እንድትገኙ የአክብሮት ጥሪውን ያቀርባል።**

**የስብሰባ ቦታ**
ሚሊኒየም አዳራሽ
የስብሰባው ቀን
ነሐሴ 30/2002
የስብሰባው ሰዓት
ከጥዋቱ 2:00 ሰዓት
ጀምሮ

**የስብሰባው አጀንዳዎች**
ሀ/ አዲስ አባላትን መቀበልና የካፒታል ማሳደግ
ለ/ በሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ተወያይቶ መወሰን
ሐ/ የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል
መ/ በተጓደሉ የቦርድ አባላት ምትክ ምርጫ ማከሄድ
ሠ/ ኦዲተሮችን መሾም

**ባለአክሲዮኖች ሁሉ**
1- የመታወቂያ ወረቀት
2- የአክሲዮን ባለቤትነት ማስረጃ
3- የውክልና ማስረጃ በመያዝ በተጠቀሰው ቦናታ ሰዓት እንድትገኙ በአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

በዚሁ አጋጣሚም አክሲዮን ማህበሩ እራስንና ቤተሰብን እንዲሁም ሕዝብንና ሐገርን ተጠቃሚ ለማድረግ በጀመረው እንቅስቃሴ አክሲዮን **ለመግዛት ፈልጋችሁ ያመለጣችሁ በሙሉ የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ እስከሚካሄድበት**

## እስከ ዛሬ 29/02 ቀን ድረስ

*በመሥራችነት መመዝገብ እንድትችሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ በመወሰኑ ዕድሉን እንድትጠቀሙበት ተጋብዛችኋል።*

**ማሳሰቢያ:- ክፍያችሁን ያላጠናቀቃችሁ አባሎቻችን በሙሉ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባው በተካሄደ ማግስት በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ለመመዝገብ ትችሉ ዘንድ የሚጠበቅባችሁን ገንዘብ በመክፈል ለፊርማ ዝግጁ እንድትሆኑ እናሳስባለን።**

*የሕብር ስኳር አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ*

**አድራሻ ሕብር ስኳር አክሱዮን ማህበር**
**ዲ አፍሪክ ሆቴል ፊት ፊት በተገነባው አዲሱ የታደሰ ተፈራ ሕንፃ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 105**
**ስልክ 0118-50-13-57/0118-50-13-58 251-910-196886/251-913-437942/251-913-368965**
**website: www.hibersugarethiopia.com, E-mail: info@hibersugarethiopia.com**



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# የዓመቱ የተቃርኖ ፅንፍ ተጠርጣሪ ቴዎድሮስ ካሳሁን

በአቤል ዓለማየሁ

ከዓመት በፊት የሚወጡ የፕሬስ ውጤቶች የቴዎድሮስ ካሳሁንን ምስል ሳይለጥፉ፣ የፍርድ ቤት ውሎውንና በእርሱ ዙሪያ የሚነሱ ሀሳቦችን ሳይዙ ወደ ማተሚያ ቤት (አንባቢ) አይሄዱም ነበር። በርካቶች ጉዳዩን የኔ ብለው ፍ/ቤት ከችሎት ታድመውታል። ብዙሐኑም «ቴዎድሮስ አልገጨም» ፖለቲካዊ አቋሙን አሳይቶበታል ብለው የሚያምኑት «ያስተሰርያል» የሚለው ዜማው ያመጣበት መዘዝ ነው በማለት በግምታዊ ስሌት በመንግስት ላይ ጥርጣሬያቸውን ይገልፁ ነበር፤ በተቃራኒውም «የለም ገጭቷል» የሚል የውሳኔ ጫፍ ላይ የደረሱም እንዲሁ።

በውጪ አገር የሚገኙ ከገዢው ፓርቲ በተቃራኒ የቆሙ ሚዲያዎች (ብሮድካስትና ድረ-ገጾች) ክሱ ፖለቲካ አንድምታ እንዳለው በማመን መንግስትን ሞጋች ፅሁፎችን ያንሸራሽሩ ነበር። የድምፃዊውን አለመግጨት በመግለፅ መፈታቱን የሚጠይቁ በርካታ ሰላማዊ ሰልፎችም በአሜሪካና በአውሮፓ ተካሂደዋል። በየአገራቱ በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ፊት ለፊት የተቃውሞ ድምፃቸውን ያሰሙም ነበሩ።

ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት 484 ቀናት ቆይታው በኋላ ነሐሴ 7 2001 ዓ.ም. ከእስር ተፈታ። ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የእስራት ጊዜውን ወደ ሁለት ዓመት ሲያቀልለት በፉጨትና በጭብጨባ የቀጠለው ችሎት ተረኛነቱን ለቴዲ እናት መኖሪያ ቤት ለቀቀ። አፍቃሪዎቹ (ወዳጆቹ) በደስታ ሰከሩ። አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴን ጨምሮ ብዙዎቹ ወ/ሮ ጥላየ አራጌ (እናቱ) ቤት በመገኘት እንኳን ለቤትህ አበቃህ አሉት።

የቤቱ በር ግን ለሁሉም ክፍት አልነበረም። ፀሐይና ዝናብ የተፈራረቀባቸው፣ ከፖሊስና ከጥበቃ ባለሙያዎች ጋር «የልግባ፣ አትገባም» ግብግብ እየገጠሙ የቴዎድሮስን የችሎት ውሎ ሰምተው፤ ሊያሰሙ የተጉ የመገናኛ ብዙሐን አባላትም ማንነታቸውን እየገለፁ እንኳን በር ላይ ባሉ ወዳጅ መሳይ ጥበቃ ተብዬዎች (ጥበቃ ሙያቸው ያልሆነ) እየተንጓጠጡ እንዳይገቡ ይከለከሉ ነበር። ሁኔታውን ዘግይቶ የሰማው (ሰማው ያለው) ቴዲ ጋዜጠኞችን ይቅርታ እየጠየቀ ያስተናግድ ነበር።

ነሐሴ 12/2001 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ አጭር ቆይታ ያደረገው አርቲስቱ ከዚህ ፅሁፍ ፀሐፊና ከጋዜጣው ማኔጂንግ ኤዲተር ጋር የጀመረው ቃለ-ምልልስ ሳይጋመስ አመስግኖ ብድግ አለ። ወሳኙ - እሱ ሆነና ቆይታችን በቂ እንደሆነ ነግሮን መጨረሳችንን አበሰረን።

ለጊዜው ተቀዳሚ ሀሳቡ እረፍት ማድረግ ብቻ መሆኑን ነግሮን ነበር፤ ኮንሰርት ማዘጋጀትና አልበም ማውጣት የቅርብ ጊዜ እቅዱ ዝርዝር ውስጥ አለመስፈራቸውንም ጭምር። ይህንን በሌሎች መገናኛ ብዙሐን ላይም ገልጿል።

ወደ 2002 ዓ.ም. እየተንደረደርን ነው፤ «ረዥም እረፍት እወስዳለሁ» ያለው ቴዎድሮስ ወር ሳይሞላው ኮንሰርት ሊያዘጋጅ ስለመሆኑ ወሬ መናፈስ ጀመረ። መስከረም 19 2002 ዓ.ም. በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ጥቅምት 1/2002 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ስታዲየም ገቢው ለኤልሻዳይ ሪሊፍ ኤንድ ጀቨሎፕመንት አሶሲየሽን ለተባለ የምግባረ ሰናይ ደርጅት የሚውል የሙዚቃ ዝግጅት እንደሚያዘጋጅ ገለፀ። ረድርጅቱ በልመና የሚተዳደሩ ወገኖችን ለመርዳት፣ ለማቋቋምና ወደመጡበት ለመመለስ የሚሰራ መሆኑ ይነገራል።ሪ

ከመግለጫው ሁለት ቀን በፊት በሒልተን አዲስ የጥላሁንን 69ኛ ዓመት ለመዘከር በተዘጋጀ ፕሮግራም ላይ በመገኘት ከእስር በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ



ሲያንጎራጉር የተደመጠበት ነው። «ብዙ ያልተነገረለት የሙያ ዲስፕሊኖች አለው» ያለውን ጥላሁን ድምፁን ለማሻሻል ሰዓት ይዞ ገንዳ ውስጥ እንደሚያሳልፍ በመጠቆም «ይህን ስንቶቻችን እናደርጋለን?» ሲል እኩያ የሙያ ባልደረቦቹን ጠይቋል። «በእኛ ጆሮ የሚደመጥ እንጂ የሚነገርለት ስላልሆነ አክብሮቱን ብቻ ብገልፅ ይቀለኛል።»

መስከረም 17 የሙያ አባቱ የጥላሁንን የልደት ቀን የሚከበርበት ብቻ ሳይሆን የስጋ አባቱ ካሳሁን ግርማሞን ያጣበት ቀን መሆኑን ያስታወሰው ቴዲ አፍሮ ከመድረክ በመውረዱ በፊት በጥላሁን ገሠሠ የቀብር ስነ-ስርዓት ላይ «በስውር ጥበብህ ሳይገባኝ ያከበርከኝ» ሲሉ የጥላሁን የጥበብ ጓዳኞቹና ልጆቹ ያቀነቀኑትን የጋራ ዜማ ለብቻው ተጫውቷል። አስቀድሞ በወጣ ፕሮግራም መሰረት ይህን ዘፈን ለማቀንቀን የተጋበዘው ቴዎድሮስ ታደሰ የነበረ ሲሆን ዜማውን ግን በድንገት የተገኘው ሞክሼው እንዲጫወተው ሲደረግ በንዴት ከማንም ጋር አላወራም እስከሚል ድረስ አሳዝኖታል።

በጥላሁን ልደት ቀን ሳይታሰብ ድምፁ የተሰማው ቴዲ አፍሮ ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት ከወጣ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅምት 1 2002 ዓ.ም. ባቀረበው ደማቅ ኮንሰርት ላይ ለአበበች ጉበና ግብረ ሰናይ ድርጅት 100 ሺህ ብር፣ ለግጥም እና ዜማ ደራሲው ይልማ ገ/አብ ከወርቅ እንደተሰራ የገለፀውን ብዕር በስጦታ ባበረከተበት በዚህ ኮንሰርት ላይ «የማይተካ» የሚባልለት ጥላሁን ገሠሠ ይጠቀምበት የነበረውን ዊልቼር መድረክ ላይ በማውጣት አበባ አስቀምጧል። «ጥላሁን ምልክታችሁ ነው/አይደለም?» ሲል ጠይቆም ከታዳሚ በጉ ምላሽ ተሰጥቶታል። በዕለቱ በስታዲየሙ ዝግጅቱን ከታደመው ይልቅ ትኬት ማግኘት ሳይችል ደጅ የቀረው ህዝብ ያይል ነበር።

## አሀዱ ጥርጣሬ

ኮንሰርቱ ከመካሄዱ በፊት አውራምባ ታይምስ ያነጋገረቻቸው የኮንሰርቱ አዘጋጆች «ፖለቲካዊ» ይዘት አላቸው ተብለው የሚታመኑት ዘፈኖቹ እንደማይቀርቡ ገለፁ፤ በኮንሰርቱ ቀንም ይሄው ተረጋገጠ። «ያስተሰርያል»ን እንዲዘፍን ጥያቄ የሚያሰሙ ድምጾች

የኢትዮጵያን ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳይ በቅርበት የሚከታተለው ዳያስፖራ ቴዲ አፍሮን «አይንህን ለአፈር» እንዳለው ይገለፃል። ሆኖም ብዙዎቹ ኮንሰርቶቹ የተመልካች ድርቅ ሲመታቸው አልታዩም። ታዳሚዎቹ አገራዊ ጉዳዮችን በቅርበት የማይከታተሉት ናቸው ይባላልም። በአገር ቤትም ቢሆን እነዚያ የተንጋጉ አድናቂዎቹ ከላይ በተገለፁም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ለቴዎድሮስ የሰጡት የአድናቆት መጠን እየቀነሰ እንደመጣ ይወራል።

ቢኖሩም ድምፃዊው ጆሮ ዳባ ልበስ አለ። ረከስታዲየም ጥቂት ርቀት ላይ በሚገኘው በሸራተን አዲስ በ1998 አዲስ ዓመት ዋዜማ በተዘጋጀ ኮንሰርት ላይ ግን ይህን ዘፈን ካልዘፈንኩ አልገኝም ብሎ እንደነበር ይነገራል።ሪ ይህንን በተቃራኒ አቅጣጫ የተረጎሙት ነበሩ። አንዳንዶች ከአቋም ለውጥ ጋር ሲያነፃፅሩት ሌሎች ደግሞ «ያስተሰርያልን ቢዘፍን አርፎ አልቀመጥ ማለት ነው። የሚወደውም ሰው ሊያዝንበት እንደሚችል ተረድቶ (ተረጋግቶ ለማረጋጋት) ነው» በሚል እንደተረዱት ለማሳየት ሞከሩ።

በአዲስ አበባ ያሚሸውን ኮንሰርቱን በውጪ አገራት ለመቀጠል በስታዲየሙ ኮንሰርት ላይ ከአንድ ሚሊየን ብር በላይ መገኘቱን አስታውቆ በቼክ በተፃፈ ሂሳብ ለኤልሻዳይ በመለገስ ወደ ፍራንክፈርት አቀና። በተከታታይ በጀርመን፣ ስዊድን፣ ኖርዌይና ሆላንድ ኮንሰርት ለማቅረብ የተፈራረማቸው የገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች ናቸው በማለት ቅሬታ የገባቸው በአገሮቹ የሚገኙ የኢህአዴግ ተቃዋሚ ወገኖች «ድምፃዊው ከእስር እንዲለቀቅ በፀሎት፣ ይፈታ ብለን ስንሰለፍ ካበነፃ ፍ/ቤት ጉዳዩ እየታየ ነውካ ብለው ይሳለቁብን ከነበሩ ሰዎች ጋር እንዴት አብሮ ይሰራል?» በማለት ታዳሚዎች በኮንሰርቱ ላይ እንዳይገኙ ቅስቀሳ ያደርጉ ነበር። በኖርዌይ የሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት በድረ-ገጾች ባሰራጩት መግለጫ ህዳር 19 2002 ዓ.ም. በኦስሎ ኮንሰርቱን ለማቅረብ የተፈራረመው ከኢህአዴግ ደጋፊ ጋር በመሆኑ «በኮንሰርቱ ላይ እንዳትገኙ» ብለው ነበር። ጉዳዩ አነጋገረ። «አሳፋሪ ተግባር» ያሉትም ነበሩ። የቴዎድሮስን ከፈለገው ወገን ጋር ውል መዋዋል መሰረታዊ መብቱን መንፈግ ነው በማለት ተቹትም። የፖለቲካ አቋም ውል ለመወያያ እንደመስፈርት መቀመጡ የ21ኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ አለመሆኑን በማስረዳት የተከራከሩ ዳያስፖራዎች ሀሳብ በድረ ገጾች ይስተጋባ ነበር። በኖርዌይ ኦስሎ የድምፃዊው ኮንሰርት አዘጋጅ አቶ ደስታ ገ/ሥላሴ «የማንኛውም ፓርቲ አባልም/ደጋፊም ሆነ ተቃዋሚ አይደለሁም።...በአክራሪ ፅንፈኞች የተጀመረ ቅስቀሳ ነው።» ሲሉ ለአውራምባ ታይምስ ገልፀው ነበር። የስዊድኑ ኮንሰርት አዘጋጅ አቶ ስሜነህ ዋቄም «ከእውነት የራቀ... 95 በመቶ በስዊድን የሚኖር ኢትዮጵያዊ ገለልተኛ የፖለቲካ አቋም እንዳለኝ ያውቃል» ሲሉ አስተባበሉ። ወሬው እውነት ከሆነ ቴዎድሮስ መረጋጋት አለመቻሉን ያሳያል ያሉም ነበሩ።

የህግ ጠበቃው ሚሊዮን አሰፋ ረበፊቼ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ኢህአዴግን ወክለው በምርጫ ያሸነፉሪ የልጁ ደንበኛ መሆናቸው ቴዲ አፍሮና ገዢው ፓርቲ ያላቸውን ቁርኝት ያሳያል የሚሉ አስተያየቶችም ተደምጠዋል፤ «ሙያን ያማከለ የስራ ግንኙነት በፖለቲካ አቋም ሳቢያ መነጋገሪያ ሊሆን አይገባም» የሚል ተቃርኗዊ ምላሾችን ባያጡም።

## አዲሱ «ያስተሰርያል»

እንደ ኢትዮ ሚዲያ ፎረም ድረ ገጽ ኤዲተር ክንፉ አሰፋ ገለጻ በቴዎድሮስ የአውሮፓ ኮንሰርቶች ላይ የሰው ቁጥርም ሆነ የመዝናናት መንፈስ ከወትሮው በእጅጉ የቀዘቀዘ እንደነበር ነው። «የህዝቡን ስሜት መቀዝቀዙን ያስተዋለው ቴዲ በሮተርዳም ኮንሰርቱ ላይ ካምን ሆናችኋል? ምን እንድጫወትላችሁ ትፈልጋላችሁ?ካ ሲል ታዳሚው «ያስተሰርያል» የሚል ምላሽ ስለሰጠው መጫወቱ የግድ ሲሆንበት ፖለቲካዊ መልዕክት ያላቸውን ስንኞች በመቆራረጥ ካየህዳሴውን ያስተሰርያልካ ተጫወተ» በማለት የገለፀው ሲሆን ያም ዘፈኑን እንዳሳነሰው ገልጾ «አዝማቹ ዜማውን ቀፎ ሙዚቃ ብቻ ነው የሚቀረው። ራሱ አምጦ የወለደውን የጥበብ ውጤት ራሱ ቆራረጠው። በውስጡ ደስተኛ እንደማይሆን መገመት አያዳግምት» ሲል «ቴዲ አፍሮ ተፈትቶ የታሰረው ብላቴና» በሚለው ፅሁፉ ላይ ገልጾት ነበር። በዜማ ያልተነኩ ፖለቲካዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮችን በማንሳት የገነባውን ስም ሊሸረሽርበት እንደሚችልም የተነገረበት ዓመት ነው፤ 2002 ዓ.ም።

የኢትዮጵያን ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳይ በቅርበት የሚከታተለው ዳያስፖራ ቴዲ አፍሮን «አይንህን ለአፈር» እንዳለው ይገለፃል። ሆኖም ብዙዎቹ ኮንሰርቶቹ የተመልካች ድርቅ ሲመታቸው አልታዩም። ታዳሚዎቹ አገራዊ ጉዳዮችን በቅርበት የማይከታተሉት ናቸው ይባላልም። በአገር ቤትም ቢሆን እነዚያ የተንጋጉ አድናቂዎቹ ከላይ በተገለፁም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ለቴዎድሮስ የሰጡት የአድናቆት መጠን እየቀነሰ እንደመጣ ይወራል። ስለ እሱ ፅፈው የሚወጡ የህትመት ውጤቶችም ተፈላጊነታቸው ወርዶ መታየቱ ለዚህ ማረጋገጫ መሆኑን የሚገልፁ አሉ። የሙያ ወዳጆቹም ስለ እሱ ሲጠየቁ ደስተኛ አለመሆናቸውን በአሉታዊ አስተያየቶችና ድምፀ ታዕቅቦ ይገልፃሉ።

## ራስን መካብ

ድምፃዊው ጥር 6 2002 ዓ.ም. «ኪነ-ፃድቅ» የሚል ስያሜ የተሰጠው የግጥም ምሽት በአዲስ ቪው ሆቴል አዘጋጅቶ ነበር። ድግሱ በቃሊቲ ማረሚያ ሳለ የፃፋቸውን ያልታተሙ ግጥሞች ለማስደመጥ ነበር። ዝግጅቱ አውራምባ ታይምስን ጨምሮ የቴዲን የችሎትና መሰል ዘገባዎች ለመዘገብ ውጣ ውረድ ያስተናገዱ የህትመት ውጤቶችን ያገለለ ነበር። የጥሪ ወረቀት ተላልፎላቸው ዝግጅቱን የታደሙ «መገናኛ ብዙሐን» አልነበሩም ማለት ግን አልነበረም።

ነጠላ ዜማዬ፣ ሾሌ ያነጪ ጠላ፣ የሊስትሮ ዕቃዬ የሚሉና ሌሎችም ከ15 በላይ ግጥሞቹን በወቅቱ ማቅረቡ ምንጮች ገልፀው ነበር።

በግጥም ምሽቱ ላይ አርቲስት ለማ ጉያ የድምፃዊው ስም መነሻ እንደሆነ በማውሳት የአፄ ቴዎድሮስን ምስል በፍሬም ያበረከቱለት ሲሆን እሱም በቁንጮ ሆኖ የተነሳውን የልጅነት ፎቶውን አበርክቶላቸዋል። የስጦታ ሚዛናዊነት መለኪያ ባያስፈልገውም ሁኔታ ለራሱ የሰጠውን የተጋነነ ግምት ያሳያል በሚል አስተችቶታል። «አፄ ቴዎድሮስና ድምጻዊ ቴዎድሮስ ምንና ምን ናቸው?» አስብሏልም።

ድምፃዊው ነፃው ፕሬስን ማግለሉን በኢትዮ ሚዲያ ፎረም ድረ ገፅ ላይ ያነበቡ አንድ አስተያየት ሰጪ «ቴዲ ቴዲ ብላችሁ መጨረሻችሁ ይሄ ሆነ?...» ሲሉ አስፍረዋል።

## ባይዘፈን ቢቀር

የቴዲ አፍሮ ዘፈኖች ሁሌም ስንኞቻቸው እየተሳበ ይመነዘራል። በቅርቡ ከለቀቃቸው ሦስት ነጠላ ዜማዎች ውስጥ «ሰላም» የሚለውም ይህ ዕጣ ገጥሞታል። «አንገት ከሚሰበር ባይበላስ ቢቀር ... ያሉት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ... ይሉኝታ ከማጣ ዛሬ ገንዘብ ልጣ... አስገምቼው ራሴን አልሞላውም ኪሴን...»የሚሉ የግጥም ስንኞች ሁሉም እንደየፍላጎቱ፣ እንደሚመስለው፣ እንደጠረጠረው፣ ሊሆን ይችላል እንዳለው ሲተረጉማቸው ይሰማል።

አንድ ባለሀብትን ለመንካት ነው፣ ብርቱካን ሚደቅሳን ለማወደስ ነው፣ ሪያሉት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋሪ ጥቅም (ስራ) አገኛለሁ ብለው በኢህአዴግ ጃንጥላ ስር ተሰባስበዋል የተባሉ የቅድመ ምርጫ ምልምል አባሎችን ለመወረፍ ነው፣ ከገዢው ፓርቲ ጋር ንክኪ አብዝተሀል በመባሉ የሰጠው ምላሽ ነው የሚሉና ሌሎች አስተያየቶችም ይደመጣሉ።

የዚህ ዘፈን መልዕክቱ እንዳለ ሆኖ «ግጥሙ ቤት ለመምታት ብቻ የተሰደረ፣ ዜማው ተቀናብሮ ያለቀ የማይመስልና ብዙ የሚቀረው፣ ድምፃዊው ለገነባው ስምና ቁመት የማይመጥን» ነው ብለው ባለሙያዎች ይገልፁታል። አዲስ ዓመትን በማስታከክ በሚሊኒየሙ ዋዜማ ያገኘውን ክብር ለመድገም አስቦ እንደለቀቀው የሚናገሩም አሉ። ዘፈኑ ግን በተለያዩ ቦታዎች እየተደመጠ ይገኛል። «መደመጥ የስራን ጥራት አያሳይም።» ያለን አንድ የሙዚቃ ባለሙያ «ድምፃዊው የፈጠራ ችሎታው አብሮት ያለ አይመስልም። የህዝብ ዜማና ግጥሞችን እያሻሻለ መጫወትን እየመረጠ እንደሆነ ያሳያል። መደመጡ ሊጠቁም የሚችለው የጥሞና ጊዜ ወስዶ ፈጣሪነቱን ይዞ ከመጣ የሙዚቃ ኢንደስትሪው አሁንም እንደሚፈልገው ነው» በማለት ተናግሯል።

የቴዎድሮስ ምስል ያለበት «ክራዲዮስ» የተሰኘ ሲዲ ከወር በፊት ገበያ ላይ የዋለ ሲሆን ከእሱ እውቅና ውጪ እንደሆነ ተነግሯል። አዘጋጆቹ (ህገ-ወጥ መንታፊዎች) ከድምፃዊው ስር ስር በማለት ዓላማቸውን የፈፀሙ ሁለት ወጣቶች ናቸው። ሁኔታው በጣም እንደሳዘነውም ተናግሯል። ሌላም የድምፃዊው ምስል ያለበት «የሙዚቃ ንጉስ» የሚል ፖስተር የተለቀቀ ሲሆን ይህን ማዕረግ ከጥላሁን ገሠሠ በኋላ «ለማንም ሲሰጥ የማይገባው» ሲሉ የሚከራከሩ ሰዎችን ቅር አሰኝቷል።

በፖለቲካዊ ቅኝት በሚሟሹ ተቃርኗዊ ፅንፎች መጠርጠሩ፣ በቅርቡ የለቀቀው «ሰላም» ነጠላ ዜማው፣ ከላይ የተገለፁትና ሌሎችም ቴዎድሮስ ካሳሁንን በዚህ ዓመትም የአነጋጋሪነት ካባን እንዳያወልቅ አድርገውታል።



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

## አቤቶ ወግ

አቤ ቶኪቻው abeto2007@yahoo.com

# «መንገድም ሕይወትም እኔ ነኝ ከኔ በቀር ወደ ፓርላማ የሚገባ የለም!» የተባለበት አመት

አዲስ አመት ሊመጣ እየተንደረደረ ነው:: ባረጀው አመት ሁለት ሺህ ሁለት ዋና ከሚባሉ ክስተቶች መካከል ምርጫ ሁለት ሺ ሁለትን የሚያኽለው አይገኝም:: ውይ ምን ነካኝ ያን የመሰለ ምርጫ እንደው እንደዘበት «ምርጫ ሁለት ሺ ሁለት» ብቻ በማለቴ በእውነት ተግሳፅ የሚገባኝ ከንቱ ሰው ነኝ:: እና እንዴት ብለህ ልትጠራው ፈልገህ ኖሯል? ቢሉኝ እልዎታለሁ... ምርጫ ሁለት ሺህ ሁለት ሲጠራ በንግግር መሀከል ከሆነ፤ ከሌሎች ሁሉ ንግግሮች ተለይቶ በድምፅ ማጉያ ይጠራ:: ይህ ብቻም አይበቃም ድምፅ ማጉያው «ኤኮ» ወይም መስተጋባት ይኑረው:: አሁንም አይበቃም የኮምፒውተር ሪሚክስ ይደረግበት:: በጽሑፍ ላይም ከሆነ ጎላ ብሎ «ቦልድ» ተደርጎ ይፃፍ:: እርሱም አይበቃም ይሰመርበት:: አሁንም አይበቃም እንደ ቅዱሳን ሰማህታት ስም በቀይ ይድመቅ:: ለምን ቢሉ ሁለት ሺህ ሁለት ዓመተ ምህረት ከመምጣቱ በፊት ስንናፍቀው የነበረ፤ አመቱ ካለቀ በኋላም ትዝታው ከአዕምሮአችን ደስታው ከልባችን ያልወጣ ነውና ምርጫ ሁለት ሺህ ሁለት ከአመቱ ክስተቶች ሁሉ ተለይቶ ክብር እና ሞገስ ይገባዋል እናላለን::

ወዳጄ እንዴት ሰንብተዋል? ዛሬ የአመቱ ጫፍ ላይ ነው የቆምነው:: ትንሽ ሸርተት ካደረገን ሁለት ሺህ ሶስት ላይ እንወድቃለን:: ስለዚህ ከመንሸራተታችን በፊት መለስ ብለን ሁለት ሺህ ሁለትን ቃኘት ቃኘት ማድረግ ይገባል:: ምንም ቢሆንኮ አመት ሙሉ አብሮን ቆይቶ ክፉና ደጉን አብረን አሳልፈናል:: ታድያ ገና ለገና አዲስ አመት መጣ ተብሎ ያለፈውን ዘወር ብለው ሳያዩ ወደ አዲሱ ግልብጥ ማለት ወረተኛ አያስብልም? ስለዚህ ዛሬ ሁለት ሺህ ሁለትን ገርመም አድርገን እለማየት አንድ ሁለት ሶስት! ቆጥረን በአዲስ መስመር እንጀምራለን::

ሁለት ሺህ ሁለትን መለስ ብለን እንመልከት ካልን በመጀመሪያ በአይናችንና በልባችን የሚመጣው ምርጫ ሁለት ሺህ ሁለት መሆኑን ተነጋግረናል:: ትዝ ይልዎታል ወዳጄ ከምርጫ ምልክት መረጣው ጀምሮ እስከ ውጤት ገለፃው የነበረውን «ማራኪ» ሂደት! እንዴ... እርስዎ እኮ ልባም ኖት እንዴት ይረሳል? አሉኝ አይደል? የምርጫ ምልክት መረጣ ላይ ምድረ ተቃዋሚ ሁላ ያቺን ታሪካዊዋን የ«ቪ» ምልክት ለኔ ለኔ ሲሏት እንዳልነበር ምርጫ ቦርድ ሆዬ «አትጨቃጨቁ ለማንም አይሰጥም» ብሎ ቢሮ ውስጥ አልቆለፈባትም?! ታድያ አሽሟጣጮች ምን አሉ? «ዘንድሮ የጣትን ምልክት የሚወዳደርበት ምርጫ ቦርድ ራሱ ነው!» አላሉም? እኛስ ምን አልን? «የራስሽ ጉዳይ!» የሚለውን ዘፈን አልጋበዝናቸውም!? እውነቱን ለመናገር ይቺ «የራስሽ ጉዳይ» የምትለውን ዘፈን እንደ ዘንድሮ ምርጫ ተጠቅመንባት የምናውቅ አይመስለኝም:: ምነው እንኳ «ነብሳቸውን ይማርና» እነ ኢዴፓ መኢአድ እና ቅንጅት ከእምዬው ገዢ ፓርቲያችን ጋር ሆነው «የምርጫ ስነምግባር ደንብ» ሲያሰናዱልን የሀሜት ጎርፍ አላጥለቀለቀንም? በተለይ መድረክ ከዚህ ቡድን ራሱን ካገለለ በኋላ በየ ኳዳ ጎድጓዳው ሁሉ «የቤተ ዘመድ ጉባኤ» እየተባለ ስነምግባር ደንቡን ሲያወጡ የነበሩትን ፓርቲዎች ከስነምግባር ውጪ በሆነ መልኩ ሲዘለፉ አልነበረም? ምነው እንኳ ሰዉ

«ቅንጅትስ ይሁን ለነብሱ ብሎ ነው
ኢዴፓም ይመቸው ድሮም ያመነ ነው
የመኢአድ ጥምቀት በማን ተሰብኮ ነው?»

እያለ «ኢፍትሀዊ» የሆነ ግጥም «ኢዴሞክራሲያዊ» ለሆ አዝማሪ እያቀበሉ ሲሸረድዱን አልነበረም? እኛስ ምን አልናቸው? በደህናው ጊዜ የወጣልንን «የራስሽ ጉዳይ» ዘፈን አልጋበዝናቸውም? ምን ይሔ ብቻ «ወሬኛም ያውራ ሀሜት ይደርድር እኛስ ሆነናል ፍቅር በፍቅር!» የሚለውን የንዋይ ደበበን ዜማ አልጨመርንላቸውም? ውይ ንዋይ ደበበ ስል ትዝ አለኝ! ጋሽ ንዋይ ራሱ የእኛ ሰው መሆኑን ያረጋገጥነው በዚህ በሰሞነ ምርጫ ነውኮ! ምነው እንኳ «ተቃዋሚዎች በዘፈኔ ቅስቀሳ በማድረጋቸው ወቀሳ ይገባቸዋል!» ብሎ የተናገረውን ረሱት እንዴ? ድሮ ድሮ አርቲስቱን በሰው ሀገር በየተቃዋሚው ሰልፍ ላይ ሁለት ጣት እያሳየ ሲያዩት የነበሩ ወዳጆቻችን «ንዋይ የመንግስት ተቃዋሚ ነው!» እያሉ ሲሉት ለካስ እርሱ የውስጥ አርበኛ ኖሯልና አላልንም አንዴ?

ምርጫ ቅስቀሳው እየበረታ ሲሄድ ፓርቲዎች ግንባሮች እና ጥምረቶቹ ሁሉም በየፊናው ሙዚቃውን እየከፈተ ከተማዋን ትልቅ ኮንሰርት የሚካሄድባት መድረክ ሲያስመስሏት ጆሯችንን እየያዝን እግሬ አውጪኝ ብለን ስንሸሽ አልነበር? ለምን ቢሉ መጀመሪያ አካባቢ በሙዚቃ ሲቀሰቅሱ የነበሩት ተቃዋሚዎቹ ብቻ ስለነበሩ በነርሱ ሙዚቃ መደሰት ቀርቶ ፈገግታ መቸር ራሱ ሊያስጠይቅ ይችላል በሚል ፍርሃት (ይቅርታ ፍርሃት የሚለው ጥንቃቄ በሚል ይቀየርልኝ) እና ሊያስጠይቅ ይችላል በሚል ጥንቃቄ የፈለገ ተቃዋሚ የፈለገ ሙዚቃ ቢያስሞዝቅ ፊት ስንነሳ አልከረምንም? በኋላ ላይ ገዢው ግንባራችንም የመንገድ ላይ ሙዚቃውን ሲጀምረው አሁን ነው መጨፈር ብለን እኛም በየመንገዱ ላይ «እነሽም እነካ» እያልን እስክስታውን ስካስነነው አልከረምንም? አንዳንዶች በገዢው ግንባር ሙዚቃ ለተቃዋሚዎች ሲጨፍሩስ አልተደረሰባቸውም? እጅ ከፍንጅስ አልያዝናቸውም?

የምርጫ ቅስቀሳ ፖስተሮች ነገርስ መች የሚረሳ ነው? በመጀመሪያ ተቃዋሚዎች ሆዬ በስዕል ደብተር ግንጣይ ፎቶግራፋቸውን እና ምልክታቸውን እያሳተሙ ምረጡን! ሲሉ እኛም «በላሸው አንጀቱን በላሸው ለቅስሳ የሚሆን ወረቀት ያጣሸው!» እያለን አልዘፈንላቸውም? ወድያው ገዢው ግንባር ሆዬ በምስኪኖቹ የተቃዋሚዎች ፖስተር አጠገብ አደገኛ ባለቀለም፣ ባለ ዲዛይን፣ ባለ ግርማ ሞገስ ፖስተር እየለጠፈ «ያልተመጣጠነ ርምጃ» አልወሰደባቸውም? ታድያስ ያኔ ህዝቤ «ያለው ማማሩ!» ሲል አልተረተም? «ኢህአዴግን ይምረጡ!» የሚሉ ስዕላ ስዕሎች እና ፅደሁፎች በከተማው ውስጥ በየአንድ አንድ ክንድ ርቀቱ አልተለጣጠፉም? ምን ይሔ ብቻ የእጅ ሰዓት የግድግዳ ሰዓት የቁልፍ መያዣ በከተማው አልተበተነም? ታድያ ይሄኔ ፕሮፌሽናል አሽሟጣጮች «እምዬ አዲሳባ የንብ ቀፎ ሆንሽና አረፍሽው?» ሲሉ አላሽሟጠጡም? አንዳንዶችስ ከንብ ስዕሉ ብዛት የተነሳ «ማር አማረኝ!» አላሉም? ይህንን መጠነ ሰፊ ቅስቀሳ የተመለከቱ ሌሎችስ «ኢህአዴግ ፈርቷል!» እያሉ አላሙንም?

በዛው ሰሞን አይደለም እንዴ ከአራት እስከ አምስት ሚሊዮን አባላት እንዳሉን ዘራችንም እንደ ምድር አሸዋ እየበዛ እንደሆነ እነሆም ከብዛታችን የተነሳ ፍርሃት በእኛ ዘንድ የለም ተብሎ የተነገረው? ምነው እንኳ ይህንን የአባላት ቁጥር የሰሙ አሉባልተኞች «ኢህአዴግ የቤተሰብ ምጣኔ አይጠቀምምና!» ሲሉ አላሸሞሩንም? በዛኑ ወቅት አይደል እንዴ አንበሳ ባስ እና ሀይገር «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው!» እያሉ የገዢው ግንባር አባላትን ወንድ ሴት ህፃናትን ሁሉ ሳይለዩ እየጫኑ ከተማውን በጡሩንባ ሲቀውጡት የነበረው:: ታድያ ህዝቤስ መቼ አፏን ይዛ ዝም አለች!

«አንቺ በአንበሳ ሆነሽ ስትጨፍሪ
እኔ በአበሳ ሁሌ ተማራሪ
በሀይገር ቅስቀሳ አንቺ ተመችቶሽ
አባል ያልሆንኩ እኔ በሀንገር ሞትኩልሽ» እየተባለ ሽሙጡ አልቀለጠም እንዴ?እ

ተቃዋሚዎች «እንግልት በዛብን መቀስቀስ አልቻልንም» እያሉ በየጊዜው በፀሀዩ መንግስታችን ላይ ክስ ቢያቀርቡ ምርጫ ቦርድ ክሳቸውን ካዳመጠ በኋላ «ልጄ እንደዚህ አያደርግም» አለ እያሉ ሀሜተኞች ሲያሙት አልነበረም? ምን እርሱ ብቻ ተቃዋሚዎች በትግራይ ክልል «አለ» የሚሉት አባላቸው በሰው እጅ ህይወቱ ሲያልፍ በሞቶ «የገዢው ግንባር እጅ አለበት» ብለው ከሰው አልነበረም? ወዲያውስ በኦሮሚያ ክልል አንድ ገዢው ግንባር የእኔ ያለው፤ ተቃዋሚዎችም የእኔ ያሉት ሰው አልሞተም? ታድያ በተለይ ገዢው ግንባር በእጩ ተመራጩ ሞት የአቶ ቡልቻን እና የዶክተር መረራን አባላቶች አልጠረጠሩም? ሰዉስ «የዘንድሮ ምርጫ ክልሎች ላይ ያስጋል ይኸው ቀብድ ሰው ይገደል ተጀመር!» እያለ ሲፈራ አልከረመም? ታድያ የሰዉ ፍርሃት ከንቱ ቀርቶ ምርጫውን ሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ፍትሃዊ ሁሉን አሳታፊ በመላው ህዝባችን ዘንድ ተአማኒነት ያገኘ ፍፁም እና ቅዱስ በሆነ መልኩ ገዢው ግንባር ሙሉ በሚሉ አላሸነፈም? ሰዉስ በዚህ ጊዜ መች ዝም አለ? «መንገድም ህይወትም እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ወደ ፓርላማ የሚገባ አንድም የለም» አለ ገዢው ግንባር አለ:: አልተባለም? ታድያስ የአመቱ ዋና ጉዳይ ምርጫ ነበር ቢባል ምን ሀሰት አለው?

ከዚሁ ጋር ተያይዞ

## ከመጨረሻው በፊት

ሰሞኑን ፀሐዩ መንግስታችን የርቀት ትምህርት የሚባል ነገር እንዲቀር አውጇል! (በቅንፍ አዋጅ እንኳ አይደለም ብቻ ዋናዎቹ ሰዎች ትዕዛዛቸው ቀርቶ «አንጥሴ» ሲሉም እንደ አዋጅ መቁጠር የኛ ፈንታ ነው ሞገስም ያስገኛል ብለን ነው) እናም የርቀት ትምህርት የሚባል ነገር እንዳንሰማ ብለዋል አሉ:: ማ? ዋናዎቹ ሰዎች... አንዳንዶች «እረ ጎበዝ ራሳችሁ በደህናው በርቀት ትምህርት ተምራችሁ ስታበቁ እኛን መከልከል ጡር አይደለም እንዴ?» እያሉ ቢጠይቁም «የራስሽ ጉዳይ» ዜማን ተጋብዘዋል አሉ:: «አሉ» ላይ አስምሩልኝ:: ታድያ ይሔ ሀሳብ የተወጠነው አሉ ከምርጫው በፊት ነበር:: ምነው ውሳኔውስ እንደ ውጥኑ ከምርጫው በፊት ለምን አልሆነም? ቢሉ መልሱ «ያ ሁሉ የርቀት ትምህርት ተማሪ፣ ያ ሁሉ የርቀት ትምህረት ላይ የሚሰራ ሰራተኛ፣ ያ ሁሉ የእነርሱ ዘመድ አዝማድ... ያ ሁሉ ወዘተ. ከምርጫው በፊት ተቀይሞ ቢሆን መልካም አልነበረምና!» ሲሉ ግምታዊ መልሳቸውን ይሰጣሉ:: የሆነ ሆኖ ግን ፀሐዩ መንግስታችን ለርቀት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለግል ትምህርት ተቋማት በሙሉ ደመና ጥሎባቸዋል::

**<u>ደመና አንድ</u>**:- የህግ ትምህረት ከዚህ በኋላ በግል ተቋም አይሰጥም::

**<u>ደመና ሁለት</u>**:- ከዚህ በኋላ በዲግሪ ተማሪዎችን የሚያስተምሩ የግል ተቋማት መንግስት በሚሰጣቸው ኮታ መሰረት ይሆናል:: ደመናው በርካቶችን እተቱ አስብሏል:: ደግነቱ ከምርጫው በኋላ ነው!

**<u>በመጨረሻም</u>**

ይሔ የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ የሀገሬን ጎረምሳ ሁሉ ቀልብ ስቧል ከማለትም በላይ ቆሌ አሳጥቷል ማለቱ ይሻላል:: ታድያ ሰሞኑን በአንዱ ኤፍ አም ጣቢያ የስፖርት ውይይት ላይ አንድ ጎረምሳ አድማጭ ደውሎ ነበር:: ወጣቱ በሊቨርፑል ውጤት ደስታ የራቀው ነው:: እንዲህም አለ::

«በሊቨርፑል ውጤት በጣም ተማርሬያለሁኝ:: ከዚህ የተነሳ አሁን አሁን አምላኬን የምለምነው ፆታዬን ቀይሮልኝ እግር ኳስ ማየቱን ትቼ ቁጭ ብዬ ቡናዬን እያፈላሁ «ገበና» ድራማን ማየት እየተመኘሁ ነው» አለ:: በርግጥ ይህ ወዳጃችን እውነትም የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ አስተሳሰቡን ሁሉ አዛብቶበታል እንጂ (እግረ መንገዴን እግዜር ይማርህ ልለው እወዳለሁ) እንጂ ድራማው ፆታ የሚለይ አይደለም:: ነገር ግን ብዬ ስቀጥል ስለ «ገበና» ድራማ የአንዳንድ ህብረተሰብ ክፍሎችን አስተያየት አገኛለሁ:: በአዲስ መስመር

አንድ ከአንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች አንዱ የሆነ ወዳጄ ይህንን ድራማ አይቶት አያውቅም:: ምክንያቱን ሲያስረዳ የማያልቅ ታሪክ ማየት አልሻም:: ይላል:: ታድያ ሰሞኑን ይህ ወዳጄ አንድ የምስራች ሰምቷል:: ««ገበና» ከአራት ክፍል በኋላ ያልቃል!» እና ወዳጄ ምን እንዳለ ያውቃሉ? «እውነትም እንደሚያልቅ ዋስትና ይገባልን እና እናያለን!» ወዳጄ አሁን መጨረሴ ስለሆነ ልመርቅዎ! እንደ «ገባና» የማያልቅ ሲሳይ ይስጥዎ! «አሜን» ካሉኝ አማን ያሰንብተን!

**ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ**

ወደ ገፅ 23 ዞሯል


# አዲስ ኮሌጅ

- **<u>አራት የቴክኖጂ ሙያዎችን በመጀመሪያ ድግሪ ደረጃ</u>** - ለእያንዳንዳቸው ዋና እና ደጋፊ ትምህርቶች የተጠናከሩ ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖችን አደራጅቶ፣
- **<u>ከ14 በላይ የቴክኒክና የቢዝነስ ሙያዎችን በአዲሱ የTVET መመሪያ መሠረት ከደረጃ I እስከ ደረጃ IV</u>** - ለያንዳንዳቸው ዋና እና ደጋፊ ኮርሶች ዎርክሾፖችን አደራጅቶ በድምሩ በ33 ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖች እና በ31 ክፍሎች የሚያሰለጥን፤ ከክልልና ከአጎራባች ሀገሮች ጭምር በምርጫ እየመጡ የሚሰለጥኑበት ለአለፉት 18 ዓመታት ተማሪውን ሥራ ፈጣሪና ተቀጣሪ ያደረገ ኮሌጅ ነው:: በመሆኑም ከየትኛውም የኒቨርስቲ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ በዝውውር የሚመጡ ተማሪዎችን ተቀብሎ በማሰልጠን ለገበያው የሚያበቃ መሆኑን እየገለጸ፤ በአዳማ ከተማ አዲስ በከፈተው ቅርንጫፍ ተማሪዎች የሚቀበል መሆኑን በደስታ ያስታውቃል

## የቴክኒክ ሙያዎች

| Occupations | Level |
|---|---|
| • Automotive electricity - Electronics | I - IV |
| • Automotive Service & Engine Overhauling | III |
| • Industrial Electrical Machine & Drive Technology | I - III |
| • Audio-Video Equipment Technology | IV |
| • Electronics office Equipment Technology | IV |
| • Electrical House Hold Appliances Technology | III |
| • General Drafting Technology | II - IV |
| • Surveying Technology | I -IV |
| • Masonry | I -IV |
| • Building Electrical Installation | I -IV |
| • Concrete work | I -IV |
| • Plumbing | I -IV |
| • Plastering | I -IV |
| • Tiling | I -IV |
| • Painting and Decorating | I -IV |
| • Building Metal work | I -IV |
| • Coble Stone Road Construction | I - III |

## የቢዝነስ ሙያዎች

| Occupations | Level |
|---|---|
| • Accounting | II - IV |
| • Office Administration and Secretarial Technology | IV |
| • Purchasing | IV |
| • Insurance | IV |
| • Marketing | IV |
| • Hardware and network Technology | III |
| • ICT Support system Service | III |
| • Web and Multimedia Technology | IV |
| • ICT Assistance | IV |

## በቴክኖሎጂ የዲግሪ ሙያዎች

| Programs | Level |
|---|---|
| • Architecture and Urban Planning | 1st Degree |
| • Automotive Technology & Vehicle Management | 1st Degree |
| • Construction Technology and Management | 1st Degree |
| • Electrical - Electronics Technology | 1st Degree |

አድራሻ:- 0116 63 56 93/94 0116 63 12 77 0911 22 18 10


PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# ምርጫ 2002

በኤልያስ ገብሩ

ከነሐሴ መጨረሻ 2001 ዓ.ም ጀምሮ ለውይይት ቀርቦ የነበረው የፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ደንብና የማስፈጸሚያ መመሪያው ከብዙ ውይይቶችና ድርድሮች በኋላ ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ሰነዶቹ በተባበረ ድምፅ መጽደቃቸው ተገልፀ:: ተደራዳሪዎቹም ኢህአዴግ፣ መኢአድ፣ ኢዴፓ እና ቅንጅት ሲሆኑ መድረክ ግን «ድርድሩ በተናጠል በእኛና በኢህአዴግ ብቻ ካልሆነ በጋራ መቀጠል አልችልም» በማለት ድርድሩን በመጀመሪያ ቀን ያቋርጣል:: የመድረክ ጥያቄ በገዥው ፓርቲ ተቀባይነት ሳያገኝ ቢቀርም መድረክ በድርድሩ ውስጥ እንዲካተት በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሳደርና የኤምባሲው የፖለቲካ ጉዳዮች ኃላፊ ባደረጉት ጥረት ተደራዳሪ ፓርቲዎች «መድረክ» ድርድሩን እንዲቀላቀል የፈቀዱ ሲሆን በስምምነቱ ላይ ፊርማቸውን ለማኖር ይስማማሉ::

መድረክም ድርድሩን ቢፈልገውም ድርድሩን ማድረግ የሚፈልገው «በተፅዕኖ ስር እንዳልሆነ፣ በምርጫ መግባቢያ ሰነድ ላይ ከማንኛውም ፓርቲ ጋር የመደራደር ችግር እንደሌለበት፣ በኢህአዴግ በቀረበ ሰነድ ብቻ ሳይሆን በመድረክ እጅ በሚገኘ በሌሎች አገሮች ልምድ መሆን እንዳለበት፣ በፓርቲው አባላት ላይ እየተፈፀመ በሚገኘው ሕገ-ወጥ ድርጊት እና እንግልት እንዲሁም በሕግ የበላይነት፣ በፖለቲካ ምህዳር መጥበብ፣ በምርጫ ታዛቢዎችና አስተዳደር ጉዳይ፣ በፖለቲካ እስረኞች ዙሪያ፣ ስለሚዲያ አጠቃቀምና ሰዓት ክፍፍል እንዲሁም የፓርቲዎች ገንዘብ ድጐማን በተመለከተ መደራደር እፈልጋለሁ ቢልም «አሁን ባለው ሁኔታ ወደ ድርድሩ ለመመለስ የሚያስችል ሁኔታ የለም» ሲል ውሳኔ ላይ ይደርሳል::

የኢህአዴግ ፅ/ቤት በበኩሉ ለመድረክ አባል ድርጅቶች በአድራሻቸው ደብዳቤ በመላክ «ራስን ከሒደቱ ያለ በቂ ምክንያት የሚያገል እርምጃን አስተካክላችሁ ወደ ድርድሩ በድጋሚ እንድትመለሱ ጥሪያችንን እናቀርባለን» ቢልም የተለየ ነገር ሳይፈጠር የድርድሩ ምዕራፍ ሁለት በምዕራፍ አንድ የመግባቢያ ሰነድ አፈፃፀም ላይ መስከረም 21/2002 ዓ.ም ተጀመረ::

18 ወራት በምስረታ ሂደት ላይ የቆየው መድረክ ከስምንት ፓርቲዎች በተወከሉ 56 አባላት አማካኝነት ምስረታውን በይፋ መስከረም 30/2002 ዓ.ም አድርጎ ለቀጣይ አራት ወራት ፓርቲውን የሚመሩ ሥራ አስፈፃሚዎችን መርጠ::

## «ታሪካዊ» ስምምነት

የአራቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ደንብ ስምምነት ዓርብ ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በሸራተን ሆቴል ተካሂዶ ትግበራው ወዲያው እንደሚጀመር ይፋ ተደረገ:: የዕለቱን የፊርማ ሥነ-ሥስርዓት በንግግር የከፈቱት በሚ/ር ማዕረግ በፓርላማ የመንግስት ዋና ተጠሪ የሆኑን አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ መድረክን አስመልክቶ «በተሳሳተ አቋም ምክንያት በግል ካልተደራደርኩ በማለት የዚህ ድርድር አካል ሳይሆን ቀርተዋል:: ሰው በግል የሚደራደረው ለግል ጉዳይ እንጂ ለአገራዊ ጉዳይ የግል የሚባል ነገር የለም» ብለዋል::

ፓርቲዎቻቸውን ወክለው ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል፣ አቶ ልደቱ አያሌውና አቶ አየለ ጫሚሶ እርስ በእርስ የተጨባበጡ ሲሆን በተለይ የአቶ መለስና ኢ/ር ኃይሉ ሲጨባበጡ ላሊበላ አዳራሽ በሞቀ ጭብጨባ ደምቆና የታዳሚዎች ፊት ፈክቶ ነበር::

አቶ ልደቱ «ስምምነቱ ታሪካዊ ሊባል ቢችልም የሚለካው ግን በትግበራ ነው» ሲሉ ኢ/ር ኃይሉም «በዚህ ድርጊት ብዙ ተወያይተናል:: ቅሬታ ቀርቶ በወዳጅነት መተያየት ጀምረናል:: ከድርድር ሌላ አለ ብሎ የሚያስብ ተሳስቷል» ካሉ በኋላ እርስ በእርስ በመናከስ የኡኡታ ፖለቲካ ማራመድ እንደማይገባ፣ ሰው የሚለካው በራዕዩ መሆኑንና አንዳንዴ ስናፈነግጥ እየከረኮሙ ለዚህ ስምምነት ያደረሱንን የኢትዮጵያ ወዳጅ አምባሳደሮች እጅግ አመሰግናለሁ» ብለዋል:: ጠ/ሚኒስትር መለስ በበኩላቸው «እኔና ኢ/ር ኃይሉ በአካል ተገናኝተን ለመነጋገር ባልቻልንበት ወቅት ሌሎች ተደራዳሪዎች የላቀ ውጤት በማምጣታቸው አመሰግናቸዋለሁ» በማለት ድርድሩና ስምምነቱን ታላቅ ክንዋኔ ሲሉ አሞካሽተውታል::

ይህ ክንውን በተለያዩ ወገኖች «ታሪካዊ» ተብሎ ደስታን ቢፈጥርም በአንፃሩ በስምምነቱ የተከፉ፣ ያልተስማሙ፣ ያዘኑና ጥርጣሬ የነበረባቸው በርካቶች ነበሩ:: የመኢአድ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና አባል የነበሩት ሻለቃ አረጋው ምርጫ ቦርድ በድርድሩ ወቅት አለመግባቱን በመጥቀስ ራሳቸውን ከፓርቲው ያገለሉበት ሁኔታ አይዘነጋም::

ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም በወቅቱ «ስምምነቱ መለስን ምንም አያስከፍለውም፣ ኃይሉ ግን ተጨባጭ ውጤት ካላስገኘ ዋጋ ይከፍልበታል» ሲሉ አውራምባ ታይምስ ላይ መጻፋቸው ይታወሳል:: የአራቱን ፓርቲዎች ስምምነት ተከትሎ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ረቡዕ ጥቅምት 25/2002 ዓ/ም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለውይይት ጠርቶ የነበረ ቢሆንም መድረክ ስብሰባውን ረግጦ ወጥቷል:: የኋላ ኋላ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ደንብ «ማን ያውጣው» በሚል ከፍተኛ ውዝግብ ገጥሞት ለፓርላማ ቀርቦ ሁሉን ፓርቲዎች ይገዛ ዘንድ የሀገሪቱ የምርጫ ሕግ አካል ሆኖ ፀድቋል::

## ዶ/ር ነጋሶና አቶ ስዬ በአንድነት

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና አቶ ስዬ አብርሃ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን መቀላቀላቸውን አስመልክቶ በጊዮን ሆቴል በተደረገው ጥሪ ላይ ንግግር ባደረጉበት ወቅት ዶ/ር ነጋሶ ኅዳር 29/1987 ዓ.ም ሕገ መንግስቱ ሲፀድቅ ንግግር እንዳደረጉ በማስታወስ «ንግግሬ ትልቅ ስህተት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ራስን መዋሸትና ማታለል ነበር» በማለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቀዋል::

## «የሥነ-ምግባር ደንቡ እየተጣሰ ነው»

የካቲት ወር መጨረሻ ላይ መኢአድ «በፓርቲዎች የጋራ ስምምነት የፀደቀው የስነ ምግባር ደንብ እየተጣሰ ነው» በሚል ጋዜጣዊ መግለጫ በማድረግ «በገዥው ፓርቲ እየደረሱበት ያሉት ተፅዕኖዎች በመጪው ግንቦት የሚካሄደውን ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ፍትሃዊና ነፃ የሚያደርጉ አይደሉም» በማለት ተፅዕኖዎቹን በዝርዝር አቅርቧል:: ኢህአዴግም መኢአድ ካቀረባቸው 30 ቅሬታዎች 27ቱ የራሱ ችግር መሆናቸውን አምኖ ተቀብሏል ማለቱ ይታወሳል::

## የአቶ ስዬ አነጋጋሪው ንግግር

አንድነት ፓርቲ በፅ/ቤት ጥር 20/2002 ዓ.ም በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት አቶ ስዬ የግንቦቱን ምርጫ አስመልክተው «እኔ በተምቤን ካላሸነፍኩ/ ገብሩ አስራት በመቀሌ ካላሸነፈ ምርጫው ተጭበርብሯል ማለት ነው» በማለት «ኢህአዴግ በምንም ተዓምር እኔን የሚያሸንፍ ተወዳዳሪ ሊያመጣ እንደማይችል አውቃለሁ» ካሉ በኋላ ንግግራቸውን በሚያጠናክር መልኩ «...እውነት መናገር አያስቆጣም» ብለው ነበር::

ይሄ አነጋገራቸውም ለረዥም ጊዜ በሕብረተሰቡ ዘንድ እንደ ትልቅ መነጋገሪያ ሆኖ «ምርጫ ከመካሄዱ በፊት፤ እንዴት እንደዚህ ዓይነት አስተያየት ይሰጣሉ?» የሚል ጥያቄ አስነስቶባቸዋል:: ገዥው ፓርቲም በሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው አቶ ሴኮቱሬ አማካኝነት መድረክ ሥነ-ምግባር ደንቡን ሳይፈርም መቆየቱን ጠቅሰው «ሕዝብ ከወዲሁ በሂደቱ ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረው ለማድረግና ብጥብጥ ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ነው:: እነዚህ ኃይሎች ከሻዕቢያ ጀምሮ እስከ ግንቦት ሰባት ድረስ ሰፊ ኔትዎርክ ፈጥረው አብረው የሚሰሩ ናቸው:: የአንድነት መግለጫ የዚህ ስትራቴጂ አንድ አካል ነው» በማለት ለአቶ ስዬ ንግግር ምላሽ ሰጥተዋል::

## የእለተ ምርጫ ጥቂት ትዝብቶች

«በተራሮች ሰንሰለት መሐል ያለችው» ሲል ወደጠራት ትግራይ የግንቦት 15/ 2002 ዓ.ም የምርጫ ዕለት ምን እንደሚመስል ተመልክቶ ለመዘገብ የተጓዘው ባልደረባችን ውብሸት ታዬ ነበር::

በወቅቱ የውብሸትን ትኩረት ስቦ የነበረው በ1990 ዓ.ም የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የኤርትራ መንግስት በአይደር በ1ኛ ደረጃ ት/ቤት ህፃናት ላይ የተፈፀመውን አስቃቂ የአውሮፕላን ድብደባና የግፍ ጭፍጨፋ እያሰቡ የቅጥር ግቢውን ዙሪያ ገብ ሲዳስሱ የ13 ህፃናት ተማሪዎች ስም ዝርዝር የያዙ የመታሰቢያ ሰሌዳዎች በአንድ የትምህርት ክፍል ፊት ለፊት መመልከቱና ይህም ት/ቤት ለግንቦቱ ምርጫ አገልግሎት ከሰጡ ጣቢያዎች ውስጥ አንዱ ሆኖ መገኘቱ ነበር:: በመጀመሪያው ሰሌዳ ላይ የአክሱማይት ገ/ስላሴ ስም ተፅፎበት ይገኛል::

በወቅቱ ከምርጫ አስተባባሪዎች አንዱ የሆነው ወጣት ብርሃኑ ኪሮስ የመራጩ

ወደ ገፅ 23 ዞሯል

# የምርጫ ካርድ ዋጋ ስንት ነበር?

በግዛው ለገሠ

ዛሬም በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ስለምርጫ ምንነት መፃፍ አንባቢን ማሰልቸት ነው፤ የምርጫ ካርድ መውሰድ ግን የምርጫውን ምንነት ከሚወስኑት አንዱ መሆኑ አያጠራጥርም::

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባሰፈረው መረጃ መሠረት ለ2002 ምርጫ የተመዘገበውና የምርጫ ካርድ የወሰደው የሕዝብ ቁጥር ከ31 ሚሊዮን በላይ ነው:: ይኸም ቁጥር በ97 ምርጫ ከተመዘገበው 27.4 ሚሊዮን በመብለጡ ዘንድሮ የሕዝብ ተሳትፎ አይሎ መገኘቱንና ይህም የሀገሪቱን የዲሞክራሲ ልምላሜ የሚያመላክት መሆኑ በቦርዱም ሆነ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ተደጋግሞ ተነግሯል:: በሁለቱ ወቅቶች ለመራጭነት ብቁ የነበው (እድሜው ከ18 በላይ የሆነ) የሕዘብ ቀጥር መጠን ግን ከግምት ሲገባ አልተመለከትንም:: ምክንያቱም የተመዘጋቢ መራጩ ቁጥር መጨመር በትክክልም የሕዝባዊ ተሳትፎ መጨመርን የሚያሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ ለመራጭነት ብቁ የሆኑ ዜጎችን መጠን መሠረት አድርጐ ማስላት ትክክለኛው ቀመር ነበርና::

በሌላ አገላለፅ በ97 ለመራጭነት ብቁ ከነበረው ሕዘብ ስንት ስንተኛው ተመዘገበ፤ እንዲሁም በ2002 ለመራጭነት ብቁ ከነበረው ሕዝብ ስንት ስንተኛው ሊመርጥ ተመዘገበ የሚለውን በማስላት ነው የሕዝባዊ ተሳትፎን መጨመር ማወቅ የሚቻለው:: በኢትዮጵያ የመራጭነት ዕድሜ መጠን መነሻ እንጂ (18 ዓመት) ማብቂያ ገደብ የለውም፤ በ1997 ዓ.ም እድሜያቸው 13 እና ከዚያ በላይ የሆነ ዜጎች ሁለ በ2002 ዓ.ም ለመራጭነት ብቁ ነበሩ፤ እናም ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን ምርጫ ቦርድም ቢሆን የፖለቲካ ተሳትፎውን መጨመር እንዲሁ በደፈናው ሲመሰክር ነበር::

ሆነም ቀረ በ2002 ምርጫ ከ31 ሚሊዮን ሕዝብ ላይ መመዝገቡ ተነግሯል:: «የምርጫ ካርድ ውሰዱ» በሚለው ቅስቀሳ ሁሉም ፓርቲ እንደየደረጃው ተሳትፏል፤ በርግጥም ምርጫ ያለካርድ ፋይዳ አይኖረውምና:: ታዲያ በዚህ ባገባደድነው ዓመት በተካሄደው ምርጫ ከካርድ ጋር በተያያዘ አስገራሚ ክስተቶችን ተመልክተናል፤ የ2000 ምርጫን ጨምሮ የሌላ ዘመን የምርጫ ካርድ ይዘው ድምፃቸውን ለመስጠት የቀረቡ መራጮች የብዙዎችን ቀልብ ስበው ነበር:: በዚህ ጉዳይ በሀገሪቱ ፖለቲካ ግዙፍ ቦታ የሚሰጣቸው ግለሰቦችም ተሳታፊዎች ነበሩ፤ ሆኖም «ሁለቱ አልታለልም» ብለው ጭራሹኑ ካልተመዘገቡት እንጀምር::

«እኔ በራሴ በግሌ ስመለከተው በ97 ተታልያለሁ» የሚሉት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ገና ምርጫው ወራት ሲቀሩት፣ ጥር 29 ቀን 2002 ዓ.ም ከአውራምባ ታይምስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ነው:: «መለስ ዜናዊ ካእንከን የሌለው ምርጫ እናካሂዳለንካ አለን:: እኔ በእውነቱ አመንኩት:: አስቲ እንየው፣ አይተነው ካልሞከርነው ይሄ ሰውዬ እውነቱን ይሁን አይሁን ማወቅ አንችልም ብዬ ታጥቄ ነተሳሁ» ይላሉ:: በወቅቱ ለሕዝባዊ ተሳትፎ ወሳኝነትም ይተጉ እንደነበር ይገልፃሉ:: «ሰው ሁሉ እንዲመዘገብ በየሳምንቱ ለአንድ ዓመት ያህል ስለምርጫው በጋዜጣ ላይ እፅፍ ነበር::... እኔም በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ተመዘገብኩ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ መረጥኩ::» ይላሉ::

ፕሮፌሰር መስፍን በድህረ ምርጫ 97 የተከሰተውን ከዘረዘሩ በኋላ በዚህኛው ምርጫ ግን ተስፋ መቁረጣቸውን ይናገራሉ:: «አንድ ጊዜ መታለል የሚቻል ይመስለኛል:: ሁለት ጊዜ ለመታለል ግን መዘጋጀት ይጠይቃል:: እኔ በበኩሌ አንዴ የተታለልኩት ይበቃኛል::» ብለዋል:: የኢትዮጵያ ፖለቲካ በተነሳ ቁጥር የእርሳቸው ስምም አብሮ መነሳቱ አይቀሬ ይሁን እንጂ፣ ፕሮፌሰር መስፍን «ፖለቲከኛ አይደለሁም» ባይ ናቸው:: በ2002 ምርጫ ተወዳዳሪም መራጭም አልነበሩም፤ ጊዜው ያለፈበት የምርጫ ካርድም በእጃቸው ሊገኝ አይችልም::

በዘንድሮ ምርጫ ጊዜ ያለፈበት የምርጫ ካርድ ይዘው ድምፃቸውን ለመስጠት ወደ ምርጫ ጣቢያ ከደረሱት ብዙ ሰዎች መካከል የኢፌዴሪ የቀድሞ ፕሬዝዳንትና በዚህ ምርጫ መድረክ/አንድነትን ወክለው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወንበር የተወዳደሩት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ይገኙበታል:: «ይኼ ቢያመልጠውማ ጉድ ይባል ነበር» የተባለለት ኢቴቪም ክስተቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማሳየት አላንገራገረም:: ዶ/ር ነጋሶ ድምጽ ሊሰጡ የመጡት የ2000 ዓ.ም ማሟያ ምርጫ ካርድ ይዘው መሆኑ ብዙዎችን ያስገረመ ክስተት ነበር::

ዶ/ር ነጋሶ አሁን በቅርቡ፣ ነሐሴ 02 ቀን 2002 ዓ.ም ከአውራምባ ታይምስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ «አጋጣሚው እንዴት ተፈጠረ? ለምርጫው ትኩረት ባለመስጠት የመጣ ይሆን?» ተብለው ተጠይቀው ነበር:: እርሳቸውም ሲመልሱ «አይደለም» በማለት ይጀምራሉ:: «ጠዋት ከቤቴ ስወጣ ካርዷ መኖሯን እና አለመኖሯን አረጋግጬ ነበር:: በኋላ ቤቴ ስመለስ ግን ኮመዲኖዬ መሳቢያ ውስጥ አግኝቻታለሁ:: ይህ በአጋጣሚ የተከሰተ ነው እንጂ ለምርጫው ትኩረት ባለመስጠት የመጣ አይደለም::» ዶ/ር ነጋሶ የቀድሞ የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት እንደመሆናቸው፣ ለመሠረታዊ ፕሬዝዳንታዊ ተቋሙ ሲባል የግላቸው ፕሮቶኮል እና ፕሮግራም ቀያሽ እንደሚያስፈልጋቸው ብዙዎች ያምናሉ፤ ለአሁኑ የኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓት የመጀመሪያው ፕሬዝዳንት እንደመሆናቸው መጠን::

ምርጫን በተመለከተ አንድ ድምጽ ወሳኝነቷ ምን ያህል እንደሆነ የምርጫ ቅስቀሳን እልህ አስጨራሽ በሆነ መልኩ የሚያካሂዱ ፖለቲከኞች ያውቁታል:: አንድ ተመራጭ ሌሎች እንዲመርጡት ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ እርሱ እራሱ ካርድ በመውሰድ እና በመምረጥ የሚሳተፍበት ክንውን አንዱ ነው፤ የምርጫው ቀን ከመድረሱ በፊትም እራሱ ካርድ ወስዶ ሌሎችም እንዲወስዱ በመወትወት::

> መለስ ዜናዊ እንከን የሌለው ምርጫ እናካሂዳለን አለን:: እኔ በእውነቱ አመንኩት:: አስቲ እንየው፣ አይተነው ካልሞከርነው ይሄ ሰውዬ እውነቱን ይሁን አይሁን ማወቅ አንችልም ብዬ ታጥቄ ነተሳሁ»

የካቲት 10 ቀን 2002 ዓ.ም ምርጫ ቦርድ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ካርድ የሚወሰድበት የመጨረሻ ቀን ነበር:: ሆኖም ጊዜው ሲቃረብ ቦርዱ ተጨማሪ አምስት ቀናት እንደሚኖሩ አስታወቀ:: ነገር ግን የተጨመረው ቀን ራሱ በቂ እንዳልሆነ የገለፁ ወገኖች ነበሩ:: የካቲት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በወጣው አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ «የምርጫ ካርድ ለመውሰድ የተጨመረው ቀን በቂ እንዳልሆነ ፓርቲዎች ገለፁ» በሚል ርዕስ በሰፈረው ዜና ውስጥ ይህንን ከሚሉ ወገኖች አንዱ ዶ/ር መረራ ጉዲና ናቸው:: በወቅቱ የመድረክ ሊቀመንበር ነበሩ:: በዚሁ የጋዜጣው እትም ላይ የሊቀመንበሩ ቃለ ምልልስ ቀርቦ ነበር:: በወቅቱ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ባውጠነጠነው ሰፊ ቃለ-ምልልስ ማብቂያ ላይም፣ «በመጨረሻ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ» ተብለው ተጠይቀው ነበር::

ዶ/ር መረራ ሲመልሱም፣ «የኢትዮጵያ ሕዝብ የምርጫ ካርድ እንዲወስድ እንጠይቃለን:: ካርዱን ከያዘ የፈለገውን የመምረጥ እድሉ በእጁ ላይ ነው:: እና ቀኑ ሳያልቅ እየተመዘገባችሁ የምርጫ ካርድ ውሰዱ እንላለን::» ብለው ነበር:: ዶ/ር መረራ ይህንን ይበሉ እንጂ በዚህ በምርጫ 2002 እርሳቸውም የምርጫ ካርድ አልወሰዱም ነበር:: አዎን፣ የምርጫውን ሂደት ለመዘገብ ወደ አምቦና አካባቢዋ ያቀናው የአውራምባ ታይምስ ዋና አዘጋጅ ፍፁም ማሞ በወቅቱ አነጋግሯቸው ይህንኑ ገልፀውለታል:: ዶ/ር መረራ እርሳቸው ይወዳደሩበት በነበረው የምርጫ ጣቢያ ይገኙ እንጂ እራሳቸውን የመምረጥ እድሉ ግን አልነበራቸውም፤ ካርዷን አልያዙምና::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# ነጻ ፕሬሱ የሚጠብቀውን የለካበት

በውብሸት ታዬ

በአገራችን ታሪክ የመጀመርያ የነበረው የ1923ቱ ሕገ መንግስት የግል ምስጢርን አስመልክቶ በአንቀጽ 26 ላይ «ማንኛውም ዜጋ የሚፃፃፈው ወረቀት በማንም ሊመረመርበት አይገባም» በሚል ሲደነግግ የንጉሰ ነገስቱን አዘማኝነት ለሌሎች አገራት ለማሳየት ካልሆነ በተጨባጭ ፋይዳ የሌለው ተደርጎ ተቆጥሮ ነበር:: ምክንያቱም ይህ ሕገ መንግስት በወጣበት ወቅት በመላ አገሪቱ የነበረው ት/ቤት አንድ /በዳግማዊ ምኒልክ ስም ተከፍቶ የነበረውና የመኳንንቱ ልጆች ብቻ ይማሩ የነበሩበት/ መሆኑ ነበር:: ይሁንና ግን ከ25 ዓመታት በኋላ ሌላ አነጋጋሪ ሕገ መንግስት ተደነገገ::

ይህ «በንጉሰ ነገስቱ መልካም ፍቃድ» የወጣ ሕገ መንግስትም እንዲሁ አነጋጋሪ አንቀጽ ነበረው:: አንቀጽ 41 የመናገርና የመፃፍ መብት እንደሚከበር ገለጸ:: ይህ እምርታ ግን በቀጣዩ አመት በወጡ አፋኝ የወንጀል ሕጎች የፕሬስ ነፃነት ጉዳይ የይስሙላ መሆኑን አረጋገጡ:: ከመነሻው ቁርጠኝነት ያልነበረበት «እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ንሳው» የሚሉት ይትበሃል በተግባር ታየ::

...ስለንጉሰ ነገስቱ የፕሬስ አዋጅ ለመነጋገር አይደለም:: ያ ሕገ መንግስት ከወጣ ከግማሽ ምዕት ዓመት በኋላም እንኳ ይኸው የ«እንዳያማሕ ጥራው...» ምስጢራዊ ፖሊሲ ነፃው ፕሬስ ላይ የራሱን ጥላ እየጣለ መሆኑን እያጠናቀቅነው ባለነው ዓመት መከሰቱን ለማመልከት ነው::

እያጠናቀቅነው ባለነው ዓመት ከተካሄዱ ጉልህ ክስተቶች አንዱ በአገር አቀፍ ደረጃ የተከናወነው ምርጫ ሲሆን ምርጫው ተቀባይነት ያለው፣ ፍትሐዊ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ፣ እና የመሳሰሉትን እንዲሆን ለማስቻል በሚል በተሻሻለው የምርጫ ሕግ አዋጅ (ቁጥር 532/1999 ዓ.ም አንቀጽ 59(4)፣ 91(4) እና 110) መሰረት ቦርዱ ያወጣው የስነ ምግባር ደንብ ነበር:: የስነ ምግባር ደንቡ «የመገናኛ ብዙኃን እና የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2002 ዓ.ም» ተብሎ ይጠራል:: ለምን ግማሽ ምዕተ ዓመት ወደኋላ መለስ ማለት አስፈለገ? ሊባል ይችላል:: ተገቢ ነው:: የንፅፅሩን አንድምታ ማመልከትም ያስፈልጋል::

## አዋጆች ዋስትና ያልሰጡት የፕሬስ ነጻነት

የሕገ መንግስታችን አንቀጽ 29 ቁጥር 4 ለዴሞክራሲያዊ ስርአት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ኃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል ይላል:: ቁጥር 6 ደግሞ ይህ መብት ገደብ ሊጣልበት ስለሚችልበት ሁኔታ የሚገልፀው እጅጉን ትኩረት ይስባል::

የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት <u>በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት</u> ሊገታ አይገባውም በሚል መርሕ ተመስርቶ በሚወጣ ሕግ ብቻ ...» /ሰረዝ የተጨመረ/ ይላል:: ይህ ድንጋጌ ለፕሬስ ነፃነቱ ዋስትና ሆኗል? ብለን ስንጠይቅ በተከታታይ የወጡት ሕጎች ይህንን የሚያጠናክሩ ናቸው ወይስ አደጋ ላይ የሚጥሉ? የሚል ጥያቄውን በጥያቄ የሚመለስ ሆኖ እናገኘዋለን::

የ2001ዱ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ በአንቀጽ 6 ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት በሚል ከዘረዘራቸው ሁኔታዎች ተደራሲዎቹ /አንባቢዎቹ/ የሚያነቡት ነገር «... ድርጊቱን እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈፀም እንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታታቸው ወይም <u>በማናቸውም ሌላ ሁኔታ የሚገፋፉቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልዕክት ...</u> ከ10-20 ዓመት ፅኑ እስራት ...::» / ሰረዝ የተጨመረ/ ይላል::

«በማናቸውም ሌላ ሁኔታ፣ የሚገፋፉቸው አድርገው ይረዱታል፣ እንዲሁም ተብሎ ሊገመት የሚችል» የሚሉትን ሶስት ሐረጎች የሚያነብ ማንኛውም ሰው «ማናቸውም ሌላ ሁኔታዎች ምንድናቸው? አንባቢዎቹ የሚገፋፉቸው አድርገው መረዳታቸው ከግላዊ እምነታቸውና የፖለቲካ አስተሳሰባቸው የሚመነጭ ከመሆኑ አንፃር ይህ ሃሳብን የመረዳት መጠን ሌላኛውን ወገን እስከ 20 ዓመት የሚያስቀጣው በምን ስነ አመክንዮ ነው? ሊገመት የሚችል የሚለውስ በአንድ የወንጀል ድርጊት ውስጥ በርካታ ተገማች ሁኔታዎች መኖራቸው ወደውጤት ያመራሉ እንጂ ሊገመቱ መቻላቸው (ደግሞ ገማቹስ ማነው?) እንዴት ጥፋተኛ ያደርጋል?...» ብሎ መጠየቁ አይቀርም::

ይህ ሕግ «በአስተሳሰባዊ ይዘትና ሊያስከትለው በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም» ከሚባልለት የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት መርሕ ተነስቶ የተደረገ ገደብ ነው ሊባል አይችልም:: የሆነ ሆኖ ይህና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ወደ 2002ቱ አዘጋገብ ስነምግባር ተያያዥ ጉዳዮች ጉልህ ክስተት ይመራናል::

ከዚያ በፊት ግን በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አማካይነት የመገናኛ ብዙኃንን አስመልክቶ በ2000 ዓ.ም የወጣውን የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅን በማስታከክ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ሲቀርቡበት ከነበሩት ቅሬታዎች ሁለቱን ብቻ በመመልከት ወደሌላኛው አነጋጋሪ የምርጫ ቦርድ የስነ ምግባር ደንብ እናልፋለን::

ባለስልጣን መ/ቤቱ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት ሥራ ወይም የዜና አገልግሎት ሥራ ለመሥራት የምዝገባ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም ባዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ተራ ቁጥር 6 ላይ የፕሬስ ሕጉን አንቀጽ 6 (ዋና አዘጋጅ ስላለው ስልጣን፣ ሊኖረው ስለሚገባ ችሎታና የሕግ ተጠያቂነት) በማጣቀስ የሕትመት ባለቤቶች ዋና አዘጋጅና ም/ዋና አዘጋጅ መሆን አይችሉም ይላል::

በማመልከቻ ቅጽ ቁጥር 9 ላይ ደግሞ የፕሬስ አዋጅ አንቀጽ 7/3/ን (በየጊዜው የሚወጣ የሕትመት ሥራን የሚሰራ ኩባንያ በተመሳሳይ ዘርፍ ካለ ሌላ ኩባንያ ውጤታማ ቁጥጥር ሊኖረው እንደማይገባ የሚደነግገውን) በማጣቀስ አመልካቹ ድርጅት መስራት ያለበት በመጽሔት ወይም በጋዜጣ ላይ ብቻ መሆኑን በመግለጽ ቀደም ሲል የነበረውን በአንድ ስያሜ መጽሔትና ጋዜጣ የማሳተም መብት ይቀለብሰዋል::

ከሌሎቹ ወቅቶች በተለየ መልኩ እያጠናቀቅነው ያለው አመት ለምን የፕሬስ ጫናዎች አጋጠሙት? ቢባል ምላሹ በአገር አቀፍ ደረጃ ከተካሄደው አጠቃላይ ምርጫ ተያያዥ ጉዳዮች የራቀ ሆኖ አናገኘውም:: «ያለማንም ጣልቃ ገብነት ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሃሳብ መሰብሰብ፣ መቀበልና ማሰራጨት» ፈተና ተጋርጦባቸው እንደነበር አብዛኞቹ የነፃው ፕሬስ ቤተሰቦች የሚስማሙበትን እውነታ ነው:: (በአንጻሩ ሳላነሳው ማለፍ የማልፈልገው ይህን ችግር ለመቅረፍ በሚል በግል ጋዜጦች ላይ የነበሩ አንዳንድ ክሶችን እስከማንሳት የደረሰ ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ ከፍተኛ ባለስልጣን አጋጥመውኝ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩ በአንድ እጅ ማጨብጨብ እንደነበር የሚያሳዩ ተግባራት በአውራምባ ታይምስና በሌሎቹ ላይ ይፈፀሙ ጀመር):: ዋና አጋጆች በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ማለትም በስልክ በደብዳቤና በመሰል መንገዶች ለማስፈራራት በመሞከር እንቅፋት ከመሆን አልፎ በመንግስት ጋዜጣ ላይ «የጥፋት ኃይሎች» እስከማለት የተደረሰበትን ተሞክሮ አንባብያን ይረሷቸዋል ማለት አይቻልም::

የመገናኛ ብዙኃንና የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ የሥነ ምግባር ደንብ ሲወጣ ግን በአንፃራዊ ሁኔታም እንኳ የተሻሉ ሊባሉ ከሚችሉት የባሰና ጉዞው የኋልዮሽ እንደሆነ ያመለከተ ሆነ:: የ«እንዳያማህ ጥራው...» ፖሊሲ በድጋሚ ተንጸባረቀ:: ይህም ከፍተኛ ክርክር አስነስቶ የነበረ በመሆኑ የተወሰኑ ነጥቦችን ብቻ በአጭሩ እንቃኝ::

## አንቀጽ 7 ቁጥር 2

«የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን በርዕሰ አንቀጾቻቸው ላይ ማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ የሚደግፍ ወይም የሚቃወም ሃሳብ ወይም አስተያየት ማቅረብ የለባቸውም::» ይላል:: እዚህ ላይ የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 29 ቁጥር 4 ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት አስፈላጊ የሆኑ ሃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ እንዲንሸራሸሩ የሚደነግግ ሲሆን ፕሬስ በተቋምነቱ የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናግድ ችሎታ እንዲኖረው ስለሚደረግለት የሕግ ጥበቃ ይገልፃል:: ይህን ሃሳብ በቀላል ምሳሌ እንመልከተው::

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ፍትሐዊ የኃብት ክፍፍል እንዲፈጠር የሚያስችል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይቀርጻል:: የመገናኛ ብዙሃኑም ይህ ፖሊሲ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓቱና ለአገር ይጠቅማል ብሎ በማመን በርዕሰ አንቀጹ «ይህ የፖሊሲ ሃሳብ ሊዳብር ይገባል፣ ለአገር ይጠቅማል» የሚል አስተየየት ሊሰነዝር ይችላል:: በሌላ በኩል አንዱ ፓርቲ በአንድ ጉዳይ ላይ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትል የሚችል አስተሳሰብ ሲያራምድ መገናኛ ብዙሃኑ «ይህ የፖለቲካ አካሄድ አገር ስለሚጎዳ ሊታረም ይገባዋል::» ሊሉ ይችላሉ:: ሜዲያ መረጃ መስጠት፣ ማስተማርና ማዝናናት የሚሉ ተልዕኮዎች ያሉት ሲሆን የፕሬስ ሕጉ መግቢያ ደግሞ አጋላጭ መረጃዎችን ሳይቀር እንዲያሰራጩ ያበረታታቸዋል:: አንቀጽ 4 -ንዑስ ንቀጽ 3/ሐ «ማንኛቸውም የመንግስት አካላት መገናኛ ብዙሃኑ የሕዝብን አስተያየት በመቅረፅ ሂደት የመሳተፍ መብታቸውን ሊያከብሩላቸው ይገባል» ይላል:: ሌላ አስገራሚ ነጥብም አለ::

የስነ ምግባር ደንቡ በአንቀጽ 9 ቁጥር 1 የምርጫ አስፈፃሚ አካላት የኤዲቶሪያል ነፃነትን ጨምሮ የሜዲያ ተቋማትን ነፃነትና <u>የፖለቲካዊ ወገንተኛነትን የመግለጽ መብት</u> ማክበር ይኖርባቸዋል» /ሰረዝ የተጨመረ/ ይላል:: በአንድ በኩል የፖለቲካ ወገንተኝነት እንኳ መከበር አለበት ሲል ይሞግታል በሌላ በኩል የፖለቲካ ፓርቲን የሚደግፍ ወይም የሚቃወም ሃሳብ ወይም አስተያየት በርዕሰ አንቀጽ መቅረብ የለበትም ይላል:: «እንዳያማህ ጥራው...» እንዲሉ::

## አንቀጽ 7 ቁጥር 4

የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት የፖለቲካ ማስታወቂያዎችን ለሁሉም እኩል በሆነ ክፍያ ያስተናግዱ በማለት ፋይናንሻል በሆኑ ድርጅታዊ አሰራሮች ጣልቃ ይገባል:: በአንድ የመገናኛ ብዙሃን ውስጥ ራሱን የቻለ የማስታወቂያና ፕሮሞሽን ክፍል ያለ ሲሆን የዋጋ ተመኖችን የሚያወጣበት መስፈርትም አለው:: ከዚህ አንፃር ለአገር አቀፍ ፓርቲዎች፣ ለክልላዊ ወይም ለግል ተወዳዳሪዎች የሚሉ አይነት መስፈርቶች ሊኖረው ይችላሉ::

## አንቀጽ 7 ቁጥር 6

የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎችና መድረኮቻቸው ፍትሐዊና ቋሚ የዘገባ ሽፋን መስጠት እንዳለባቸው ይደነግጋል:: አውራምባ ታይምስ ከብሮድካስት ባለስልጣን ኃላፊዎች ገጥሟት ከነበረው ውዝግብ አንዱ ለተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰፊ ሽፋን ትሰጣላችሁ (በተለይ የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ ለነበረው ፣መድረክ፣) የሚል እንደነበር ይታወሳል:: የጋዜጣዋ ዝግጅት ክፍል በወቅቱ ይዛው የነበረው በስነ አመክንዮ ላይ የተመሰረተ አሰራር «በእርግጥ ፍትሐዊ ሽፍን መሰጠት አለበት፤ ፍትሐዊ ማለት ግን «ለሚገባው የሚገባውን ያህል መስጠት» ማለት እንጂ የፖለቲካ ፓርቲነት ሰርተፍኬት ስለያዘ ብቻ አንድና እኩል ሽፋን መስጠት የ«ፍትሕ»ን መርሕ ማፋለስ ነው ስንል ተከራክረናል:: እንደእውነቱ ከሆነ በዚህ ዙሪያ ብዙ ማለት ይቻል ነበር:: - ጊዜም፣ ቦታም፣ ሌሎች ነገሮችም ይገድቡናል እንጂ::

# የኢህአዴግ፦ 100%

በሱራፍኤል ግርማ

ከአምስት ዓመታት በፊት እንደተከናወነው ምርጫ 97 ሕዝብ ለሂደቱ ብዙም ትኩረት ሰጥቶት ያልተስተዋለው የዘንድሮው ምርጫ ቀልብ መሳብ የጀመረው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫውን ጊዜያዊ ውጤት ይፋ ሲያደርግ ነበር:: በምርጫ ቦርዱ የተገለፀው የኢህአዴግ 99.6ን ማሸነፍ በአገሪቱ ብቻ ሳይሆን በዘመናዊው ዓለም የምርጫ ታሪክ ውስጥ ከተከተቡት ግራ አጋቢ ውጤቶች ውስጥ አንዱ ለመሆን በቃ::

ገዥው ግንባር ብቻውን የተወዳደረ እስኪመስል ድረስ ያገኘው ለመቶ በመቶ የቀረበ ውጤት (ኘ 100ን) በምርጫው የተካፈሉ ተቀናቃኞቹን ከማስደንገጡ በላይ ግንባሩ ራሱ ያልጠበቀው መሆኑን ሊቀመንበሩ አቶ መለስ ዜናዊ ከምርጫው በኋላ ተናግረዋል:: በዚያን ሰሞን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ «ሕዝቡ ከ50 እስከ 75 በመቶ ድምጽ ይሰጠናል ብለን የጠበቅን ቢሆንም በውጤቱ ግን ከ99 በመቶ በላይ ድምጽ አግኝተናል» ሲሉ አረጋግጠዋል:: ነገር ግን አቶ መለስም ሆነ ሌሎች በእሳቸው ሊቀመንበርነት በሚዘወረው ኢህአዴግ ውስጥ ከአመራርነት እስከ ተራ አባልነት ያሉ «ያልተጠበቀውን ውጤት» ያስገኘ ላቸውን ሕዝብ ሲያመሰግኑ ቢሰነብቱም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውጤቱን ወዲያውኑ ነበር እንደማይቀበሉ ያስታወቁት::

በተለይም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) አመራር የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲና ውጤቱን የገለፁበት አባባል የ99.6 በመቶው «ድል» በተቃዋሚው ጐራ የቱን ያህል ተቀባይነት እንደሌለው የሚያሳይ ነው:: ግንቦት 18 ቀን 2002 ዓ.ም በጥምረቱ ጽ/ቤት በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት ዶ/ሩ እንዲህ ነበር ያሉት፣ «ምርጫው ከቅርጫም ያነሰ ነው፤ ቅርጫ እንኳን ሥነ-ሥርዓት አለው:: ኢህአዴግ ይህንን ምርጫ በዓለም ላይ ያሉትን መሸወጃዎች ሁሉ ተጠቅሞ ለማሸነፍ ሞክሯል::»

ዶ/ር መረራ ውጤቱን «ኢህአዴግ ነውረኛ የፖለቲካ ድራማ ነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተጫወተው» በማለትም ጭምር ገልፀውት የነበረ ሲሆን ምርጫው ተካሂዶ በነበረበት ወቅት የመድረኩ ወቅታዊ ሊቀመንበር የነበሩት ፕ/ር በየነ ጴጥሮስም በዚያው መግለጫ ላይ የማጭበርበር ደረጃ እንዳለውና የዘንድሮውን ለመገመት ጨርሶ እንደሚያዳግት መናገራቸው ተፎካካሪዎች በነበሩበት ሒደት ኘ 100ን የሆነ ውጤት ማስመዝገብ በራሱ የተለመደውን የምርጫ ተጭበርብሯል እሰጥ አገባ እንደሚያካርረውና «ለመጭበርበሩ» እንደ አንድ ምሳሌነት ሊውል እንደሚችል ጠቁመዋል::

## ተስፈኞቹስ?

የምርጫ 2002 ነጋሪት መጐሰም ከጀመረበት የዚህ ዓመት መባቻ ወዲህ የግንቦቱ ምርጫ ውጤት ምን ሊመስል እንደሚችል አንዳንድ ክስተቶችን መሠረት ያደረጉ የማለዳ ትንበያዎች እንደነበሩ የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቅርበት የሚከታተሉ ያስታውሱታል:: በተለይም በተወሰኑ ፓርቲዎች ተፈርሞ ኋላም በፓርላማ ፀድቆ ላልፈረሙትም ፓርቲዎች ጭምር ገዥ ሕግ ሆኖ የወጣው የፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ ኢህአዴግ ደንቡን ለፈረሙት ፓርቲዎች የተወሰኑ የም/ቤት ወንበር ሊያጋራቸው፣ አለፍ ሲልም የፓርቲዎቹ መሪዎች አንዳንድ የመንግስት ሹመቶች ሊሰጧቸው እንደሚችሉ ሲተነብዩ ለቆዩት መላምቶች መሠረት እንደነበር አይዘነጋም:: በተለይ መኢአድ እና ኢዴፓ የተጠቀሰውን ሰነድ በማፅደቃቸው ከኢህአዴግ ቀጥሎ በርካታ የም/ቤት መቀመጫ ሊያገኙ አንደሚችሉ ተስፋ እንደነበራቸው ብዙዎች አስተያየታቸውን ሲሰጡ የሰነበቱ ቢሆንም ተስፋው ከቀቢፀ ተስፋነት ሳይዘል ቀርቷል::

የኢህአዴግ አሸናፊነት መታወጅን ተከትሎ ባሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጠው መኢአድ፣ ኢህአዴግ የሥነ-ምግባር ደንቡን በመጣስ ምርጫው ተዓማኒነት እንዳይኖረው ማድረጉን በማስታወቅና ለተገኘው የኢህአዴግ የ99.6ን «ድል» የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን በድምጽ መስጫ ዕለት ፍፁም ወገንተኝነት መሆንን በምክንያትነት በማስቀመጥ ሰነዱ ውጤት አልባ እንደሆነ ገልፅዋል::

ከሁሉም ከሁሉም የኢዴፓው አቶ ልደቱ አያሌው የፓርላማ ወንበር ሊያገኙ አለመቻላቸው ብዙዎችን ያስደመመ ነበር፤ በተለይ ከቀድሞ ቅንጅት በኋላ እርሳቸውን ከኢህአዴግ ጎን በቀጥታ ያሰለፏቸው ወገኖች ኢህአዴግ «ይህን ያህል አምርሯል» እስከማለት መድረሳቸው ይታወቃል::

## ሁለቱ የኢህአዴግ አጃቢዎች

ከ547 የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መቀመጫዎች ውስጥ 545ቱን በመውሰድ በአገር ውስጥም በውጪም የተደበላለቀ ስሜት እንዲፈጠር ያደረገው ኢህአዴግ በሚቀጥለው ዓመት ወደ 4ኛው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ብቻውን ከመግባት የተረፈው ለቅንጣት ነው፤ ተርፏል ከተባለ:: ከኢህአዴግ የተረፉትን ሁለት ወንበሮች የወሰዱት አንድነት/መድረክን ወክለው በአዲስ አበባ ወረዳ 6 የተወዳደሩት አቶ ግርማ ሰይፉ አና በከፋ ዞን ጊምቦ የምርጫ ጣቢያ በግል የተወዳደሩት ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ ናቸው::

ምንም እንኳን የተፎካከሯቸውን የኢህአዴግ እጩዎች በማሸነፍ ወደ ፓርላማ የመግባት ዕድል የገጠማቸው ሁለቱ ግለሰቦች ቢሆኑም ዶ/ር አሸብር በምረጡኝ ቅስቀሳቸው ወቅት በይፋ እንደተናገሩት የኢህአዴግን ፖሊሲዎች በፅኑ የሚደግፉ ከሆነና በምክር ቤቱ በሚኖራቸው ቆይታም ከኢህአዴግ አባላት የተለየ ሀሳብ የማያመነጩ ከሆነ ሁኔታው የተቃዋሚዎችን ቁጥር ወደ አንድ የሚያወርደው ይሆናል:: እንዲያው ነገሩን ገነን እናድርገው ከተባለ ደግሞ፣ አቶ ግርማ ሰይፉ መቀመጫ ያሸነፉ ብቸኛው የመድረክ ተወዳዳሪ መሆናቸውን በሰሙ ሰሞን ለአውራምባ ታይምስ በሰጡት ቃለ-ምልልስ «እኛን ካልመረጣችሁ ኢህአዴግን ምረጡ እያልን እንቀሰቅስ ነበር» ማለታቸውን እናስታውሳለን::

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በአገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ ከተፈጠሩ መልካም ጅምሮች መካከል አንዱ የነበረውን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት አደጋ ላይ እንደጣለ የተነገረለት የዘንድሮው ምርጫ ውጤት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ 20 ዓመታትን ወደ ኋላ እንዲመለስ ማድረጉን በተቃዋሚው ወገን ያሉ ፖለቲከኞች ያስገነዝባሉ:: ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም የአውራምባ ታይምስ እንግዳ የነበሩት አቶ ተመስገን ዘውዴ ስለቀጣዩ ም/ቤት «...ፓርላማው የአንድ ፓርቲ አመለካከት ብቻ የሚንፀባረቅበትና ምንም ዓይነት የተለያዩ ሀሳቦች የማይነሱበት ነው የሚሆነው» ይላሉ:: «ይሄ ደግሞ ለዴሞክራሲ፣ ለሰላምና ለልማት የሚጠቅም አይደለም::... አሁን ግን ኢህአዴግ የተለየ ሐሳብ ያላቸውን በሙሉ ገፍትሮ አስወጥቷል::»

በሌላ በኩል ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ተቃዋሚዎች የፓርላማ መቀመጫ ባይኖራቸውም አብረው ለመስራት ፍቃደኛ መሆናቸውን ለገለፁበት ንግግር የአረና/መድረክ ተወዳዳሪ የነበሩት አቶ ገብሩ አስራት ከምርጫው በኋላ በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ «እንኳን የፓርላማ መቀመጫ ሳይኖረን ፓርላማ የነበሩት ተቃዋሚዎች ሀሳባቸው መቼ ተቀባይነት አግኝቶ ያውቃል?» በማለት መጠየቃቸው ይታወሳል::

## እንዴት ሊሆን ቻለ?

ለኢህአዴግ «ያልተጠበቀ» ውጤት መመዝገብ የየራሳቸው አስተዋጽኦ የነበራቸው ክስተቶች የተስተዋሉ ሲሆን የአብዛኞቹም መነሾ ምርጫ 97 ነው:: ማንኛውም በምርጫ ተሳታፊ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ወደ ወድድሩ ሲገባ ቀድሞ የነበሩበትን ድክመቶች ወደ ኋላ መለስ በማለት ፈትሾና አስተካክሎ እንደመሆኑ በምርጫ 97 በአዲስ አበባ ሙሉ ለሙሉ እንዲሁም በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች ያላሰበው ሽንፈት የደረሰበት ኢህአዴግ ለዘንድሮው ምርጫ የቤት ስራውን በሚገባ ማከናወኑን በተደጋጋሚ ጊዜያት ሲገልፅ ቆይቷል::


ኢህአዴግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከሰራቸው ተግባራት ውስጥ አባላቱን በከፍተኛ ቁጥር መጨመር አንዱ ሲሆን በዚህም ረገድ የአባላቶቹን ቁጥር ወደ አራት ሚሊዮን ገደማ አድርሻለሁ ብሏል::

በጥቅምት ወር 2002 ዓ.ም ለንባብ የበቃው የኢህአዴግ የንድፈ-ሀሳብ መጽሔት አዲስ ራዕይ ባስቀመጠው የምርጫ የሂሳብ ስሌት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ከ18 ዓመት በታች በመሆኑ የመራጩ ቁጥር ከ30 ሚሊዮን በላይ ሊሆን እንደማይችል በመገመት ግንባሩ ካሉት 4 ሚሊዮን አባላት ውስጥ እያንዳንዱ ከራሱ ውጪ ኢህአዴግን የሚመርጡ አራት ሰዎችን ቢያዘጋጅ በያንስ ሁለት ሶስተኛውን ድምፅ ሊያገኝ እንደሚችል በግልጽ ተንትኖ ነበር:: (ምንም እንኳን ውጤቱ ከግምት በላይ ቢሆንም::) ነገር ግን ይህ ሂደት ጠባቡን የፖለቲካ ሥነ-ምህዳር ይበልጥ እንዳዳፈነው በመግለጽ «የጠርናፊ እና ተጠርናፊ ሥርዓት» የሚል ትችት በበርካቶች ተሰንዝሮበታል፤ ለዚህ ኘ100ን «ድልም» በዋና ምክንያትነት ተጠቅሷል::

ከዚህ በተጨማሪ በአጠቃላይ ከተሰጠው ድምጽ ውስጥ ኢህአዴግ በጊዜያዊ ውጤቱ ምርጫውን ማሸነፉ እንደተገለፀ፣ ሂውማን ራይትስ ዎች የተባለው ዓለማቀፍ ተቋም ያወጣውን የተቃውሞ ሪፖርት ተከትሎ ማክሰኞ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ግንባሩ የጠራው ሰላማዊ ሰልፍ «በአንድ ሌሊት ይሄ ሁሉ ዝግጅት፣ «የሕዝቡ ድምፅ ይከበር» እና መሰል የውጭ ኃይል ወቃሽ መፈክሮች እንዴት ሊዘጋጁ ቻሉ?» የሚል ጥያቄ አጭሮ ነበር:: እንዲሁም ክስተቱ ቀደም ሲል ውስጥ ውስጡን ሲወራ የነበረውን የምርጫውን «የተበላ ዕቁብነት» አረጋግጧል በማለት የተቹት ወገኖችም ነበሩ::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com




# የቴአትር እና የፊልም ሰፈር ምርጦች

**እንደተለመደው የዓመቱን ምርጥ የቴአትር እና የፊልም ውጤቶችና ባለሞያዎች ይዘን መጥተናል:: በቴአትር እና በፊልም ሞያ የተሰማሩ በርካታ ግለሰቦች በአገሪቱ ውስጥ አሉ:: በዓመት ውስጥ ከ20 በላይ ቴአትሮች ለተመልካች እየቀረቡ ሲሆን ከ40 በላይ ፊልሞችም ተዘጋጅተው ለተመልካች ቀርበዋል:: ጥቂት የቴአትር ቤቶች እና በየጊዜው ቁጥራቸው እያደገ የሚሄድ ሲኒማ ቤቶች እየተመለከትን ነው:: መንግስት በዚህ የሞያ ዘርፍ ከፍተኛ ተጠቃሚ ሲሆን፣ በመቀጠል የሲኒማ ቤት ባለቤቶች እና ቴአትር ቤቶቹ ገቢያቸው ቀላል አይደለም:: እንደ ከዚህ ቀደም ዓመታት ሁሉ አሁንም ባለሞያው ግን ካሉበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሊወጣ አልቻለም::**

በወንድማገኝ ኃይሌ

## ሲ ኒ ማ

በበርካታ ሲኒማ ቤቶች ፊልሞቻችን እየታዩ ናቸው:: አዲስ ፕሮግራም ከጀመሩት ሲኒማ ኢትዮጵያ እና በራስ ቴአትር ስር ከተቋቋመው እስቴሪዮ ጀምሮ በኢምፔሪያል ሆቴል፣ ካዛንቺስ አካባቢ የተከፈተው ዮፍታሔ ሲኒማ፣ አሰራሩን በአዲስ መልክ ያዋቀረው የጐተራ አካባቢው አጐና ሲኒማ፣ ኤግዚቢሽን ማዕከል ውስጥ ያለው ሴባስተፖል ሲኒማ፣ አለም ሲኒማ፣ ኤድናሞል ውስጥ የሚገኘው ማቲ ሲኒማ፣ ለበርካታ ጊዜያት ሲኒማ በማቅረብ ቀዳሚ የሆኑት አምባሳደር ሲኒማ፣ እና ሲኒማ አምፒር፣ በአዲስ አበባ ቴአትር እና ባህል አዳራሽ፣ በብሔራዊ ቴአትር በነዚህ ሁሉ አዳራሾች ፊልሞቻችን እየታዩ ነው:: ይህም ይበል ያሰኛል::

ፊልምን በሚመለከትም ጥቂት የውድድር ድርጅቶች መግለጫዎች እያወጡ በዚያው መቅረታቸው የሚታወስ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ ኢንተርናሽናል ፊልም ፌስቲቫል ግን እስካሁን ሥራውን ለመስራት እየጣረ ነው:: በአቶ ዘላለም ወ/ማሪያም እና በወ/ሮ ማጅዳ አብዱ አማካኝነትም ዘንድሮ የአጫጭር ፊልም ፌስቲቫል ሣምንት በብሔራዊ ቴአትር በደማቅ ሁኔታ ተካሂዷል:: በየጊዜው እየደከመ የመጣው የአውሮፓውያኑ ፊልም ፌስቲቫል ከወትሮው እጅግ ደብዝዞ ተካሂዳል የኪውባ፣ የኢራን፣ የእስፓኒሽ ተናጋሪ አገሮች ፊልም ፌስቲቫሎችም እንደተለመደው ብዙ ሕዝብ ሳያያቸው ለሕዝብ ተከፍተው አልፈዋል::

የፕሮዲውሰሮች ማህበር በዚህ ዓመት በትንሹ የተንቀሳቀሰ ሲሆን የፊልም ሰሪዎች ማህበር አሁንም ድምፁን አጥፍቶ አለም የለምም ሳይባል ለዓይን እንደናፈቀን ዓመቱ ሊገባደድ ጫፍ ደርሷል::

በተሻለ ሁኔታ ከነብዙ ውጣ ውረዶች እየተንቀሳቀሰ ያለው አላኖስ የፊልም ሰሪዎች ማህበር ነው:: ይህ ማህበር በፊት ይሰበሰብበት ከነበረው ቦታ የአዳራሽ ለውጥ አድርጐ ፒያሣ በሚገኘው የሩሲያ ባህል ማዕከል ፑሽኪን አዳራሽ ውስጥ ገብቷል:: አላቲኖስ ዛሬ ከችግኝነት አድጐ ዛፍ ሆኗል:: ቅርንጫፎቹም መታየት ጀምረዋል፤ የትወና ቅርንጫፍ፣ የአዘጋጆች ቅርንጫፍ፣ አጠራጣሪው የድርሰት አፃፃፍ ቅርንጫፍ በቃቀል እንዳንዳቸው ቅርንጫፎች የራሳቸውን ፕሮግራም በየሣምንቱ ያደርጋሉ:: የዓመቱ ምርጥ ማህበር እንዳንለው ሌላ አብሮት የሚወዳደር የለምና ለዘንድሮው ይሁን ብለን በደፈናው ክብር እና ምስጋናችንን እንገልፃለን::

ባለቀለም ህልሞች፣ ላገባ ነው፣ ይሉኝታ፣ ሚስጥሩ፣ በራሪ ልቦች፣ ማክቤል፣ ሮዳስ፣ መላክ፣ ቫኬሽን ፍሮም አሜሪካ፣ ከልብ፣ አዲስ ሙሽራ፣ ከፍቅር በታች፣ ውበት ለፈተና፣ ከባቢሎን ማዶ፣ እውነት፣ የምረቃው ምሽት፣ ግማሽ ሰው፣ ትስስር፣ አስከሬኑ፣ ቤርሙዳ፣ የታፈነ ፍቅር፣ የእግር ዕጣ፣ ታስራለች፣ የሮቢካ፣ ነገ፣ አራቱ ሻማዎች፣ ትግስት፣ ምክንያት፣ ይቅርታ፣ አማን፣ ዳፋ፣ ጣምራ፣ ስስት፣ ማንነት፣ ኸስሃ፣ አፍሮኒዝም፣ የመሳሰሉ ፊልሞች በ2002 ዓ.ም ለሕዝብ ታይተዋል::

ሸዋፈራሁ ደሣለኝ፣ ሰለሞን ቦጋለ፣ ሽመልስ በቀለ፣ ሣምሶም ታደሰ /ቤቢ/፣ ይገረም ደጀኔ፣ ግሩም ኤርሚያስ፣ በርካታ ፊልሞች ላይ በመሳተፍ በቁጥር ቀዳሚ ሲሆኑ ዮናስ ብርሃነ መዋ እና ቢኒያም ወርቁ ደግሞ ከ4 በላይ ፊልሞችን ለተመልካች በአዘጋጅነት አቅርበዋል:: ይሉኝታ፣ በራሪ ልቦች እና አዲስ ሙሽራ የተሰኙ ፊልሞችን በደራሲነት ቢኒያም ወርቁ በማቅረብ ቀዳሚ መሆኑ ይሰማናል::

ዘንድሮ የተለያየ ትጋት ለፈጠሩ ሰዎች ክብር መስጠት ብንጀምር መልካም ነው፤ እና...

### የዓመቱ ምርጥ የፊልም ሰው

በተከታታይ ለበርካታ ዓመታት በፊልም ሥራ ላይ የራሱን አስተዋፅኦ ሲያደርግ ቆይቷል:: ግማሽ ሰው፣ ሚስጥሩ፣ ማክቤል፣ ትስስር፣ የታፈነ ፍቅር የተባሉ ፊልሞችን በዚህ ዓመት ለተመልካች አቅርቧል:: የሚያስመሰግን ትጋት ነውና **ዮናስ ብርሃነ መዋ** የዓመቱ ምርጥ የፊልም ሰው ልለው ወደድኩ::

### የዓመቱ ምርጥ ኤዲቲንግ

የተሻለ ነገር ለመስራት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ተደርጎበታል:: ኤዲተሩም ሊበረታታ ይገባል:: ወደፊትም የተሻለ ነገር እንጠብቃለን:: በኛ እይታ የዓመቱ ምርጥ ቅንብር **ዳፋ** ፊልም ነው::

### የዓመቱ ምርጥ የካሜራ ሥራ

በዚሁ ዓመት በርካታ ባለሞያዎች እንዳሉ ብዙዎች ፊልሞች አመልክተዋል፤ የሚያስመሰግንም ነው:: የኔ ምርጫ ግን የዓመቱ ምርጥ ካሜራ ሥራ **መላክ** ፊልም ነው::

### የዓመቱ ምርጥ የፊልም ፕሮዲውሰር

የበርካታ ፊልም ፕሮዲውሰሮች ፊልም መስራትን ብቻ የፊልም ፕሮዲውሰሩ ተግባር አድርገው ይቆጥሩታል:: ፊልም መስራት ብቻ ሣይሆን ፊልሙን በተገቢው መንገድ ማስተዋወቅም ቀዳሚ እና ትልቅ ነገር ነው:: ዘንድሮ በጥሩ ሁኔታ ፊልሞቻቸውን ለማስተዋወቅ ጥረት ካደረጉት መካከል «ማክቤል»፣ «ትስስር»፣ «ባለቀለም ህልሞች»፣




«አዲስ ሙሽራ»፣ «አስክሬኑ» እና «በራሪ ልቦች» ቀደምቶቹ ናቸው:: ከሁሉም በላይ ግን የ«**አስከሬኑ**» ፊልም ማስታወቂያ አስገራሚ እና የብዙዎችን ትኩረት የሳበ ነበር ስለሆነም የዓመቱ ምርጥ ፕሮዲውሰር ልንለው ይገባል::

የዓመቱ ምርጥ ረዳት ሴት ተዋናይት

በርካታ ሴት ተዋንያን በዓመቱ ውስጥ አይተናል:: በረዳት ተዋናይነት ግን የዓመቱ ምርጥ ሆና የተገኘችው የበራሪ ልቦች **ቅድስት ገብረ ሥላሴ** ናት:: ፊልሙ ውስጥ ብቅ ብላ በምትጠፋበት በዛች ቅፅበት ከአይምሮ የማይጠፋ አጨዋወት ታሳየናለች፤ እና የዓመቱ ምርጥ ረዳት ሴት ተዋናይት ብንላት ቢያንሳት እንጂ አይበዛባትም::

### የዓመቱ ምርጥ ረዳት ወንድ ተዋናይ

በርካታ ረዳት ተዋንያን በዚህ ዓመት አይተናል:: በግማሽ ሰው ፊልም ላይ፣ ቫኬሽን ፍሮም አሜሪካ፣ በአራቱ ሻማዎች፣ በቤርሙዳ ፊልም፣ በአስከሬኑ ፊልም ላይ በርከት ያሉ ተዋንያን በረዳትነት ችሎታቸውን አሳይተዋል:: በእኔ እይታ የዓመቱ ምርጥ ረዳት ተዋናይ ግን የእግር ዕጣ ፊልም **ፈለቀ አበበ** ነው::

### የዓመቱ ምርጥ ሴት ተዋናይት

ይሉኝታ፣ ማክቤል፣ አራቱ ሻማዎች፣ ታስራለች ፊልሞች ላይ ዋና ገፀ-ባህሪያትን ወክለው የተጫወቱ ተዋንያን የሚያስደስት ትወና አሳይተውናል:: በእኔ እይታ የዓመቱ ሴት ተዋናይት ግን ከየታፈነ ፍቅር **ዮዲት መንግስቱ** ናት::

### የዓመቱ ምርጥ ወንድ ተዋናይ

በርካታ መሪ ተዋናዮች በዚህ ዓመት ውስጥ ብናይም **ሠለሞን ቦጋለ** በራሪ ልቦች ላይ ያሳየው አጨዋወት ግን ወደር የለውም:: በ30 ዓመት ውስጥ የሚገኝ ገፀ-ባህሪይ እና 50ዎቹ ላይ ያለ ሁለት የተለያዩ ስብዕናዎች ለማለት ይቻላል በሚገባ ተጫውቶ አሳይቶናል:: እናም የዓመቱ ምርጥ ተዋናይ ልንለው ይገባል::

### የዓመቱ ምርጥ ድርሰት

ብዙ ድርሰቶች ከተለያዩ ቦታዎች ቀርበዋል፤ አንዳንዶች ተገልብጠው፣ አንዳንዶቹ ግን በትክክል ንፁህ ፈጠራ ታይቶባቸዋል:: ብዙ ጥሩ ድርሰቶች በዚህ ዓመት ታይተዋል:: እኔ የዓመቱ ምርጥ ደራሲ ብዬ የምመርጠው የሮዳስ ፊልም ደራሲ **ኤልያስ ሽፋ** ነው::

### የዓመቱ ምርጥ ዝግጅት

አበረታች የሆኑ ብዙ ዝግጅቶች አይተናል:: የዓመቱ ምርጥ ዝግጅት ግን በእኔ እይታ **መላክ** ፊልም ሲሆን አዘጋጁ **እስክንድር አሊ** ነው::

### የዓመቱ ምርጥ ሲኒማ ቤት

ከላይ እንደገለፅኩት በርካታ ሲኒማ ቤቶች መኖራቸው የሚያስመሰግን ነው:: ከመካከላቸው አብዛኞቹ ቀጥታ ለትርፍ ብቻ ስለሆነ የሚሰሩት የፊልሙን ሥራ አካሄድ ይጐዱታል ብዬ አስባለሁ:: እንደ ኤድናሞል ፊልም ለመምረጥ ጥረት ቢደረግ፣ እንደ ሴፓስቶፖል ሲኒማ አድሎ ባለማድረግ ሁሉም ተጠቃሚ እንዲሆን ጥረት ቢደረግ መልካም ነው:: ሌላው ከሚያስከፍሉት ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት ማቅረብ ከትልልቆቹ ሲኒማ ቤቶች ይጠበቃል:: 25 ብር እና 30 ብር እያስከፈሉ የተበላሸ ሽንት ቤት ማቅረብ ምን እንደሆነ አልገባኝም:: ውሃና ሣሙና ለማግኘት የማይቻልበት መፀዳጃ ምንድነው? ሲሆን ሲሆን ዘመናዊ አድርጐ እጅ ማድረቂያ ጭምር ሲጠበቅ እጅግ አሣፋሪ በሆነ ሁኔታ የሽንት ቤት ወረቀት እንኳን የሌላቸው ሲኒማ ቤቶች ለሰው ባይጨነቁ የሲኒማ ሥራውንም ክብር አብረው ይዘው ነውና የሚታዩት ሊያስቡበት ይገባል:: አንድ ተመልካች ገንዘቡን የሚከፍለው ለሚያየው ፊልም ነው እንጂ ለሶፋው አይደለም ግን የአንዳንድ ሲኒማ ቤቶች አስተሳሰብ ለሶፋው ይመስላል እና ይህም ሊታሰብበት ይገባል ሲኒማ ብሎ የመጣ ሰው በከፈለው ገንዘብ መጠን ተመጣጣኝ አገልግሎት ሊሰጠው የግድ ይገባልና ቢታሰብበት መልካም ነው::

እያደጉ ያሉት ሲኒማ ቤቶቻችን በአብዛኛው የአገር ውስጥ ፊልሞችን እያሳዩ በመሆናቸው ደስታችን ወደር የለውም:: ዛሬ ዛሬ ፊልሞች ከጠዋቱ 5:30 ጀምሮ እስከ ምሽቱ 4:00 ሰዓት ድረስ በሲኒማ ቤቶቻችን መታየታቸው ትልቅ ኩራት ነው:: ስለሆነም የዓመቱ ምርጥ ሲኒማ ቤታችን ቅዳሜ እና እሁድ ከ5:30 የሚጀምር የፊልም ፕሮግራም ያለው፣ ከሰኞ እስከ እሁድ ደግሞ በመደበኛነት በ8፣ በ10፣ በ12 እና ምሽት 2:00 ሰዓት ላይ በቀን ውስጥ 4 እና 5 ፕሮግራሞችን ለሕዝብ የሚያቀርበው **አለም ሲኒማ** ነው:: አለም ሲኒማ የአገር ውስጥ ሲኒማዎችን ብቻ ለሕዝብ በማቅረብ ላይ ሲሆን አንዳንድ የአሰራር እና የእንግዳ አቀባበል ጉድለቶችን ቢያሻሽል ለወደፊቱ በዚሁ ክብሩ ይቀጥል ይሆናል የሚል እምነት አለ::

የዓመቱ ምርጥ እና ታታሪ ባለሙያዎች መጪው ዓመት መልካም የሥራ ዘመን እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ::

## ቴ አ ት ር

በዚህ ዓመት ጥቂት አዳዲስ ቴአትሮች ብቻ ለተመልካች መቅረብ መጀመራቸው፣ እንዲሁም ከግማሽ በላይ ቴአትሮች ዘመን ተሻግረው አሁንም ዘመን ለመሻገር እየተንደረደሩ ስለሆነ በተናጥል የቴአትሮች ውድድር ማድረግ አዳጋች ነው:: ግና በአጠቃላይ ዓመት ውስጥ ኮከብ የሆኑ ጥቂት ባለሞያዎችን ልጥቀስ::

### የዓመቱ ምርጥ የቴአትር ፕሮዲውሰር

**ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ**:- አዲስ የሆኑ ሀሳቦችን በድፍረት በመጀመሩ እጅግ ባልተለመደ መንገድ ቴአትር ቅዳሜ ማታ እና እሁድ ማታ ለማሳየት በመድፈሩ፣ ይህም የተሳካ በመሆኑ ከፕሮዲውሰርነቱ ባሻገር ሁለት ድርሰት ለሕዝብ አቅርቦ አንድ ቴአትር በማዘጋጀቱ የዓመቱ የቴአትር ባለሞያ ነው::

### የዓመቱ ምርጥ የቴአትር አዘጋጅ

**ተሻለ ወርቁ**:- ሁለት የመድረክ ቴአትሮችን አዘጋጅቶ ለሕዝብ እያቀረበ ሲሆን አንድ ቴአትር ላይ ደግሞ ድርሰት በማቅረብም ተሳትፏል:: ይህ ወጣት ባለሞያ ትጋቱ ከእሱ አልፎ ለሌሎችም መነቃቂያ ሲሆን የሚታይ ነው:: ከዚህ ሁሉ በመቀጠል በቴአትሩ ላይም በተዋናይነት በመሳተፍ አገልግሎቱን ለሕዝብ እያቀረበ ነው፤ እናም የዓመቱ ተመስጋኝ ሰው ቢሆን አይበዛበትም::

### የዓመቱ ምርጥ የቴአትር ደራሲ

**ባዩሽ ለአለማየሁ**:- ይህቺ ምርጥ ተዋናይ ዘንድሮ በሁለት ተውኔቶች ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርጋለች:: ዘወትር ረቡዕ በሀገር ፍቅር በሚታየው ረመጥ ቴአትር እና ዘወትር አርብ በመታየት ላይ ባለው ፎርፌ ቴአትር ላይ በደራሲነት ተሳትፋለች፤ እናም የዓመቱ ምርጥ የቴአትር ደራሲ ናት::

የዓመቱ ምርጥ ወንድ የቴአትር ተዋናይ

**ሳምሶም ታደሠ /ቤቢ/**:- ሐሙስ ትዳር ሲታጠን፣ ዓርብ ፎርፌ፣ ቅዳሜ ሜዳልያ፣ እሁድ ህንደኬ፣ እሁድ ማታ ሩብ ጉዳይ የተባሉትን ተውኔቶች በብቃት ለሕዝብ እያቀረበ ያለ ወጣት ነው:: ታዲያ የዓመቱ ኮከብ ማን ሊሆን ነው? ... ሳምሶም ታደሰ /ቤቢ/::

### የዓመቱ ምርጥ ሴት የቴአትር ተዋናይት

**ባዩስ አለማየሁ**:- በርካታ እንስት ተዋናዮች በሣምንት ውስጥ በሁለት ቴአትሮች ላይ በመሳተፍ ላይ ናቸው:: ግና ረቡዕ፣ ሐሙስ፣ ዓርብ እና እሁድ በሀገር ፍቅር ቴአትር መድረክ ላይ የምናያት ባዩሽ አለማየሁ የዓመቱ ምርጥ ተዋናይት ብንላት አይበዛባትም::

### የዓመቱ ምርጥ ቴአትር ቤት

**የሀገር ፍቅር ቴአትር**:- ራስ ቴአትር፣ ቴአትር ለሕዝብ ማቅረብ ካቆመ ረዘም ያለ ጊዜው ነው:: ሜጋ አንፊ ቴአትር ሥራውን ሙሉ ለሙሉ አቁሟል:: አዲስ አበባ ቴአትር እና ባህል አዳራሽ አንደንዴ ጭራሽ ቴአትር ቤት መሆኑ እስኪዘነጋ ድረስ እሁድ እንኳን ቴአትር ማቅረብ ሳይችል እናየዋለን፤ በእርግጥ በአሁኑ ወቅት ቅዳሜ እና እሁድ ሁለት ቴአትሮችን እያቀረበ ነው:: እንደተለመደው የሕፃናት እና ወጣቶች ቴአትር ምንም ዓይነት የአሰራር ለውጥ ሳያደርግ ቅዳሜ እና እሁድ ጠዋት ብቻ ለልጆች ቴአትር ያቀርባል፤ ምንም ምንም ዓይነት ማሻሻያ ወይም ምንም ዓይነት አዲስ እንቅስቃሴ ሳናይ ዘመናት ተቆጥረዋል:: እጅግ ውጤታማዎቹ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር እና የሀገር ፍቅር ቴአትር ሆነው ነው የሚታዩኝ:: ብሔራዊ ቴአትር ከሣምንቱ 7 ቀናት 6ቱን ቀናት ቴአትር ይቀርብበታል:: የዓመቱ ኮከብ ቴአትር ቤት «የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር» ተብሎ ተቋቁሞ ዛሬ «ሀገር ፍቅር ቴአትር» ለመባል የበቃው አንጋፋ ቴአትር ቤት ዛሬ 9 (ዘጠኝ) ቴአትሮችን በሣምንት ውስጥ እያቀረበልን ነው:: ከሰኞ እስከ እሁድ በየቀኑ ቴአትሮች የሚቀርቡ ሲሆን በተጨማሪም ቅዳሜ ማታ እና እሁድ ማታ በአዲስ ፕሮግራም ቴአትር ለሕዝብ በማቅረቡ የዓመቱ ኮከብ ቴአትር ቤት ያሰኘዋል::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# መ ዝ ና ኛ

## የዓመቱ ጥቂት አንዳፍታዎች


### የምትነዳትን ቮልስ ዋገን መኪና ማርሽ እያቀያየርክ የፍጥነቷን ልክ መጨመርና መቀነስ ትችላለህ:: ህይወትንስ?



በደንብ እንጂ ገንዘብ ሲኖርህ (ያገኘህ ጊዜ) አትሩጥ፣ አትጨህ፤ ስታጣ ደግሞ አትደበቅ፣ አትፍራ:: በማርሽ እየተቆጣጠሩ መኖር ማለት ይሄ ነው::

**ደረጀ ኃይሌ**
/ሚያዚያ 2 ቀን 2002 ዓ.ም/

### ምነው ባልተፈጠርኩ የሚያስብሉ ነገሮች አጋጥምዎት ያውቃል?



ወይ ጥጋብ! ይሄ ጥጋብ ነው:: እምነት ስላለኝ ፈጣሪዬ ላይ ለምን ተፈጠርኩ አልለውም:: ችግርም ቢመጣ እሱ ይመልሰዋል እንጂ በእርሱ ሥልጣን መግባት አልፈልግም::

**ጋሽ ውብሸት ወርቃለማሁ**
/ህዳር 29 ቀን 2002 ዓ.ም/

### ራስዎን ወይስ ዓለምን እየመሰሉ ነው የኖሩት?



ዌል ይሄ አስቸጋሪ ነው:: ጥልቅ የሆነ ፍልስፍና ነው:: ዓለምን አልመስልም ለማለት የምትኖረው ዓለም ውስጥ ነው:: ...ከዓለም ልትማር ትችላለህ ሁሉንም መገልበጥ ግን የለብህም::

**ዶ/ር ወልደ መስቀል ኮስትሬ**
/የካቲት 6 ቀን 2002 ዓ.ም/

### አንተ ከመቃብር በላይ የሚቀመጥ ስም አኖራለሁ ብለህ ታስባለህ?



በሚገባ! በእዚህ ሙያ ውስጥ ሲወድቅም ሲነሳም አብሬው ነው ያለሁት:: አቅሜን ካወቅሁትና እንደምችል ከተረዳሁ የእኔን ዘመን ፈጥሬ ማለፍ እመኛለሁ::

**ዓለማየሁ ታደሰ**
ሚያዚያ 16/2002


### ፍቅርን እንዴት ትረጂዋለሽ?



.... ፍቅር የሌለው ሰው ምንም የለውም:: የጓደኛ ፍቅር አለ፣ የቤተሰብ ፍቅር አለ፣ የልጅ ፍቅር አለ:: ዓለም ላይ ብዙ ችግር ሲፈጥሩ የምናየው ያለ ፍቅር ያደጉ ሰዎች ናቸው:: ከሁሉም በላይ ፍቅርን አግኝቶ ያደገ ሰው ለሌላው ፍቅር መስጠት ይችላል:: መፅሐፉም እኮ ይላል፤ «ፍቅር ከሁሉም ይበልጣል::»

**ሐመልማል አባተ**
/ሰኔ 19 ቀን 2002 ዓ.ም/

### ... ትርጉም ምንድነው?



...ያለምንም ውጫዊ ተፅዕኖ በራስህ አመዛዝነህ ...ርን ማድረግ ነው:: «ዝናን እንዴት ...ታላችሁ?» ብለው ይጠይቁኛል:: ዝናን ... ካልቻልክ የተጠመደ ፈንጂ ማለት ነው:: ...ብዙ ችግር የለም:: ...እኔ ነፃነቴን በጣም ... የትም ቦታ ልታገኘኝ ትችላለህ:: የመብራት ... ልታገኘኝ ትችላለህ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ...ረብሸህም:: ነፃነት የምታሳጣው ራስህን ...::

**ፀደኒያ ገ/ማርቆስ**
/የካቲት 13 ቀን 2002 ዓ.ም/

### ህይወት ምን አስተማረችህ?



ህይወት በየማለዳው አዲስ ነው:: እንግጠም፣ እንቀኝ ካልን እያንዳንዱ ቀን ውብ ነው:: በዚህ ውብ ቀን ለአገርና ለሕዝብ ምን ውብ ነገር በሰራሁ እያልኩ እጨነቃለሁ:: እያንዳንዱ ቀኔን ስገመግም የባከነ ቀን አለኝ:: በዚህ ምክንያት ከህይወት የተማርኩት ፀፀት ነው::

**ደራሲ ጌታቸው በለጠ**
/ታህሳስ 24 ቀን 2002 ዓ.ም/

### ...ትኖሪው በምክንያት ነው? የምታደርጊያቸው ነገሮች ሁሉ ምክንያታዊ ናቸው?



ስሜታዊነት የሰው ባህሪይ ነው:: ሁሉን በምክንያት ማድረግ የሚቻል አይመስለኝም:: ነገር ግን በምክንያታዊነት የማምን ሴት ነኝ::

**ሐረገወይን አሰፋ**
/መጋቢት 11 ቀን 2002 ዓ.ም/

### ህይወትን በእግር ኳስ መግለፅ የሚቻል ይመስልሃል?



እቺ ኳስ ትታይሃለች [ቢሮው ውስጥ ለጌጥ ወደተቀመጠችው ትንሽ ጥቁርና ነጭ ኳስ እየጠቆመኝ] እኔ ከኳስ ጋር የምለይ አይመስለኝም ነበር:: የዕጣ ፈንታ ነገርም በእግር እንኳን ባልጫወት በእጄ ስለኳስ እፅፋለሁ:: ሊሴ አብሮኝ ይማር የነበረ ጓደኛዬ ከአሜሪካ መጥቶ «የምጠብቅህ ኳስን ለብሔራዊ ቡድን ተሰልፈህ እየተጫወትክ ስምህ ሲጠራ እንጂ በእጅህ አልነበረም» ብሎኛል:: የእግር ኳስ ፍቅሬን በመፃፍም ቢሆን ተወጥቼዋለሁ:: ...እናም ኳስ ለእኔ ዋና የህይወት መገለጫዬ ነች:: ስለ ኳስ ምን ብዬ እንደምነግርህ አላውቅም:: እግር ኳስ ለእኔ ከድራግም (ሱስ) በላይ ነው::

**ሁሴን አብዱልቀኒ**
/ሰኔ 12 ቀን 2002 ዓ.ም/

### ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ «ወሬ» የሚመስሉ ዘፈኖች ተበራክተዋል ይሄን እንዴት ታየዋለህ?



እንዳልኩህ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ማደግ ያለባቸው ዘፈኖች አሉ:: አሜሪካ አልያም ጃፓን ማደግ ያለባቸው ዘፈኖችም አሉ:: ምናልባት ከስታይል ጋር በተያያዘ አሁን አሁን በወሬ ደረጃ ዘፈኖች እየመጡ ናቸው:: ግን እኛ የራሳችን ማንነት አለን:: የሚስተዋሉት ችግሮች ካልተስተካከሉ እና ወደ ኢትዮጵያዊነት ካልተመለስን ወሬ አይደለም ገና ለቅሶም ተቀላቅሎ የሚዘፈንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል::

**ሙሉ ገበየሁ**
/ሐምሌ 24 ቀን 2002 ዓ.ም/



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# አንፀባራቂውን ኮከብ የመፍጠር ስትራቴጂ






ጉዳዩ በዴንማርክ፣ ኮፐንሀገን የተደረገው የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ከመካሄዱ እስቀድሞም የዓለም አቀፍ ሜዲያዎችን ትኩረት የሳበ ነበር፤ የዓለም መንግስታት የሚገኙበት ይህ ጉባኤ ለዓለም ሙቀት መጨመር ተጨባጭ መፍትሔ ያመጣ ይሆን? በሚል::

አፍሪካም እንደ አህጉር ተደራዳሪ ልዑኳን ልካ ነበር፤ የልዑኩ መሪ ደግሞ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ነበሩ:: ድርድሩ ያልታሰበ አቀጣጫ በያዘበት አጣብቂኝ ላይ አቶ መለስ ባዶ እጅ ከመመለስ ይሻላል በሚል አዲስ የመደራደሪያ ሀሳብ አቅርበው መመለሳቸው ይታወሳል:: ፕሮፖዛሉ ድሃ አገሮች የአየር ጠባይ ለውጡን ለመቋቋምና የካርበን ልቀትን ለመቆጣጠር እንዲችሉ እ.ኤ.አ ከ2006-2012 በየዓመቱ 10 ቢሊዮን ዶላር፣ በኋላም ወደ 50 ቢሊዮን እንዲያድግና ከ2020 በኋላ 100 ቢሊዮን ዶላር፣ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲደረግላቸው የሚል ነበር:: አቶ መለስ ይህን በማድረጋቸው ከተወሰኑ የአፍሪካ ሲቪል ማሕበራት ቡድኖች ተቃውሞ ገጥሟቸው እንደነበርም ይታወሳል::

ከዚህ ሁሉ በፊት የሆነውን ግን ብዙ ኢትዮጵያውያን በድማሜ ያስታውሱታል:: በአቶ መለስ የሚመራው የአፍሪካ የተደራዳሪዎች ልዑክ በአዲስ አበባ የተደረገለት የሽኝት ስነ ስርዓት እስካሁን ከብዙዎች አእምሮ የማይጠፋ ተውኔታዊ ምስል ፈጥሮ አልፏልና! እንዲያውም አንድ የስነ ልቦና ጠበብት ክንውኑን ከጥንታዊው የንግስና በዓለ ሲመት ጋር በማነጻጸር ሳያስፈልግ የተኳሸ ሲሉ ተችተውታል:: በአስፈላጊነቱ ዙርያ ለተነሳላቸው ጥያቄ ባለሙያው ሲመልሱ «አንዘንጋ! ያለነው ሁለንተናዊ ክንውኖች የቀጥ በቀጥ ውሳኔ በሚጠይቁበት የዘመን ምዕራፍ ላይ ነው::...» ካሉ በኋላ ነገሩ እንኳ ወዲህ ነው ሲሉ የግለሰብን ፖለቲካዊ ስብዕና የማግዘፍ ፍልስፍና ስለባተበት ዳራ ያወሳሉ:: «በምስለ መስኮት /ቴሌቭዥን/ የቀረበውና የተዋጣለት የመድረክ ተውኔት የመሰለው ያ ትዕይንት ባለፉት ዓመታት ሲሰራ የቆየው ጠ/ሚ/ሩን ማዕከል ያደረገ የሕዝብ ግንኙነት ስራ የመጨረሻ ክፍል ነበር::»

ይህ ዕለት ከህፃናት እስከ አረጋዊው ፣ ከመምህራን እስከ ተማሪው፣ ከድንበር ጠባቂው ሰራዊት እስከ አርሶ አደሩ ከተመራማሪው እስከ አርቲስቱ፣እስከ ነጋዴው፣ እስከ ሽማቹ፤... ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍል የተወከሉ መልክተኞች «በዓለማችን ላይ ለተጋረጠው ችግር መፍትሔ ሊያመጣ የሚችል ልዑክ መሪ ለአቶ መለስ» አደራውን አቀበሉ:: አቶ መለስም የእያንዳንዱ መልክተኛ አደራ እጅ እየነሱ ይቀበሉ ነበር:: መቼም ይህ የሽኝት እና «የአደራዎችን» ዝግጅት የተመለከተ የዋህ ሰው የዓለማችን ዕጣ ፈንታ በእኒህ መሪ እጅ እንዳለ በመገመት በተመስጦ ተስፋ ማድረጉ አይቀርም::

የአቶ መለስ ዜናዊን ሁለንተናዊ ስብዕና በማግዘፍ በድርጅታቸውም ሆነ በመንግስት መዋቅር ውስጥ አቻ አልባ የማድረጉ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ በየፌናው ሲከናወን ቆይቷል የሚሉ ወገኖች የሚያነሱት ሌላው ነጥብ የዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የተጫወተው ሚና ነው:: ወደፍፅምና በተጠጋ አኳኋን በያዝነው ዓመት የተንፀባረቀው አቻ አልባ ተክለ ስብዕና ላለፉት አምስት ዓመታት እየተኮተኮተ ያደገ ነበር ይላሉ:: እንዲያውም አንዳንዶቹ የስነ አመክንዮ መፋለስ ያለባቸው ናቸው ሲሉ ይከራከራሉ:: እስኪ የተወሰኑትን እንይ::

## ሽልማቶቹ...

የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጠ/ሚ/ር መለስ ለአፍሪካ እግር ኳስ ማደግ ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በሚል «ጐልድ - ኦርደር ኦፍ ሜሪት አዋርድ» ሸለማቸው:: ጠ/ሚ/ሩ ከዚህ ተቋም ይህን መሰሉን ሽልማት አገኛ ለሁ ብለው የሚገምቱበት ጠጨባጭ ሁኔታ እንዳልነበር ይነገራል:: የስፖርቱ ቤተሰቦች እንደሚሉት አቶ መለስ ቀደም ሲል ለዘርፉ የሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን / ቻይናዎች የእግር ኳስ ስታዲየም ሊገነቡ በመጡበት ወቅት የሚቀድመው የምግብ እህል ወይስ ይህ? በሚል ንፅፅር በመቃወማቸው ስታዲየሙ ኬንያ ውስጥ መገንባቱ ይጠቀሳል /የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ለሁለት ተከፍሎ አገሪቱ ከዓለም አቀፍ ውድድሮች ስትታገድ ሁሉ ያ «ከፍተኛ አስተዋጽኦ» አልታየም::


ይህም ከአጠቃላዩ የግለሰብ ማዕከላዊነትን ለሕዝብ ግንኙነት ስራ የመጠቀሙ የረዥርም ጊዜ ስልት አንዱ ከመሆን የዘለለ ተልዕኮ አልነበረውም አሰኝቷል::

የሩዋንዳ መንግስት ከፍተኛውንና የሩዋንዳን የብሔራዊ ነፃነት ሜዳሊያ ሸልሟቸዋል:: በሌላ ወቅት ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ ሰላምን ለማስጠበቅ በኢጋድ አማካይነት ላበረከቱት አስተዋጽኦ የዓለም ሰላም ሽልማት ተሰጥቷቸዋል::

በአፍሪካ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ትራንስፎርሜሽን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ በሚል «Tabor 100» በተሰኘው ተቋም «የዓመቱ ዓለም አቀፍ መሪ» እንዲሁም መቀመጫውን በአሜሪካ ባደረገው «አፍሪካን ታይምስ» ጋዜጣ ከዚያ በፊት ዴዝሞንድ ቱቱ እና ኔልሰን ማንዴላ የተሸለሙትን «የአፍሪካ ታላቅ የፖለቲካ አመራር ሽልማት» ተሸላሚ ተደርገዋል::

ይህም ብቻ አልነበረም:: በዓለም አቀፍ

# የአመቱ አሳዛኝ ክስተት



በዳዊት ከበደ



ዕለተ ሰኞ ጥር 17 ቀን 2002 ዓ.ም ንጋት ላይ የሊባኖስ ርዕሰ ከተማ ከሆነችው ቤሩት ተነስቶ ከጧቱ 1:50 ላይ አዲስ አበባ ለመድረስ «ራፊክ ሀሪሪ» ከተሰኘ የአገሪቱ አየር ማረፊያ የተነሳው ቦይንግ 737 የበረራ ቁጥር 409 የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመንገደኞች አውሮፕላን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ 82 ተሳፋሪዎችንና ስምንት የአውሮፕላኑ ሰራተኞችን እንደያዘ በሜዲትራኒያን ባህር የተከሰከሰበት አጋጣሚ ከአመቱ አሳዛን ክስተቶች ቀዳሚው ነው::

51 ሊባኖሳዊያን 31 ኢትዮጵያውያን (ስምንት የአውሮፕላኑ ሰራተኞችን ጨምሮ) ሁለት እንግሊዛዊያን ከካናዳ፣ ፈረንሳይ፣ ኢራቅ፣ ሩስያ፣ ሶሪያና ቱርክ ደግሞ አንዳንድ ዜጎችን እንደያዘ ለአደጋ የተጋለጠውማ በዚህም የበርካታ አለምአቀፍ ሚዲያዎችን ትኩረት የሳበው ይህ የአውሮፕላን አደጋ ትክክለኛ መንስኤው እስካሁን በግልጽ አልታወቀም::

አደጋው በተከሰተ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ የአገሪቱ የትራንስፖርትና የስራ ሚኒስትር የሆኑት ጋሐዚ አርዲ «ስህተቱ ፓይለቱ አቅጣጫ እንዲቀይር ተነግሮት ያንን ባለመፈፀሙ የተከሰተ ነው» ማለታቸውን ተከትሎ የአገሪቱ ሚዲያዎች በፓይለቱ ላይ ዘመቻቸውን አጧጧፉት:: ይህ ሁሉ የተባለው ግን የአውሮፕላኑ መረጃ መመዝገቢያ ጥቁር ሳጥር (black box) ባልተገኘበት፤ የነፍስ አድን ሰራተኞች አስከሬን ማውጣት ባልጀመሩበት፤ በአጠቃላይ ምንም አይነት የመረጃ ፍንጭ ሳይገኝ በስሜት ብቻ የተሰነዘረ አስተያየት እንደነበር አያጠያይቅም::

የአገሪቱ ሚዲያዎች እነዚህን መሰረታዊ እውነታዎች ግምት ውስጥ ከማስገባት ይልቅ በስሜት የተሰነዘረውን አስተያየት ተቀባብለው በማስተጋባታቸው በአገር ውስጥ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ቁጣ እንዲቀሰቀስ ምክንያት ሆኗል:: የኢትዮጵያ መንግስትም የምርመራው ውጤት በመስኩ ባለሙያዎች ሳይገለጽ የአለም አቀፍ አቬየሽን ህግን በጣሰ አኳኋን በፓይለቱ ላይ ጣት የመቀሰር ድርጊት እንዲቆም ጥሪ ከማቅረቡ ባሻገር በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን የተመራ አንድ የልኡካን ቡድን ከአገሪቱ ባለሰልጣናት ጋር እንዲነጋገር መላኩ ይታወሳል:: የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሀዘን ቀን ያወጁ ሲሆን፤የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም በሰዓቱ ልማታዊ አርሶ አደሮችን ለመሸለም ከተዘጋጀባት ጅጅጋ ከተማ የሐዘን መግለጫ አስተላልፈው ነበር::

አውሮፕላኑ በተከሰከሰበት ሰዓት በአካባቢው አስቸጋሪ የአየር ፀባይ መኖሩ ይገለጽ እንጂ በስፍራው የነበሩ የአይን እማኞች ግን አውሮፕላኑ ከመከስከሱ ከደቂቃዎች በፊት የእሳት ነበልባል ይታይበት እንደነበር በወቅቱ ለሬውተርስ አስተያየት ሰጥተዋል:: አንዳንድ አለምአቀፍ ሚዲያዎች ይህንና ሌሎች ተጨማሪ መላምቶችን መነሻ በማድረግ ነበር የኋላ ኋላ ጉዳዩ ከሽብር ጥቃት ጋር ለማያያዝ የተሽቀዳደሙት::

አንዳንድ የሊባኖስ ባለስልጣናትና የአገሪቱ ማዲያዎች ስህተቱ የፓይለቱ እንደሆነ ግምታዊ መላምት መስጠታቸውን ተከትሎ ክስተቱ ሊባኖስ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ አሉታዊ ተፅእኖ መፍጠሩ አልቀረም:: በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ልዩነታቸውን ወደ ጎን በማድረግ ለአየር መንገዱ ያላቸውን ቅን አጋርነት ያሳዩበት አጋጣሚም ነበር:: በውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያን ድረ-ገጾች የቤይሩት ሚዲያዎች የተሳሳተ አሉታዊ ዘገባ ከማሰራጨት እንዲቆጠቡ ድምጻቸውን በማሰማት ረገድ የላቀ ድርሻ ነበራቸው::

የቤይሩት ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በወቅቱ በሰጡት አስተያየት አንዳንድ አሰሪዎቻቸው ወደ ሆስፒታል ሄደው የዘመዶቻቸውንና ጓደኞቻቸን አስከሬን እንዳይጎበኑ እስከ መከልከል ደርሰው እንደነበርና በተለይ ጀሚላ የተባለች ወጣት «ዘ-ስታር ዴይሊ» ለተሰኘ ጋዜጣ በሰጠችው አስተያየት «በአደጋው እህቷን ያጣች ወጣት ወደ ሆስፒታል ሄዳ የእህቷን አስከሬን እንዳትመለከት አሰሪዋ በግልጽ ከልክሏታል:: ለማን አቤት እንደምንል ጨንቆናል» ማለቷ አይዘነጋም::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ግርማ ዋቄ በወቅቱ «ለመደምደሚያ ከመቸኮላችን በፊት መንስኤው እስኪጣራ ድረስ ብንጠብቅ ምናለበት?» በማለት የተዛባ መግለጫ በመስጠት ለተጠመዱ ባለስልጣናትና ሚዲያዎች ምላሽ መስጠታቸው ይታወሳል::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ አደጋው እንደተከሰተ የቴክኒክ ኤክስፐርቶች ቡድን ወደ ስፍራው ልኮ ነበር:: በአሜሪካ ዩኒቨርስቲዎችና የግል ተቋማት በከፍተኛ ኤክስፐርቶችን ጨምሮ የቦይንግ ኩባንያ ኢንጂነሮች፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድና የሊባኖስ ባለሙያዎች እንዲሁም ለጉዳዩ ቅርብ የሆኑ አካላት ጉዳዩን መርምረው እውነተኛውን የምርመራ ውጤት ይፋ ያደርጉ ዘንድ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ግፊት እንዲደረግ የጠየቁ ሲሆን «በተለይ የአየር መንገዱ ማኔጅመንት በዘርፉ ብቃት ያላቸው ሙያተኞችን በማሰማራት የተቋሙን የዘመናት ዝናና መልካም ስም እስከወዲያኛው ሊያስጠብቅ ይገባል» ሲሉ ዶክተር ኢንጅነር መንግስቱ ጥሪ አቅርበው ነበር:: አቶ ግርማ ዋቄ አደጋው ከደረሰ ከአንድ ወር በኋላ በፅህፈት ቤታቸው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በምርመራው ሂደት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባለሙያዎች የማግለል ሤራ እየተካሄደ መሆኑን ለአውራምባ ታይምስ ተናግረዋል:: ይህም ሆኖ የአደጋውን እውነተኛ መንስኤ ምን እንደሆነ እስከዛሬ ድረስ በይፋ የተገለፀ ነገር የለም:: በአደጋው ህይወታቸውን ያጡ ኢትዮጵያዊያን ስርዓተ ቀብር በቅድስት ስላሴ ካቴድራል በርካታ ባለስልጣናትና የአየር መንገዱ ሰራተኞች በተገኙበት ተከናውኗል::

> አውሮፕላኑ በተከሰከሰበት ሰዓት በአከባቢው አስቸጋሪ የአየር ፀባይ መኖሩ ይገለጽ እንጂ በስፍራው የነበሩ የአይን እማኞች ግን አውሮፕላኑ ከመከስከሱ ከደቂቃዎች በፊት የእሳት ነበልባል ይታይበት እንደነበር በወቅቱ ለሬውተርስ አስተያየት ሰጥተዋል



እኤአ ከ2008 ጀምሮ ሦስት አለም አቀፍ ሽልማቶችን የተቀበለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ «የ2001 ዓ.ም ጉልህ ክስተቶች» በሚል ርዕስ የዛሬ አመት በታተመው አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት የአመቱ ስኬታማ ተቋም ተብሎ መመረጡ አይዘነጋም::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

> አንድ የቀድሞ የሕወኃት አመራር አባል «በድርጅቱ ውስጥ አንድን አመራር አጉልቶ ማውጣት የማይታወቅ እንዲያውም የሚነቀፍ ነበር::...» ካሉ በኋላ «...ከ1993ቱ የአመራሩ መሰንጠቅ ጀምሮ ግን ሁኔታው በአስገራሚ ሁኔታ ተለወጠ::» ይላሉ::

ደረጃ ያላቸውን የአፍሪካ መሪነት ትራክ ተቀባይነት ጠብቀው እንዲቀጥሉ የሚያስችሏቸው ተደራራቢ ስልጣኖች መቀዳጀታቸው አልቀረም::

በግሎባል ኳሊሽን ፎር አፍሪካ በሊቀ መንበርነት፣ የቤጂንግ አክሽን ፕላንን ለማዘጋጀት አይነተኛ ሚናቸውን በመግለጽ በጉባኤው ወቅት በመተሳሳይ ኃላፊነት የአፍሪካ ኮሚሽነር፣ በአፍሪካ ሕብረት አማካይነት የኔፓድ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር፣ በኮፐን ሀገኑ ኮንፈረንስ የአፍሪካ ተደራዳሪ (ተወካይ) መጨረሻም በዚህ ዓመት በተባበሩት መንግስታት በአየር ለውጥ መዛባት ለሚደርሰው ጉዳት ካሳ ለሚከፍለው የአማካሪ ቡድን ሊቀ መንበር ተደርገዋል::

ከምርጫው መጠናቀቅ በኋላ በጊዜያዊነት የተገለፀውን ውጤት በማስታከክ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ለተገኙ አባላትና ደጋፊዎቻቸው የድል ንግግር ሲያደርጉ ከላይ የተመለከትናቸው ጥምር ምንጮች ሲያከናውኗቸው የቆዩት ጠቅላይ ሚኒስትሩን አግዝፎ የማውጣት ተግባራት ሥራቸውን መስራታቸው ታየ:: አንድ የቀድሞ የሕወኃት አመራር አባል «በድርጅቱ ውስጥ አንድን አመራር አጉልቶ ማውጣት የማይታወቅ እንዲያውም የሚነቀፍ ነበር::...» ካሉ በኋላ «...ከ1993ቱ የአመራሩ መሰንጠቅ ጀምሮ ግን ሁኔታው በአስገራሚ ሁኔታ ተለወጠ::» ይላሉ::

አሁን በብዙዎች አእምሮ ውስጥ የሚመላለሰው በአንድ በኩል ባልተለመደ ሁኔታና ለተለያየ አላማዎች ሲባል የሚደረገው ግነትን ማላበስ በተጨባጭ የቆመበት መሰረት እና የሚጠብቀው ዕጣ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ነው::

## "እስኪነክሱ ማንከስ"

ጠ/ሚ/ር መለስ ለአፍሪካ የእግር ኳስ እድገት ባበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በሚል (አገራትን በአህጉሩ የደረጃ ሰነጠረዥ የመጨረሻው ደረጃ ትገኛለች) ከፍተኛውን ሽልማት ሲሰጣቸው ያጫረው ትዝብት በሌሎቹ መስኮች ሲንፀባረቅ ቢቆይም በተለይ ምዕራባውያን ለጠቀሜታቸው ሲባል ይከተሉት የነበረው የማዳመቅ አካሄድ በአንድ ጉዳይ ፈተና ላይ መውደቁ ነበር:: ይኸውም የአቶ መለስ በስልጣን መንበሩ ላይ እንደተሰየሙ መኖር የፈጠረው አንድምታ ነው::

በመርሕ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ አመራርን በሚከተሉ አገራት የአንድ መሪ ምትክ አልባ ሆኖ መቀጠል የግለሰቡ የላቀ ብቃት የፈጠረው ሳይሆን የስርዓቱን አፋኝነትና ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት መስፈን ስፈራ ባለመስጠት የሚፈጠር አምባገነንነት ተደርጎ ይወሰዳል:: በዚህ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ነበር በምዕራባውያን ጋዜጠኞች ጉትጎታ የጠ/ሚ/ሩ «ስልጣን በቃኝ» የሚል ቃል የተደመጠው:: የስልጣን «በቃኝ» ንግግራቸው ትኩረት ስቦ የቆየ ቢሆንም በያዝነው ዓመት መገባደጃ ላይ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተገኝተው "ድርጅቴ ተመካክሮ በወሰነው መሰረት ከኢህአዴግ ሊቀ መንበርነቴም ሆነ ከጠ/ሚ/ርነቱ የምለቀው ከአምስት ዓመት በኋላ በመሆኑ እስከዚያው ታገሱ" ሲሉ አቋማቸውን ይፋ አድርገዋል:: - "እስኪነክሱ ማንከስ" እንዲሉ::

በዚህም በአፍሪካ በአምባገነነታቸው ምዕራባውያን አምርረው የሚቀፏቸውን የሮበርት ሙጋቤን፣ የኦማር ቦንጎን፣ የሞቡቱንና የዚያድ ባሬን ከሁለት አስርት በላይ አገዛዝ ሪከርድ ተጋርተዋል:: «ይህ ሁኔታ በአጠቃላይ ስርዓቱ ሆነ በአቶ መለስ ታሪክ ላይ የራሱን ጥላ ይጥላል::» ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ::

እያጠናቀቅነው ባለነው ዓመት የወጡ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሪፖርቶችም ከአቶ መለስ አንፀባራቂ ገድል ጀርባ ያለውን እውነታ አጋላጭ ናቸው ተብለዋል:: ምንም እንኳ የመንግስት ቃል አቀባይ መ/ቤት ከሪፖርቶቹ አብዛኞቹ ቀደም ሲል ከነበሩ ዓመታት ተቀድተው የተነገሩ ናቸው ቢልም ተፅዕኖውን ማለሳለስ ግን አልተቻለም:: የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት፣ ሂውማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢንተርናሽናል ከእነዚህ ተቋማት የተወሰኑት ብቻ ቢሆኑም የሪፖርቶቻቸው ባሕሪ ተመሳሳይነት በጠ/ሚ/ሩ አንጸባራቂ ገፅታ ላይ የሚኖረው የጠራ ጫና የሚታወቀው በአዲሱ የበጀት ዓመት አፈጻጸም ላይ ነው ተብሎ ይገመታል:: ለጊዜው የቅርብ የቤት ሥራ የነበረው ምርጫ 2002 ያለብዙ ፈታኝ ሁኔታ መሪ ተዋናዩን አንጸባራቂ ኮከብ አድርጎ አልፏል::

# ኤሴክስ የትምህርት ተቋም አክሲዮን በመሸጥ ላይ ነው!



ቀደም ብሎ ሲልቪያ ፓንክረስት መታሰቢያ የትምህርትና ስልጠና ተቋም አ/ማ በሚል መጠሪያ የተቋቋመው አሁን የኤሴክስ የትምህርት ተቋም አክሲዮን ማህበር በሚል ስያሜ ተለውጧል::

ኤሴክስ (ESSEX):- ሲልቪያ ፓንክረስት በኢጣሊያ ወረራ በግፍ ለተገደሉ ኢትዮጵያውያን መታሰቢያ እንዲሆን በርስቷ ላይ ያሰራችው ሃውልት የሚገኝበት ስፍራ ነው::

**1. የቦርድ አባላት:-**

| | |
|---|---|
| ዶ/ር ወሮታው በዛብህ | ሰብሳቢ |
| ዶ/ር ኢንጂነር ፀጋ ጥበቡ | ም/ሰብሳቢ |
| አቶ ከርሴማ ሙዘይን | ፀሐፊና አባል |
| አቶ ሰሎሞን ግዛው | አባል |
| ወ/ሮ ትዝታ አሰፋ | አባል |

**2. የትምህርት ተቋሙ ለአባላቱ የሚያስገኛቸው ጥቅማ ጥቅሞች**

- ከ50 % በላይ ትርፍ
- ለልጆች ቅድሚያ የመማር እድል
- ከመሰል ተቋት ጋር በመደራደር የሕንፃ ባለቤት መሆን
- ከፍተኛ ለውጥ ማምጣትና የትምህርት ባለሙያዎችን ማስገኘት የሚችል ተቋም መገንባት
- አዳሪ ትምህርት ቤቶች ማቋቋም

**3. የአክሲዮን አሻሻጥ ዝርዝር:-**

- የአንድ አክሲዮን ዋጋ ብር 1000
- የአገልግሎት ዋጋ 7 %

**4. የአከፋፈል ሁኔታ ሙሉ ክፍያውን በመክፈል ወይም**

ሀ. 40% በግዥ ወቅት
ለ. 30% ከመጀመያው ክፍያ ከ6 ወራት በኋላ
ሐ. 30% ከሁለተኛው ክፍያ ከ6 ወራት በኋላ

**5. የሚፈቀደው ዝቅተኛው ኢንቨስትመንት 5 አክሲዮኖች የአገልግሎት ክፍያውን ጨምሮ ..........ብር 5350**

**6. የሚፈቀደው ከፍተኛ ኢንቨስትመንት 2000 አክሲዮኖች የአገልግሎት ክፍያ ጨምሮ ................ብር 2,140,000**

7. ለበለጠ መረጃ:-

- አራት ኪሎ ከቱሪስት ሆቴል ወይም ከተስፋ ገብረስላሴ ማተሚያ ቤት ወረድ ብሎ ከሚገኘው ጂኒየስ የስልጠናና የምክር አገልግሎት ማዕከል ቅጥር ግቢ ውስጥ እና
- ሸገር ህንፃ 5ኛ ፎቅ /ቦሌ መድኃኒዓለም አጠገብ/ ቢሮ ቁጥር 505 እንገኛለን::

ስልክ ቁጥር 011-6526386
ሞባይል 0911-452013 0911-407753
0911-681147 0921-014410 0920-716658


# በሲነር ላይን የፅህፈት መሳሪያዎች ይጠቀሙ




**ውበት ልስላሴና ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያላቸው የተማሪ ደብተሮች!**

**High Quality And Well Designed Excercise Books!!**

www.sinarline.com




PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# ጊቤዎቹ፤ በአመቱ የተጋፈጡት ፈተና

በኤልያስ ገብሩ

ጥር 1 ቀን 2002 ዓ.ም የአል-ጃዚራ የቴሌቭዥን ጣቢያ «በአፍሪካ ታላቁ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክት በኢትዮጵያ እየተገነባ ነው» ሲል ዘገበ:: ረቡዕ ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም ጉሀ ሲቀድ ብዙ የተወራለት፣ የተነገረለትና የአገሪቷን የኃይል አቅርቦት በእጅጉ ያቃልላል የተባለው ግልገል ግቤ 2 የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ሁሉም ነገር ተጠናቆለት መራቂ የክብር እንግዶቹን እየተጠባበቀ ነው::

ከዚህ ቀን ቀደም ብሎ ኢቴቪ በጉዳዩ ላይ አንድ ዶክመንታሪ ፊልም አቅርቦ ነበር:: የዶክመንታሪው ዘጋቢ ጋዜጠኛ በኃይል ማመንጫው ታናል ውስጥ ባሉ ደረጃዎች እየወጣና እየወረደ፤ ላቡ «ጠፍ» እያለና ድምጹ እየተቆራረጠ የኃይል ማመንጫውን ዘመናዊ አሰራርና ሌሎች ነገሮች በተቻለው ሁሉ ለተመልካች እያሳየ በመግለጽ ሲደክም ተስተውሏል:: በፊልሙ ላይ የተለያዩ የመንግስት ባለስልጣናት ስለ ኃይል ማመንጫው አብስረዋል::

420 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለውና ከ480 ሚሊዮን ዩሮ በላይ የፈጀው የኃይል ማመንጫ 45 በመቶ በኢትዮጵያ መንግስት፣ ቀሪው 52 በመቶ ደግሞ በአውሮፓ የኢንቨስትመንት ባንክ እገዛ እንደተሸፈነ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ምህረት ደበበ በምረቃው ዕለት በኢቴቪ ቀጥታ ስርጭት ገልፀው ነበር:: «በሙያ ህይወቴ ታላቅ ስኬት ነው» ሲሉም በታላቅ ደስታ ተናግረዋል:: «የኢትዮጵያን ገጽታ ለመቀየር እየተሰሩ ካሉ ሥራዎች አንዱ ነው» ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሲሆኑ፣ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስትር የሆኑት አቶ አለማየሁ ተገኑ በበኩላቸው «አይቻልም» የተባለው ሲቻል እንዳዩና የአገሪቷን የኃይል እጥረት በመጠኑ ግልገል ግቤ 2 እንደሚያቃልል ጠቅሰዋል::

«ይህ ለአገራችን ትልቅ ስኬት ሲሆን ስኬታችንም የብዙዎች መስዋዕትነት የተከፈለበት ነው» በማለት እንባ በተቀላቀለበት ስሜት ንግግር አድርገው የነበሩት ደግሞ የፕሮጀክቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ኢ/ር ስመኘው በቀለ ናቸው::

በምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ የጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፍራንኮ ፈራንቲኒ፣ የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽፈራሁ ሽጉጤ፣ ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች መገኘታቸው ሲታወቅ በግምባታው ላይ ስምንት ሰዎች መሞታቸው በእለቱ ተጠቅሷል::

## «በሬ ወለደ»

ከምርቃቱ ከአንድ ወር በኂላ በኃይል ማመንጫው ላይ አደጋ እንደደረሰ ወሬዎች በስፋት ይናፈሱ ጀመር:: የጣሊያን ሚዲያዎችም ግልገል ግቤ 2 አደጋ እንደገጠመው ዘገቡ::

የካቲት 5 ቀን 2002 ዓ.ም ሳምንታዊው ነጋድራስ ጋዜጣ «ግልገል ግቤ 2 እክል ገጠመው» በሚል ርዕስ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው የኃይል ማመንጫ በገጠመው የዋሻ መዘጋት ሥራ ማቆሙን ዘገበ:: ጋዜጣው ማብራሪያ እንዲሰጡበት ያነጋገራቸው የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ምህረት ነጋሽ «በሬ ወለደ ነው» በማለት ጉዳዩን እንዳጣጣጣሉት ጋዜጣው ጨምሮ አስነብቦ ነበር::

በወቅቱ በይፋ የተገለፀ የመብራት ፈረቃ አይኑር እንጂ በተደጋጋሚ የሚጠፋበት ሁኔታ ተስተውሎ ነበር::

## አዎ፣ ጊቤ 2 ችግር ገጥሞታል


ይህንን ዘገባ የያዘው ነጋድራስ ጋዜጣ ገበያ ላይ በዋለበት ዕለተ ዓርብ (የካቲት 6 ቀን 2002 ዓ.ም) «በግልገል ጊቤ ሁለት የኃይል ማመንጫ ግንባታ ላይ አደጋ ደርሶበታል» መባሉን በተመለከተ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በጋራ በመሆን የግንባታውን ሥራ ከሰራው የሳሊኒ ኮንስትራክሽን ኃላፊዎች ጋር በሂልተን ሆቴል ለአገር ውስጥና ለውጭ ጋዜጠኞች መግለጫ ሰጡ::

ከጥር 13 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ጣቢያው እንደሚያስፈልገው መጠን የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የሚያስችለውን የውሃ ግፊት መቀነስ / pressure drop/ ባህሪይ የተስተዋለበት በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካሎች ትኩረት ስቦ ለተከታታይ ቀናት የኃይል ማመንጨት ተግባሩ ሳይቋረጥ የችግሩን መንስዔ ለማወቅ ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ መቆየቱትን የተናገሩት የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስትር አቶ አለማየሁ ተገኑ በመጨረሻ ችግሩ ተባብሶ ሌላ ጉዳት እንዳያደርስ ለማድረግ ሲባል ጣቢያው ከጥር 16 ቀን 2002 ዓ.ም ምሽት ጀምሮ ሥራ እንዲያቆም መደረጉን ገለፁ::

ለችግሩ መፍትሔ እንዳለውና መንግስት፣ ግንባታ ላይ ያሉ ሠራተኞች፣ የሥራ ተቋራጭ አማካሪ መኃንዲሱና ኮርፖሬሽኑ ችግሩን ለመፍታት እየተረባረቡ እንደሚገኙ የጠቆሙት ሚኒስትሩ የደረሰውን አደጋ አስመልክቶ ለሕብረተሰቡ ለምን አልተገለፀም? ተብለው ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ «የተፈጠረውን ችግር ከህብረተሰቡ ለመደበቅ አይደለም» ካሉ በኂላ በምክንያትነት የችግሩን ምንነት መጀመሪያ ላይ ለይቶ ለመግለጽ አስቸጋሪ ስለነበረ መሆኑን አስረድተው ነበር:: በማከልም የጥገናው ሥራ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ በወቅቱ መናገር እንደሚከብድ ምላሽ ሰጥተዋል::

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ ምህረት ደበበም ስለ ተከሰተው ችግር ለጋዜጠኞች ሲገልፁ በወቅቱ የኃይል ማመንጫው ገና በፍተሻ ዘመኑ ላይ እንዳለ ተናግረው «ችግሩ ከተከሰተ በኂላ በኃይል ማመንጫው ሥራ ሲስተምና በግድቡ ላይ የኦፕሬሽን ክትትል ማድረግ ጠይቋል:: የኃይል ማመንጫውን ሥራ አቁሞ መመርመር ተገቢ ነው:: ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ለሚዲያ ምን ተብሎ ይነገራል:: ልክ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ አደጋ ብዙ መላ ምት ሊነገር ግን ይችላል» ብለዋል::

የፕሮጀክቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ኢ/ር ስመኘው በቀለ በበኩላቸው «የፈረሰው ድንጋይ እንደ ግድብ ታናሉን አንቆ ይዞታል... ሚዲያዎች አይዟችሁ እንድትሉን እንፈልጋለን::» ያሉበት ሁኔታ ነበር:: ይህንንና ከአደጋውም በኂላ በአገሪቷ የኤሌክትሪክ ኃይል በከፍተኛ ሁኔታ ይቋረጥ እንደነበር አውራምባ ታይምስ በየካቲት 7 እና በመጋቢት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ዕትሙ ማስነበቡ ይታወሳል:: በሚያዚያ ወር ውስጥ ግን የኃይል ሥራው 8.46 ኪሎ ሜትር መሰራቱን፣ ችግር ተፈጠረ የተባለበት ቦታ ለመድረስ 500 ሜትር እንደሚቀርና ቀሪው ጥገና ሥራም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ መንግስት ገልጾ ነበር::



ጠ/ሚ መለስ የግልገል ጊቤ 2 ኃይል ማመንጫ ሥራ ሲያስጀምሩ

## የፈጀውን ይፍጅ የተባለለት ጊቤ 3

የግልገል ጊቤ 1 እና 2 ተከታይ ፕሮጀክት የሆነው ጊቤ 3 የሐይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግንባታ ገና ከጥንስሱ ጀምሮ ነበር ተቃውሞ የገጠመው:: ለተቃውሞው መነሻ የሆነው ግድቡ በሚሰራበት ጊዜ ወሰን ተሻጋሪው ኦሞ ወንዝ ኬንያ ውስጥ ለሚገኘው ቱርካና ሐይቅ ዋና ገባር በመሆኑ የግንባታው ዕውን መሆን የሐይቁን ህልውና ይፈታተናል በሚል መላምት ነው::

ከዚህ ባሻገር በግዙፍነቱና ሊያመነጭ በሚችለው ከፍተኛ የኃይል መጠን አስደናቂነቱ የተነገረለት ጊቤ 3 «በኬንያ እና ኢትዮጵያ ድንበር ላይ የሥነ-ምህዳር ቀውስ ይፈጥራል» በሚል ለግድቡ ግንባታ ማስኬጃነት የሚውለውን ገንዘብ ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ አበዳሪ ተቋማትና መንግስታት እንዳታገኝ የተለያዩ ወገኖች በርካታ ጥረቶችን ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወሳል::

በተለይ መቀመጫውን ለንደን ያደረገው «ሰርቫይቫል ኢንተርናሽናል» እና በካሊፎርኒያ የሚገኘው «ኢንተርናሽናል ሪቨርስ» የተሰኙት ተቋማት በግድቡ የተነሳ የኦሞ ወንዝ ተፈጥሯዊ መስመሩን ስለሚቀይር የወንዙን ዳርቻ ተከትለው ሰብሎችን በመዝራት እና አሳ በማስገር የሚተዳደሩት የሐመር እና ስዌጉ ጉሳ አባላት የሆኑ ከ200 ሺ. በላይ ሰዎች ከተፈጥሯዊ አካባቢያቸው የመፈናቀልና በአካባቢውም የተፈጥሮ መዛባት አደጋ ሊያጋጥም እንደሚችል ይወተውታሉ:: ለግንባታው የሚያስፈልገውን 1.4 ቢሊዮን ዶላር የዓለም ባንክ፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ እና የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ፣ እንዲሁም የጣሊያን መንግስት በብድርም ሆነ በእርዳታ መልክ ለኢትዮጵያ እንዳይሰጡ ሌት ተቀን የተቋማቱን በር ሲያንኳኩ ነበር:: ከአቶ መለስ መንግስት ጋር የከረረ ፍጥጫ ውስጥ ገብተው እንደነበረም ይታወቃል::

መቀመጫውን በሉክዘምበርግ ያደረገው የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ኢትዮጵያ ለምታስገነባው የግልገል ግቤ 3 ኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግንባታ አከባቢያዊና ማሕበራዊ ተጽዕኖዎችን ለማጥናት ሊመደብ የነበረውን ገንዘብ ማቋረጡን ሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም አስታውቆ ነበር::

የኢትዮጵያ መንግስትም በበኩሉ በግድቡ ዙሪያ ከኬንያ መንግስት ጋር በጋራ በመሆን በተሰራው ጥናት በአካባቢው ላይ የሚደርስ አሳሳቢ ችግር እንደማይኖር፣ በግድቡ ግንባታ የተነሳ ለሚፈናቀሉ ዜጎች አስፈላጊውን እርዳታና ዜጎቹንም ወደሌላ ቦታ እንዲሰፍሩ እንደሚያደርግ በወቅቱ አስታውቋል::

ምንም እንኳን ገንዘቡ እንዳይሰጥ ሰፊ ዘመቻ ተካሂዶ የነበረ ቢሆንም የቻይና መንግስት 500 ሚሊዮን ዶላር ለኢትዮጵያ ለመለገስ ተስማምቶአል:: ግንባታው ሲጠናቀቅ ከ1800 ሜጋ ዋት በላይ ኃይል የማመንጨት አቅም እንደሚኖረውና «የአፍሪካ ትልቁ ግድብ ይሆናል» ተብሎ የሚጠበቀውን ጊቤ 3 ለመገንባት ቀደም ብሎ ኮንትራቱን ወስዶ ከነበረው ሳሊኒ ኮንስትራክሽን በተጨማሪ ዶንግፋንግ የተሰኘ የቻይና ኤሌክትሪክ ኩባንያ በጥምረት የሚሰራው ይሆናል::

በቅርቡም ጠ/ሚኒስትር መለስ በጽ/ቤታቸው ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ወቅት ጉዳዮን አስመልክቶ ከአውራምባ ታይምስ ጥያቄ ቀርቦላቸው ማብራሪያ ሲሰጡ «የእነሱ ፍላጎት አፍሪካ የኂላ ቀሮች ሙዚየም ሆና ለዘላለም እንድትኖር ነው» ብለው ነበር:: «ይህንን የሚያደርጉት ደግሞ የሚያስፈልጋቸውን ግድብ ሰርተው ከጨረሱ በኂላ ነው:: ዜጎቻቸውን እየላኩ ኂላ ቀር እና ራቁታቸውን የሚሄዱ ሕዝቦችን እየተመለከቱ እንዲዝናኑላቸው ስለፈለጉ ብቻ የግድቡን ግንባታ ማስተጓጎል ይፈልጋሉ» ያሉት አቶ መለስ «ግድቡ ፈለጉትም አልፈለጉትም በተያዘለት ፕሮግራም ተገንብቶ ይጠናቀቃል:: ከፈለጉ መዝለል ይችላሉ» ብለዋል::

አክለውም ለግድቡ ግንባታ ገንዘብ ድጋፍ በሚያደርጉ ድርጅቶች ሳይቀር ከሦስት ጊዜ በላይ ጥናት ተደርጎበት ምንም ዓይነት አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሌለው መጀመሪያውኑ መረጋገጡን ጠቅሰው «ችግሩ ጥናት አሊያም የተፈጥሮ ሚዛን የማዛባት ጉዳይ አይደለም» በማለት በፍራንክሊን ሩዝቬልት አስተዳደር በአሜሪካን ኮሎራዶ የተገነባውን ሆቨር ግድብ በምሳሌነት ጠቅሰዋል:: ጠ/ሚኒስትሩ «ይህ ግድብ የተፈጥሮ ሚዛን በማዛባትና ሰብዓዊ ቀውስ በማስከተል ተወዳዳሪ የለውም ሆኖም አሜሪካዊያን ግድቡን ከመስራት ያገዳቸው ኃይል አልነበረም» ሲሉ ተከራክረዋል:: «እነ ሰርቫይቫል ኢንተርናሽናል ያኔ አልነበሩም» የሚሉት አቶ መለስ «ምዕራባውያን የሚያስፈልጋቸውን ግድብ ሰርተው እስኪያጠናቅቁ ነበር የሚጠብቁት» ብለዋል::

የሆነ ሆኖ በዚህ ባገባደድነው ዓመት ጊቤዎቹ አንኳር ርዕሶች ነበሩ:: በአግባቡ ተጠናቀው ሥራ ይጀምሩ እንጂ ትሩፋታቸው ከኢትዮጵያ አልፎ ለጎረቤት አገራትም እንደሚተርፉ ተነግሯል:: በርግጥም ይህ መሰሉን ፈተና ተቋቁመው የመብራት ፈረቃ ላማረረው ሕዝብ የብርሃን ተስፋዎች ይሆኑ ይሆን?

# «ኢሳት» - አወዛጋቢው የቴሌቪዥን ጣቢያ

«እኛ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) መስራቾች፣ በተባበሩት መንግስታት ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 19 ላይ የተቀመጠውን "ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት በማንኛ ውም መንገድ ሀሳቡን በነፃነት የመግለፅ፤መረጃዎችንና ሀሳቦችን በሁሉም የመገናኛ ብዙሐን ያለገደብ የማስተላለፍ ነጻነትና መብት አለው" የሚለውን መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት የምንቀበለው ብቻ ሳንሆን፤ይህንን መብት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለብን ከሚለው እምነታችን በመነሳት የቴሌቪዥን ጣቢያችን አንፀባራቂ መርህ ሆኖ እንዲቀጥል አበክረን እንንቀሳቀሳለን ከዚህም እምነታችን በመነሳት ይህን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን አቋቁመናል:: እምነታችንን ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጋችንን በተመለከተ ፍርዱን ለህዝብና ለታሪክ እንተዋለን» ይላል በድረ ገፁ ላይ የሰፈረው የቴሌቭዥን ጣቢያው ኤዲቶሪያል ፖሊሲ መግቢያ::

በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ነዋሪ በሆኑ ታዋቂ ኢትዮጵያውያን ተነሳሽነት እየተገባደደ ባለው የ2002 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ተቋቁሞ በዕለተ ዓርብ ግንቦት 6 ቀን 2002 ዓ.ም የሙከራ ስርጭቱን የጀመረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) በኤዲቶሪያል ፖሊሲው ላይ ከተዘረዘሩ ዓላማዎች ውስጥ «ዜጎች ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲያንፀባርቁ፣ ትክክለኛና ተአማኒ የሆነ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ እውነተኛ የመረጃ ፍሰት ለአንድ ነፃ አገር የማዕዘን ድንጋይ በመሆኑ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረገው ትግል የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል» የሚል ይገኝበታል::

ይህ የቴሌቪዥን ጣቢያ የሙከራ ስርጭት መጀመሩን ተከትሎ በአገር ውስጥና በውጭ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ የሳተላይት ዲሽ ገበያ በአንድ ሳምንት ውስጥ በእጥፍ እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል::

በግንቦት ወር መጨረሻ ለአውራምባ ታይምስ ቃለ ምልልስ የሰጡት የቴሌቭዥን ጣቢያው ቃል አቀባይ (እና ከመስራቾቹ አንዱ) የሆኑት አቶ አበበ በለው ጣቢያውን የማቋቋም ሀሳብ እንዴት እንደተጀመረ ሲያብራሩ



«ሲጀመር "ቴሌቪዥን እንክፈት!" የሚል ሀሳብ አይደለም የተነሳው ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ የሆነ ኢትዮጵያዊያን ለኢትዮጵያዊያን የሚገኙበት ሚዲያ በጣም ያስፈልጋል የሚል ነበር ይላሉ:: አቶ አበበ አያይዘውም «በአጠቃላይ ትክክለኛ ሚዲያ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ማግኘት ስላልተቻለ ይህ ችግር ነው ያወያየንና ያቀራረበን:: ታዲያ ምን ብናደርግ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ትክክለኛ መረጃ ሊያገኝ የሚችለው በእኛ አቅምስ ምን እናድርግ የሚል ሀሳብ በውይይት ዳበረ... እናም እንግዲህ እንዲህ እያለ ሁላችንም የሚያገናኝ አንድ ድርጅት ተፈጠረ» ብለዋል::

## የጣቢያው ባለቤቶች

ቃል አቀባዩ እንዳሉት የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ባለቤት የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብትና የዲሞክራሲ አራማጅ ግብረኃይል የተሰኘ ድርጅት ነው:: የቴሌቭዥን ጣቢያው የቦርድ አባላት ደግሞ:-

ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማሪያም - ሊቀመንበር
አቶ ግደይ ዘርዐጽዮን - ም/ሊቀመንበር
ሜሮን አህዱ - ዋና ጸሐፊ
ዶ/ር ኮንቲ ሙሳ - ረዳት ዋና ጸሐፊ
አቶ አበበ በለው - ቃል አቀባይ
አቶ ንአምን ዘለቀ- አባል
አቶ ሙሉጌታ ሉሌ - አባል
ሉሲት መስፍን - አባል
አቶ አበበ ገላው - አባል
አርቲስት ታማኝ በየነ - አባል
ዶ/ር ሽክስፒር ፈይሳ - አባል
ዶ/ር አዚዝ መሀመድ - አባል
አቶ ፍሬህይወት ሳሙኤል- አባል መሆናቸውን በጣቢያው የምስረታ ወቅት ይፋ የተደረገው የፕሬስ መግለጫ ያስረዳል::

የቴሌቭዥን ጣቢያውን ያቋቋሙ ግለሰቦች አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን ከያዘው አካል ጋር በተለያየ ወቅት ቅራኔ ውስጥ የገቡ፣ በሰብዓዊ መብት አያያዙ አጥብቀው የሚተቹት፤ የተወሰኑት የቴሌቪዥን ጣቢያው ማኔጅመንት አባላት ደግሞ ምርጫ 97ን ተከትሎ በተፈጠረው ውዝግብ ለእስር የተደረጉ አሁንም በሌሉበት የተፈረደባቸው በመሆኑ የቴሌቭዥን ጣቢያው ከሙከራ ስርጭቱ ጀምሮ በኢትዮጵያ መንግስት ዘንድ በጥርጣሬ አይን እንዲታይ ምክንያት ሆኗል- ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች::

የቴሌቭዥን ጣቢያው በኤዲቶሪያል ፖሊሲው ላይ ካሰፈረው «ፍፁም ገለልተኛ የመሆን መርህ» አንፃር እነዚህ ከኢህአዴግ ጋር ቅራኔ ውስጥ የገቡ የቦርድና የማኔጅመንት አባላት ገለልተኛ ሆነው ለማንም ሳይወግኑ ለመስራት ከባድ አይሆንባቸውም ወይ? የሚል ጥያቄ ከአውራምባ ታይምስ የቀረበላቸው የጣቢያው ቃል አቀባይ «ኢሳት የአንድን ፓርቲ አስተሳሰብ ብቻ ለይቶ የማይደግፍ የማያቀነቅን ነው ስንል የማናቸውም ፍልስፍና ወይም ፖሊሲ የማናቀነቅን እነሱ ብቻ ነጥረው መውጣት አለባቸው ብለን የማንሰብክ ነን ማለታችን ነው» ካሉ በኂላ «ለማንም አንወግንም ስንል ግን ከፖለቲካ ውጪ ነን ማለታችን አይደለም ከፖለቲካ ውጪ የሆነ ህይወት ያለ አይመስለኝም... በቴሌቪዥን ጣቢያው የሚሰሩ ግለሰቦች ያላቸው የተቃውሞ ጉዳይ የራሳቸው ጉዳይ ነው:: "መንግስትን የሚቃወም እዚህ ውስጥ አይቀጠር የኃላፊነት ቦታ አይያዝ" ማለት ግን አንችልም:: መንግስትን የሚደግፍ ሰው ካለ እና ሞራል ኖሮት አብሮን መስራት ከፈለገ የምንከላከልበት ምክንያት የለም» ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል::

## ውዝግቡ

የቴሌቭዥን ጣቢያው የመጀመሪያው የመረበሽ አደጋ የገጠመው የሙከራ ስርጭት በጀመረ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ነበር:: በወቅቱ ካልታወቀ አቅጣጫ ወደ ቻናሉ ሞገድ እንደሚለቀቅበት በመግለጽ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናክሮ እንደሚመለስ ባስታወቀው መሰረት ከሳምንታት በኂላ ፍሪኩዌንሲውን ቀይሮ ተመለሰ:: ሆኖም በድጋሚ ሌላ ተመሳሳይ ፈተና ገጠመው:: በዚህ ወቅት ይፋ የተደረገው መግለጫም በገደምዳሜ ካልሆነ በስተቀር ተጠያቂው የኢትዮጵያ መንግስት መሆኑን የሚገልጽ ሀረግ በመግለጫው አላካተተም ሆኖም በተመሳሳይ ፈተና ለሶስተኛ ጊዜ ሲቋረጥ ተጠያቂው የኢትዮጵያ መንግስት መሆኑን የሚያመለክቱ መረጃዎች እንዳሉት ይፋ አደረገ::

የጣቢያው ቃል አቀባይ የሆኑት አቶ አበበ በለው፤ ቃለምልልሳቸው በአውራምባ ታይምስ በታተመ በአራተኛው ቀን ኢትዮ ቻናል ጋዜጣ «አስተማማኝ» ያላቸው ምንጮቹን ዋቢ በማድረግ ይህ የቴሌቭዥን ጣቢያ በሻዕቢያና በግብጽ መንግስታት የገንዘብ ድጎማ እንደሚደረግለት አስታውቆ ነበር:: ጋዜጣው አቶ አበበ በቃለምልልሱ ወቅት ለአውራምባ ታይምስ የሰጧቸውን ምላሾች አንድ በአንድ በመንቀስ በፊለፊት ገጹ፣ በርዕሰ አንቀጹና በልዩ ዘገባ መልክ ለቴሌቭዥን ጣቢያው ሰፊ ሽፋን በመስጠት ተችቷል:: ከሦስት ሳምንት በፊት ስለ ቴሌቭዥን ጣቢያው አስተያየት እንዲሰጡ ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ መለስ ዜናዊ ጣቢያውን በተመለከተ ምንም አይነት አስተያየት መስጠት እንደማይፈልጉ መግለጻቸው ይታወሳል::

በእነዚህና በሌሎች ውዝግቦች ምክንያት የአውራምባ ታይምስ ዝግጅት ክፍል በዘንድሮው የአመቱ ጉልህ ክስተቶች ዳሰሳው ኢሳትን የአመቱ አወዛጋቢ የቴሌቭዥን ጣቢያ ሲል ሰይሞታል::



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# ዓመቱ በአክሳሪው የታሪክ ንግድ ውስጥ - ፪

በውብሸት ታዬ

በዓለም የስልጣኔ ታሪክ ውስጥ ቀደምት ስፍራ ከሚሰጣቸው አገራት አንዷ በሆነችው አገራችን ስለአክሱም ስልጣኔ የተዘገቡልን ድርሳናት በበቂ ሁኔታ ተደራጁ አይሁኑ እንጂ ክንዋኔዎቹን አስመልክቶ ያሉት መረጃዎች የሚፋለሱ አይደሉም:: ይህ እንደዘመናችን አቆጣጠር በመጀመሪያው መቶ ክ/ዘመን የጀመረ የስልጣኔ ታሪክ እስከ 7ኛው መቶ ክ/ዘመን ልዕልናውን ጠብቆ ከተጓዘ በኋላ በተለያዩ ተፅዕኖዎች መዳከም ጀምሮ በ8ኛው መቶ ክ/ዘመን ላይ ሙሉ ለሙሉ ከሰመ::

የታሪክ ተመራማሪዎች ከ7ኛው መቶ ክ/ዘመን እስከ 12ኛው መቶ ክ/ዘመን ባሉት 500 ዓመታት የሚታወቅ ምንምነገር የለም! ሲሉ ያረዱናል:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ባሕልና ታሪክ በአንድ መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር ብቻ ወስኖ ማዕከሉን በዚያ አከባቢ ያደረገው ስርወ መንግስት ሲከስም «ለ500 ዓመታት ምንም አይታወቅም::» ማለቱ ጥያቄ የሚያጭርና የራሱ አንድምታ ያለው በመሆኑ ጉዳዩን ለታሪክ ተመራማሪዎችና እንደሁኔታውም ለፖለቲካ ተንታኞች የምንተወው ቢሆንም የሚያስቆጭ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም::

የታሪክ ፀሐፍት «የጨለማው ዘመን /The dark age/ ሲሉ በሰየሙት በዚህ ረዥም ጊዜ ውስጥ በአከባቢው «ምን ተከናወነ?» የሚለውን ለመመለስ እየተደረጉ ያሉ የአርኪኦሎጂ ምርምሮችን ግኝት በከፍተኛ ጉጉት የሚጠባበቀው የዓለም ማሕበረሰብ በተለይም የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ ይገመታል:: እንደምሳሌነት ከላይ የተጠቀሰውን አነሳን እንጂ በተለያዩ ዘመናት፣ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በነበሩ ባሕላዊና ታሪካዊ ሁነቶች ላይ ያሉን በፅሁፍ የተጠናቀሩ መረጃዎች በጣም ጥቂት፣ በሌሎች ወገኖች /የውጭ ጸሃፍትና የባለታሪኩን ጥልቅ እሴቶች በዝርዝር የማያውቁ ወገኖች/ የተዘጋጁ ስለነበር ታሪካዊ ዋጋቸው ጥያቄ ላይ የሚወድቅ ነው:: በሌላ በኩል ግን ዘመናዊው የታሪክ አጠናን ስልት ይህን ክፍተት ሊሸፍነው ይችላል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል::

ከታሪክ ጠቀሜታ አንጻር ወደ 7ኛው መቶ ክ/ዘመን መለስ በማለት «ለምን? እንዴት?» እያልን በቁጭት እንጠይቅ እንጂ ባለንበት ዘመን ውስጥ ያውም ባለፉት ሃያ እና ሰላሳ ዓመታት ውስጥ የተከናወኑ ድርጊቶች እንኳ በተዛባና ጥንቃቄ በጎደለው መንገድ እየተዘገቡ ለንባብ በመብቃታቸው ትውልድ እያከሰሩ እንደሚገኙ ባለፈው ሳምንት ልዩ ቅኝታችን ምሳሌ በማጣቀስ መዳሰሳችን ይታወሳል::

በታሪክ ስም ሲነገድ ሁልጊዜ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ያተርፋል፤በዚያው ልክ ትውልድ ይከስራል:: ይህን አካሄድ ለማረምም ማሕበረሰቡ ንቁ እና በስነ አመክንዮ ተጠየቅ የሚሞግት መሆን እንዳለበት ይመከራል:: የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ባለባቸው አገራት በጽሁፍ አማካይነት የታሪክ መፋለስን የሚፈጥሩ ወገኖች በቀላሉ የሚጋለጡ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በዚሁ ዘርፍ ላይ የሙሉ ጊዜ ምርምር የሚያደርጉ ባለሙያዎች ስላሉ ዜጎቻቸው ከዚህ መሰሉ አደጋ የተጠበቁ ይሆናሉ:: ከዚህ እሳቤ በመነሳት ባለፈው ሳምንት የልዩ ቅኝት አምድ ዳሰሳችን ላይ ያነሳናቸውን ነጥቦች ተከትሎ ከበርካታ አንባብያን ገንቢ አስተያየቶችን ስናስተናግድ ሰንብተናል::

በተለይ በቅኝታችን የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ያነሳነው «አንድ ቀን ደግሞ እንዲህ ሆነላችሁ...» አይነት አቀራረብ ያለው «ሕይዎት በመንግስቱ ቤተ መንግስት» ፅሁፍ እንዳሳሰባቸው የገለፁልን ወገኖች ብዙ ናቸው:: በአስተያየቶቹ ላይ ከተነሱት ነጥቦች የተወሰኑት የኢትዮጵያውያንን የሞራል እሴት ወደጎን ባደረገ አገላለፅ ከገፅ 24-41 ብቻ በስርዓቱ ውስጥ የነበሩ ወገኖችን «መሐይማን፣... እንደጉንዳን እየተግተለተሉ፣...» ልዩ የጥበቃ ብርጌዱን «ቅልብ ሰራዊት» እና በመሳሰሉት ቃላት ሲገልጹ ዘረኝነት የተጠናወታቸው አንዳንድ 'ነጮች' እንኳ የተውትን ቀለምን መሰረት ያደረገ አመለካከት በማንጸባረቅ ፕሬዝዳንቱን «ጥቁር፣ ጥዝኩ» ሲሉ ማንቋሸሻቸው በሌሎች አጋጣሚዎች ሊደገም የማይገባው አካሄድ ነው ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል::

የቅኝታችን ዘውግ ያጠነጠነው በቀድሞው ስርዓት ወታደራዊና ፖለቲካዊ ክንውኖች ዙሪያ በተለያየ መጠን ተሳትፎ የነበራቸው ፀሐፊዎች /ሁሉም አይደሉም/ ለንባብ ባበቋቸው መፃሕፍት ላይ እንደነበር ይታወሳል:: በዛሬው የልዩ ዕትም ዝግጅታችን በዓመቱ ውስጥ ለንባብ ከበቁ መፃሕፍት ውስጥ በዋንኛነት አንዱን ብቻ በአጭሩ የምንቃኝ ሲሆን ከዚያ በፊት ግን የምናነሳው ነጥብ አለ::

በቀድሞው ስርዓት ዙሪያ የሚፃፉ መፃህፍትን አስመልክቶ በዚህ ዓመት ለአንባብያን ካደረስናቸው መረጃዎች ሁለቱ ፕ/ር መሳይ ከበደ በምርምር ላይ ተስርተው እያዘጋጁት የሚገኘው፣ የቀድሞው ፕሬዝዳንት ኮ/ል መንግስቱ ደግሞ በ17 ዓመቱ ስርዓተ መንግስታቸውና ተያያዥ ሁነቶች ላይ የፃፉት መፅሐፍ ይገኝብታል:: ሁለቱም መፅሐፍት እስካሁን ለንባብ ባይበቁም ይዘታቸውን ለማወቅ ግን ተችሏል::

በአሁኑ ወቅት በሰሜን አሜሪካ «ኦሃዮ» ግዛት በዴይተን ዩኒቨርሲቲ በማስተማር ላይ የሚገኙት ፕ/ር መሳይ ከበደ ከሁለት ወር በፊት ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ «Indeology and Elit Conflicts: Autopsy of the ethiopian Revolution» የሚል ርዕስ ያለው መፅሐፍ በማዘጋጀት ላይ መሆናቸውን መግለፃቸው ይታወሳል:: ፕ/ሩ በዚህ መፅሐፋቸው በመሬት ባለቤቱ ቡድን፣ በሲኒየር ወታደራዊ ኦፊሰሮች፣ በጁንየር ኦፊሰሮች፣ ብሔርን ማዕከል ባደረጉ ቡድኖች፣ በደርግ የተለያዩ አንጃዎች መካከል የነበረው በርካታ ገፅታ እንዲሁም የምሁራን አለመግባባቶች እንዴት ወደ ርዕዮተ ዓለም መካረር እንደሚያመሩና የመሳሰሉትን በጥልቀት እንደሚዳስስ ገልፀዋል:: ከያዝነው ቅኝት አንፃር አክሳሪ ወይስ «አትራፊ» የሚለውን በጊዜው እንደርስበታለን::

ሁለተኛው በኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም የተፃፈው ረቂቅ ነው:: ረቂቅ ፅሁፉን ያነበቡ ምንጮቻችን እንደገለፁት ኮ/ሉ በዚህ መፅሐፋቸው ራሳቸውን መከላከላቸው ባይቀርም በአንፃራዊ ሁኔታ ግልፅነት አንፀባርቀዋል የተባለ ሲሆን ከ1953ቱ የመለዮ ለባሾች መፈንቅለ መንግስት አንስቶ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ስለተከናወኑ አበይት ሁነቶች ዳስሰዋል:: መፅሐፉ በያዝነው ዓመት አጋማሽ ላይ ለንባብ ይበቃል ተብሎ ቢጠበቅም በአንዳንድ ቴክኒካል ጉዳዮች ሳይሳካ መቅረቱም ተጠቁሟል:: በዛሬው የልዩ እትም ቅኝታችን በዚህ ዓመት መጀመርያ ላይ የታተመውንና «ጄኔራሎቹ» የሚል ስያሜ የተሰጠውን መፅሀፍ በአጭሩ እንመለከታለን::

«ጄኔራሎቹ» የተፃፈው የወታደራዊ ደህንነት ባለሙያ እንደሆኑ በገለፁት ሻ/ል ኢዮብ አባተ መሆኑ ከመነሻው ትኩረት ይስባል:: ምክንያቱም በስርዓቱ ውስጥ የተከናወኑ ለሕዝብ ይፋ ያልሆኑ በርካታ ወታደራዊ ምስጢሮች የሚገኙ በመሆናቸው ነው:: ፀሐፊው የመፅሐፋቸው ዘውግ አድርገው የተነሱት የ1981ዱን በጄኔራል መኮንኖች የተካሄደ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራና ተያያዥ ጉዳዮች ሲሆን በክንውኑ ዙሪያ እስካሁን ከወጡት መረጃዎችና መደበኛ ባልሆነ የሃሳብ መለዋወጫ መንገድ ሲገለፁ ከነበሩት የተለየ መረጃ ለማግኘት የሚያነሳሳ ይሆናል:: እንዲሁም ደራሲው ይህ ሥራቸው የተሻለ መስራት ለሚፈልጉ ወገኖች የመንደርደሪያ ኃሳብ ይሰጣል ብለው እንደሚያምኑ ገልፀዋል::

## ስማ በለው -1

ሐሳቡ በመርሕ ደረጃ ሊበረታታ የሚገባው ሆኖ እናገኘዋለን:: ይሁንና ግን ፀሐፊው እንዳሉት በእርግጥም የመንደርደሪያ ሃሳብ ይሰጣል ወይ? ስንል እራሳቸው የተንደረደሩት ቀደም ሲል ለንባብ የበቁ የፅሁፍ መረጃዎችን በመቀጣጠል መሆኑን በራሳቸው አንደበት ይመሰክሩልናል:: አዲስ ዘመንን ሰርቶ አደርን ጨምሮ የተለያዩ ጋዜጦችን፣አምስት መጽሔቶችንና አስራ ሰባት መጻሕፍትን በዋቢነት ተጠቅመዋል:: ይህም የሚጠበቅና ማኛውም የታሪክ ጸሐፊ ሊከተለው የሚገባው አሰራር ነው:: - ጸሐፊው ይህን ያደረጉበትን ምክንያት ሲገልጹ ግን በአንድ ወጥ መፅሐፍ ተጠቃሎ ስላልቀረበ ወይም ተዘጋጅቶ ስላላየሁ ነው ይሉናል:: (ገጽ - 7)

ችግሩ የተለያዩ ጋዜጦች፣ መፅሔቶችና መፃሕፍት በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ያሰፈሯቸውን መረጃዎች በአንድ ወጥ ሥራ ማቅረቡ አይደለም:: በእነዚያ መፃሕፍት ውስጥ የተነገሩት ነገሮች ምን ያህል ተዓማኒ ናቸው? ይህንንስ ለማረጋገጥ ምን ተሰርቷል? የሚለው ነው:: እስኪ የተወሰኑ ነገሮችን እንመልከትና ወደዋናው ቅኝታችን እንመለሳለን::

ጋዜጠኛና ደራሲ ገነት አየለ በ1994 ዓ.ም ለንባብ ባበቃችው «የሌ/ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ትዝታዎች» ቁጥር 1 ከገፅ 346-351 ላይ በግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም ስለሆነው ኮ/ል መንግስቱን ጠይቄ የሰጡኝ ምላሽ በሚል ካሰፈሩት ውስጥ ቀጥሎ ያሉት አንኳር ነጥቦች ይገኛሉ::

'... አምስት ሰዓት ኬንያ ናይሮቢ ደረስኩ:: ...አራፕሞይን /የኬንያውን ፕሬዝዳንት/ ላነጋግር ነበር::... የፖሊስ ኮሚሽነሩን ላኩና ተቀበሉኝ:: አብረን ሻይ እየጠጣን አንድ መልዕክተኛ መጣና አንድ መልዕክት ቀስ ብሎ ነገራቸው::... በፈቃዴ ስልጣኔን መልቀቄን ከሳቸው አፍ ሰማሁ:: ... አዲስ አበባ ደወዬ ጄ/ል ተስፋዬን ላነጋግር እፈልጋለሁ አልኩ:: አልተቻለም::... በኬንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ስላልነበር ካውንስሉ መጥቶ አገኘኝ:: ... ሻለቃ ደመቀ ባንጃው «እኛ ወደአገራችን እንመለስ» አለኝ:: ለመመለስ ነጻ ናችሁ አልኳቸው::...'

በ«ጄኔራሎቹ» መጽሐፍ ከገፅ 287-291 እነዚህ ሃሳቦች አጻጻፋቸው ብቻ ቀየር ብሎ እንዲህ ይደገማሉ «... ከቀኑ አራት ሰዓት ተኩል [ከላይ ካየነው ሰላሳ ደቂቃ ተቀንሶለት] ናይሮቢ ኬንያ ደረሱ:: የፖሊስ ኮሚሽነሩ መጥቶ አነጋገራቸው::... ጥቂት ቆይቶ አንድ መልዕክተኛ (የፕሮቶኮል ሹማቸው) የቴሌግራም መልዕክት ለአራፕሞይ ሰጣቸው:: እሳቸውም ጉዳዩን ለባለቤቱ / ለመንግስቱ/ ነገሩ:: ... ኮ/ሉ አዲስ አበባ ጄ/ል ተስፋዬጋ ደወሉ::... በወቅቱ በኬንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር አልነበሩም:: ...ሻለቃ ባንጃው ወደአገሬ እመለሳለሁ አሉ:: ...ወዘተ...»

የዚህ አይነቱ ስማ በለው /cut and paste/ የሁለትዮሽ ጉዳት አለው:: የመጀመርያው የሚታወቁ ነገሮችን መደጋገም በተደራሲው ላይ የሚፈጥረው አሰልቺነት /ኢኮኖሚያዊ ስሌት ውስጥ ሳንገባ/ ሲሆን ሁለተኛው ግን በጥንቃቄ ልናየው የሚገባንን ጉን ይመለከታል::

ቀደም ሲል በተመለከትነው የገነት አየለ መፅሐፍ ውስጥ ኮ/ሉ በእርግጥ የተባለውን ነገር ሁሉ ተናግረውታል ብለን ብንቀበል እንኳ ሰውየው ራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ ወይም በሌሎች ግላዊ ምክንያቶች ሁነቶቹን አዛብተው ቢገልፁ በዚያ ንግግራቸው ላይ ተመስርቶ የማጣራት ሥራ ያልተሰራበት የታሪክ ዘገባ « የተሻለ ሥራ ለሚሰሩ በቂ መንደርደሪያ ለመስጠት» እንዴት ይውላል? አባባሉንም ክብደት ያሳጣዋል::

ለሌላ ሥራ በቂ መንደርደሪያ መረጃ ሊሆን ከሚችሉ አይነተኛ ምሳሌዎች አንዱ «አባቴ ያቺን ሰዓት» በሚል ርዕስ በደረጀ ደምሴ /በ1981ዱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ የተገደሉት የሜ/ጄ/ል ደምሴ ቡልቶ ልጅ/ በተዘጋጀው መፅሐፍ ከገፅ 290-375 ያለው የጄኔራሉን የጦር ሜዳ ውሎ ማስታዎሻዎች ሊጠቀስ ይችላል:: ይህ ቅኝት በሚዘጋጅበት ወቅት ያነጋገርናቸው አንድ የቀድሞ ጄኔራል መኮንን /ከ30 ዓመት በፊት ከጄ/ል ደምሴ ጋር በአንድ ቀን የብ/ጄኔራልነት ማዕረግ እንዳገኙ ገልፀውልናል/ እነዚያ የግል ማስታወሻዎች በወቅቱ በቀጠናው ስለነበረው ወታደራዊ ክንውን ማጥናት ለሚፈልጉ ወገኖች ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ጠቁመዋል::

«ከጉዳዩ ወታደራዊ መረጃነት አንጻር በዚህ መንገድ ማቅረቡ እንዴት ይታያል? የሚለውን ለጊዜው ብንተወው ከታሪካዊ ፋይዳው አንፃር ግን የግል ማስታወሻዎቹ እያንዳንዷ ገፅ አንዳንድ መፅሐፍ ሊወጣው ይችላል::» ብለዋል::

## ስማ በለው - 2

ወደ «ጀኔራሎቹ» ስንመለስ በ1981ዱ የመፈንቅለ መንግስት ክንውን ዙሪያ የአስመራውንና የአዲስ አበባውን በየፈርጁ የሚተርኩበት መንገድ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን:: በእርግጥ በ1981 ዓ.ም የተካሄደውን መፈንቅለ መንግስት አስመልክቶ በርካታ መፃሕፍት ተፅፈዋል:: ሜ/ጄ ሁሴን አሕመድ «መስዋዕትነት እና ፅናት» በሚል ርዕስ በ1997 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ለንባብ ባበቁት መፅሐፋቸው /ሌላ ጊዜ እንመለስበታለን/ በመፈንቅለ መንግስቱ ላይ የአይን እማኝነታቸውን አክለው ከገለፁበት አንስቶ፤ እስካሁን የጠቃቀስናቸው መፃህፍት በተለያየ መጠን ሄደውባቸዋል:: ከዚህ አንፃር ምን አዲስ ነገር እናገኝ ይሆን?» የሚለውን ፍለጋ ፍሬ አልባ የሚያደርጉብን ድግግሞሾች ከመኖራቸውም ባሻገር የስማ በለው ችግሩ እዚህ ላይም በእጅጉ ተንፀባርቆ ይታያል::

ምንም እንኳ ፀሐፊው የወታደራዊ ደህንነት ባለሙያ እንደነበሩ በመግቢያቸው ላይ የገለፁልን ቢሆንም አንዳንዶቹ መረጃዎች የተአማኒነት ዋጋቸውን ጥያቄ ላይ የሚጥል መገለጫ እናገኝባቸዋለን:: በተለይም በስልክ ልውውጦቹና በስበሰባ አጀንዳዎቹ ላይ ይታያል:: አሁንም በጣም የተወሰኑትን እንመልከት::

ተደረጉ ከተባሉት የስልክ ልውውጦች አንዱ:-

«ኮ/ል ተስፋዬ ለፕሬዝዳንቱ ልዩ ረዳት ስልክ ሲደውሉ ያነሳችው ልጅ... አለች:: ሻ/ል መንግስቱ ቀርበው ሲነጋገሩ...ሌላ ስልክ አቃቸለ»-ገጽ 108

«ጄ/ል መርዕድ ለጄ/ል ሰሎሞን ስልክ ደውለው...ሲሏቸው ጄ/ል ሰሎሞን እንዲህ ሲሉ መለሱ::...» - ገጽ 136

«ፕ/ት መንግስቱ የደረሳቸውን መልዕክት አንብበው እንደጨረሱ ከፍተኛ ቁጭት፣ብስጭትና መረበሽ በአንድ ጊዜ ተደበላለቀባቸው::...ስልክ ደውለው ... ጠ/ሚ/ር ፍቅረ ስላሴ ሲመልሱላቸው ...»እና የመሳሰሉትን የሁለት ወገን ምልልሶች እንዴት ሊያገኟቸው እንደቻሉ እንኳ የተለየ ማብራርያ ሳያቀርቡ ያስነብቡናል:: በከፍተኛ ጄኔራል መኮንኖች ስለተደረጉ ምስጢራዊ ስብሰባዎችም በተመሳሳይ አቀራረብ የንግግሮቹን ይዘት ቃል በቃል በማስፈር አስቀምጠዋቸዋል:: እያጠናቀቅነው ባለነው ዓመት ሌሎች ሥራዎችም ለንባብ በቅተዋል:: በቀጣዩ ሳምንት ከእነዚህ አንዳንዶቹንና ከልዩ የዝግጅት ክፍላችን ተጨማሪ ሰነዶች ጠቃሚ ያልናቸውን በመያዝ ቅኝታችንን እንቋጫለን::

> «ጄኔራሎቹ» የተፃፈው የወታደራዊ ደህንነት ባለሙያ እንደሆኑ በገለፁት ሻ/ል ኢዮብ አባተ መሆኑ ከመነሻው ትኩረት ይስባል:: ምክንያቱም በስርዓቱ ውስጥ የተከናወኑ ለሕዝብ ይፋ ያልሆኑ በርካታ ወታደራዊ ምስጢሮች የሚገኙ በመሆናቸው ነው::


ማስታወቂያ

## ታሳቅ የምስራች ለእንጉዳይ ሰልጣኞች በሙሉ

ጣዕም እንጉዳይ ማሠልጠኛ ማዕከል ለእንጉዳይ ሰልጣኞች በዘርፉ በተካኑ መምህራን ስልጠና በመስጠት፣ ዘርን በመሸጥና ካሰለጠናቸው ተማሪዎች የእንጉዳይ ምርትን ዳጎስ ባለ ገንዘብ እንቀበላለን:: ከዚህም በተጨማሪ በማህበር ተደራጅተው ለሚመጡ ሰልጣኞች በነፃ ስልጠና እንሰጣለን::

በዚህም መሰረት:-

| ምርትን | በኪሎ | ብር |
|---|---|---|
| አይስተር | 1 ኪሎ | 80 ብር |
| ሺታኪ | 1 ኪሎ | 100 ብር |
| በተን | 1 ኪሎ | 120 ብር ካሰለጠንናቸው ተማሪዎች |

እንቀበላለን::

ለበለጠ መረጃ ስልክ 0911 79 39 68
0920 84 57 09
0914 75 77 54

አድራሻ:- መገናኛ ቀበሌ 24 የነገው ሰው ት/ቤት
አለፍ ብሎ ዝሜ ህንፃ ቢሮ ቁጥር 10

C enima


ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# ሃይቲ፡- የዓመቱ አስከፊ የተፈጥሮ አደጋ ሰለባ

## ከስድስት ወራት በፊት

ከካረቢያን አገራት አንዷ የሆነችውን ሃይቲ፣ ከበርካታ የዓለም አገራት የተለየች የሚያደርጓት ታሪኮች ባለቤት ናት፡፡ ከላቲን አሜሪካ አገራት ከቅኝ አገዛዝ ነፃነቷን በመጀመሪያ ያወጀች አገር ናት፤ ከድህረ-ቅኝ አገዛዝ በኋላ በጥቁሮች የተመራ መንግስት በመጀመሪያ የታየውም በሃይቲ ነው፤ ከድህነት አልፎ ከድህነት ጠለል እጅግ በታች ናቸው ከሚባሉ የዓለም አገራት መካከል ከቀዳሚዎቹ ተርታ የምትሰለፍ የመጨረሻ ምስኪን አገር ናት፡፡

ይህችን አገር በጥር 4/ 2002 የመታትና በ200 ዓመታት ውስጥ ካጋጠሟት እጅግ የከፋው የመሬት መንቀጥቀጥ (በርዕደ መሬት መለኪያ 7.0 የተለካ)፣ የተፈጥሮ አስከፊ ገፅታን በጉልህ ያሳየ ነበር፡፡ የአገሪቱ መንግስት ባወጣው ሪፖርት ላይ ባስቀመጠው ግምት መሰረት በአደጋው 230 ሺህ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ 300 ሺህዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ቁጥራቸው ከአንድ ሚሊዬን የሚበልጡ ሰዎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፡፡ ሪፖርቱ ጨምሮ እንደገመተው፣ 250 ሺህ መኖሪያ ቤቶች እና 30 ሺህ የንግድ እንቅስቃሴዎች ይደረጉባቸው የነበሩ ሕንፃዎች ተደርምሰዋል ወይም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

እጅግ ከባድ ጉዳት በሃይቲ ዋና ከተማዋ - ፖርት-ኦ-ፕሪንስ - እና በከተማዋ አቅራቢያ ባሉ አካባቢዎች ርዕደ መሬቱ በመሰረታዊ ደረጃ ጉዳት አድርሷል፡፡ ትላልቅ ሕንፃዎች ወደፍርስራሽ ክምርነት ተለውጠዋል፤ ታሪክ ከሆኑ ሕንፃዎች መካከል የአገሪቱ ቤተ-መንግስት፣ ሕግ አውጭ ምክር ቤት ሕንፃ፣ የፓርት-ኦ-ፕሪንስ ካቴድራል እና የአገሪቱ ትልቁ እስር ቤት በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአደጋው ከሞቱ ግለሰቦች መካከል የፖርት-ኦ-ፕሪንስ ሊቀጳጳስ ጆሴፍ ሴርጌ ሚዬት፣ የአገሪቱ መንግስት ቀንደኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት መሪ ሚቻ ጋይላርድ እና መቀመጫውን በዋና ከተማዋ አድርጎ የነበረው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሃይቲ ተልዕኮ መስሪያ ቤት ሕንፃ በመደርመሱ ድርጅቱ ያጣቸው የተልዕኮው ዋና ኃላፊ ሂዱ አናቢ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ብዙ አገራት ለሃይቲ የእርዳታ እጃቸውን ዘርግተው ነበ፡፡ አብዛኞቹም የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት፣ የነፍስ አድንና የሕክምና ሰጭ ቡድኖችን፣ ኢንጂነሮችንና ድጋፍ ሰጭ የተባሉ ወታደሮቻቸውን በማሰማራት ተፈጥሮአዊ ርህራሄያቸውን አሳይተዋል፡፡ ሆኖም፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች መቋረጥ፣ የአየር፣ የምድርና የባሕር ትራንስፖርት መጨናነቆች፣ የሆስፒታሎችና የኤሌክትሪክ ኃይል ማሰራጫ ተቋማት መደርመስ እና ኃይል የማሰራጫ መስመሮች ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ እስከመሆን ደረጃ ደርሰው የነበረ በመሆኑ አፋጣኝ የነፍስ አድን እና የእርዳታ ጥረቶችን በእጅጉ ነበር ያስተጓጎሉት፡፡

ከቀውሱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ፈጣን ምላሽ ወዲያ ለተጎጂዎች እንዳይደርስ እንቅፋት የሆኑት እነዚህ እክሎች በርካት የእርዳታ ሰራተኞችና ከአደጋው የተረፉ ሰዎች መረር ያለ ቁጣቸውን እንዲያሰሙ ያደረጋቸው ነበር፡፡ የእርዳታው መዘግየት ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሰዎች የራሳቸውን እርምጃ እንዲወስዱ የገፋፋ ነበርና አልፎ አልፎ ዝርፊያዎችና ኃይል የተቀላቀለባቸው አመጾች ታይተዋል፡፡

የፖርት-ኦ-ፕሪንስ የመቃብር ሥፍራዎች በአስክሬኖች በመጨናነቃቸው የጅምላ መቃብሮች መጠቀም አማራጭ የሌለው አማራጭ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የመሬት መንቀጥቀጡ ያደረሰውን ጉዳት ቃላት የሚገልፁት አይደለም፡፡


## ከስድስት ወራት በኋላ

ከመሬት መንቀጥቀጡ ስድስት ወራት በኋላ የወጡ መረጃዎች እንደሚያስረዱት፣ 98 በመቶ ፍርስራሽ ከከተመዋ ለማንሳት ተችሏል፡፡ 1.6 ሚሊዬን ሰዎች አሁን ድረስ ራሳቸው በሰሯቸው ድንኳኖች፣ የተራድዖ ድርጅቶችና ለጋሽ አገራት በሰጧቸው ድጋፎች በቆሙ መጠለያዎች ኑሮን በመግፋት ላይ ይገኛሉ፡፡ በርካታ ቤት ንብረታቸውን በአደጋው የተነጠቁ ሰዎች ተቀያሪ መኖሪያ ቤት ሊሰራላቸው ቀርቶ በአሁኑ ወቅት የሚኖሩባቸው መጠለያ ድንኳኖች እንኳን እየፈረሱባቸው ይገኛል፡፡ ሁሉም መጠለያዎች ማለት ይቻላል የኤሌክትሪክ ኃይልና የንፁህ ውሃ አቅርቦቶች የሏቸውም፡፡

በጊዜያዊነት የተሰሩ ሆኖም ቋሚ በመሰሉ የመጠለያ ስፍራዎች የሚፈጸሙ ወንጀሎች እተበራከቱ መሆናቸውን ዘገባዎች ያመላክታሉ፡፡

ከርዕደ መሬቱ አምስት ወራት በኋላ ለተጎጂዎች በቂ እርዳታ የተሰበሰበ ሲሆን በግንቦት ወር ውስጥም ለእያንዳንዱ የተፈናቃይ ቤተሰብ 37 ሺህ ዶላር ቼክ ለመስጠት ያስቻለ የገንዘብ መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰብስቧል፡፡

▷ ማስታወቂያ ◁




# ነፍሳቸውን ይማር

**በዚህ እያገባደድን ባለነው 2002 ዓ.ም በአንድም ሆነ በሌላ መንግድ ሀገራቸውን ሲያገለግሉ ቆይተው በሞት የተለዩን ዜጎቻችን በሙሉ ነፍሳቸው በገነት ያርፍ ዘንድ ምኞታችን ነው፡፡ ሰናይት ግርማ ጥቂቶቹን እንዲህ ትዘክራለች፡፡**

## አርቲስት ኢያሱ በርሔ

በመቀሌ ከተማ 1949 ዓ.ም የተወለደው ጥበበኛው ኢያሱ በርሔ የእውቀትና የትምህርት ማዕዱን የቀሰመው በአፄ ዮሐንስ 4ኛ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነበር፡፡ በ1968 ዓ.ም የህወሓትን የትጥቅ ትግል የተቀላቀለው እያሱ በትግሉ ወቅት፣ ትግሉን የሚያነቃቁ ማህበራዊና ፖለቲካዊ፣ ባህላዊም ዜማዎችን በመድረስና በመዝፈን፣ እንዲሁም ሙዚቃዊ ድራማን በማስተዋወቅ ይታወቃል፡፡ በጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም በአላማጣ የጥምቀት ከተራ በዓል «የልማት ከተራ» የተዘጋጀበትን መድረክ ሲመራና ሲያስተባብር በነበረበት ወቅት ድንገት ራሱን ስቶ ለህልፈተ ሕይወት የበቃው በዚህ ዓመት ነበር፡፡

## ድምፃዊ ደረጀ ዱባለ

ድምፃዊ ደረጀ ዱባለ «ግዴለም ልቤ ይችላል» በሚለው ዘፈኑ የሚታወቅ ሲሆን ለበርካታ ዓመታት በብሔራዊ ቴአትር በድምፃዊነት አገልግሏል፡፡ ፈረንሳይ አገር ባጋጣሚ ሄዶ በነበረበት ወቅት ከጓደኛው ጋር ሆኖ ድንገት ይታመማል፡፡ ሆስፒታል ሄዶ ሲመረመር ከጭንቅላት ጋር የተገናኘ (ምንነቱ በደንብ ያልታወቀ) ህመም እንዳለበት ይነገረዋል፡፡ ከሆስፒታሉ ሳይወጣ ህክምና መከታተል እንዳለበት ስለተነገረው ህክምና ይጀምራል፡፡ ህመሙ ከጊዜ ወደጊዜ እየበረታበት ይመጣል፡፡ ለወራት ያህል በተገጠመለት መሣሪያ አመካኝነት ህይወቱ መቆየት ችሎ ነበር፡፡ መሣሪያው ከተነቀለ መሞቱ እርግጥ እንደሆነ የህክምና ዶክተሮቹ ስላወቁ በዚህ ሁኔታ እስከመቼ ይቀጥል? የሚል ጥያቄ ይፈጠራል፡፡ በመጨረሻም ባለቤቱ እና ልጁ ወደ ፈረንሳይ በማቅናት ያዩታል፡፡ በኋላም መሣሪያው ከተገጠመለት አካሉ ላይ በስምምነት ከተነቀለለት በኋላ በህይወት መቆየት የቻለው ለሁለት ቀናት ብቻ ነበር፡፡

## ድምፃዊት ማናልሞሽ ዲቦ

በሚያስረቀርቅ ድምጿ የኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ፣ ውበትን፣ ፍቅርን እንዲሁም «አትንኩብኝ» የምትላቸውን ኩሩ ሕዝቦች የምታሞካሽ የባሕል ሙዚቃ አቀንቃኝ ድምፃዊት ማናልሞሽ ዲቦ ህዳር 12 ቀን 2002 ዓ.ም ምሽት ላይ የዚህን ዓለም ስንክሳር ጥላ እስከወዲያኛው ማሸለቧ የብዙዎችን ልብ በሐዘን ሰብሮ ነበር፡፡

## ኮሎኔል ሳህሌ ደጋጎ

ኮሎኔል ሳህሌ ደጋጎ እድሜያቸውን በውል ባያውቁትም በ1923 ዓ.ም እንደተወለዱ ይገመታል፡፡ ይህ ከሆነ የሞቱት በ97 ዓመታቸው ነው ማለት ነው፡፡ የሙዚቃ ህይወታቸው የጀመረው በ1940 ዓ.ም በክብር ዘበኛ የሙዚቃ ቡድን ውስጥ ነው፡፡ ለሀገራችን ታላላቅ አንጋፋ ድምፃውያን ግጥምና ዜማዎች ደርሰዋል አቀናብረዋል፡፡ ጠያቂ እንደናፈቁ (በተለይ የሙያ ጓደኞቻቸውን) የሚያስፈልጋቸውን በቂ ህክምናም ሳያገኙ ይህችን ዓለም የተሰናበቷት በያዝነው ዓመት መጋቢት ወር መባቻ ላይ ነው፡፡

## አቶ ዘውዴ ነሲቡ

አቶ ዘውዴ ነሲቡ ከአባታቸው አቶ ነሲቡ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ወለተ ኢየሱስ በ1871 ዓ.ም በአንኮበር መወለዳቸው ይነገራል፡፡ ከ11 ዓመታቸው ጀምሮ የአፄ ምኒልክ አገልጋይ በመሆን ንጉሱ እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ በቤተ-መንግስት ውስጥ አገልግለዋል፡፡ አቶ ዘውዴ ነፍሳቸው ከስጋቸው እስከተለየበት ጊዜ ድረስ ኑሯቸውን በአንኮበር አድረገው ቆይተዋል፡፡

## አትሌት ደጀኔ ብርሃኑ

አትሌት ደጀኔ የከራይ ቤቶች ሯጭ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ በተካሄደ የሩጫ ወድድር ላይ በባዶ እግሩ በማሸነፍ ያስገረመው አትሌት ደጀኔ ብርሃኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ስም ካስጠሩ አትሌቶች ተርታ ይመደባል፡፡ የግል ማህደሩ 1.84 ሜትር ቁመት እንደነበረው ይጠቁማል፡፡ በ2000 ዓ.ም በአልጀርስ በተካሄደው የአፍሪካ የሩጫ ውድድር በ10 ሺህ ሜትር የብር ሜዳሊያ፤ በ2004 ሞናኮ ላይ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ የፍፃሜ ውድድር ላይ የብር ሜዳሊያ አምጥቷል፡፡ አትሌቱ ባለፈው ሳምንት በመኖሪያ ቤቱ ራሱን አጥፍቶ መሞቱ ተሰምቷል፡፡ 12:54.15 በ5 ሺህ ሜትር ፣ 27:12.22 በ10 ሺህ ሜትር፣ 02:08.46 በማራቶን የግል ምርጥ ሰዓቶቹ ነበሩ፡፡

## ረዳት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገበየሁ

በደቡብ ወሎ ወረኢሉ ከተማ ታህሳስ 18 ቀን 1957 ዓ.ም ረዳት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገበየሁ ተወለዱ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት የክፍሉ አባል ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በጣም በጥቂት ዓመታት ውስጥ ከአምስት በላይ ጥናታዊ የምርምር ፅሁፎችን፣ የተለያዩ የማስተማሪያ ፅሁፎች፣ በተለያዩ ጋዜጦችና መፅሔቶች ላይ የተለያዩ ሥነ-ፅሁፋዊ መጣጥፎችን በማሳተም ይታወቃሉ፡፡ ረዳት ፕ/ር ብርሃኑ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ለመያዝ ሁለት ወራት ሲቀራቸው በድንገተኛ ህመም ከዚህች ዓለም የተለዩት በዚሁ ዓመት ሐምሌ ወር መጀመሪያ ላይ ነበር፡፡

## የኮልፌው ዘግናኝ የትራፊክ አደጋ

ቅዳሜ ሐምሌ 24 ቀን 2002 ዓ.ም ጠዋት ላይ በኮልፌ 18 ማዞሪያ አካባቢ ኮንቴነር የጫነ ከባድ መኪና ብዙዎችን ለሞት የዳረገ ዘግናኝ አደጋ አደረሰ፡፡ በዚህ አጋደም ምክንያት 26 ሰዎች ህይወታቸው ማለፉንና 44 ሰዎች ከባድ እና ቀላል ጉዳት እንደደረሰባቸውም ታውቋል፡፡ በወቅቱም ክሬን በመጥፋቱ የተነሳ አንድ ሰው ለ5 ሰዓታት ያህል በአደጋው ውስጥ ሆኖ በህይወትና በሞት መካከል ሆኖ መቆየቱ አሳዛኝ ክስተት ነበር፡፡

## ጋዜጠኛ ደምሴ ጽጌ

ደምሴ ጽጌ ከጋዜጠኛነቱ ባሻገር «ፍለጋ» እና «ምትሃት» በተሰኙ ርዕሶች አጫጭር ልብ ወለዶችን እንዲሁም «ትንግርት» የተባለ የትርጉም ሥራ አሳትሟል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ ተነባቢነት ያለውን የዴል ካርኒጌን መጽሐፍ ከደራሲ ባሴ ሀብቴ ጋር በመተርጎም «ጡብታ ማር» በሚል ርእስ ለህትመት አብቅቷል፡፡ ጋዜጠኛ ደምሴ ያጋጠመውን የኩላሊት ህመም በሀገር ውስጥና ከአገር ውጭ ሲታከም ከቆየ በኋላ ባገባደድነው ዓመት አጋማሽ በመጋቢት ወር ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡

ለቤተሰቦቻቸው እና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው በሙሉ ከልብ የመነጨ መፅናናትን እየተመኘን ነፍስ ይማር እንላለን፡፡

ስለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# ብራና ማተሚያ ቤት የተቃዋሚ መሪዎችን ፎቶ የያዘን መፅሔት እንዳይታተም አገደ

በሐምራዊ ጀነራል ቢዝነስ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ስራ እየታተመች በየወሩ ለአንባቢያን የምትቀርበው ሐምራዊ መፅሔት መጪውን አዲስ አመት ምክንያት በማድረግ አርቲስቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ፖለቲከኞች ያስተላለፉትን መልእክት በመያዝ ወደ ብራና ማተሚያ ቤት ከገባች በኋላ በማተሚያ ቤቱ ኃላፊዎች «የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ስለተካተቱበት አናትምም» መባላቸውን የመፅሔቱ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ፍቃዱ ማህተመወርቅ ለአውራምባ ታይምስ ገለፁ::

በአገራችን በተለያየ ዘርፍ የተሰማሩ ታዋቂ ሰዎች የአዲስ አመት ምኞት እንዲያስተላልፉ መፅሔቷ ዕድል መስጠቷን ያስታወሱት አቶ ፍቃዱ በዚህም መሠረት ከተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች አቶ ስየ አብርሃና ዶ/ር መረራ ጉዲና ከመንግስት ደግሞ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ም/ኃላፊ የሆኑት አቶ ሽመልስ ከማልን መጋበዛቸውንና አቶ ሽመልስ አይመቸኝም በማለታቸው ማስተናገድ እንዳልተቻለ አስታውቀዋል::

አቶ ፍቃዱ በማተሚያ ቤት ያጋጠማቸውን ሁኔታ ሲገልፁ «ስራችንን አጠናቀን ባለፈው ረቡዕ የመፅሔቱን ይዘት ወደ ማተሚያ ቤቱ ከላክን በኋላ ኃላፊዎቹ የመፅሄቱን እያንዳንዱ ገጽ በማንበብ ተቃዋሚዎች ስለተካተቱበት አናስተናግድም የሚል ምላሽ ተሰጠን» ይላሉ::

ብራና ማተሚያ ቤት በኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ስር የሚገኝ ተቋም መሆኑን የገለፁት አቶ ፍቃዱ «በህገ መንግስቱ ገለልተኛ እንደሆነ የተነገረለት ተቋም የሚያስተዳድረው ማተሚያ ቤት ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚ የሚል ስሌት ውስጥ መግባቱ ያሳፍራል» ብለዋል::

በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አውራምባ ታይምስ የማተሚያ ቤቱ ስራ አስኪያጅ በስልክ ለማነጋገር ሞክሮ የስራ አስኪያጁ ፀሐፊ ወደ ፋብሪካ በመሄዳቸው ሲመለሱ ደውሉላቸው ያሉን ሲሆን ከሰአት በኋላ በድጋሚ የስልክ ጥሪ ስናደርግ ቢሮ ውስጥ እንደሌሉ ስለተገለጸልን አስተያታቸውን ማካተት አልተቻለም::

ከአንድ አመት በፊትም ዕንቁ መፅሄት በብራና ማተሚያ ቤት ተመሳሳይ ችግር የገጠማት ሲሆን አውራምባ ታይምስ መፅሄትም ተቃዋሚዎችን የሚመለከት ዘገባ በመያዟ ብራና ማተሚያ ቤት እንዳትታተም ማገዱ ይታወሳል::

ሐምራዊ መፅሄት በሌላ ማተሚያ ቤት ህትመት ተጠናቆ በዛሬው ዕለት ገበያ ላይ መሆኗን ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል::

# «የምንዛሪ ተመን ዝቅ ማለቱ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ያለውን ተወዳዳሪነት ያሻሽላል»

ብሔራዊ ባንክ

# «የምንዛሪ ተመኑ ኢንዱስትሪውንም ይጎዳዋል»

አቶ ተመስገን ዘውዴ

በሱራፍኤል ግርማ

ነሐሴ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በብሔራዊ ባንክ በተደረገው የብር የምንዛሪ ተመን ማስተካከያ መሰረት ብር ከአሜሪካን ዶላር ጋር ያለው የምንዛሪ ተመን ከ13.6262 ወደ 16.3514 ዝቅ እንዲል መደረጉ የሚታወቅ ነው::

ብሔራዊ ባንክ የማስተካከያው ዋና ዓላማዎች ካላቸው መካከል፣ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በአገር ውስጥ ገበያ ያላቸውን ተወዳዳሪነት ማሻሻል አንዱ ነው:: በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡት የኢኮኖሚ ባለሙያ አቶ ተመስገን ዘውዴ፣ « . . . በምን ዓይነት መልኩ አይተውት እንደሆነ አይገባኝም:: የዋጋ ግሽበቱ ሁሉንም ነው የሚጐዳው:: ለኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ እቃዎች ከውጭ የሚገቡ እንደመሆናቸው መጠን የብር የምንዛሪ ተመን ዝቅ እንዲል መደረጉ ኢንዱስትሪውንም ይጐዳል» በማለት ማሻሻያ የሚኖረውን አሉታዊ ጎን ገልፀዋል::

በዋና ዓላማነት ከተዘረዘሩት ሌሎች ነጥቦች ውስጥ «በሀዋላና አገልግሎቱ ዘርፍ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ፍሰት ማጠናከር» የሚለው ተካቷል:: ከዚህም እሳቤ ጋር እንደማይስማሙ የሚገልፁት የኢኮኖሚ ባለሙያው፣ ዓላማው «ቁንፅል አመለካከት» መሆኑን ጠቅሰዋል፤ «ገና ለገና ጥቂት የሕብረተሰብ ክፍል ሀዋላ ይጠቀማል ተብሎ ብዙኃኑን መጉዳት ተገቢ አይደለም» ብለውም ተችተውታል::

የተደረገው ማሻሻያ የዋጋ ንረት እንዲባባስ አያደርግም የሚለው የብሔራዊ ባንክ መግለጫ «ትክክል አይደለም» እንዳልሆነ ያስገነዘቡት ባለሙያው፣ «መንግስት ቢያምን ባያምንም፣ አሁን ያለነው በዋጋ ግሽበት አዙሪት ውስጥ ነው:: በዚህ ወቅት ላይ የገንዘብ መውደቅ የሸቀጦችን ዋጋ በማናር ቀውስ ይፈጥራል:: ሁኔታው በቶሎ ካልተስተካከለ በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በጀርመን ተከስቶ ሰዎች ገንዘብ በዘንቢል ተሸክመው ጥቂት ዕቃ ብቻ እንዲገዙ ያስገደዳቸውን አይነት ግሽበት መፈጠሩ አይቀርም» ብለዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ከረቡዕ ጀምሮ የአንድ የአሜሪካ ዶላር የምንዛሪ ዋጋ 16.35 ብር ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በሸቀጦች ላይ የዋጋ ጭማሪ መከሰቱን ነጋዴዎችና ሸማቾች ገልፀዋል:: ጭማሪው ከታየባቸውና ከውጪ ከሚገቡ ዕቃዎች መካከል ከፍተኛ የዋጋ ለውጥ ያሳዩት የኤሌክትሮኒክስ ምርቶች ናቸው:: መርካቶ አካባቢ የቴሌቭዥንና የመሰል እቃዎች ነጋዴ የሆነ አንድ ወጣት ለአውራምባ ታይምስ እንደገለፀው፣ በቴሌቪዥን ላይ በሁለት ቀናት ውስጥ ብቻ የሶስት መቶ ብር ጭማሪ ታይቷል:: አዲስ ብሉይ የተባሉ ነጋዴም በበኩላቸው ተፈላጊነቱ የጨመረው ዲሽ የ300 ብር ጭማሪ በማሳየት በአሁኑ ሰዓት አንድ ዲሽ ዋጋው 1810 ብር መድረሱን ተናግረዋል::

አስተያየታቸውን ከሰጡን ሸማቾች መካከል አንዷ የሆኑት ወ/ሮ ፌቨን ሰሎሞን ማሻሻያውን ተከትሎ በዕቃዎች ላይ ጭማሪ ማጋጠሙ አዲስ ባይሆንም «በአንድ ጊዜ የበርካታ መቶ ብሮች ጭማሪ ግን ግራ አጋቢ ነው» ብለዋል::

### ከመስከረም 1/2003 ጀምሮ የአንድ ብር ሳንቲሞች ሥራ ላይ ይውላሉ

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ታትመው በሕጋዊ የመገበያያ ገንዘብነት በማገልገል ላይ ካለው የባለአንድ ብር የወረቀት ገንዘብ ጐን ለጐን፣ ከመስከረም 1 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የሳንቲም አንድ ብር በስራ ላይ እንደሚውል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስታወቀ::

የወረቀት ገንዘብ አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል የሚጠቀምበት በመሆኑ የስርጭት ዝውውሩና መጠኑም በፍጥነት እያደገ ከመሆኑ አኳያ የአልግሎት ዕድሜው አጭር እንደሆነ ያስታወቀው ብሔራዊ ባንክ፣ ከዚህም የተነሳ አገሪቱ ገንዘቡን ለማሳተም፣ ለማስቀመጥ፣ ለመምረጥ፣ ለማጓጓዝ እና ለማስወገድ የምታወጣው ውጪ ከፍተኛ በመሆኑ እና ሕብረተሰቡ ንፁህና በደህና ሁኔታ ያለን ገንዘብ ለመጠቀም ያለውን ፍላጎት ለማርካት የባለአንድ ብር ሳንቲም በዝውውር ላይ እንዲውል ማድረግ ማስፈለጉን ገልጿል::

ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 5/1/፣18/2/ እና 27/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የባለአንድ ብር ሳንቲም አስቀርጾ ከመስከረም 1 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ እንደሚያውለው ገልጾ፣ አሁን በዝውውር ላይ ከሚገኘው የባለአንድ ብር የወረቀት ገንዘብ ጋር ጐን ለጐን አገልግሎት የሚሰጥ፣ ላምጭው እንዲከፈል ሕግ የሚያስገድድ የኢትዮጵያ ገንዘብ በመሆኑ ሕብረተሰቡ የአንድ ብር ሳንቲሙን እንደሌሎች የሀገሪቱ ገንዘቦች ሁሉ እንዲገለገልበት አሳስቧል::



በመቅደስ ፍ...
tigi.vi...

# «አንቺ ...የዓመቱ ምርጥ ሴት!»

ይህ እያጠናቀቅነው ያለነው 2002 ዓ.ም በ2001 ዓ.ም መጨረሻ ላይ «ይህን እንሰራለን» ብለን ቃል የገባንለት ዓመት ነው:: በዚህ ዓመት ውስጥ ስለሴቶች በተለያዩ ሚዲያዎች ብዙ ተብሏል:: መንግስትም እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ብዙ ነገር እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል:: ያ ምን ያህል ውጤታማ ሆኗል? የዚህን የ2002ን ዓመት ድክመት ለ2003 ላንደግም ቃል ገብተን እቅዳችንን እንጀምር::

«አውራምባ ታይምስ» ጋዜጣ «ሴቶችን በተመለከተ» የሚወጡ ጽሁፎችን ማስተናገድ ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ ያሉትን ህብረተሰቡ በድጋሚ ቢያያቸው ይጠቅማሉ ያልናቸውን እንደሚከተለው ከልሰን አቅርበነዋል::

## ከልማድ ቀንበር ነፃ መውጣት

ሴቶች በፖለቲካ ተሳትፎአቸው ደካማዎች ናቸው ብዬ መደምደም ባልችልም ቢሳተፉ እንኳ ተሳትፎአቸው በፍራቻ የተመላ ነው:: ለ2002ቱ ምርጫ ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ በነበረበት ወቅት የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር ቢያደርጉም የሴቶች በመድረኩ ላይ አለመታየት አሳፋሪ ነገር ነበር:: በ2008ቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ወቅት ሸንጣቸውን ገትረው ይሞግቱ እንደነበሩት እንደነ ሳራ ፖሊንና የአሁኗ የውጭ ጉዳይ ምኒስትር ሂላሪ ክሊንተን አይነት ጠንካራ ሴት ፖለቲከኞች ኢትዮጵያ ያስፈልጋታል::

## የይስሙላ ድጋፍና የሞራል ንግድ

አገራችን ካላት የህዝብ መጠን 50 በመቶ ያህሉ ሴቶች መሆናቸው እሙን ቢሆንም በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በተለያዩ ተፅዕኖዎች ስር ከመውደቅ አልዳኑም:: በዚህ ሊያልቅ ቀናቶች በቀሩት ዓመት ውስጥ በሴቶች መብት ጉዳይ ብዙ ነገሮች ተብለዋል:: የሚባለውን ያህል ውጤት ተገኝቷል? መንግስትን ማቆለጳጰስ ትተው በሃሳብ የበላይነትን ሊፈትኑ የሚችሉ ሴቶችን ለምን አልተመለከትንም? ስለሌሉ ነው? እየተሰበከ ያለው ለመንፈስ ልዕልና የሚያበቃ ሳይሆን ከንቱ የሞራል ንግድ ስለሆነ እንጂ::

## ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ

በዚህ እያጠናቀቅን ባለነው ዓመት «እናት ለምን ትሙት» በሚል ሃሳብ የተመሰረቱ ብዙ ማስታወቂያዎች ተሰቅለዋል:: በወሊድ ምክንያት የሚደርስ አደጋ ከግል ይልቅ የመንግስት የህክምና ተቋማት ላይ ይበረታል:: ከፊሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የመንግስት የህክምና ተቋማትን ሲጠቀም ግድ ይላል:: በመንግስት ተቋማቱ የሚታየው ቸልተኛነት ደግሞ ለእናቶች ሞት እንደዋነኛ ተጠያቂነት ይቆጠራል:: ትውልድ ትውልድን መተካት አያቆምምና መጭውን ዓመት በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ ሴቶችን ቁጥር አሁን ካለንበት ዓመት ይቀንስ ዘንድ የሚመለከታቸው ተቋማትና ወገኖች ከልብ ኃላፊነታቸውን ይወጡ::

## የትውልዱ መሰረተ የሚቀረፅባቸው መቼቶች

አንድን ትውልድ ለመቅረጽ የመጀመሪያው መነሻ ቤተሰብ እንደሆነ ሁሉ የሴት ልጅ ጫናም ከቤተሰብ የሚጀምር ይመስለኛል:: አንድን ወላጅ ልጅህ/ሽ ለምን ተገረዘች ብለን ብንጠይቅ መልሳቸው «እቃ ትሰብራለች፣ ለባሏ አትታዘዝም፣ ቀለብላባ ትሆናለች...» ነው:: ይህ በማስረጃ ያልተረጋገጠና ኋላቀርና ጎጂ ሃሳብ እውነታው የት ድረስ ነው?

ሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ልጆች ያሏቸው ወላጆችን ብንወስድ ቤተሰብ ለነሱ የሚያቀርበው ስጦታ ይገርማል:: ለሴቷ አሻንጉሊት ለወንዱ ሽጉጥ! ያ በራሱ ወንዱን የበላይነት እንዲሰማው እና ለአመፅኝነት እንዲዘጋጅ የሚያደርገው ነው ብዬ አስባለሁ:: ለቀጣዩ ጊዜ የምንቀርጸው ትውልድ ከዚህ የፀዳ ይሁን::

## ሁላችንም «እምቢ!» የምንለው

«ሴት ልጅ እንደ ዝምድና ማጠናከሪያና እንደንግድ ለምን ትቆጠራለች?» የሚለው አንዱ ጥያቄዬ ነው:: ዘመን ዘመንን ቢተካም ስልጣኔ ስልጣኔን ቢተካም ያልተለወጠ ነገር ነው - የሴት ልጅ ንግድ:: በአንዳንድ ገጠራማ አካባቢዎች ሴት ልጅ ለባሏ ጥሎሽ የምትሰጥበት አጋጣሚ ስላለ ሴት የወለደ «ጉድ» እንደወለደ ተደርጎ ይታሰባል:: ወደ መሃል አዲስ አበባ ስንመጣስ? ከአንድ «ጥሩ» ከተባለ ቤተሰብ የተገኘች ሴት ልጅም ብትሆን ለንግድ ትቀርባለች:: እድሜ ለአባቷ! እሱ የተቀመጠበት ወንበር ቀዝቃዛ ከሆነ የሞቀ ወንበር ስለሚያስፈልገው ብቻ ልጁ ትሸጣለች:: «እምቢ» ካለች ልክ እንደገጠሯ ሴት በግድ የሚሆን ነገር የለም:: «ምነው ልጄ ህይወቴን ሙሉ ላንቺ ኖሬ?» የቤተሰብን ሃዘን ለመቀበል ድፍረት የላትምና ትሸጣለች:::: ይህ አይነቱ ዘመናዊ ባርነት ሊታሰብበት የሚገባ ነገር ነው::

## የነገውን ትውልድ ስናስብ

አሁን ባለንበት በ2002 ዓ.ም «መኃልየ መኃልይ ዘቼቺኒያ» «ሰዓት እላፊ» እና «ወሲባዊ ውስልትና ዘአዲስ አበባ» የተሰኙ መጽሐፎች ለንባብ በቅተዋል:: መጽሃፍ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ዘላቂ ሃብት በመሆኑ መጪው ትውልድ የባለፈውን ትውልድ የሚያይበት መስታወት እንዲሁም መጪው ትውልድ ራሱን ካለፈው ትውልድ ጋር የሚያነፃጽርበት ነው:: አንዳንዶቹ ግን ሴትን ልጅ በተቃራኒው እንድንገነዘባት የሚያደርጉ ሆነው ይነበባሉ:: ከላይ የገለፅኳቸው አይነት ጠቀሜታቸው ሳይሆን «አፈንጋጭነታቸው» የጎላ መጽሃፍት ቢታቀቡ የሚል አስተያየት የእኔ ብቻ እንዳልሆነ እተማመናለሁ::

## በህይወት ውስጥ ቀላል ነገር የለም

ሴት ሆይ! የመልካም ነገርም የመጥፎ ነገርም ሱስ እንዳለው ልብ ብለሻል? እና ዛሬ በወጣትነት እድሜሽ በሃብቱ ሊያማልልሽ ይችላል ጓደኞችሽ ከትምህርት ቤት ወደ ቤት በእግራቸው ሲጓዙ አንቺ በዓላማ አናጣቢው የመኪና መስኮት አሻግረሽ ስትመለከቻቸው የበለጥሻቸው እና የተወደድሽ መስሎ ሊሰማሽ ይችላል:: ነገር ግን አስተውሎ የተራመደ ነው ብዙ ርቀትን የሚጓዘው እንደሚባለው በህይወት ውስጥ ቀላል ነገር የለም፣ ዛሬ የበራልሽ መስሎ የታየሽ መንገድ ነገ በጭለማ ይሞላልና::

## አስተዋዮች የሚሉትን ማድመጥ

በሞቀው የምሽት ብርሃን ላይ ያለልብስ የቆመች የምትመስል ሴት ማስተዋል የተለመደ ሆኗል:: ሴቶች እህቶቻችንን ለዚህ ህይወት የጋበዛቸው ነገር ምንድነው? ብለን መላ ምቶችን አስቀምጠናል:: ገንዘብ አጥተው ነው፣ ቅንጦት ነው፣ ቁጥጥር ጠልታ ነው... የሚሉትን ነጥቦች አንስተናል:: ምንም ይሁን ምን ግን ክብራቸው ተነጥቋል:: ሚዲያዎችም የእነሱን ችግር አድምጦ ለህዝብ ማሰማት ብቻ መፍትሄ ሊሆን አይችልምና ከዚህ የበለጠ ነገር ይደረግ::

ላንቺ ግን አስተዋዮች እንዲህ ይላሉ:: «የጎዳናው አታላይ ህይወት የሚቀመው ዛሬ አንቺ ስትወስኚ ነው:: ዛሬም አልረፈደም:: አሁን ላይ ምንም የማይመስልሽ የምሽት ጉዞሽ ትርፉ አመድ ነውና አስቢበት»

## ትማራለች? እንግዲያውስ ...

ወንድ የቤት ሰራተኛ ያውቃሉ? በፍፁም:: ቢኖርም የጣታችንን ቁጥር እንኳ ለመሙላታቸው እጠራጠራለሁ:: ይህ በሴቶች ላይ የወደቀው ኃላፊነት በአሰሪዎቻቸው ቀልሎ የሚታይበት ነገር አሳፋሪ ነው:: እንዲሁም ሰራተኛዋ እንዳትማር የሚደረግ የአሰሪዎች ተቃውሞም ራስ ወዳድነት ነው ባይ ነኝ:: በቤታችሁ ያለችው ሰራተኛ ትማራለች? ካልተማረች መጪው ዓመት ለእሷ ብሩህ ይሆን ዘንድ ብዕርን ከወረቀት የምታውልበትን እድል ፍጠሩላት::

## ትዳራችሁ እንዲቆይ

የጋብቻ አማካሪ አም ጌሪ ኒውማንን በማጣቀስ የቀረበው ይህ ጽሁፍ ትዳራችሁ እንዲቆይ አንቺ ለኑሮሽ ማበርከት ያለብሽን ነገር ያሳያል:: ያንቺም ሆነ የእሱ ቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ሁለታችሁንም ሊፈትን አፍገባም እንዲሁም በወሲብ መጣጣም ብቻ ትዳራችን ይቆያል በለሽም አታስቢ:: ያ ብቻውን የትም አይደርስምና ትዳርሽ እንዲቆይ ያንቺ በብልሃት የተሞላ አካሄድ ወሳኝነት አለው::

## አንተ ራስ እሷ አንገት ...ታዲያ ምን አለበት?

እሷ ከእሱ በእድሜ ልትበልጥ ትችላለች፣ የስራ መደቧም ከእሱ ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል እንዲሁም እሷ የበለጠ ተከፋይም ልትሆንም ትችላለች:: ያ በሁለታችሁ ግንኙነት ምን ለውጥ ያመጣል? አንዳንዶች ግን እነኚህ ነገሮች መሃከላቸው ካሉ ፍፁም አይቀበሉትም:: የኑሯችሁ በእቅድ አለመሞላት ሊለያችሁ ይችላል እንጂ ከላይ የተጠቀሱት ነገር ሁለታችሁ ማሃል ለውጥ ሊያመጡ እንደማይችሉ ተገንዝባችሁ የመጪው ዓመት እቅዳችሁን ዛሬ ጀምሩት::

## በሷ ልብ እንድትቆይ

አንተ በእሷ ልብ እንድትቆይ ቢሊየነር ወይም መንዛሪ መሆን የለብህም:: ሴቶች በተለየ መንገድ ነው ልባቸው ውስጥ የሚያቆዩህ:: አንተን የሚያስቡህ እኮ በአሳቢነት ነው::: አንተ ትዝ ስትላት ለሷ ቅንነትህ ተንከባካቢነትህ ነው ትዝ ሊላት የሚገባው:: ለሷ በመንዛሪነትህ እንድትወድህ ከሆነ እሷ ስለብርህ ብቻ ስታስብ ትዝ እንድትላት ይሆናልና::

## በሱ ልብ እንድትቆዪ

ጭቅጭቅ፣ ፈተና ወይም እሱን አለማመን በእሱ ልብ ቁጭ እንድትይ የሚያደርጉ ነገሮች አይደሉም:: አንቺ በአስጨናቂ ሁኔታም ስለተከታተልሽው እሱን ከምንም ነገር አትመልሽውም:: እንዲሁም አንድን ነገር ከሱ ብቻ በመጠበቅ አሰልቺ ሴት አትሁኚ:: ያንቺም ሆነ የሱ ለራሳችሁ ትልቅ ግምት እና ክብር መስጠት ከጎናችሁ ላለው ሰው ትልቅ ግምት እንድትሰጡ የሚያደርገው:: አንቺ በሱ እሱ ባንቺ ልብ ውስጥ እንድትቆዩ ይረዳልና::

## የዓመቱ ምርጥ ሴት

በህይወት ውስጥ ስንት ፈተናዎች አሉ መሰላችሁ!? ጾታዊ ልዩነትን በተመለከተ ደግሞ የእሷ ይብሳል:: የእሷ ጫና የእኔ ከሚሏት ከቤተሰቦቿ ነው የሚጀምረው:: ያን ብትቋቋመውም ከህብረተሰቡ የሚደርስባት ተፅዕኖ በዚህ አያበቃም:: ነገር ግን ለአላማዋ ወደኋላ የምትል ሴት አይደለችም:: የእነሱ እሷን መንቀፍ ጎትቶ ሊያስቀራትም አይችልም:: ጥንካሬዋ ምን ድረስ እንደሆነ ታሳያቸዋለች:: ለእነሱ ጉንተላ ጊዜ ሳትሰጥ ያሰበችውን መንገድ ዝም ብላ ትቀጥለዋለች:: በሚገርምና በአስደናቂ ውጤትም አልፋ ታሳያቸዋለች - አሳይታቸውማለች:: እንደሷ ይሄን ትዕግስት አልባ መንገድ ማን ይወጣዋል? እንደእሷ ለቆመለት ዓላማ ማን ይፀናል?

አመት ዓመትን ይተካል:: ስለዚህ «የሴቶች የጥንካሬ ብቃት» በተነሳ ቁጥር ይሄን ሁሉ የተቋቋመችው ሴት ለሁላችንም በየዓመቱ «የዓመቱ ምርጥ ሴት» ናት::

# የተለያዩ የግል ኮሌጆች ተማሪዎቻቸውን በማስመረቅ ላይ ይገኛሉ

### የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂና ንግድ ሥራ ኮሌጅ

የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂና ንግድ ሥራ ኮሌጅ ነሐሴ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ከዘጠኝ መቶ በላይ ተማሪዎችን በዲግሪና በዲፕሎማ ያስመርቃል:: የኮሌጁ ፕሬዝዳንት አቶ አህመድ ኑሪ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ኮሌጁ ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች የሚያስመርቀው ለ7ኛ ጊዜ ሲሆን ከተመራቂዎቹ ውስጥም የሴቶች ቁጥር ይበልጣል:: ከተመራቂዎቹ መካከል አንድ መቶ ለሚሆኑት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነፃ የትምህርት ዕድል የተሰጠ ሲሆን በሚቀጥለው ዓመት ከ2000 ተማሪዎች በላይ ለማስመረቅ ዕቅድ ይዟል:: በኮሌጁ ቅጥር ግቢ በሚካሔደው የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ላይ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት እንደሚገኙ ተገልፅዋል::

### አራዳ ጊዮርጊስ ሜዲካል ኮሌጅ

አራዳ ጊዮርጊስ ሜዲካል ኮሌጅ ነሐሴ 29 ቀን 2002 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በጤና ሳይንስ በዲፕሎማ ፕሮግራም ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች በአዲስ አበባ ቲያትርና ባህል አዳራሽ በደመቀ ሥነ-ሥርዓት ያስመርቃል:: በዕለቱ 182 ተማሪዎችን በክሊኒካል ነርሲንግ እና 60 ተማሪዎችን በሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ ያስመርቃል:: እንዲሁም ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ለሚገኝ እና ከፍለው መማር ለማይችሉ 20 ተማሪዎች ነፃ የትምህርት እድል በመስጠት ለማህበረሰቡ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ መሆኑን የኮሌጁ ፕሬዚደንት ዶ/ር ነጋ ገ/ሚካኤል ገልጸዋል::

### አየር ጤና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ

አየር ጤና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለሦስት ዓመት በክሊኒካል ነርስ፣ በላቦራቶሪ ቴክኖሎጂ እና በፋርማሲ ቴክኒሽያን በደረጃ 4 መርሐ ግብር ያሰለጠናቸውን 104 ተማሪዎች ነሐሴ 30 ቀን 2002 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሑሑ አዳራሽ በድምቀት ያስመርቃል:: ኮሌጁ በ1997 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን እስካሁን ባለው የሥራ ሂደት የአሁኖቹን ተመራቂዎች ጨምሮ 275 ተማሪዎችን ደረጃው በሚፈልገው ብቃት እና ክህሎት ያስመረቀ ሲሆን በቀጣይም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በጤና ኤክስቴንሽን በደረጃ 3 እና 4 አዲስ ሥልጠና በተጨማሪ የሚከፍት መሆኑን የኮሌጁ ፕሬዚደንት አቶ ምህረቱ ቁሜ ገልፀው ተቋሙ 12 ወንዶች 21 ሴቶች በድምሩ 33 ተማሪዎችን በነፃ እና የግማሽ ክፍያ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ማድረጉን አስታውቀዋል:: በእለቱ የቴክኒክ እና ሙያ ሥራ ኃላፊዎች እና የተጠሩ የክብር እንግዶች እንደሚገኙ ተገልፅዋል::

### ትሮፒካል ኮሌጅ ኦፍ ሜድሰን

ትሮፒካል ኮሌጅ ኦፍ ሜድሰን በሜዲካል ላቦራቶሪ፣ በፋርማሲና በክሊኒካል ነርሲንግ በዲፕሎማ፣ በተጨማሪም ቢ.ኤስ.ሲ ነርስ እና የጤና መኮንኖችን በዲግሪ ሐሙስ ነሐሴ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ያስመረቀ ሲሆን ከተመራቂዎቹ መካከል በቢ.ኤስ.ሲ ዲግሪ 14፣ በዲፕሎማ ደግሞ በሜዲካል ላቦራቶሪ 48፣ በፋርማሲ 55፣ በክሊኒካል ነርሲንግ 179 በድምሩ 296 ወጣቶችን ማሰልጠኑን ገልጿል ኮሌጁ በየዓመቱ ከፍለው ለመማር አቅም የሚያጥራቸውን ወጣቶች እየተቀበለ ነፃ የትምህርት ዕድል የሚሰጥ ሲሆን ዘንድሮም 35 ተመራቂዎች የዕድሉ ተጠቃሚዎች መሆናቸውን የኮሌጁ ፕሬዚደንት አቶ መዝገቡ ውበቴ ገልጸዋል::

### አድማስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ

አድማስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አዲስ አበባ ባሉ ካምፓሶቹ በደረጃ 3 እና 4 መርሐ ግብር በድግሪ ፕሮግራም ያሰለጠናቸውን 1864 ተማሪዎች በ6 ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ልደት አዳራሽ በዛሬው ዕለት ያስመርቃል::

### ዳሎል ኮሌጅ

ዳሎል ኮሌጅ ለአምስተኛ ዙር በዲፕሎማ እና በሰርተፍኬት ያሰለጠናቸውን 257 ተማሪዎች በገነት ሆቴል አዳራሽ ነሐሴ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ያስመርቃል::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ልዩ ዕትም

# እጣ ፈንታው አሳዛኝ የሆነው የሚዲያ ተቋም

# አዲስ ነገር

በአቤል ዓለማየሁ

በተለይ በአሜሪካ የሚከሰቱ ዓመታዊ ጉልህ ክስተቶችን በማካተት በሪደርስ ዳይጀስት ካምፓኒ አማካኝነት ከ1868 ዓ.ም አንስቶ ለገበያ እንደሚውለው «ማሻስ ሠቄቄቁሳ ▪ቁቂሮቃሮሰ» መፅሐፍ አይነት በአገራችን ቢኖር የአዲስ ነገር ጋዜጣን በድንገት መቆምና የአዘጋጆቹን አገር ጥሎ መሰደድ በአንኳርነት ስለ መከተቡ ማንም ጥርጣሬ ሊገባው አይችልም::

ጥቅምት 16 ቀን 2000 ዓ.ም. የተመሰረተችው አዲስ ነገር ጋዜጣ ገበያ ላይ 110 ሳምንታት ያህል ቆይታለች:: በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለ2002 ዓ.ም. አዲስ ዓመት ዋዜማ ይዛ ከወጣችው ልዩ ዕትም (ቁጥር 001) ጋር በድምሩ 111 ጊዜ ማተሚያ ቤት ገብታ በመውጣት ከአንባቢያን ጋር ተገናኝታለች::

የጋዜጣዋ ባለቤቶችና ባልደረቦች የጋዜጣዋን ስራ አቋርጠው ከአገር ለመውጣት ያበቃቸው በአዲሱ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅና በወንጀል መቅጫ ህግ ከፍተኛ ቅጣት ሊያስከትሉ የሚችሉ ክሶች እየተሰናዱባቸው ስለመሆኑ መረጃውን ከመንግስት አካባቢ ካሉ ታማኝ ምንጮቻቸው በማግኘታቸው መሆኑን ገልፀው ነበር::

የጋዜጣው ኤክሲኪዩቲቭ ኤዲተር ዐቢይ ተ/ማርያም ከጋዜጣዋ መቆም በኋላ ከእንግሊዝ ለአውራምባ ታይምስ ሁኔታውን አስመልክቶ ሲገልፅ «የአዲስ ዘመን አጉዳፊ ዘመቻ ተቃውሞውን ጀምሯል፣ ማስፈራሪያዎች ነበሩ፣ የተወሰኑ አዘጋጆች ላይ ክስ ተመስርቷል:: ነገር ግን ጋዜጣዋን ለመዝጋት የሚያበቃ አልነበረም:: ወደ ኦክስፎርድ (እንግሊዝ) ከመጣሁ በኋላ ግን ነገሮች እጅግ በፍጥነት እየጨመሩ መጡ:: ስም የማጉደፍ ዘመቻው አደገ፣ ግላዊ (የተናጠል) ወከባዎች ጨመሩ:: እናም የፀረ-ሽብርተኝነትና የወንጀል ሕጉን በመጠቀም የተወሰኑ አዘጋጆች ላይ ክስ የመመስረት መሰናዶው ተጀመረ:: ... የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የደረስነው በፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉ ላይ መሠረት ያደረጉት ክሶች በቅርቡ እንደሚመሰረቱ ስናውቅ ነበር» በማለት ነበር:: ሰፊ ስርጭትና ተነባቢነት የነበራት ጋዜጣዋ በድንገት መቆምና የባልደረቦቿ መሰደድ አነጋጋሪ ሆኖ ነበር:: አንባቢዎችና ጋዜጣ ሻጮችም ፊታቸው እስኪቀላ ድረስ ሁኔታው ድንጋጤን ፈጥሮባቸው ነበር::

ለመንግስት ታማኝ መሆናቸውን በማሳየት የሚታወቁ የመንግስትና «የግል» የመገናኛ ብዙሐን ጋዜጠኞቹ ለመሰደድ ያስቀመጧቸውን ምክንያቶች ለማጣጣልና ለማጠልሸት በ«ክብ ጠረጴዛ» ዙሪያ ተወያይተዋል::

ህዳር 26 ቀን 2002 ዓ.ም. «በህትመት ኮፒ መጠን ከአዲስ አድማስ ቀጥሎ ሰፊ ስርጭት ያላት» ሲል ያስነበበው ጋዜጣው አጋጣሚውን በመጠቀም ልዕልናውን ለማሳየት ምክሯል በማለት የተቹት ነበሩ:: ጋዜጣው

> «አጋርነት ለምን?» ካላችሁ የቆመው ከህግ አውጪ፣ ከህግ አስፈፃሚና ከህግ ተርጓሚው አካል ቀጥሎ አራተኛው የመንግስት አካል የሚል ያልተፃፈ መጠሪያ ያለው ሚዲያ (መገናኛ ብዙሐን) አንድ አካል የሆነ ተነባቢ ጋዜጣ ስለሆነና ለብዙሐኑ ኪሳራው ስለሚያይልም ጭምር ነው::

በጉዳዩ ላይ አነጋግሬ መልስ ሰጡኝ ያላቸው የካኢትዮጵያ ብሔራዊ ጋዜጠኞች ህብረትካ ፕሬዚዳንት አቶ አንተነህ አብርሃም «በአዘጋጆቹ የተነሳው ቅሬታ መሰረት የሌለው ነው:: የሰጡት ምክንያት ጥገኝነት ከመጠየቅ ፍጆታ በዘለለ መልኩ አናየውም::» በማለት የአዲስ ነገሮችን የስደት ምክንያት አጣጥለውታል:: አያይዘውም ጋዜጣዋ የደረሰባት ያለመሸጥና የመመለስ ችግር ለኪሳራ ስላበቃቸው አጋጣሚውን ከፖለቲካ ጋር በማያያዝ ጥገኝነት ለማግኛ እንደተጠቀሙበት ገልፀው ነበር:: አውራምባ ታይምስ ህዳር 29/2002 ዓ.ም የአዲስ ነገርና አዘጋጆቿን አስመልክታ ባወጣችው ልዩ ዳሰሳ ላይ አስተያየት የሰጡ የጋዜጣው ባልደረቦች፣ አንባቢዎች፣ ጋዜጣ አከፋፋዮችና ጋዜጣ አዟሪዎች ማስረጃዎችን በመደርደር ሪአትራፊ እንደሆኑ በአሀዝ በማሳየት፣ ተመላሽ ስላለመሆኑ በመጠቆምሪ የአቶ አንተነህን ሀሳብ «ጥሬ ውሸት» በማለት አጣጥለውት ነበር:: የአዲስ ነገር ማኔጂንግ ኤዲተር መስፍን ነጋሽ «አዲስ ነገርን በማሳጣት የራሳቸውን ጋዜጣ ዝናና ክብር ለማግዘፍ ለሚሞክሩትም ቢሆን በኛ የደረሰው እንዲደርስባቸው አልመኝም» ሲል በዚሁ ጋዜጣ ላይ ምላሽ ሰጥቷል::

አሜሪካ ኤምባሲ፣ ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ድርጅትና ሌሎች ተቋማት ለጋዜጣዋ መቆምና ለአዘጋጆቹ መሰደድ መንስኤ ከመንግስት በኩል የተለያዩ ጫናዎች መብዛት መሆኑን አስረድተው የነበረ ሲሆን ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተቋማቱ መግለጫ

አዘጋጆቹ ያወጡትን መግለጫ የተንተራሰ (ኮፒ- ፔስት) እና በቀጥታ የተገለበጠ መሆኑን በመጠቆም እንደማይቀበሉት አስታውቀዋል:: «የስልክ ጠለፋ፣ማስፈራሪያና የፅሁፍ መልዕክቶች ደርሶናል» ሲሉ የገለፁት አዲስ ነገሮችን አስተያየት አስመልክቶ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ሽመልስ ከማል ለአውራምባ ታይምስ «ማነው የደወለው? ማነው አስፈራሪ ፅሁፍ የላከላቸው ማንነቱ ያልታወቀ አካል ስለደወለ/ስለፃፈ አገር ይለቀቃል ማለት ነው?» ሲሉ ጥያቄያዊ ምላሻቸውን ሰጥተው ነበር::

በጉዳዩ ዙሪያ የተለያዩ ተቃርኗዊ መላ ምቶች ሲሰጡም ነበር:: ጋዜጣዋን አቁመው አዘጋጆቹ የተሰደዱት የመንግስትን ጫና በትክክል መቋቋም ከብዷቸው ነው፣ ክስ እየተደገሰላቸው መሆኑን ባያውቁ ኖሮ አይወጡም ነበር፣ «የመንግስት ቅርብ ነን» ያሉ ሰዎች ሞጋች ብዕራቸውን ለመገላገል ሲሉ በነገሯቸው ወሬ ተታለው የውሳኔ ችኩልነት ታይቶባቸዋል (ተሸውደዋል) እና ሌሎችም አስተያየቶች ተደምጠዋል::

በአሁኑ ሰዓት የተሰደዱት የአዲስ ነገር አዘጋጆች በአሜሪካ፣ በአውሮፓና በአህጉራችን አፍሪካ ተበታትነው ይገኛሉ:: ከአራት ወር በፊት ይፋ ያደረጉት ሮሳሳሽቋቃስሽስቈቄቃቋቁሽቃስ.ሰቄቂ ግን ከሙያዊ ወደ ቤተሰባዊ ግንኙነት ያደገው አንድነታቸው መሳሪያ ሆኖ እያሰባሰባቸው ይገኛል:: ድረ-ገፁ ቅድመና ድህረ ምርጫ ሁተታዊ ትንታኔዎችን ጨምሮ የተለያዩ አገራዊ ፅሁፎች የጋዜጣው ባልደረባ በነበሩና በተጋባዥ ፀሐፊዎች ይቀርብበታል:: ድረ-ገፁ ካለፉት ሁለት ወራት አንስቶ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመክፈት አስቸጋሪ ነው (አይነበኝም::)

## የሚዲያው አጋርነት

ሐሙስ ህዳር 24 2002 ዓ.ም. ማለዳ የአውራምባ ታይምስ ባልደረቦች ቢሯችን ከመድረሳችን በፊት በእጅ ስልኮቻችን የተቀባበልናቸውን መረጃ አምነን ለመቀበል ቸግሮን ነበር:: ወደ አዲስ ነገር ባልደረቦች የመታነውም ስልክ ዝግ መሆኑ ጥርጣሬውን አበረታው:: የተለያዩ ምንጮቻችንም «አዎ አዲስ ነገር ቆመች፤ ባልደረቦቿም ተሰደዱ» ቢሉንም እስከ ማክሰኞ ድረስ ስራ ላይ ነበሩ የሚሉም መኖራቸው የቱን እንመን የሚያስብል ነበር:: እኩለ ቀን ላይ ያገኘነው ለእውነት የቀረበ መረጃ ከሀዘን ድባብ ውስጥ ከመግባት የሚያድን አልነበረም:: በስራ ላይ የነበሩ የጋዜጣዋ የኤዲቶሪያል ቡድን አባላትም ከሰዓት በኋላ በመሰባሰብ በጉዳዩ ዙሪያ ተመካክረንትም ነበር:: ይፋዊ መግለጫ ከአዲስ ነገር አባላት ባለመገለፁ «ምን እንስራ» የሚለው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ አልደረስንም ነበር:: ማምሻውን በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ቃለ-ምልልስ እንዳላቸው ስለ ሰማን ያንን መሠረት አድርገን ውሳኔ ላይ መድረስ እንደሚቻል ተስማማን:: በተለያየ ወቅት የጋዜጣዋ ዋና አዘጋጅ የነበሩት መስፍን ነጋሽ፣ ዐቢይ ተክለ ማርያምና ታምራት ነገራ በአሜሪካ ድምጽ ላይ «ደረሰብን» ስላሉት ጫናና ጋዜጣዋን ለመዝጋት ስለደረሱበት ውሳኔ ከገለፁ በኋላ አጋርነታችን ስለሚያሳይ ዘገባ ሁላችንም አስበንበት እንድንመጣ በስልክ ተነጋገርን::

«አጋርነት ለምን?» ካላችሁ የቆመው ከህግ አውጪ፣ ከህግ አስፈፃሚና ከህግ ተርጓሚው አካል ቀጥሎ አራተኛው የመንግስት አካል የሚል ያልተፃፈ መጠሪያ ያለው ሚዲያ (መገናኛ ብዙሐን) አንድ አካል የሆነ ተነባቢ ጋዜጣ ስለሆነና ለብዙሐኑ ኪሳራው ስለሚያይልም ጭምር ነው:: ለአንድ ሳምንት የአውራምባ ታይምስን ህትመት ማቋረጥና መደበኛ አምዶችን በማጠፍ «አዲስ ነገር»ን የሚመለከት ልዩ ዳሰሳ ማቅረብ በሚል ከቀረቡት ሁለት ሀሳቦች ውስጥ ሁለተኛው በማሸነፉ የማክሰኞ የመጨረሻ እትማችንን ህዳር 29 2002 ዓ.ም. ከአዘጋጆቹ ጋር ቆይታ በማድረግ፣ ሰፊ ሀተታዊ ፅሁፍ በማዘጋጀት፣ በ«አዲስ ነገር» መዘጋት አትራፊው ማነው? የሚል ጠያቂ ኮመንታሪ በማሰናዳት እንዲሁም በህግ የበላይነትና በአቤቶ ወግ አምድ ላይ ይህንኑ የተመለከቱ ፅሁፎች በማስፈር ከአንባቢዎች ጋር መገናኘታችን ይታወሳል:: የአዲስ ነገር አምደኛ ብርሃኑ ደቦጭም «የአዲስ ነገር ቆይታዬ» በሚል ርዕስ አዲስ ነገር ውስጥ ስለተመለከተው መልካም ጉንና ከጋዜጣዋ መቆም በኋላ ስለተባሉ ነገሮች ማቅረቡ ይታወሳል:: ጋዜጣችንን ስለ አዲስ ነገር ያቀረበውን ሰፊ ሽፋን የተመለከተ የአንድ ኤፍ ኤም የሬዲዮ ጣቢያ አሽሟጣጭ «አዲስ ነገር ጋዜጣ ቆመች፤ አዘጋጆቿም ተሰደዱ፤ አውራምባ ታይምስ ሄዳችሁ ለቅሶ መድረስ ትችላላችሁ» ሲል አሽሟጦም ነበር:: ነጠላቸውን አዘቅዝቀው ደራታቸውን ደልቀው ወደ ስራቸው ተመለሱ ያሉንም ነበሩ:: የተለያዩ ሚዲያዎችም አጋርነታቸውን ለማሳየት ሞክረዋል::

አዲስ ነገርን አስመልክቶ የተስተዋለው ሌላ አነጋጋሪ ጉዳይ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በፅህፈት ቤታቸው ስለጉዳዩ ተጠይቀው «አዲስ ነገርንም አዲስ ዘመንንም አላነብም» ማለታቸው እንደነበር ይታወሳል::

ሁሉን አቀፍ በመሆን የአንባቢያንን ትኩረት ስባ የነበረችው የአዲስ ነገር ጋዜጣ መቆም በአፋኝ ህጎች ታጥሮ ፅልመት ለወረሰው የአገራችን ፕሬስ እንደ ተጨማሪ የአደጋ ደወል ታይቷል::

አዲስ ነገር ጋዜጣ ህዳር 18/2002 ዓ.ም. የሦስተኛ ዓመት 110ኛ እትሟን በማውጣት በድንገት መቆምና የአዘጋጆቹ መሰደድ ከዓመቱ ጉልህ ክስተቶች መሀከል አንዱ ነው::

# የዓመቱ ቴክኖሎጂያዊ የፈጠራ ሥራዎች

በአብዱ መሐመድ

በዓለማችን በተለያየ ዘርፍ ጥናት የሚያደርጉ ምሁራንና ሳይንቲስቶች በየጊዜው አዳዲስ የጥናት ውጤቶችን ለንባብ ያበቃሉ ወይም ያስደምጣሉ:: ምሁራኖቹ ከሚያቀርቧቸው የጥናት ውጤቶች ውስጥ አብዛኞዎቹ መሠረታዊውን ሳይንሳዊ ንድፈ ሀሳብ በመንተራስ አካባቢ የማይበክሉ፣ ኃይል የሚቆጥቡ፣ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን የሚሰሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው:: የዚሁ የጥናት ዘርፍ አንዱ በሆነው ህክምና ላይ የሚቀርቡ ጥኖቶችም አበረታችና ተስፋ ሰጪ በሚሉ ጅምር ሥራዎች ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው::

በዛሬው ፅሁፍ ትኩረት ሰጥተን የምንመለከተው በ2002 ዓ.ም ለውጤት ከበቁ የምርምር ዘርፎች መሠረታዊ ንድፈ ሀሳቦች ላይ ከመንተራስ ባለፈ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የተላበሱ፣ ወጣ ያሉ የጥናት ውጤቶችንና በነባሩ አሰራር ላይ የጎላ ለውጥ ያደረጉ የምርምር ሥራዎችን ነው::

## ታዳሽና ኃይል ቆጣቢ የቴክኖሎጂ ምርምሮች

ባገባደድነው ዓመት ከ192 በላይ ርዕሰ ብሔሮች በኮፐንሀገን የተሰበሰቡት ዓለማችንን ወደ የጋመ እሳትነት እየቀየረና የተፈጥሮ አደጋዎችን እያስከተለ ለሚገኘው የአካባቢ ሙቀት መጨመር ዕልባት የሚያስገኝ አጀንዳ ላይ ለመምከር ነበር::

አካባቢን የማይበክሉ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን በመገንባትና በካይ የሆኑ የተቃጠሉ ጋዞችን በመቀነስ ላይ ያተኮረውን አጀንዳ ተግባራዊ ለማድረግ ምሁራን በያዝነው ዓመት ለውጤት ማብቃታቸውን ከገለፁ የምርምር ውጤቶች አንዱ በያዝነው ወር ለውጤት የበቃው ኃይል ቆጣቢ አምፖል ነው::

ታይም መጽሔት ነሐሴ 2/2010 (እ.አ.አ) ያስተዋወቀው «ኦሌድ» (ሑኋ) የተባለው አምፖል ቀደም ሲል ሥራ ላይ ከዋለው አምፖል 80 በመቶ ኃይል ቆጣቢና 20 ዓመት ያለማቋረጥ አገልግሎት የሚሰጥ፣ እንዲሁም ለየት ያለ ቴክኖሎጂ የተላበሰ ነው::

## ቀደም ሲል ሥራ ላይ የዋሉ

«ኢንካዴሰንት» የተባሉትን አምፖሎች እስከ 2010 ከአገልግሎት ውጪ ለማድረግ ቀዳሚ የሆኑት አሜሪካ እና የአውሮፓ ሕብረት ያሳለፉት ውሳኔ በሀገራችንም ተግባራዊ እየሆነ ነው:: አሁን በየመኖሪያችን እየሰቀልነው የምንገኘው ኃይል ቆጣቢ አምፖል ከቀድሞው ኢንካንዴሰንት አምፖል የሚለየው በሙቀት የሚባክነውን ኃይል የሚቀንሱና የጎላ ብርሃን የሚሰጡ ኬሚካሎች የተቀቡ መስታወቶችና በአነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚደምቁ «ሬዚስተሮች» በመዘጋጀቱ ነው::

ከገበያ ውጪ እየሆነ በመጣውም ይሁን ኃይል ቆጣቢ ሆኖ የመጣው አምፖል ብርሃን የሚሰጡት የኤሌክትሪክ ኃይል ሲያርፍባቸው እየጋሙ ብርሃን በሚፈጥሩ ሬዝስተሮች የሚያገኙትን ብርሃን በየአቅጣጫው በማንፀባረቅ ነው::

አዲስ ቴክኖሎጂ ተላብሶ ብቅ ያለው «ሊድ» ከነባሩና ከተተኪው የሚለየው የኤሌክትሪክ ኃይል ሲያገኘ ብርሃን የሚያመነጨው በፈለገው መጠንና ቅርጽ የሚዘጋጀው ተጣጣፊ ፕላስቲክ መስታወት በመሆኑ ነው:: «ሎሜክስ» በተባለ ሴሚኮንዳክተር የሚዘጋጀው ይህ አምፖል እንደ ፀሐይ በውስጡ ያመቀውን ብርሃን የሚረጭ እንጂ ከአንድ የጋለ ሽቦ የሚመጣውን ብርሃን የሚያንፀባርቅ አይደለም:: በፈለግነው ቦታ፣ ግርግዳ ላይ አልያም ኮርኒስ ላይ የምንለጥፈውን አምፖል ለማዘጋጀት የአውሮፓ ሕብረት 27 ሚሊዮን ዶላር መለገሱን በጥናት ዘገባው ሰፍሯል:: ይህንን አምፖል በ2012 ገበያ ላይ [illegible] ዶላር ገቢ ለማወራረድ እየተጣደፉ [illegible] ጀነራል ኤሌክትሪክ፣ የጃፓኑ ኮኒካ ሚኒሎታ እና የጀርመኑ ኦስራም ካምፓኒዎች ናቸው::

በዚሁ ዘርፍ የለንደን ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ ሌሪዱፓንት ከሱፍ ዘይት የአውቶሞቢል ነዳጅ ለማምረት የሚያስችል ጥናት ያቀረቡት በያዝነው ዓመት ነው:: የሱፍ ዘይትን ከአየርና ውሃ ጋር ለማዋሀድ የሚረዱ ሁለት አብላይ ኬሚካሎችን (ሰሮቋሮቁቮቋቋቋ) በመጠቀም የሱፍ ዘይት ሙቀት ሲያገኝ የሚተነውን የሃይድሮጅን ጋዝ በሃይብሪድ ፊዩል እንዲንቀሳቀሱ ለተዘጋጁ አውቶሞቢሎች የኃይል ፍጆታ ይውላል::

## በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ የቀረቡ የጥናት ውጤቶች

በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ በያዝነው ዓመት ለውጤት ከበቁ ወይም ጥናታቸው ከተጀመረ የቴክኖሎጂ ምርምሮች በጉግል እና በአፕል ካምፓኒ የተዘጋጁ የሞባይል ቀፎዎች ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እንዲሰሩ ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው:: ከዚህ ውስጥ በቀጥታ ከአቅጣጫና ጊዜ ጠቋሚ ሳተላይት «ጂፒኤስ» ጋር እየተገናኙ ማንኛውንም የካርታና መረጃ እንዲያገኙ፣ በከተሞች ውስጥ በፈለጉት አቅጣጫ እንዲከንፉ፣ የልጆቻቸውንና የወዳጆቻቸውን እንቅስቃሴ እንዲከታተሉ የሚያስችሉ ናቸው:: ከዚሁ በተጨማሪ የጣት መዳፍን በስክሪናቸው ላይ በማሳረፍ እንደ መፅሐፍ እየተገለጡ የፈለጉትን የሙዚቃ የቪዲዮ፣ ወዘተ አገልግሎቶች በፍጥነት መጠቀም እንዲቻል ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው::

ከዚህ ወጣ ባለ መንገድ የማይክሮሶፍት ካምፓኒ በአሜሪካ የፈጠራ ባለቤት ፍቃድ ቁጥር 6754472 የተመዘገበው የቴክኖሎጂ ጥናት የሰው ልጅ ሰውነትን እንደ ኮምፒዩተር ኔትዎርክ በመጠቀም እንደማንኛውም የኤሌክትሪክ ቁስ ኃይል እና ዳታ (መረጃ) እንዲያስተላልፍ ያቀደ ጥናት ነው::

በዚሁ ጥናት «ፐርሰናል ኤርያ ኔት ወርክ» በተባለው ቴክኖሎጂ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን ተንቀሳቃሽ ስልክንና «ፐርሰናል ዳታ አሲስታንስ» የተባሉ መሣሪያዎችና ኮምፒውተሮችን በገመድ አልባ የጨረር ቴክኖሎጂ (ሠሽቈስቁስቋቋ ሶሽሳሽቁሽቋቮ) ለማገናኘት የሰውን ልጅ እንደ ኔትዎርክ ማማ ለመጠቀም ነው:: በዚህ ቴክኖሎጂ የሰውነት ቆዳ ላይ የሚለጠፈው ኪፓድ በሰዎች ጫማ ሥር በመቀመጥ እንደ ቀድሞ ሰዓቶች እንቅስቃሴን ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል እየቀየረ (ቀሽቃስቋሽሰ ቅቁብስቈ ሰቄቃባስቈቋቁቈ) በሚያገኘው ኃይል የኔትዎርክ ግንኙነትን እንዲያቀላጥፍ ለማድረግ ታቅዷል::

ኢንቴል ካምፓኒ «ቪ-ቭ ሆሞ ሚዲያ ሲስተም» የተባለ፣ ለ31 ሚሊዮን ሰዓት የሚተላለፍ የፊልምና የቴሌቪዥን ፕሮግራም ቀድቶ ማስቀመጥ የሚችል ሚዲያ ሰርቨር ያዘጋጀው ቀደም ባሉት ዓመታት ነው:: ይህንን መነሻ በማድረግ ያጠራቀማቸውን ፕሮግራሞች «ሲንግል ቦክስ» በተባለ ፕሮግራም በቴሌቪዥንና በኮምፒዩተር ማሰራጨት ቢጀምርም የአብዛኛውን ግለሰቦች ፍላጎት ማሟላት አልቻለም በዓለማችን በቢሊዮን የሚገመት ሕዝብ የሚፈልገውን ፕሮግራም በፈለገው ቦታ በሞባይል ስልኩ መከታተል ይፈልጋል:: ችግሩ የሞባይል ስክሪኖች የተሟላ



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

# ግንቦት 7ዎች በርቀት የቃኙት የሞት ፍርድ

በርግጥ ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና ከፌዴራል ፖሊስ የተዋቀረው የጋራ የፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል የሽብር ሴራውን ስለማክሸፉ መግለጫ ያወጣው ሚያዚያ 16 ቀን 2001 ዓ.ም ነው:: «በአገራችን ሰላማዊ ትግል አብቅቷል በማለት የደም ማፍሰስን መንገድ እንደብቸኛ የትግል ስልት ያወጀው ራሱን ግንቦት 7 ብሎ የሚጠርውና በውጪ ሀገር በእነ ሬዶ/ርሪ ብርሃኑ ነጋ የተቋቋመው የፀረ-ሰላም ቡድን ሕገመንግስታችንንና ሕገመንግስታዊ ሥርዓታችንን በኃይል ለመገርሰስ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ በማድረግ የወታደራዊ ንዑስ ቡድን እና የሲቪል ንዑስ ቡድን በሚል በአገር ወስጥ ያደራጀው የሽብር መረብና እንቅስቃሴ በፀጥታ ኃይሎች ከሽፏል::» ነበር የሚለው መግለጫው::

በቁጥጥር ስር የዋሉ ግለሰቦች ማንነት በይፋ ተገልፆ «ባለስልጣናትን ለመግደል፣ መንግስታዊ የልማት ተቋትን ለማውደምና ሕገመንግሰቱንና ሕገመግግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማናጋት ሞከረዋል» በማል በ46 ሰዎች ላይ ክስ የተመሰረተውም ሰኔ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ነበር:: ይሁንና ግን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ወንጀል ችሎት በተከሻሾቹ ላይ የመጨረሻ የቅጣት ውሳኔውን ያስተላለፈው በዚህ ባገባደድነው ዓመት፣ ታህሳስ 13 ቀን 2002 ዓ.ም ነው::

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ (የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር) እና አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ (የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ዋና ፀሐፊ) ጨመሮ 13 የንቅናቄው የአመራር አባላት በሌሉበት፤ ብ/ጄ ተፈራ ማሞ፣ አቶ አሳምነው ፅጌ፣ ኰ/ል ፋንታሁን ሙሃባ፣ ሌ/ኮ ደምሰው፣ ሻለቃ አዳሙ ጌትነት፣ ሻለቃ ሲሳይ አበራ፣ ሻምበል አዘዘ፣ እና ሌሎች መኮንኖች፤ እንዲሁም አቶ ፅጌ ኃብተማርያምን /የአቶ አንደርጋቸው ፅጌ አባት/ ጨምሮ ከሃያ በላይ ሲቪል ሰዎች በእነ ብ/ጄ ተፈራ ማሞ መዝገብ የተካተቱ ተከሳሾች ነበሩ::

ፍርድ ቤቱ ለስድስት ወራት ገደማ ጉዳዩን ሲመረምር ከቆየ በኋላ ግንቦት 7ዎችን ጨምሮ በ40 ተከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ብይን ሰጠ::

ከዚያም የ1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ በተፈጠረው ከስተት «ሕገመንግስቱንና ሕገመንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ ሞክራችኋል» ተብለውና ተፈርዶባቸው ለእስር ከተዳረጉ በኋላ የቅድመ ሁኔታ ይቅርታ ተደርጎላቸው የተፈቱ፣ ነገር ግን አሁን ጥፋተኛ የተባሉ ሁለት የግንቦት 7 አመራሮች፣ ማለትም ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እና አቶ መሉነህ እዩኤል የቅድመ ሁኔታ ይቅርታቸው እንደተነሳ (እንደተሰረዘ) ተገለፀ:: (የቀድሞ የቅንጅት አመራር የነበሩትና በዚሁ የክስ መዝገብ ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉት አቶ መላኩ ተፈራም ይቅርታቸው ተነስቷል::)



አቃቤ ሕግ የግንቦት 7 አመራሮችን ጨምሮ 38 ተከሳሾች «የሞት ቅጣት ይገባቸዋል» ሲል የቅጣት አስተያየቱን ቢሰጥም በዚህ የክስ መዝገብ የሞት ፍርድ የተፈረደው በአምስት ግለሰቦች ላይ ነበር:: ማክሰኞ፣ ታህሳስ 13 ቀን 2002 ዓ.ም የተሰየመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ወንጀል ችሎት በንቅናቄው ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ አቶ መሉነህ ኢዮኤል፣ አቶ መስፍን አማን እና በአቶ መላኩ ተፈራ ላይ የሞት ቅጣት ወሳነ:: ከአምስቱ የሞት ፍርደኞች

ውስጥ (ከአቶ ተፈራ በቀር) አራቱ የግንቦት 7 አመራር አባላት በሌሉበት ነበር የተፈረደባቸው:: የተቀሩት የንቅናቄው ዘጠኝ አባላት ደግሞ በእድሜ ልክ እስራት እንዲቀጡ ፍርድ ቤቱ በሌሉበት ውሳኔ አስተላለፈባቸው::

ከዚህ በተጨማሪ የዶ/ር ብርሃኑ እና የአቶ አንዳርጋቸው ንብረት እዲወረስም ፍርድ ቤቱ ወስኗል::

ይህ ፍርድ በዓለማቀፍ መገናኛ ብዙሃን መነጋገሪያ ሆኖ በነበረበት ሰሞን በሌሉበት የተፈረደባቸው የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራሮች የፍርድ ሂደቱ ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ እንደነበርና ቀድሞውኑ ከዚህ የተለየ ነገር እንዳልጠበቁ መግለፃቸው ይታወሳል:: የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ምክትል ኃላፊና በዘንድሮ ምርጫ ተዳድረው የፓርላማ መቀመጫ ያገኙት አቶ ሽመልስ ከማል በበኩላቸው «አስቀድሞ የሚታወቅ ፍርድ የለም፤ ምናልባት እናውቃለን የሚል ካለ የሰራውን በልቦናው የሚያውቅ ነው» በማለት መመለሳቸው ይታወቃል::

ሁኔታው ለግንቦት 7 የበለጠ ብርታት ይሆነው እንደሆን እንጂ ለኢትዮጵያ መንግስት የሚፈይድለት ነገር እንዳልነበር በወቅቱ አስተያየታቸውን የሰጡ ወገኖች ነበሩ:: በተለይ ሞት እና እድሜ ልክ የተፈረደባቸው ግለሰቦች ለኢትዮጵያ መንግስት ተላልፈው እንዲሰጡ ጥረት ይደረግ እንደሆን ጠ/ሚኒስትር መለስ ተጠይቀው፣ «ነገሩን እናየዋለን:: ጠቃሚ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከታየ ይደረጋል:: ይህን ያህል ጠቃሚ፣ አስፈላጊ ካልሆነ ብዙ ላይገፋበት ይችላል» ማለታቸው የፍርድ ሂደቱን ሚና አጠያያቂ እንዳደረገው መከራከሪያቸውን ያቀርባሉ::

እነዚህ ወገኖች የግለሰቦቹ መቀጣት ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ ላየሆን የሚችልበት እድል ካለ፣ በተመሳሳይ መልኩ የመከሰሳቸውንም አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ እንደሚከተው ይናገራሉ:: በሌላ በኩል ጉዳዩ ከሽብርተኝነት ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ሊያያዝ የሚችልበት መንገድ በመኖሩ ግንቦት 7 እና አመራሮቹ ዓለማቀፋዊ (ወይም የምዕራባዊያንን) ድጋፍ፣ ቢያንስ በይፋ እንዳያገኙ የሚያደርግ ፖለቲካዊ ግብ ሊኖረው እንደሚችልና ለዚህም ከቅጣቱ ይልቅ ፍርዱ ብቻውን በቂ እንደሚሆን የገለፁም ነበሩ::

የሆነ ሆኖ «ሁሉን አቀፍ» የትግል ስልት እከተላለሁ በማለት ላይ የሚገኘው ግንቦት 7 ንቅናቄ 13 የአመራር አባላቱ «ባለስልጣናትን ለመግደል፣ መንግስታዊ የልማት ተቋማትን ለማውደምና ሕገመንግስቱን እና ሕገመንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማናጋት» አሲረዋል ተብለው፣ አራቱ የሞት ቅጣት እና ዘጠኙ ደግሞ የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው በዚህ ባገባደድነው ዓመት ነበር::

ምስሎችን ማቅረብ አይችሉም ወይም በቴሌቭዥንና በኮምፒዩተር እንደምንመለከተው ዓይናችንን የሚያጠግብ ምስል አያቀርቡም:: ለዚሁ መፍትሄ ዘይጃለሁ የሚለው የኢንተል ካምፓኒ በገመድ አልባ ቴክኖሎጂ በኢንተርኔት የሚተላለፉ የቪዲዮ የሙዚቃና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን በሞባይላችን እየቀዳን የቤታችንን ግርግዳ እንደስክሪን በመጠቀም በፈለግንበት ቦታ የተሟላ ምስል የምንመለከትበት «ፓትዮ ስክሪን» የተባለ ከ2-3 ሜትር ስፋት ያለው ተጣጣፊ ስክሪን እያዘጋጀ ነው::

በማይክሮሶፍት ከቀዳሚዎቹ ሰባት ኤክስፐርቶች አንዱ የሆኑት ኖሳ ኦሞ ኢጉይ «ስፒች ሪኮግኒሽን» በተባለው ቴክኖሎጂ እያዘጋጁት የሚገኘው «ኒርቫና» የተባለ ሶፍትዌር ቀዳሚ በሆኑ በቻይና፣ በፈረንሳይኛ፣ በጣሊያንኛ፣ በስፓንሽ፣ በጃፓንኛ፣ በኮሪያና በሩሲያ ቋንቋ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ መልሱን ካዘጋጀ በኋላ በተፈለገው ቋንቋ መልስ የሚሰጥ ነው::

በዚሁ ዘርፍ የአውሮፓ ሕብረት «ቲሲ ስፓር» ለተባለው ጥናት ፕሮጀክት 10 ሚሊዮን ዶላር በመመደብ የጀርመኑ ሲመንስ ካምፓኒ እያዘጋጀ የሚገኘው «ሲመንስ ሌክቸር» የተባለው መሣሪያ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረሱ የተነገረው በያዝነው ዓመት ነው:: ይህ መሣሪያ በአውሮፓ ሕብረት አባል አገራት የሚነገሩትን ቋንቋዎች ከተናጋሪው አፍ እየቀዳ አድማጩ በሚፈልገው ቋንቋ በመለወጥ የሚያስደምጥ ነው:: በሚቀጥለው ዓመት የመጨረሻ ጥናቱን ጨርሶ ሥራ ላይ እንደሚውል የተነገረው ይህ መሣሪያ ሕብረቱ ለትርጉም የሚያወጣውን ወጪ ከማስቀረቱ በተጨማሪ እንግሊዝኛ ቋንቋ ለዘመናት ይዞት የነበረውን የበላይነት ለማስቀረት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ተብሏል::

በአውሮፓ ሕብረት በተሰጠ የገንዘብ ድጋፍ የኖኪያ ካምፓኒ በማዘጋጀት ላይ የሚገኘው የሞባይል ሶፍትዌር በቻይና ቋንቋ የሚተላለፈውን የሞባይል ጥሪ በእንግሊዝኛ የእንግሊዘኛውን ደግሞ ወደ ቻይና እየለወጠ እንግሊዝኛ ተናጋሪዎችን ከቻይና ሕዝብ ጋር በቀጥታ በስልክ ለማገናኘት የሚያስችል ነው:: የመጀመሪያ ሙከራውን ያደረገውም በያዝነው ዓመት ነው::

ካሊፎርኒያ በሚገኘው የናሳ ምርምር ጣቢያ ናኖ ቴክኖሎጂ በተባለው አዲስ ጥናት በቅርብ ዓመታት ለውጤት እንደሚበቃ የሚቀጠበቀው መሣሪያ ድምፅ አልባ ንግግሮችን ወደ ድምፅ የሚቀይር ነው:: በግለሰቦች ጉሮሮ ላይ የሚለጠፈው ይህ መሣሪያ የግለሰቡን የአፍ እንቅስቃሴና ድምፅ በሚያወጣው ትናጋ ላይ የሚፈጠረው ርግብግቦሽ እየመዘገበ ተቀብረው የሚቀሩ ድምፅ አልባ ንግግሮችን /ሰብ ቮካል ወርድስ/ ወደሚነበብ ፅሁፍና ወደሚደመጥ ንግግር ይለውጣል:: ከዚሁ በተያያዘ በአትላንታ የሚገኘው ኤክሲዳ ካምፓኒ የሰዎችን ድምፅ ርግብግቢት እየመዘገበ በመረጃ ሳጥን የደህንነት ቁልፍ ውስጥ (ቅሮቋቋብቁቌሳ) በማስቀመጥ ግለሰቦች ኮምፒዩተሮቻቸው ወይም የመረጃ ሳጥናቸው ውስጥ ያለውን መረጃ በድምፅ ለይተው የሚከፍቱበትን ጥናት እያገባደድኩ ነው ብሏል::

በእንግሊዝ በአብዛኛው የሴቶች ችግር የሆነውን የመኪና ቁልፍ ከቦርሳቸው በመፈለግ የሚያባክኑትን ጊዜ መቆጠብ የሚያስችል በእጅ አሻራ የሚከፈት የመኪና የበር ቁልፍና የኳድሮ ማብሪያ ጥናት በሊቨርፑል ዩኒቨርስቲ እየተዘጋጀ ነው:: በኬንያ የሚታተመው ዴይሊ ኒውስ የጀርመን ሳይንቲስቶች ቁሶችን በማይታይ ሳጥን ውስጥ ማስቀመጣቸውን ወይም የማይታይ ሳጥን ማዘጋጀታቸውን የዘገበው በመጋቢት 2002 ነው::

በትራንስፖርት ዘርፍ የቀረቡ የፈጠራ ውጤቶች

በያዝነው ዓመት በትራንስፖርት ዘርፍ ከቀረቡ አዳዲስ የፈጠራ ውጤቶች ቀዳሚ የሆነው የጃፓን ተመራማሪዎች ብዙዎች የዘመናት ፍላጐት ለነበረው ጥያቄ ምላሽ የሰጠ በምድርና በአየር ላይ የሚጓዝ «አውሮፕላን መኪና» እና ከፊቱ ደንቃራ ሲገጥመው የሚዘል መኪና ማዘጋጀታቸውን የገለፁት ባለፈው ሐምሌ ወር ነው::

«ሮዴብል ኤር ክራፍት» የተባለችውና 800 ፓውንድ የምትመዝነው አውሮፕላን-መኪና ተገጣጣሚና ተጣጣፊ የሆኑ ክንፍና አራት ጎማዎች ያሏት ሲሆን በምድር ላይ በጐማ ትጓዛለች፤ በአየር ላይ ክንፏን ዘርግታ ትከንፋለች፤ በ2010 ማብቂያ ላይም ተግባራዊ ሙከራዋን አጠናቃ ለገበያ ትቀርባለች ተብሏል:: በዚሁ ዘርፍ የጃፓን ተመራማሪዎች በጥምረት ያዘጋጁት ሌላዋ አውቶሞቢል ከፊት ለፊቷ የሚገጥማትን ደንቃራ ለመዝለል የሚያስችል ቴክኖሎጂ የተላበሰች መሆኗን ያሳወቁት በሐምሌ ወር የመጨረሻ ሳምንት ነው::

## በሕክምናው ዘርፍ የተደረጉ ጥናቶች

በመካከለኛው ምስራቅ ተነባቢ ከሆኑ ጋዜጦች ቀዳሚ የሆነው ገልፍ ኒውስ የሩሲያ ሳይንቲስቶች የሰው ልጅ በተፈጥሮ የሚያዘጋጀውን ወተት የሚታለቡ ፍየሎች በዘረ-መል ምህንድስና ማዘጋጀታቸውን የዘገበው በነሐሴ 2002 የመጀመሪያ ሳምንት ነው:: በዚሁ ዘገባ እንደሰፈረው ተዳቅለው ለውጤት የበቁት ፍየሎች መታለብ የጀመሩት ወተት ከእናት ጡት ወተት የሚገኘውን «ላክቶፈረን» የተባለ ንጥረ ነገር በውስጡ የያዘ ነው::

ከሞስኮ ወጣ ብሎ በሚገኝ ጎልትሶቭ በተባለ የምርምር ተቋም በዘረ-መል ምህንድስና የዳበሩት ፍየሎች «ላክ 1 እና ላክ 2» የተባለ ስያሜ የተሰጣቸው፣ ሕፃናትን ከቫይረስና ከባክቴሪያ የሚከላከለውን «ላክቶፈን» የተባለውን ሆርሞን የያዘ ወተት ማዘጋጀት መጀመራቸውን በመንተራስ ነው:: ፍየሎቹ በዘረ-መል ምህንድስና እንዲዘጋጁ የጥናት ወጪውን የሸፈኑት የሩስያና የቤላሩስ መንግስታት በመሆናቸው በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ከነዚህ ፍየሎች ዝርያ የሚወጣውን የሰው ወተት የሚጠጡት በሁለቱ ሀገራት የሚኖሩ ሕፃናት ብቻ መሆናቸውን «ሪያኖቬሲቲ» የተባለውን የሩሲያ ጋዜጣ በመጥቀስ ገልፍ ኒውስ ያቀረበው የጥናት ዘገባ ያስረዳል::

▷ ማስታወቂያ ◁



## የነፍስ አድን ጥሪ

ልጃችን ሜላት መሀሪ የ19 አመት ወጣት ስትሆን በ2002 ዓም የ12ኛ ብሄራዊ ፈተና ወስዳ በከፍተኛ ውጤት ፈተናውን በማለፍ የልጅነት ህልሟ የነበረውን ዶክተር የመሆን ተስፋ ሰንቃ አዲሱን ህይወቷን እየናፈቀች ነበር::

ሆኖም እሷም ፣ እኛም ባላሰብነው ሁኔታ የደም ካንሰር በህክምናው አጠራር ፦ሰበቋስ ላቮቅሻቌሯቁሮቋቌ ላስቡቀስቋሽሮ በሽታ ተጠቂ ሆና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በመተኛት ህክምናዋን በመከታተል ላይ ትገኛለች:: የሀኪሞች ቦርድም ህክምናዋ በሀገር ውስጥ ስለሌለ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጪ ሀገር ሄዳ መታከም እንዳለባት ወስኗል:: ለህክምናዋ ማስፈፀሚያ ወደ አንድ ሚሊዮን ብር ገደማ ተጠይቋል:: ይህን ብር ለመሸፈን አቅማችን ስለማይችል የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ የተቻለውን እንዲያደርግ እና ልጃችንን ከሞት አድኖ ከህልሟ ጋር ያገናኝልን ዘንድ በፈጣሪ ስም እንጠይቃለን::

**ልጃችንን መርዳት ለምትፈልጉ**
**ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስላሴ ቅርንጫፍ በወ/ሮ ሮማን ተፈሪ አካውንት ቁጥር 68848 ወይም በስልክ ቁጥሮች**

**0911410579**
**0910800665**
**0910066463 ደውለው መርዳት ይችላሉ::**




PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ስፖርት

በአቤል ዓለማየሁ
abel.awramba@gmail.com

# የዓመቱ ጉልህ ስፖርታዊ ክስተቶች




## የዓመቱ ምርጥ አትሌት ኢማነ መርጋ

የኢትዮጵያ ተስፈኛ አትሌትነቱን እያስመሰከረ የሚገኘው ኢማነ መርጋ በግሪክ ተሰሎንቄ ካፍታንዘግሊዮ ስታዲየም በተካሄደው የዓመቱ የዓለም አትሌቲክስ ውድድር ፍፃሜ ላይ በ5 ሺህ ኬኒያዊያኖቹ ሚካህ ኮጐ እና ኤድዊን ሶይን ቀድሞ አሸናፊ ነበር:: ሦስቱም አትሌቶች ተከታትለው የገቡ ሲሆን አሸናፊው አትሌት የተለየው በ«ፎቶ ፊኒሽ» ነበር:: ኢማነ በዳይመንድ ሊግ የሩጫ ውድድር በ5 ሺ.ህ ሜትር በነጥብ ብልጫ በማምጣት አሸናፊ፣ ሆኗል:: ኢማነ በዓመቱ ተደጋጋሚ ድል በማስመዝገቡና ታላቅነቱን በማሳየቱ የዓመቱ ምርጥ አትሌት ስትል አውራምባ ታይምስ መርጣዋለች::

## የኃይሌ ቶስታ

ፕላኔታችን የምንግዜም ታላቅ አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ መስከረም 10 2002 ዓ.ም. ለ36ኛ ጊዜ በተካሄደው ዓመታዊው የበርሊን ማራቶን 2.06.08 በመግባት ለአራተኛ ተከታታይ ዓመት የውድድሩ አሸናፊ ነበር:: ማራቶንን ከ2.04 በታች የገባ ብቸኛው የዓለማችን ሰው (ኃይሌ) በሁለት የበርሊን ማራቶን በተከታታይ ሪኮርድ የሰበረ ሲሆን በዚህም ውድድር 30 ኪሎ ሜትሩን ሮጦ ያጠናቀቀበት 1.27.49 27ኛ የዓለም ሪከርዱ ሆኖ ተመዝግቧል:: በሴቶች ኢትዮጵያዊቷ አፀደ ሀብታሙ 2.24:47 በመግባት ማሸነፏም ይታወሳል::

ኃይሌ በፈረንጆች የአዲስ ዓመት ዋዜማም በጀርመን ቢትበርገር በተካሄደ የ8 ኪሎ ሜትር የጐዳና ላይ ሩጫ 22:23 በመግባት አሸናፊ ነበረ:: «ከኃይሌ ጋር መሮጥ ከአንበሳ ጋር እንደመታገል ነው» ሲል የኃይሌን ታላቅነት የገለፀው ኬኒያዊው ሻድራክ ላጋት 22:48 በመግባተ ሁለተኛ ሲወጣ ኪፐ ኮሪር ሦስተኛ ነበር::

ኃይሌ በጥር ወር በተካሄደው የዱባይ ማራቶን ላይ ሪከርድ ለመስበር አስቦ ባይሳካለትም በቦታው በተከታታይ ለሦስተኛ ጊዜ በማሸነፍ ቶስታ (ሃትሪክ) ሰርቷል::





## ደምሴ ዳምጤ

ኾ ሆስፒታል ገብቷል

ለ40 ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኝነት ውስጥ የጐላ ድርሻ ያበረከተው ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ በሁለት ዓይኑ ላይ ለደረሰበት ህመም ማሳከሚያ ያረዳው ዘንድ በተደረገለት የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም 710 ሺ.ህ ብር ገደማ ተሰባስቦለታል:: በታይላንድ ባንኮክ በመጓዝም ህክምና አድርጐ መመለሱ ይታወቃል:: ደምሴ ለአትሌቲክስ ስፖርት ብዙ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ በሶደሬ ጠ/ጉባኤ ጉባኤ ባደረገበት ወቅት 23.5 ሚሊየን ብር እንዳለው ያሳወቀው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የእርዳታ እጁን አለመዘርጋቱ አነጋጋሪ ነበር:: ሼህ መሀመድ ሁሴን አልአሙዲ የህክምናውን ሙሉ ወጪ እንደሸፈኑለትም ይታወቃል::

ደምሴ ዳምጤ በአሁኑ ሰዓት ኩላሊቱን ታሞ በሳንቴ ከፍተኛ ክሊኒክ ከገባ ዛሬ አምስተኛ ቀኑ ነው:: የጤንነቱ ሁኔታ በመልካም ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ለአውራምባ ታይምስ ገልጿል:: ለተጨማሪ ህክምናም መስከረም 5 ወደ ባንኮክ ይጓዛል::



## ተስፋዬ ኦርጌቾ

የቀድሞ የኢትዮጵያ ብ/ቡድንና የቅ/ጊዮርጊስ ተጨዋች ለነበረው ተስፋዬ አርጌቾ የእርዳታ ማሰባሰቢያ ጨዋታ መስከረም 26 ቀን በአዲስ አበባ ስታዲየም ተደርጎለት በማዳ ገቢና ከድርጅቶችና ግለሰቦች እርዳታ 330 ሺ.ህ የተሰበሰበለት ሲሆን ወደ ታይላንድ ህክምና ጤንነቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል:: በአሁኑ ሰዓትም ወደ አሜሪካ - አትላንታ ተጉዞ ስራ እየሰራ ቤት ተከራይቶ ኑሮውን በጥሩ ሁኔታ እየመራ እንደሚገኝ ታውቋል:: በ1985 አሙኒኪ፣ ፊኒዳ ጆርጅና ዳንኤል አሞካቺን ያካተተው የናይጄሪያ ብ/ቡድን ኢትዮጵያ 1-8 ስታሸንፍ ብቸኛዋን ጐል ያሳረፈው እሱ ነበር::

## የዓለም ዋንጫ በኢትዮጵያ

በደቡብ አፍሪካ የተወደሰችበት የ2010 የዓለም ዋንጫ ህዳር 08 2002 ዓ.ም አዲስ አበባ መምጣቱ የሚታወስ ሲሆን የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ሚ/ር ወ/ሮ አስቴር ማሞን ጨምሮ ከፍተኛ ባለስልጣናት ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በመገኘት አቀባበል አድርገውለት ነበር:: በአፍሪካ የዛሬው ትክክለኛው ዋንጫ ነው / አይደለም የሚል መነጋገሪያ ነበር::

## የሉሲ ያልጠበቀ ሽንፈት

የካቲት 28 2002 ዓ.ም. ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የታንዛኒያ አቻውን በአዲስ አበባ ስታዲየም የገጠመው የኢትዮጵያ ሴቶች ብ/ቡድን ባልተጠበቀ ሁኔታ 3-1 የተሸነፈ ሲሆን በመልሱ ጨዋታ ኣቻ በመውጣት በአጠቃላይ ውጤት ተሸንፎ ከውድድሩ ተሰናብቷል::

## የጥንዶቹ ድል

በህዳር ወር የመጀመሪያው ሳምንት መጨረሻ ለ26ኛ ጊዜ በሆላንድ ናይሜገን በተደረገ 15 ኪሎ ሜትር ውድድር በሴቶች ከ2005 በኋላ የመጀመሪያ የጐዳና ላይ ሩጫ ያደረገችው ጥሩነሽ ዲባባ 46.28 በመግባት የዓለም ሪከርድ በማስመዝገብ አሸናፊ የነበረች ሲሆን የትዳር አጋሯ ስለሺ ስህንም ውድድሩን 42.14 በመግባት አሸናፊ ነበር::




## 9ኛው ታላቅ ሩጫ

ህዳር 13 2002 ዓ.ም ለ9ኛ ጊዜ በተካሄደው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ውድድር ላይ 33 ሺ.ህ የሚጠጉ የተመዘገቡና 2 ሺ.ህ የሚጠጉ ያልተመዘገቡ ሯጮች ሮጠዋል:: በወንዶች አቋርጦ ለመውጣት ተቃርቦ እንደነበር የገለፀው ጥላሁን ረጋሳ (28.36) የውድድሩን ሪከርድ በመስበር ሲያሸንፍ አበራ ኩማና ፈይሳ ሌላሳ ሁለተኛና ሦስተኛ ወጥተዋል:: በሴቶች ኮረኒ ጃሊላ (33.03) ስታሸንፍ አማን ጉዳናና በላይነሽ አሊጂራ ሁለተኛና ሦስተኛ ወጥተዋል:: በቶዮታ የአምባሳደሮች ውድድር የኖርዌዩ አምባሳደር ጄንስ ፒተር ለ4ኛ ተከታታይ ጊዜ አሸናፊ ነበሩ::

## የቅ/ጊዮርጊስ 9ኛ ድል

ቅ/ጊዮርጊስ ተከታዩ ደደቢትን በ26 ነጥብ በመብለጥ ለ9ኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ዋንጫን አንስቷል:: አንጋፋው ክለብ በአፍሪካ ሻምፒዮንስ ሊግ ከሱዳኑ ኤል ሜሪክ ጋር ተጋጥሞ በደርሶ መልስ ተሸናፊ በመሆን ከመጀመሪያ ዙር መሻገር ሳይችል የቀረ ሲሆን በምስራቅና መካከለኛው የክለቦች ውድድር ላይ በሩዋንዳው ኢፒ አር በጭማሪ ሰዓት ተሸንፎ ሁለተኛ ወጥቷል:: ይህም በአገራችን ሪከርድ ነው:: ጊዮርጊስ ሰርቢያዊውን አሰልጣኝ ስሬዲዮቪች ሚሉቲን ሚቾ ጋር ያለው ኮንትራት ያበቃ ሲሆን ባለፈው ሳምንት ጣሊያናዊውን ጁሴፔ ዶሴናንና ጣሊያናዊ ምክትላቸውን ቀጥሯል:: ሁለቱ አሰልጣኖች ቡድኑን ለአንድ ሳምንት ያህል ልምምድ ካሰሩ በኋላ ወደ አገራቸው የሄዱ ሲሆን በቅርቡ እንደሚመለሱ ይጠበቃል::

## ደደቢት የጥሎ ማለፍ አሸናፊ

ደደቢት ከቅ/ጊዮርጊስ ጋር ለጥሎ ማለፍ ዋንጫ ተጫውቶ ተጋጣሚው 5 የቀይ ካርዶችን በማየቱ በፎርፌ አሸናፊ መሆን ችሏል:: በጨዋታው የቅ/ጊዮርጊሱ ሳልሀዲን ሰይድ ዳኛን መማታቱ ከዓመቱ አሳፋሪ ምድብ ውስጥ ይካተታል:: ሁለት ዓመትና የገንዘብ እንዲሁም ዳኛው ያወጡትን የህክምና ወጪ እንዲሸፍንም በፌዴሬሽኑ ተወስኖበታል:: ደደቢት መህመት ታይፋት የተባሉ ቱርካዊ በዋና አሰልጣኝነት ጋናዊው ሱሊ ሞሃመድን በምክትል አሰልጣኝነት ሾሟል::

## የመሰረት 4ኛ ተከታታይ ድል

ኢንተርናሽናል አማተር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሚያዘጀው የዓለም የቤት ውስጥ ውድድር ከኢትዮጵያ ጋር ዲፕሎሲያዊ ግንኙነቷ በተቋረጠው ኳታር ለሦስት ቀናት ከመጋቢት 3-5 የተካሄደ ሲሆን መሠረት ደፋር 4ኛ ተከታታይ የቤት ውስጥ ድሏን ለማስመዝገብ ችላለች:: በ1500 ሜትር በባለቤቷ ዳዊት ዘርጋው የምትሰለጥነው ቃልኪዳን ገዛኸኝም የውድድሩ አሸናፊ እንደነበረች ይታወሳል::

## ጥሩ ብቻ

በኬኒያ ናይሮቢ ከሐምሌ 21-25 በተካሄደው 17ኛ የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያ ወርቅ ያገኘችው በጥሩነሽ ዲባባ በ10ሺ.ህ ሜትር ብቻ መሆኑ አነጋጋሪ ነበር::

## አዲሱ የብ/ቡድን አሰልጣኝ

የኢትዮጵያ ብ/ቡድን ኦፌም ኦኔራ የተባሉ የዘር ሐረጋቸው ከናይጄሪያ የሚመዘዝ እንግሊዛዊ ዜግነት ያላቸው አሰልጣኝ መቅጠሩን ሰኔ 20 2002 ዓ.ም በሸራተን አዲስ በተካሄደው የፊርማ ስነ ስርዓት ላይ አረጋግጧል::

እኚህ ጥቁር ቁመታም የብ/ቡድኑ አሰልጣኝ ለሼፊልድ ዩናይትድ፣ ለብራፎርድ ሲቲ እና ለሌሎችም ክለቦች መጫወታቸውን ስዊዲን ሲቲ፣ ጂሊንግሀምና ሊንበን ሲቲን ከ2005 - 2008 ባሉት ዓመታት ማሰልጠናቸውን ተናግረዋል:: «ኢትዮጵያን የሚያስደስት ውጤት ለማምጣት እሰራለሁ» ያሉት አሰልጣኙ ዋሊያዎቹን ይዘው በዚህ ወር በወዳጅነት ጨዋታ በኬኒያ 3-0 ሲሸነፉ፣ ቻድን 1-0 አሸንፈዋል:: የኢትዮጵያ ብ/ቡድን በነገው እለት በሚጀመረው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የጊኒን ብ/ቡድን በነገው እለት በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ይገጥማል:: ኦፌም ኦኔራ ወርሃዊ 13 ሺ.ህ ዶላር ቤትና መኪና የተሰጣቸው ሲሆን ከአንድ ወር ከሁለት ሳምንት በላይ ቡድኑን አዘጋጅተዋል::

በኢትዮጵያ እና በጊኒ ቡድኖች መካከል የሚካሄደውን ጨዋታ የሚመሩት አራቱም ዳኞች ከዚምባቡዌ ሲሆኑ ኮሚሽነሩ ቻርልስ ማስቤ የተባሉ ኡጋንዳዊ መሆናቸውን የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አስታውቋል::





PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

ማስታወቂያ

ትክክለኛው የብራዚል የሻወር ውሃ ማሞቂያ

ተመሳስለው ከተሰሩ ፈጣን የሻወር ውሃ ማሞቂያ ምርቶች ይጠንቀቁ ትክክለኛውን የብራዚል የሻወር ውሃ ማሞቂያ ይጠቀሙ




Brazmart International General Trading Plc.
Address!- • Urail Alem Brehan Plaza 1st Floor #106
1. ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ዓለም ብርሃን ፕላዛ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 106
2. ለቡ አደባባይ ፊት ለፊት ሳሙኤል ህንፃ
በማንኛውም የቧንቧና የሻወር ቤት እቃዎች መሸጫና እንዲሁም በየህንፃ መሣሪያ መደብሮች ያገኙታል::
ሲገዙ ትክክለኛ የብራዚል ምርት መሆኑን ያረጋግጡ!
Tel. 251-11 552 -6011 /12 Fax 251-11-5526012

# የጊዮርጊሱ ግርግር

ቀንበር ለሚሰቃየው ወገናችን የሚቆረቆረው? የትኛው መሪ ይሆን ፍትህ ለተነፈጉት፣ ወንጀል ሳይሰሩ በየእሥር ቤቱ ለሚማቅቁት ወገኖች የሚያስበው? ማን ይሆን ከሽራተን፣ ከቤተ መንግስት፣ በቦሌ መንገድ ካሉ ዳንኪራ ቦታዎች፣ በየቦታው ከተሰሩ የታጠሩ የሀብታም ሰፈሮች ወጥቶ ሴቲቱን ለመርዳት መኪናውን የሚያቆመው?

እንደውም እንዳየነው ከሆኑ፣ የኑሮ ውድነት በአንድ በኩል እያሰቃየው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ በፍርሃትና በሰቀቀን አንገቱን ደፍቶ «እሺ ጌታዬ» ብሎ በአገሩ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲኖር አልተደረገምን?

ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ የት ነው ያሉት? አንድ ሰው ተኩሰው ገድለዋል? አምስት ሳንቲም ከሰው ኪስ ሰርቀዋል? በሕክምና ሞያቸው ቀዶ ጥገና ሲያደርጉ መቀስ ሆድ ውስጥ ረስተዋል? የአሁኑ የአገራችን ጠቅላይ ሚኒስትር በፓርላማ ሲናገሩ እንደሰማነው፣ «ሌቦች፣ ወራዶች...» ብለው ተሳድበዋል? እስቲ የሚደፍር ካለ ይንገረን... እስር ቤት እያሉ በበረታባቸው ሕመም ምክንያት እስኪሞቱ ድረስ ለዚያ ሁሉ ዓመታት በእስር እንዲሰቃዩ መደረጋቸው ምን ወንጀል ቢፈጽሙ ነው?

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የት ነው ያለችው? ቱሃንና አይጥ በሚሯሯጡበት ቃሊቲ እስር ቤት አይደለምን? ምንድን ነው ወንጀሏ? ዳኛ የነበረች ጊዜ ጉቦ በላች? በውጭ አገር ጉብኝት ባደረገች ጊዜ ጦርነት አወጀች? የአገር ባለስልጣናትን ሰደበች? ገንዘብ ሰረቀች? ሕገ መንግስቱን አልቀበልም አለች? «ይቅርታ ጠይቃ፣ ይቅርታ አልጠየኩም ብላለች፣ አጭበርብራለች» ይላሉ አቶ መለስ:: በርግጥስ ብርቱካን ሚደቅሳ ይቅርታ አልጠየኩም ብላለች? እንደውም ቃሌ በተሰኘው ጽሁፏ በአገር ሽምግልና ወግ መሠረት «ሕዝብንና መንግስትን ይቅርታ መጠየቁን አልክድም» አይደለም ያለችው?

ታዲያ ይሄ ሁሉ የሚያሳየው በአሁኑ ወቅት በአገራችን ባሉ መሪዎች ዘንድ የምናየው የልዑል መኮንን ዓይነት ሐዘኔታን፣ ፍቅርን፣ ርህራሄን፣ ሰላምን፣ በጎነትን ሳይሆን ጭካኔን፣ ክፋትን አይደለምን?

ከላይ እንደጠቀስኩት ጄኔራል አማን አንዶም ጠመንጃ ካነሱት ጋር ያለ ቅድመ ሁኔታ ለመነጋገር ደፍረው ነበር:: ጠመንጃ ያነሳው ጠመንጃውን ካስቀመጠማ ምን ንግግር ይባላል? «እምቢ አሻፈረኝ ብሎ የሸፈተን ጠመንጃህን አስቀምጥና እንነጋገር» ቢባል ከወዲሁ በጠመንጃ ካልተሸነፈ በቀር እሺ ሊል አይችልም::

አቶ መለስ በቅርቡ ለሰላም እንደቆሙ ገልጸውልናል:: ከግንቦት ሰባትና ከኦነግ ጋር ለመነጋገር ፍቃደኝነታቸውን አሳውቀዋል:: «በሕገመንግስቱ አምነው፣ ሕገመንግስቱን ለመከተል ፍቃደኛ እስከሆኑና በሰላም ለመታገል (ጠመንጃቸውን ለማስቀመጥ) እስከወሰኑ ድረስ» እነ ኦነግ አገር ውስጥ መንቀሳቀስ እንደሚችሉ ነው የጠቆሙት::

መቼም የሰላም ሀሳብን የሚጠላ የለም:: ከማንም ይምጣ፣ ማንኛውም የሰላምና የእርቅ ሀሳብ የሚደገፍ ነው:: ነገር ግን ይህ የአቶ መለስ የሰላም ሀሳብ፣ ገና ከአቶ መለስ አንደበት እንደወጣ ያኔውኑ፣ እራሳቸው አቶ መለስ በተግባራቸው ሽረውታል:: ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ትፈታለች ወይ ተብለው ሲጠየቁ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳይ የሕግ ጉዳይ እንደሆነ ነበር የገለጹት::

እንዴት ተደርጎ ነው ታዲያ በሰላም የሚታገሉትን እያሰሩ፣ በውጭ ያለውንና ነፍጥ ያነሳው ተቃዋሚ አቶ መለስ ዜናዊን አምኖ ነፍጡን የሚያስቀምጠው? እንዴት ተደርጎ ነው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ቃሊቲ እየማቀቀች፣ በሰላም ይታገሉ የነበሩት እንደ አቶ በቀለ ጂራታ ከአገር እንዲሰደዱ እየተደረገ፣ የኦነጉ አቶ ዳውድ ኢብሳ ወይንም የግንቦት ሰባቱ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ የአቶ መለስን የሰላም ጥሪ አምነው በሰላም ለመታገል አገር ቤት የሚገቡት?

እንግዲህ አቶ መለስና ጓደኞቻቸው በርግጥ ለሕዝብ እናስባለን፣ ለድሃ እንቆረቆራለን የሚሉ ከሆነ፣ በአገራችን ሰላም እንዲሰፍን በርግጥ ፍላጎት ካላቸው፣ በሥራቸው ያሳዩን:: ፈረንጆች «ዋር ኢዝ ዘ ሚት?» እንደሚሉት ወሬውና ጩኸቱ፣ ጋዜጣዊ መግለጫው ይብቃና በፖሊሲና በተግባር የተጨበጠ ነገር ያሳዩን::

የፊታችን አዲስ ዓመት መልካም አጋጣሚዎች ከፍቶላቸዋል:: ካሉበት አጥር ወጣ ብለው የጊዮርጊስን ግርግር መመልከት ይኖርባቸዋል:: ያልሆነውን ነው ከሚሉ አማካሪዎቻቸው ባሻገር በጓዳ በሕዝቡ ዘንድ የሚነገረውን ማዳመጥ መቻል አለባቸው:: የሕዝብን ልብ ትርታ ያዘቸውን ዳግማዊት ጣይቱ ብጡል ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በአስቸኳይ መፍታት ይኖርባቸዋል:: የልዑል መኮንን ዓይነት ርህራሄና የድሃ ፍቅር ልባቸውን ሊሞላ ይገባል:: ጄኔራል አማን አንዶም ጦራቸውን ወደ ሰገባው ከተው በንግግርና በውይይት በወንድማማቾች መካከል የተፈጠረውን ቀውስ ለመፍታት እንደሞከሩት ሁሉ፣ እነርሱም በሕዝቡ ላይ የጫኑትን የፍርሃትና የጭቆና የጡንቻ አቁመው፣ እራሳቸውን በሕዝብና በታላቁ እግዚአብሔር ፊት አዋርደው፣ የሰላም የወንድማማችነት፣ የመከባበር ባህል እንዲሰፋ ጉልህ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል::

ላለፉት ዓመታት የተመኘነውና ተስፋ ያደረግነው አልሆነልንም:: ዓመቱን በሐዘን ነው ያጠናቀቅነው:: የ2002 ዓመትን ከጥቂት ቀናት በኋላ እንሰናበተዋለን:: እንደ 2002 እና ያለፉት ዓመታትስ 2003 ዓ.ምን አያደርግብን! በዚህ አዲስ ዓመት እግዚአብሔር ቸሩን ያሰማን!

መልካም አዲስ ዓመት!

# ምርጫ 2002...

ቁጥር ጋብ ማለቱን አይቶ የሰቆቃው በትር በወረደበት ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ በዝግታ ከሚወርደው እንባው ጋር እየታገለ ለውብሸት እንዲህ ሲል ነገረው «ማንኛውም ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰብዓዊ ፍጡር ይፈጽመዋል ተብሎ ከሚገመተው የዘለለ ነበር::.. እንግዲህ ይህ ለምን ሆነ ይባላል? እህል ከአፈር የማይለዩ ህፃናት ፊደል እየቆጠሩ በአውሮፕላን ቦንብ ሲደበደቡ?» ባልደረባችንም በወጣቱ አዕምሮ ውስጥ ተሰንቅሮ የቀረ ያልተመለሰ ጥያቄ እንዳለ ጠቅሶ በአንድ የትምህርት ቤት በር ላይ የተቀመጡ ሁለት ታዳጊ እንስቶችም በከፊል ራሳቸውን ሸሽገው ወደ እነሱ እያዩ ከአይኖቻቸው ላይ እንባቸውን ሲጠርጉ መመልከቱን «ከባድ ነበር» በማለት ምርጫውን አስመልክቶ በፃፈው ፅሁፉ ላይ አስነብቦናል:: የምስኪኖቹ ሰማዕታት የመታሰቢያ ሰሌዳዎች በየዓመቱ እንደሚታደስ እንደተገለፀለት፣ ከእነዚህ ሰሌዳዎች ጀርባ ባለው የትምህርት ክፍል ግድግዳ ላይ አንዲት እናት በጥቃቱ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባትን ህፃን /ምናልባት ህይወቷ ያለፈ/ ተንበርክካ ስታነሳ ህፃኗ መላ ሰውነቷ በደም የተለወሰ እንደሆነ፣ የህጻኗ የመማሪያ መፅሀፍትና ደብተሮቿ ሜዳው ላይ መዝረክረካቸውንና እናቲቱ ሲገለፅ በማይችል ኃዘን እንባዋን እየዘራች ወደላይ፣ ወደ «እግዜር አገር» እንደምትመለከት የተሳለውን ስዕል ተመልክቶ ማዘኑን በብዕሩ ለአንባቢያን ገልጿል::

ውብሸት በግል አስተያየቱ «ለህፃናቱ መታሰቢያ መደረጋቸው ትክክል ነው፤ ከዚህ በላቀ ሁኔታም ሊዘከሩ ይገባቸዋል፣ በልባችን ውስጥም በፍቅር እናስታውሳቸዋለን:: በአንፃሩ ግን መቃናት ያለበት ሁኔታም አለ» ብሎ ነበር::

አስከትሎም እርስዎ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ተንቀሳቅሰው በሚያስተውሉት ሁኔታ ጥልቅ የሰቀቀን ስሜት የሚፈጥርብዎ ከሆነ ሁኔታውን በየዕለቱ እየተመለከቱ ወደ መግቢያ ክፍሎቻቸው የሚገቡት ህፃናት በስጋት ስነ ልቦና አይሰቃዩ ይሆን? ይህስ በቀሪው ሕይወታቸው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ አይኖርም? በሌላ በኩል ይህን ተቋም ለሌላ የልማት ተግባር በማዋል ለመማርያነት የሚያገለግል ሌላ አማራጭ መፈለግ አይቻልም? የዘርፉ ባለሙያዎች፤ የክልሉ መንግስትና ውድ አንባቢያንስ ምን ሃሳብ አላችሁ? ሲል ይጠይቃል::

## የ«ማያባራው» የስልክ ጥሪ

«ድንኪ ሌላም ገፅታ ነበረው» የሚለው አቤል «ኑሮቁቁ ሰስቃ-ቋስቄ» ይመስል ቶሎ ቶሎ የእጅ ስልኮች ያቃጭሉ እንደነበር፣ የኢህአዴጉና የሲቪል ማህበረሰብ ታዛቢዋ ሴት ስልክ ደጋግሞ በማቃጨል የድንኪ ባለሪከርዶች እንደነበሩ፣ ከኢህአዴግ ታዛቢው አፍ «ገና ነው፣ የመረጥነውንና ያልመረጥነውን ብዛት እየለየን ነው፤ ደርሷል፤ አሁን ሊከፈት ነው፣ ኮሮጆው ተከፍቶ የድምጽ መስጫ ሳጥን እየተስተካከለ ነው፣ ጥሩ ነን፣ እናሸንፋለን» የሚሉ ቃላቶች ለደዋዮች ይደርሱ እንደነበር፣ የሲቪል ማሕበረሰብ ታዛቢ የሆነች ሴት «ምርጫው ነፃ፣ ፍትሐዊ፣ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና በሕዝብ ዘንድ ታማኝነት ያለው ነው» በማለት በሰባት ደቂቃ ውስጥ ሦስት ጥሪ ማስተናገዷንና የምታስተላለፋቸው መልዕክቶች ውጤት አብሳሪነት በሚያሳይ መልኩ «ጥሩ እየሄደ ነው፣ በጣም ጥሩ ነው» ስትል እንደነበረ ገልጿል::

የተኛችዋን ህፃን ልጇን ታቅፋ ተደጋጋሚ የስልክ ጥሪ የምታደርገዋ ታዛቢ በድንኪ ውስጥ ያለውን ድባብ በመረበሽ የብዙ ሰዎች መነጋገሪያ አጀንዳ እንደነበረች አቤል ጠቁሞ የምርጫ አስፈፃሚውና በጥበቃ ስራ ላይ የነበረች ሴት ስልክም በተደጋጋሚ ማቃጨሉ ተናግሮ «ያበቃው ድምጽ ቆጠራው ብቻ ሳይሆን እሳት መሞቁ፣ ማንቀላፋቱና ክርክሩም ነበር» ሲል ከሌሊቱ 7.00 ሰዓት ወደ ቤቱ ለማቅናት ከምርጫ ጣቢያው መንቀሳቀሱን ባልደረባችን አውግቷል::

## ምርጫው እንዴት ይሆን?

ግንቦት 14/2002 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦና ጉደር ከተማ የተካሄደውን ምርጫ ለመመልከት ወደ ስፍራው አምርቶ የነበረው የአውራምባ ታይምስ ዘጋቢ ፍፁም ማሞ ነው:: በጉዞ ላይ በመኪና ውስጥ ሆኖ «እኔን ጨምሮ፣ ሁሉም ተሳፋሪዎች በቀጣዩ ቀን ስለሚካሄደው ምርጫ እንደሚያወቁ እርግጠኛ ነበርኩ» የሚለው ፍፁም፣ ሆኖም እጅግ በጣም ሳይሆን በጣም ባስገረመው መልኩ አንዳቸውም ስለምርጫው አለማወ ራታቸውና አለመናገራቸውን በመታዘብ «እንደኔው በእዝነ- ልቦናቸው ጥያቄዎችን እያወጡና እያወረዱ ይሆናል፤ ምርጫው በሰላም ይከናወናል ወይስ አይከናወንም? ፍትሃዊነቱስ? ተዓማኒነት ይኖረው ይሆን?» የሚሉ የጥያቄዎች መዓት በሀሳቡ ተመላልሰውበት ነበር::

በምርጫው ዕለትም በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች እየተዟዟረ ሂደቱን የተከተለ ሲሆን የመድረክ ፓርቲ በተዘዋዋሪነትና በየምርጫ ጣቢያዎች ከመደባቸው ታዛቢዎቹ በስተቀር ሁሉም የሌሎች ፓርቲ ታዛቢዎች በምርጫው ሂደት ውስጥ ምንም እክል እንዳልገጠማቸው ጠይቆ የተረዳውን ባልደረባችን ገልጿል:: ረከኢህአዴጉ አቶ ደሳለኝ ቤካ በስተቀርሪ

በአብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጡ ምስጢራዊነት እንዳልተጠበቀ፣ በአንዳንድ ጣቢያዎች መራጩ ድምፁን የሰጠው በግልጽ በአካባቢው የነበሩ ፈታሾች እየተመለከቷቸውና ድምጽ መስጠት የተጀመረው የምርጫ ወረቀቶች ከመቆጠራቸው በፊት እንደነበረ ለመድረክ በተዘዋዋሪ ታዛቢነት ይንቀሳቀሱ የነበሩት አቶ ደሳለኝ ጉዲሳ ተናግረዋል::

## ቆሎና ጠላ ለሕዝብ ታዛቢዎች

ፍፁም ማሞ ወደ ጣመዒ ምርጫ ጣቢያ ከረፋፈደ በኋላ በድጋሚ ሲመለስ መለስተኛ ግርግር የሚመስል ድባብ መመልከቱን፣ በጣቢያው ለሕዝብ ታዛቢዎች ቆሎና ጠላ እየቀረበላቸው እንደነበረ፣ የቆሎው ባይገርመውም የጠላው ግን እንዳስደመመው፣ በጣቢያው የመድረክ ተዘዋዋሪ ታዛቢና ከመራጭ ፈታሾች ጋር ለአጭር ጊዜ የቆየ አለመግባባት መከሰቱን፣ ላለመግባባቱ ምክንያት «ፈታሾች መራጮች ድምፃቸውን በድምጽ መስጫ ወረቀታቸው ላይ ምልክት ሲያደርጉ ቆመው ሲመለከቱ ተመልክቻለሁ» የሚል ውንጀላ ከመድረክ ታዛቢ መሰንዘሩ እንደሆነና ፈታሾችና የምርጫ ጣቢያው አስተባባሪ «ውንጀላው ሀሰት ነው» በሚል የፈጠሩት ጠንከር ያለ ጭቅጭቅ እንደነበር በትዝብቱ አስቀምጧል::

በአምቦ ዩኒቨርስቲ የምርጫ ጣቢያ ያነጋገራቸው አራት ተማሪዎች የድምጽ መስጫ ወረቀት ስላልደረሳቸው መምረጥ አለመቻላቸውን ጠቅሰው ድምፅ መስጠት እስከሚያበቃበት ሰዓት ድረስ ከዚሁ ምርጫ ጣቢያ ደጃፍ እንደማይነቃነቁ በመግለጽ ለፍጹም የሚመለከተውን አካል «እባክህ ጠይቅልን?» ብለው በሰጡት ኃላፊነት መሠረት የምርጫ ጣቢያዎች አስተባባሪ የሆኑትን አቶ ምስጋናው አንጁሉ ሲጠይቅ የምርጫ ወረቀቶቹ እንደዘገዩባቸውና ወረቀቶቹጩም እንደሚመጡ ነገሩት::

ከፍፁም ትዝብቶች መካከል በአንዳንዶቹ ጣቢያዎች በድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ መራጭ ምርጫውን በሚስጥራዊነት መንገድ እንዲመርጥ ተብለው የተሰሩ ቤቶች የተሸፈኑም፣ ያልተሸፈኑ በእርግጠኝነት እንደነበሩ፣ በተለይ በአንደኛው የምርጫ ጣቢያ ያገኘው የአካባቢ ኃላፊ በምርጫ ጣቢያ አከባቢ መቆሙ አግባብ አለመሆኑና ኃላፊው ጣቢያው አከባቢ መገኘቱ በራሱ በመራጩ የአከባቢው ነዋሪ ላይ የራሱ አንዳች አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ እንደማያጠራጥር ነው::

እንዲሁም እስከ ምሽት 1:20 ሰዓት ድረስ ባልተጀመረው የምርጫ ቆጠራ ላይ በተለይ የመድረክና የመኢአድ ታዛቢዎች የማስታወሻ ደብተራቸውን እያዩ «ስህተት ተፈጥሯል» ያሉትን እየጠቀሱ ከአስፈፃሚው ጋር መነጋገር መቀጠላቸውንና በንግግራቸውም በቀላሉ የሚላቀቁ ረእና የተላቀቁሪ እንደማይመስለው ፍጹም በወቅቱ ጠቅሶ ነበር::

## «ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ አይደለም»

በወረዳ 17 ዞን 3 የምርጫ ጣቢያ ረፋድ 4:45 ሰዓት ላይ ድምፃቸውን የሰጡት ኢንጂነር ግዛቸው የምርጫ አስፈፃሚ የነበሩትን አቶ መስፍን ወ/ሰማያትን ከተመለከቷቸው በኋላ በ97 ምርጫ የኢህአዴግ ታዛቢ አሁን ደግሞ የምርጫ አስፈፃሚ ሆነው መቅረባቸውን፣ ይህም ደግሞ ኃጢያት አለመሆኑንና አቶ መስፍን ኢህአዴግ መሆናቸውን በፈገግታ ይናገራቸዋል:: አቶ መስፍንም ከ30 ደቂቃ በኋላ ስለጉዳዩ ስንጠይቃቸው «የዛሬ አምስትም ሆነ አስር ዓመት የኢህአዴግ ታዛቢ አይደለሁም:: አልነበርኩምም:: ዝም ብለው ነው የሚናገሩት:: እንዲህ ሲሉ ማስረጃ ይዘው ማቅረብ አለባቸው» የሚል ምላሽ ሰጥተው ነበር::

ከአፍታም በኋላ የተለያዩ የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች እስከአሁን የነበረውን የድምፅ አሰጣጥ ሂደት እንዴት ተመለከቱት? ብሎ ለኢ/ር ግዛቸው ላቀረቡላቸው ጥያቄ «በአጠቃላይ በአሁኑ ደረጃ ምርጫው ነፃና ፍትሐዊ አለመሆኑ ተረጋግጧል» ካሉ በኋላ ለዚህ «መረጃ ልሰጣችሁ እችላለሁ» በማለት መረጃቸውን መግለጽ ቀጠሉ:: ይህች ምላሻቸው ወዲያው በተለያዩ የአገርና የውጭ መገናኛ ብዙሃን በዕለቱ ሲዘገብ ዋለ:: በነጋታው ጥዋት ኢ/ር ግዛቸው «ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ አለመሆኑ ተረጋግጧል» ላሉት የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ መጠየቃቸው በኢቴቪ ተገለፀ::

## ከምርጫ እለት በኋላ

የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑካን ቡድን መሪ ሚ/ር ቲጂስ በርማን በምርጫው እለት የምርጫውን መጠናቀቅ ተከትሎ በብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ በሰጡት መግለጫ «ተቃዋሚዎች ካሰሙት ያልተረጋገጡ ሪፖርቶች ውጭ በእለቱ የተደረገው የድምጽ አሰጣጥ ዲሞክራሲያዊ ነበር» ብለው ዝርዝር ነገር ከመናገር ተቆጥበዋል:: በነጋታውም ምሽት ላይ የኢትዮጵያ ሲቪክ ማህበራት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ምርጫው ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ተዓማኒ መሆኑን በሂልተን ሆቴል ከገለፁ ከሰዓታት በኋላ ምርጫ ቦርድ በጊዜያዊ የምርጫ ውጤት ኢህአዴግ ማሸነፉን አረጋግጠዋል::

በቀጣዩ ቀን የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ባቀረበው የመጀመሪያ ሪፖርቱ «በብዙ ቦታዎች በገዢው ፓርቲ እና በሕዝብ አስተዳደሮች መካከል ያለው ወሰጣዊ መለያየት የደበዘዘ ነበር:: ገዢው ፓርቲ የምርጫ ቅስቀሳ ዝግጅቶቹን ሲያካሂድ የመንግስትን ንብረት በቅስቀሳ ሂደቱ ላይ እንዳዋለ ቡድኑ ታዝቧል::» ብሏል::

ረቡዕ እለት መኢአድ እና መድረክ የግንቦት 15ቱን ውጤት ለመቀበል የሚያስችል ተዓማኒነት ያለው ሁኔታ ባለመኖሩ እና ምርጫው በነፃና ገለልተኛ አስፈፃሚ አካላት እንዲሁም ታዛቢዎች በተገኙበት ምርጫው እንዲደገም ጧት እና ከሰዓት በኋላ ከፍተኛ አመራሮቻቸው በተገኙበት በጽ/ቤታቸው ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተው ነበር:: ሁለቱም ፓርቲዎች «ምርጫው ይደገም» የሚለውን ቅሬታቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ከምርጫ ቦርድ አንስቶ እስከአገሪቷ የመጨረሻ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቢሄዱም በሁሉም ዘንድ አቤቱታቸው ውድቅ እንደተደረገባቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

CPU COLLEGE

# ሲፒዩ ኮሌጅ

DEGREE

COMPUTER SCIENCE

MIS

Information Technology
- IT Assistance
- Web & Multimedia
- IT Support & System Service
- Hardware & Network Technology

ACCOUNTING

SECRETARIAL SCIENCE

TVET

*በሁሉም ሙሉ እውቅና!*

www.cpu.edu.et

E-mail cpu.pvt@ethionet.et

☎ 011 155 6398, 011 810 1107

ሲፒዩን ሳይጎበኙ የሚማሩበትን አይወስኑ!

18 - Years of Academic Excellence



# አየር ጤና
## የጤና ሳይንስ ኮሌጅ

## ሙሉ ዕዉቅና ያለው ኮሌጅ!

ለ2003 ዓ.ም እንኳን አደረሳችሁ እያለ፤ ለአዲስ ዓመት ለ7ኛ ዙር
በቀንና በማታዉ የትምህርት ፕሮግራም በጥራት ለማስተማር **ምዝገባ ጀመረ**::

*በደረጃ 4 (Level IV) የትምህርት መርሀ ግብር!*

- በክሊኒካል ነርስ፤
- በፋርማሲ ቴክኒሺያን፤
- በሜዲካል ላብራቶሪ ቴክኒሺያን - የትምህርት መስኮች የሚያሰለጥን የጤና ተቋም ነዉ.
- በጤና ኤክስቴንሽን እና በኮምፒተር ስልጠና፤ ሰልጣኞችን በመቀበል አስፈላጊዉን ያሟላ::

በትምህርት ቢሮ ባወጣው መስፈርት መሠረት ምዝገባ ሳይ ነን!

**ከአጫጭር ስልጠናዎች ጋር:-**

- መሠረታዊ የኮምፒውተር ትምህርት፤
- ልዩ የቋንቋ ስልጠና የሚሰጥ የጤና ኮሌጅ::

**ስለ ኮሌጃችን ይህን ያውቃሉ!!**

- በረዥም የስራ ልምድ ባካበቱ ባለሙያዎች ታቀፈ፤
- ጥራትን መሰረት ያደረገ የተሟላ የትምህርት አሰጣጥ፤
- በመልካም አስተዳደር የተገነባ፤
- በሲዲ (CD) የታገዘ የላይብረሪ አገልግሎት፤
- የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ዉጤት የሆኑ የህክምና መማሪያ መሳሪያዎች ባለቤት፤
- በቂ የተማሪዎች የተግባር ልምምድ፤
- አመቺ የቦታ አቀማመጥና የመማሪያ ክፍሎች
- ዓላማችን ሀገር ተረካቢ ትዉልድ በተመጣጠነ ክፍያ ጥራት ባለው ት/ት ብቁ ባለሙያ ማፍራት ነው::


**ማየት ማመን ነው !**

**ያለን ቦታ ዉስን ስለሆነ ፈጥነው ይመዝገቡ?**

አድራሻ:-
እንደ ስያሜአችን አየር ጤና አካባቢ ዘነብ ወርቅ «አለርት» ሆስፒታል ከፍ ብሎ::
✉ 552 code 1033 ☎ 011-8200137
ሞባይል: 0910-635207 /0911-472321 E-mail mhreec@yahoo.com


▷ ማስታወቂያ ◁




ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት



PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com